

# ከመጋቢት
# እስከ መጋቢት

ቅጽ 3 VOL 3

መጋቢት ፪፻፲፫ ዓ.ም

የኢፌደሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አህመድ(ዶ/ር) ከመጋቢት 24 ቀን 2012ዓ.ም እስከ መጋቢት 24 ቀን 2013ዓ.ም ድረስ የደረጓቸው ንግግሮች እና ያስተላለፏቸው መልእክቶች

ከመጋቢት እስከ መጋቢት

ኢትዮጵያ: አዲሲቷ የተስፋ አድማስ
ETHIOPIA: A NEW HORIZON OF HOPE

መጋቢት
፪፻፲፫ ዓ.ም
ታተመ

ISBN 978-99944-3-357-5

ከመጋቢት እስከ መጋቢት

# ከመጋቢት
# እስከ መጋቢት

ቅጽ 3 VOL 3



መጋቢት ፪፻፲፫ ዓ.ም | የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አህመድ(ዶ/ር) ከመጋቢት 24 ቀን 2012ዓ.ም እስከ መጋቢት 24 ቀን 2013ዓ.ም ድረስ ያደረጓቸው ንግግሮች እና ያስተላለፏቸው መልእክቶች

ኢትዮጵያ: አዲሲቷ የተስፋ አድማስ
ETHIOPIA: A NEW HORIZON OF HOPE

# ከመጋቢት

## እስከ መጋቢት

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር) ከመጋቢት 24 ቀን 2012 ዓ.ም እስከ መጋቢት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ያደረጓቸው ንግግሮች እና ያስተላለፏቸው መልእክቶች

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

2021 G.C
፳፻፲፫ ዓ.ም

ቅንብር፣ አርትዖትና ዝግጅት -
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

**የዚህ መጽሐፍ ገቢ ለበጎ አድራጎት የሚውል ነው።**

Copyright © 2021 Office of the Prime Minister – Ethiopia

ነሐሴ ፳፻፲፫ ዓ.ም - ይኽን መጽሐፍ ከጽ/ቤቱ ፍቃድ ውጭ የትኛውንም መሳሪያ ተጠቅሞ ማባዛትም ሆነ አሳትሞ ማሰራጨት በሕግ የተከለከለ ነው።

# ማውጫ

አጭር መቅድም vii

## ክፍል አንድ – የአማርኛ ንግግሮች

አረንጓዴ አሻራን በተመለከተ የተደረገ ውይይት 3
ኢትዮጵያ፦ አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት 16
የሸገር ዳቦ ምርቃት ንግግር 29
የጀሞ-ዊንጌት መንገድ ምርቃት ንግግር 35
በታቦር ተራራ ላይ ስለ አረንጓዴ ዐሻራ የተላለፈ መልዕክት 41
የምስጋና ንግግር 47
የበጎ አድራጎት ገንዘብ ርክክብ 50
የገንዘብ ኖት ቅያሬን በማስመልከት የተደረገ ንግግር 53
ግብር ከፋይነት ያሸልማል 62
የፌዴራል ፖሊስ ትርኢት ላይ የተደረገ ንግግር 68
የባህር ዳር ኢንደስትሪያል ፓርክ ምርቃት ላይ የተደረገ ንግግር 72
ለገበታ ለሀገር የተደረገ ድጋፍ ምስጋና 77
የሶማሌ ክልል መንገድ ምርቃት ላይ የተደረገ ንግግር 79
በሶማሌ ክልል የስንዴ ማሳ ጉብኝት ላይ የተደረገ ንግግር 81
ከመከላከያ መኮንኖች ጋር የተደረገ ውይይት 83
የብልጽግና ፓርቲ ማኒፌስቶ 95
ሀገርን እና ሕዝብን ማገልገል ያኮራል! 107
የጎጃም ስንዴ ማሳ ጉብኝት ላይ የተደረገ ንግግር 117





የአማራ ክልል የልማትና የብልጽግና መንገዶች 122
የይርጋለም አግሮ ኢንደስትሪያል ፓርክ ምርቃት ንግግር 128

## Kutaa Lama – Haasaawwan Afaan Oromoo

Haasawaa Wayita Pirojektii Daandii Jalqabsiisan Dambidoollootti Dhiyeessan 139
Haasawaa Wayita Pirojektii Daandii Eebbisan Shaambuutti Dhiyeessan 150
Haasawaa Wayita Pirojektoota Daandii Jalqabsiisan Ambootti Dhiyeessan 158
Shashamannee 165
Piroojektii Ekkoo Tuuriizimii 170

## Part Three – English Speeches

Speech about Covid-19 in the African Union 187
Ethiopia's Green Legacy 190
UN 75th Anniversary Speech 193
The 75th UN General Assembly Speech 198
The 70th Regional Committee Meeting 205
Putting an End to Impunity: The Case for Enforcing Federal Laws in Tigray 210
Justice Shall Prevail 215
The Inauguration of the Hawassa – Moyale

## የአማርኛ ንግግሮች


500 km asphalt road 220
Climate Ambition Summit 224
UNECA Keynote Address 227
Djibouti Speech 236
FT Meeting 241


## ክፍል አራት – የአማርኛ መግለጫ እና መልእክቶች


የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመግታት የተወሰዱ እርምጃዎች 255
የኮሮና ወቅታዊ መግለጫ 266
ያልፋል አትጠራጠሩ 269
ኮቪድ 19 በተመለከተ የተላለፈ መልእክት 276
የፋሲካ በዓልን በማስመልከት የተላለፈ መልእክት 285
ለታላቁ የረመዳን ወር የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት 291
በኮሮና ወቅት ስለምርጫ የተደረገ ንግግር 296
ለዒድ አልፈጥር የተላለፈ መልእክት 312
ትናንትን በነገ መነጽር 318
በወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የተላለፈ መልዕክት 322
የሕዳሴ ግድብ የመጀመሪያ ዙር ውኃ ሙሌትን በማስመልከት የተላለፈ መልእክት 329
የዒድ አል-አድሐ በዓልን በማስመልከት የተላለፈ መልእክት 337
በየአካባቢያችን የሚገኙ የግጭት ነጋዴዎችን በጋራ እንከላከል 342
የዘመን መለወጫ ንግግር 351
የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት ለተማሪዎች 361




## ከመጋቢት እስከ መጋቢት


የመስቀል በአል መልእክት 366
የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት ለኢሬቻ 373
የሰሜን እዝን ጥቃት በተመለከተ የተሰጠ መግለጫ 380
በሕግ ማስከበር ዙሪያ የተሰጠ መግለጫ 384
የሕግ ማስከበር እርምጃውን በማስመልከት የተላለፈ መልእክት 390
የገና በአል መልእክት 398
የጥምቀት በአል በማስመልከት መልእክት 404
የ125ኛውን የዐድዋ ድል በዓልን በማስመልከት የተላለፈ መልእክት 411


## ሃሙሽተ ክፍሊ


መግለፂ ትግርኛ 423
መግለፂ ትግርኛ 427

# አጭር መቅድም

የሀገር መሪዎች በተለያዩ መርሃ ግብሮች ላይ የሚያደርጓቸውን ንግግሮች ሰንዶ ማስቀመጥ በሁለት በኩል ጥቅም አለው፡፡ በአንድ በኩል የመሪዎቹ ንግግሮች የመንግስትን አቋምና አካሄድ፣ እንዲሁም ዘወትራዊ ክንውኖችን ይጠቁማሉ፤ እናም ስለ ሀገር ነባራዊ ሁኔታ የተሻለ መረዳት እንዲኖር እነዚህን ሰነዶች መመልከት ብዙ ልፋት ይቀንሳል፡፡ ወቅታዊ ፖሊሲዎችን ለመገምገም እና በምን ዓይነት ስትራቴጂዎች እንደተፈጸሙ ለማወቅ እንደ መነሻና ማነጻጸሪያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ከንግግሮቹ መካከል አንዳንዶቹ የያዙት ፍሬ ሐሳብ መሪዎች ለሀገር የሰነቁትን ርዕይ እና አሳካዋለሁ ብለው የገቡትን ቃል ኪዳን ጭምር ስለሚሆን፣ ከዓመት በኋላ ምን ያህሎቹ ርዕዮች ግባቸውን ለመምታት ጉዞ ላይ ናቸው? ምን ያህሎቹስ ቃል በተገባው ልክ ተፈጸሙ? የሚለውን ለመገምገም ያስችላል።

በሌላ በኩል ይኽ ሰነድ ከታሪካዊ ፋይዳውም አንጻር ሊታይ ይችላል፡፡ ንግግሮችና መልዕክቶቹ በሚገባ ተሰንደው ሲቀመጡ ለሚመጣው ትውልድ እንደ ጥሩ ማጣቀሻ መጽሐፍና የታሪክ ሰነድ ሆነው ማገልገላቸው አይቀርም፡፡ ምንያቱም በእያንዳንዱ ንግግርና መልዕክት ውስጥ የዚህ ዘመን መልክ አለ፤ ዘመኑ ምን እንደሚመስል በከፊል ያሳያሉ፡፡ ስለሆነም በከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና በተለያዩ የምርምር ድርጅቶች የሚገኙ ተማሪዎችና ተመራማሪዎች ለሚያካሄዷቸው ሥነ መንግሥታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ሌሎችም ጥናቶች መነሻና የመረጃ ምንጭ ሆነው





ያገለግላሉ፡፡ ከእኛ በኋላ የሚመጣው ትውልድ ምን ዓይነት የሀገር መሪና የመንግሥት አስተዳደር እንደነበረው በትንሹም ቢሆን ከዚህ ሰነድ መገንዘብ ይችላል፡፡ ስለዚህ የመንግሥት መሪን ፍሬ ከናፍር ሰንዶ ማስቀመጥ ለወቅታዊ የተደራጀ የመረጃ ምንጭነት ባለፈ፣ ለትውልድ የታሪክ ሰነድ ሆኖ እንደሚያገለግል መታወቅ አለበት፡፡

በዚህ እሳቤ ላይ በመመርኮዝ ክቡር ዶ/ር ዐብይ አህመድ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር የፌደራል መንግሥትን እንዲመሩ ሐላፊነት ከተረከቡበት ከመጋቢት 24፣ 2010 ዓ.ም ወዲህ ያደረጓቸው ንግግሮች ዓመቱ መጨረሻ ላይ ተሰብስበው በመጽሐፍ መልክ ይሠነዳሉ፡፡ ከዚህ ቀደም ሁለት ቅጾች የወጡ ሲሆን ይኼኛው ሦስተኛ ቅጽ ነው፡፡ ከመጋቢት 2012 ዓ.ም እስከ መጋቢት 2013 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በልዩ ልዩ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ መድረኮች ላይ በሦስት ቋንቋዎች ያደረጓቸውን ንግግሮች ተካትተዋል፡፡

**መልካም ንባብ!!**

**የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት**





# ክፍል አንድ

## የአማርኛ ንግግሮች

# አረንጓዴ አሻራን በተመለከተ የተደረገ ውይይት

ግንቦት 6፣ 2012 ዓ.ም.

የአረንጓዴ አሻራ ወይንም ግሪን ሌጋሲ ብለን ባለፈው የጀመርነው የችግኝ ተከላ ስራ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ኢትዮጵያ ውስጥ እስከ 20 ቢሊየን ችግኝ መትከል እና ማብቀል ከቻልን የኛንና የአካባቢውን ሥነ ምህዳር በመቀየር ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል የሚሉ ጥናቶች አሉ። 20 ቢሊየን ችግኝ በአንድ ዓመት መትከል በብዙ መልኩ ስለማይቻል በአራት ዓመት ውስጥ ለማከናወን አስበን ነው እየሰራን ያለነው። አምና በነበረው እንቅስቃሴ ምንም እንኳን አብዛኛው እንቅስቃሴ በውስጥ የነበረ ቢሆንም በኋላ ለህዝቡ በገለጽንበት ወቅት የነበረው ምላሽና ተሣትፎ እጅግ የሚያበረታታ ነበረ። እኛ የአምናን እየተከልን ለዘንድሮ ሰፋ ያለ ዝግጅት ጀምረናል።

የማንኛውም ህልም ስኬት፣ የማንኛውም ራእይ ክንውን በሒደትና በቀጣይነት (በኮንቲኒቲ) ውስጥ ነው የሚረጋገጠው። አንድን ነገር ጀምሮ በመተው ልሕቀትን (ኤክሰለንስን) ማረጋገጥ አይቻልም። አስር ሺህ የሚሮጥ ሰው መቶ ሜትር በጣም በፍጥነት ቢሮጥ እና ቢያቋርጥ አስር ሺህን መከወን አይችልም። ትላልቅ ነገር ማሰባችን አግባብ ሆኖ ግን ቀጣይነቱ ነው ባህል የሚሆነው። ቀጣይነት ነው ወደ ልሕቀት





የሚወስደው። አምና ስንጀምር በሙሉ ልብ የተሳተፉ፣ ምናልባት እየተጠራጠሩ የገቡ፣ እምብዛም ያልተሳተፉ ሰዎች ካሉ ዘንድሮ በምናረጋቸው እንቅስቃሴዎች ብዙዎቹን እናሳትፋለን ተብሎ ይጠበቃል።

ችግኝ ተከላ እና አረንጓዴ ከባቢ መፍጠር አሁን አሁን ባሉ ጥናቶች የማይነካው ሴክተር የለም። በጤና ከፍተኛ ተጽዕኖ አለው፣ በአካባቢ ጥበቃ ከፍተኛ ተጽዕኖ አለው፣ በኢኮኖሚ፣ በኢነርጂ በጣም ተጽዕኖ አለው። በቅርቡ እንኳን ጃፓን በተደረገ ጥናት ፎረስት ባዚንግ ብለው ነው ያጠኑት። በዛፍ አካባቢ ብዙ ጊዜ የሚያጠፉ ሰዎች ስፖርት በመስራትም ይሁን ወክ በማድረግ፣ በማንበብ፣ ዛፍ ያለበት አከባቢ ብዙ ጊዜ የሚያጠፉ ሰዎች የልብ ምታቸው፣ የደም ዝውውራቸው እና የጭንቀት (stress) መጠን በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል በማለት በሳይንሳዊ መንገድ አጥንተዋል። በዚያ ብቻ ሳይሆን ባደጉት ሃገራት በከተማ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎችና ከከተማ ወጥተው በገጠራማ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች እንቅልፍ በሚያስወስዱ መድሃኒቶች የመተኛት ደረጃቸው በጣም ይለያያል። በከተማ አካባቢ ብዙዎቹ ባደጉት ሃገራት ከ50 በመቶ በላይ ይጠቀማሉ። በጣም ጭንቀት ይበዛል፤ በኑሮ ዘይቤአቸው ምክንያት ገጠረማ አካባቢዎች ላይ ጭንቀት ይቀንሳል። እና ይሄ ዝም ብሎ ድንገት የሆነ ሳይሆን ጥናት እንደሚያሳየው በሀብት ከምችትና በሃብት ስርጭት ከገጠር ከተሞች ይበልጣሉ:: ነገር ግን በውስጥ ሰላም፣ በጤናና በመተኛት ገጠር አካባቢ ይሻላል። ይሄ ከተፈጥሮ ጋር ባለ ትስስር የሚመጣ ነው።

ሌሎች ጥናቶችም እንደሚያሳዩት፣ በርካታ ችግኝ ያለባቸውም አካባቢዎች የመሬት መንቀጥቀጥ ቢያጋጥም፣ ከፍተኛ ዝናብ ቢያጋጥም በቀላሉ የመጠቃት እድሉ ይቀንሳል። ምክንያቱም አከባቢን የመያዝ፣

የመጠበቅ እድላቸው ሰፊ ስለሆነ። ዛፍ መትከል ለኛ እንደ መዝናኛ ነው፤ ከዚያ በላይ ደግሞ አካባቢያችንን መጠበቅ ነው። ነገ ትደግ ትበልጽግ የምንላት ኢትዮጵያም ምንም እንኳን ብር ብታከማች፣ ነዳጅ ብታወጣ፣ ወርቅ ብታወጣ፣ አካባቢው አረንጓዴ ካልሆነና ካልጸዳ ብልጽግናን በምሉዕነት ማረጋገጥ አይቻልም። የእድገት መጨረሻው ከአካባቢ ጋር ተስማምቶ መኖር ነው። የደስታ መጨረሻውም ትልቅ ፎቅ ላይ መኖር ብቻ ሳይሆን እዛ ፎቅ ውስጥ ቢያንስ አበባ ወይንም ዛፍ ማየት ነው።

ስለዚህ ይህንን እድል አግኝተን የምንሰራ ሰዎች እንደ እድለኛ ትውልድና ሰዎች ራሳችንን ማሰብ አለብን። ይሄ ነገር አዋጭ መሆኑን አምና ከጀመርን በኋላ፣ "አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ እናደርጋታለን" በሚል ፕሮጀክት የጀመርናቸው ስራዎች ትክክለኛ የአረንጓዴ አሻራ (Green Legacy) ስራ አዋጭና ጠቃሚ እንደሆነ ብዙ ትምህርት ተገኝቶበታል። ለምሳሌ የእንጦጦ ፕሮጀክታችን ምናልባት ኮሮናው ከተስተካከለ ከሚቀጥለው ወር ጀምሮ አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል። ይሄ ኮሚቴ አንዱ ስራው መጀመሪያ እንጦጦን ማየት፣ የወንዝ ዳር ማጽዳት ፕሮጀክቱን ማየት፣ በየክልሉ ያሉትን የነርሰሪ ፕሪፓሬሽን ማየት ይሆናል።

እንጦጦ በፈለግነው መመዘኛ ብንወስድ ዓለም ላይ ባሉ ዋና ከተሞች ውስጥ እንደ አንድ ምድራዊ ገነት ሊወሰድ የሚችል ቦታ ነው። እጅግ የሚያምር ገጸ ምድር ያለው፣ የአየሩ ንጽህና በጣም የሚገርም፣ ነገር ግን ለዓመታት ተቀምጦ እኛ ማየት ሳንችል ቀርተን፣ ሳንጠቀም ቀርተን የቆየ ሃብት ነው። እንጦጦ ውስጥ ዛፎቹን ነው ያገኘነው እንጂ ዛፎቹን እነማን እንደተከሉ በስም አላገኘንም። የሆኑ የማናውቃቸው ኢትዮጵያዊያን እናትና አባቶቻችን ተክለውታል። ስም የለም። አሁን





ግን ቢያንስ ሃምሳ ሜትር ርዝመት ያለው ዛፍ እንጦጦን ሞልቷል። በጣም ረጃጅም ናቸው። የተከሉ ሰዎች አሁን እኛ ልንዝናናበት፣ ስፖርት ልንሰራበት እንደምንጠቀም ላያውቁ ይችላሉ። በህይወት ካሉ የሚያውቁም ሊኖሩም ይችላሉ።

እኛም አሁን የምንሰራው ስራ እንዲሁ ለትውልድ ይሸጋገራል። አሁን የምንተክለው ዛፍ ነገ ልጆቻችን እያመሰገኑ በስምም ባያውቁ እንኳን የሚጠቀሙበት ስለሚሆን ከትውልድ ቅብብሎሽ አንጻርም እጅግ አስፈላጊ ስራ ነው። በወንዝ ዳር ማጽዳት ፕሮጀክቱ ምናልባት ሰሞኑን ትጎበኛላችሁ ብዬ አስባለሁ፤ እሱንም በዚህ ወር መጨረሻ ሙሉ በሙሉ ስራ እንዲጀምር ይሆናል፤ ከአምስት ሺህ በላይ ችግኞች ሳይሆኑ ትላልቅ ዛፎች ተተክለዋል። ይሄ ቦታ ገለጣ ቦታ ነበር። ሸራተን ፊት ለፊት ያለው አሁን ሲከፈት ግን ለአንዳንዶቻችሁ ግራ በሚያጋባ መንገድ በዛፍ ተሞልቷል። አምስት ሜትር፣ ስድስት ሜትር፣ ሰባት ሜትር ትላልቅ ቁመት ያላቸው ዛፎች ከያሉበት መጥተው ተተክለዋል።

በዚያ ሂደት ውስጥ የተማርነው ትምህርት አንድ ቦታ ፕሮጀክት ቀርጸን ስንሰራ ችግኝ ተክለን ሁለት ሶስት አመት መጠበቅ የግድ እንዳልሆነ ዛፎች ካሉበት ተነቅለው መጥተው፣ እንደሰው ግሉኮስ ተሰቷአቸው፣ እያንዳንዱ ዛፍ ግሉኮስ አለው፣ የሚሞት እና የሚድን ዛፍ ይለያል። ይሄን ኢትዮጵያዊያን በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቀስመውበታል። ፕሮጀክቱ ሲመረቅ ሰው ጫካውን እና አበባውን፣ ሳሩን በሚያይበት ወቅት በጣም በርካታ ሰው እናንተን ጨምሮ ሲጀመር ጀምሮ እነዛ ጫካዎች እንደነበሩ ሊያስብ ይችላል። አሰራሩ፣ ባህሪው እና ውጤቱ ያንን ስለሚያመላክት።

ነገር ግን ፕሮጀክቱ እየተሰራ ከፕሮጀክቱ ጎን ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊየን ገደማ የአበባ ችግኝ የያዙ ነርሰሪዎች ነበሩን። የትላልቅ ዛፍ ነርሰሪ እና የአበባ ነርሰሪ ነበረን፤ ከሸራተን በላይ ልክ ስራው ተሰርቶ መጠናቀቅ ደረጃ ሲደርስ እነዚያ እየመጡ ሲሰካኩ አሁን የወዳጅነት አደባባይ (Friendship Square) የምንለው ከሸራተን ፊትለፊት ያለው ፕሮጀክት እናንተም ስትጎበኙ እንደምትታዘቡት አዲስ አበባ ውስጥ የሚጎሉንን በርካታ ነገሮች የሚሞላ ነው። አንደኛው ከተማችን ውሃ የለውም፣ ሐይቅ የለውም ይታወቃል። ከአንድ ሄክታር በላይ ቦታ ላይ ሁለት ሺህ ሊትር የሚይዝ ሰው ሰራሽ ሐይቅ ተሰርቷል። ይሄን ሰው ሰራሽ ሐይቅ በማዘጋጀት ሒደት ውስጥ ትምህርት ስለወሰድን እንጦጦ ላይም መሰል ሰው ሰራሽ ሐይቅ ለመስራት መነሻ ሆኖናል። ሁለተኛው እያንዳንዱ እዛ የተቀመጡ የግንባታ ስራዎች ከሙቶ ሃያ እስከ ሙቶ አርባ ኪሎ ግራም የሚመዝኑ ለትውልድ የሚሸጋገሩ በጣም ጠንካራ የሆነ ዝም ብሎ ፓርክ የመስራት ሳይሆን ለትውልድ በሚሸጋገር መልኩ በውበትም፣ በጥራትም የተሰራ ነው።

እዚያ ቦታ ላይ በድንጋይ ስራ ውስጥ ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መገኛ መሆኗን የሚያሳይ፣ የሰው ዘር ከኢትዮጵያ ተነስቶ ወደ ተቀረው ዓለም እንዴት እንደሄደ የሚያሳይ ኪነጥበባዊ መግለጫ አለው። እዚያ ቦታ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የሁሉም ብሄሮች ብሄረሰቦች ስም ከሶስት ሙቶ ኪሎ ግራም በማያንሱና በማንኛውም ወቅት ሊፈርሱ ወይንም ሊበላሹ በማይችሉ ድንጋዮች የእያንዳንዱ ብሄር ስሙ በቪአይፒ አምፌ ተቀምጧል። ስትሄዱ ጸማይን ታያላችሁ፤ ጸማይ ማነው? ብሎ የሚጠይቅ የአዲስ አበባ ሰው ወደ ፊት አይኖርም። በኛ ውስጥ ያሉ ብሄሮች እያንዳንዳቸው በስማቸው ዛፍ ተተክሏል። ስማቸው በጉልህ





በትክክለኛው ቦታ ተቀምጧል፤ ይሄ ህብረ ብሄራዊነታችንን ለማጠናከር በእጅጉ የሚያግዝ ነው።

በቀላል አማርኛ የወንዝ ዳር ማጽዳት ፕሮጀክት ውስጥ ያለው የወዳጅነት አደባባይ በማንኛውም መመዘኛ የትም ዓለም ላይ ያለ አደባባይ ከዚህ ይሻላል ብሎ ለመናገር የሚያስደፍር አይደለም። በጥራትም፣ በገጸ ምድር አቀማመጥም፣ በያዛቸውም አጠቃላይ ኪነ ህንጻ ይዘት ምናልባት ቢሰፋ ቢጠብ ሊባል ይችል እንደሆን እንጂ ከጥራት አንጻር በጣም አስደናቂ ነው። ከመስቀል አደባባይ እስከ ቸርችል ጎዳና ድረስ የሚሰራውም ስራ እንደዚሁ። መስቀል አደባባይን በሚመለከት አንዳንድ ነገሮች ይሰማሉ፤ ዋናው የመስቀል አደባባይ ፕሮጀክት ሃሳብ የገንዘብ እጥረት ነው የያዘን እንጂ ቢያንስ ግምሽ ሚሊየን ሰው መሰብሰብ እና ለተለያዩ ሕዝባዊ ስብሰባዎችና ዝግጅቶች (occasions) ማዋል የሚያስችል ቦታ ማድረግ ነው ሃሳቡ።

የመስቀል በአል መነሻው የኦርቶዶክስ እምነት ቢሆንም አሁን በዓለም ቅርስነት በመመዝገቡ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ቅርጽ ስለሆነ በርካታ ቱሪስቶች የምንስብበት አንዱ የኢትዮጵያዊነትን ባህል እና ማንነት የምናሳይበት መድረክ በመሆኑ ያ ቦታ ለዚያ አላማ ብቻ ሳይሆን የተለያየ ሕዝባዊ ዝግጅት ቢፈጠር እስከ ግማሽ ሚሊየን ሰው እንዲይዝ፤ ግን ደግሞ ዛፍ እንዲኖረው፣ ሳር እንዲኖረው የመኪና ፓርኪንግ እንዲኖረው ታስቦ፤ በአስፓልት የምናውቀው የመስቀል አደባባይ ቦታ ከቦሌ መንገድ ጀምሮ እስከ ወደ ሜክሲኮ መሄጃ ድረስ ያለው ከመሬት በታች (Underground) በማድረግ መኪኖች በዚያ እንዲያልፉ እና ሙሉ አስፋልቱና ወደ ኤግዚቢሽን የሚወስደው ከመሬት በላይ ያለው መሔጃያ (upstairs) ሰው እንዲይዝ እና ባቡሩ

ደግሞ ያበላሸውን ቅርጽ በሚቀይር መንገድ ባቡሩ ስር ለቪአይፒ መቀመጫ እንዲሆን ነው ሙሉ ዲዛይኑ።

ያ አደባባይ የተለያየ ጉዳይ ሲኖረን በርከት ያለ ህዝብ ወጥቶ የሚጠቀምበት እንዲሆን ታስቦ ነገር ግን አስፋልትን ከመሬት በታች ማድረግ አሁን ባለው ሁኔታ ከገንዘብ አንጻር ስላልተቻለ በስሩ ከአንድ ሺህ በላይ መኪና ፓርክ መያዝ እንዲችል ተደርጎ፣ ከላይ ዛፎችና ሳሮች እንዲኖሩት ሆኖ፣ አሁን ያለውን አቅም በያዘ መንገድ ተመልሶ ለመስቀል እንዲደርስ ነው እየተሰራ ያለው። እሱ ፕሮጀክት ግን እስከ ቸርችል ጎዳና ይሄዳል። እስከ ማዘጋጃ ቤት ድረስ ይሄዳል። ባለፈው አመት ከቦሌ እስከ አራት ኪሎ ሰርተናል፤ አሁን ደግሞ ወደ እዚያ እያሰፋን ነው ያለነው።

እዚህ ያላችሁት እንድትገነዘቡ የምፈልገው ነገር አዲስ አበባንም መቀየር ያስፈልጋል፤ አካባቢውንም መቀየር ያስፈልጋል። አካባቢን መቀየር መድከም መቆሸሽ ይፈልጋል፤ መሬት መንካት ይፈልጋል። ስናድስ ማፍረስ ይፈልጋል። ምንም ነገር ሳይፈርስ የተሻለ የሚያምር መሆን አይችልም። በተለይ በተገቢው ብቃት ካልተገነባ የተገነባ ደግሞ ከሆነ በየጊዜው እድሳት ማድረግ ያስፈልጋል። ይሄንን ስናደርግ በሶስት አራት አመት ውስጥ አዲስ አበባ ውስጥ በጣም በርካታ ፓርኮች፣ መዝናኛ ቦታዎች ይፈጠራሉ። ልጆቻችን ለብዙ ነገር የሚደመሙ የሚገረሙ አይሆኑም። ለምሳሌ በአንድነት ፓርክ  የተሰራው የእስሳት ማቆያ (zoo) አዲስ አበባ ላይ የተለያየ አእዋፋት ለማየት እድል ይሰጣል። እንዲህ እያደረግን ከተፈጥሮ ጋር እየተዋሃድን ስንሄድ ብልጽግናችን እውን ሊሆን ይችላል።





ይህንን ስራ የአንድ ክረምት ስራ ሳይሆን ቀጣይነት የሚጠይቅ፣ በሃገር ብልጽግና ውስጥ በሁሉም መስክ ተጽዕኖ የሚያመጣ፣ በጣም አስፈላጊ ስራ እንደሆነ ማሰብ ያስፈልጋል። የመንግስት ሃላፊዎች ህዝብን ለማገልገል ኮንትራት ስንወስድ ከተሰጡን ግዴታዎች አንዱ የህዝቡን ህይወት ማዘመን-ማሻሻል፣ የሚመለከቱትን ስራዎች ማቀድ እና መስራት ነው። ታዋቂ ሰዎችና በዚህ ስራ ብትሳተፉ ብለን የለየናችሁ ሰዎች ደግሞ በብዙ መልኩ ከግል ጥቅም፣ ከግል ስራ ያለፋችሁ በሃገር ጉዳይ ላይ ከተቀጠርነው ሰዎች ባልተናነሰ የሚመለከታችሁ በዚህ ጉዳይ አመራር ብትሰጡ፣ ትውልድ ብታቀኑ ለእናንተም ክብር-ኩራት፣ ለሃገራችሁም ጥቅም ነው ብለን ያሰብነውን ሰዎች ነው የሰበሰብነው። የቀሩ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ተጨማሪ ቢጨመሩ የበለጠ ጥቅም ያለው፣ ግን እኛ ካለማወቅ ወይንም ከጥድፊያ የተነሳ የዘነጋናቸው ሰዎች ካሉ በሂደት እያከልን እንሄዳለን።

ዘንድሮ ያለው የዝናብ ግምት  ከመደበኛው በላይ ልናገኝ እንደምንችል እንጠብቃለን፡፡ አምና ከብዙ አመት በኋላ ከፍተኛ ዝናብ አግኝተናል። የበልግ ዝናብ እንደምታዩት በጣም ቆንጆ ነው። ዐየር ንብረቱም በብዙ መልኩ ጥሩ እየሆነ መጥቷል። የዘንድሮ የክረምት ዝናብ መጠቀም ከቻልን፣ ከተከልን እና አብዛኛው ከያዘ ከሁለት ሶስት አመት በኋላ በዝናብ መጠናችንም፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በሚያጨቃጭቁን አብዛኛው ኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይም አዎንታዊ ተጽዕኖ ስለሚኖረው በሙሉ እና በሃላፊነት ስሜት ይሄን ስራ በማሳካት ውጤታማ እንድንሆን ታስቦ ነው የዛሬው መነሻ መድረክ የተዘጋጀው። ከአምናው በተሻለ ሊያግዙን የሚፈልጉ በርካታ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች አሉ። በበጀትም በሃሳብም እነሱን እንጠቀማለን።

ከአምናው በተሻለ በጣም በርካታ ወጣቶች ሊሳተፉ እንደሚችሉ ይጠበቃል። የሚዲያ ሰዎችም ከዚህ አንጻር ሰፊ ስራ ሊሰሩ እንደሚችሉ ይጠበቃል። ይሄንን ነገር በማከናወን መጻኢ የኢትዮጵያን እጣ ፈንታ ማዘመን-ማበልጸግ እንድንችል ነው የዘንድሮ የአረንጓዴ አሻራ ቀደም ብለን ተዘጋጅተን እንድንጀምር ያስፈለገው። የኮሚቴው ስራ የክልል አመራሮች ስላሉ በየክልሉ መጀመሪያ ነርሰሪዎችን መጎብኘት ይሆናል። ዝግጅቱ አለ ወይንስ የለም የሚለውን መጎብኘት ያስፈልጋል። ተከፋፍለን እነሱን መጎብኘት፤ አዲስ አበባ ያሉትን ፕሮጀክቶች መጎብኘት ይገባናል፡፡ ይሄ ምን ያክል አረንጓዴ አካባቢ ዛፍ መትከል መዝናናት ብቻ ሳይሆን ለእይታ ያለውን ትርጉም ያሳውቀናል፡፡ አሁን በጀመርነው ብንቀጥል ደግሞ በሌሎች ሃገሮች ከምንቀና በሃገራችን ማየት የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር እንደምንችል፤ ከመቶ ሚሊየን በላይ ህዝብ ያለው ሃገር እንደነዚህ አይነት ትላልቅ ሃሳቦች ወስዶ ለመከወን የሚችል መሆኑን እናሳያለን።

ከዓለም አቀፍ ሁኔታ አንጻርም ብዙ ጊዜ የምንለምን ሳይሆን አዳዲስ ነገሮች አስበን፣ ሰብሰብ ብለን፣ ተጋግዘን በማከናወን ለሌሎች ትምህርት መስጠት የምንችል መሆኑን እናሳያለን። እነዚህ ይደማመሩና የምንፈልገውን ሃገር፣ የምንፈልገውን ሁኔታ ይፈጥራል።

ይሄ ማለት ችግኝ ስንተክል ሁሉም ችግኝ ይበቅላል ማለት አይደለም፤ ልጅ ሲጸነስ ሁሉም ይወለዳል ማለት አይደለም፤ ሁሉ ቢወለድ ሁሉ ያድጋል ማለት አይደለም፤ ሁሉ ቢያድግ አባት እናት ይጦራል ማለት አይደለም። የጎረቤት ልጅ አባት እናቱን ስላልጦረ መውለድ እንደማንተወው ሁሉ ችግር እና ፈተና ባየን ጊዜ አንቆምም፤ እየተጋፈጥን፤ እየሰራን፣ እየለወጥን አሻራችንን ማሳረፍ ነው የሚጠበቅብን። ኮሮና አለ፤ በጣም በርካታ እንቅፋቶች ሊነሱ ይችላሉ።





በዚህ ውስጥ ግን ዛፍ እንተክላለን፤ በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ ጥንቃቄ እያደረግን ዛፍ እንተክላለን። ሌላ የሚያጋጥመን ፈተና ካለ ፈተናውን እየተቋቋምን እንተክላለን። ሁለቱ የማይተካኩ፣ አንዱ አንዱን የማይሸፍን፣ ነገር ግን ሁለቱም ለየራሳቸው የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ስለሆኑ።

ስለዚህ እንደ ፈተና የሚታዩት ከበጀት፣ ከበሽታ ሁኔታ እና ከአጠቃላይ ከጂኦፖለቲክሱ ጋር የተገናኙ ሁኔታዎችን ማንሳት ይቻላል። ሁሉንም ተቋቁመን፣ ለሁሉም በቂ የሆነ የሰው ሃይል ስላለን፣ ዘርፈ ብዙ ዐቅሞችን የሚጠቀም አመራር በመገንባት ከሰራን ሁሉንም በድል መወጣት እንችላለን። ከዚህ አንጻር የዛሬው ኮሚቴ ከአምናው በተሻለ ከፍተኛ ዝግጅት አድርጎ ለሃገርም ለራሱም ኩራት የሆነ ስራ እንዲሰራ ይጠበቃል። ለዜጎቻችን እንደ አምናው 40 ችግኝ በነፍስ ወከፍ ልንል እንችላለን፤ የኮሚቴ አባላት ግን ቢያንስ 100 ችግኝ በነፍስ ወከፍ ይጠበቅባችኋል። ስለዚህ የክልል አመራሮች ታዋቂ ሰዎችን የምናስተምረው እየተከልን ነው።

አሁን ባለው ጥናት አንዱ ዛፍ ሲቆረጥ ለሌላኛው መልዕክት ይልካል፣ ይነጋገራሉ፤ ጥቃት እየመጣ ነው። በብዙ መልኩ መደመርን፣ በብዙ መልኩ ትብብርን፣ በብዙ መልኩ የመተባበር ሃይል የማይፈርስ፣ የማይጎዳ፣ የማይጠቃ መሆኑን ከዛፍ መማር ይቻላል። ከሰው ጋር የምናጠፋውን ጊዜ፣ ፌስቡክ ላይ የምናጠፋውን ጊዜ ቀንሰን ውሏችንን ችግኝ ጋር ብናደርገው ስንለምደው ያው ጣዕሙ ይገባናል።

የዛፍ አንዱ ጥቅሙ ከተንከባከብከው አይክድህም። አስተምረህ አስተምረህ ስራ ሲይዝ እንደሚከዳህ ሰው አይደለም። ከተንከባከብከው ላንተም፣ ለአላፊ አግዳሚውም ጥላ ይሆናል። ፍሬ

ይሰጣል። የተንከባከበውን የሚከድ አይደለም። ዛፍ ተክሎ፣ ቡና ተክሎ ተንከባክቦ የሚከስር ሰው የለም። ጥቅም አለው። በብዙ መልኩ፣ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድም እየተረጋገጠ የመጣ ስለሆነ፣ ልክ እንደ ዘመቻ ስራ ሳይሆን እንደ ኑሮ ዘይቤ መያዝ አለብን። በጣም ጠቃሚ ነገር ስለሆነ መኪና ከመንዳት ቀንሰን፣ ላፕቶፕ ላይ የምናጠፋውን ሰዓት ቀንሰን የተወሰነ ጊዜ ከዛፎች ጋር ማሳለፍ፤ የጓሮ አትክልቶችን እንደ ቃሪያ፣ ሽንኩርት፣ ቲማቲም መትከል እና ኦርጋኒክ ነገር መመገብ፤ ያው የምታውቁት ነው ጥቅሙ።

ይሄንን ባሕል ማስፋት ያስፈልጋል። በትክክልም ደግሞ ያቀራርባል። አብረን እየተጫወትን፣ እየዘፈንን፣ እየዘመርን ሄደን፣ ተክለን ስንመለስ አብረን ስንበላ፣ አብረን ስንጠጣ፣ ከዚያም ካለፈ ጭቃውን ስንረጫጭ፣ ያ ሁሉ በጣም የራሱ የሆነ ነገር ስላለው ጠቃሚ ነው እንደተባለው ያስፈልጋል።

የዛፍ ችግኝን በሚመለከት ለምሳሌ አቡዳቢን ብንወስድ አርባ ሚሊየን ችግኝ ነው ያላቸው፤ ከሁለት ሚሊየን ጀምረው አርባ ደርሰዋል። አሁን ባለው በሚያነሱት ሃሳብ "ከአርባ በላይ መሄድ አንችልም፤ ምክንያቱም በጣም ከፍተኛ ውሃ ይጠይቃል። ከፍተኛው እዚያ አከባቢ ነው" ብለው ያስባሉ። እኛ ደግሞ በቀን ምን ያክል እንደምንተክል ታውቃላችሁ። ይሄንን የተሰጠንን እድል በመጠቀም ለልጆቻችን በመትከል፣ በማስዋብ፣ በማንጻት ማስተማር ከቻልን በሚቀጥሉት አስር አመታት ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የኑሮ ዘይቤ ለውጥ ማምጣት የሚያስችል ልምምድ ሊኖረን ይቻላል። ወደ ውጪ ሃገር ያለውንም ምልልስ በተለይ መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች ወደ ሞምባሳ ወደ ዱባይ የሚያደርጉትን የጉብኝት ጉዞ መቀነስ ይቻላል። ለዚህ የሚመቹ በጣም በርካታ ነገሮች አሉ። እንጀምረው፣ እንስራው ውጤቱ





በራሱ ሃይል እያበዛ ስለሚሄድ በዚያ መንገድ ስኬታማ መሆን ይቻላል።

የአማራ ክልል ልምድ ጠቃሚ ነው፤ በኦሮሚያም፣ ቤኒሻንጉልም በሶማሌም፣ በአፋርም በጣም ጥሩ ጥሩ ስራዎች አሉ። እሱን ሰብሰብ አድርገን በሃገር ደረጃ የዘንድሮውን ችግኝ ህዝባችንን በሚያቀረርብ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን በሚያሳልጥ፣ የዝናብ ወቅትን በማያሳልፍ፣ ከኢኮኖሚ አኳያ አዋጭ በሆነ፣ ብዙ ብክነት የማያስከትል፣ ኪሳራን የቀነሰ፣ በሂደት የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን በሚያደርግ መንገድ ለማሳካት እንረባረብ። ከእናንተ የሚጠበቀው ማስተማር፣ መትከል፣ ማሳየት፣ ያን ካደረግን ካለምንም ጥርጥር እናሳካዋለን የሚል እምነት ነው ያለው።

የዓለም አቀፍ ተቋማትም ከወትሮው በተለየ ድጋፍ አላቸው። አምና ፈራ ተባ እያሉ ትንሽ አግዘውናል። ዘንድሮ ግን ብዙዎቹ ቃል እየገቡ ስለሆነ እንጠቀማለን፤ ችግኝ እንተክላለን፡፡ በችግኝ ምክንያት ገንዘብ እናመጣለን፤ በችግኝ ምክንያት ዶላር እናመጣለን። ለሰዎች የስራ እድል እንፈጥራለን። ስፖርት የማይወዱ ሰዎች በዚያው አሳብበው ስፖርት እንዲሰሩ እናደርጋለን። ኢትዮጵያን አረንጓዴ የማድረግ እና የዝናብ ፍላጎቷን እናሳድጋለን።

የኢትዮጵያ ዝናብ ከተቋረጠ ግድብ ቢሰራም ባይሰራም ውሃው ይደርቃል። በቀጣይነት ውሃ ማምረት መቻል አለብን። እኛ ያን ለማድረግ ደግሞ ትልቁ መፍትሔ ዛፍ መትከል ነው። ለኛም ለሌሎችም። ሌሎች ያን ስላማያውቁ ነው የማያደርጉት የሚለውን ግምገማ ለእነሱ ትቼ፣ እኛ ግን በማንም ላይ ጥገኛ ሳንሆን፤ ስለሚጠቅመንና ስለሚያስፈልገን ተረባርበን በመትከል አምስት ቢሊየን

እናሳካለን። ከዚህ ተምረን በሚቀጥሉት ሁለት አመታት ደግሞ ተጨማሪ ስራ በመስራት ከባቢ አየሩን ለማስተካከል ጥረት ይደረጋል። እየተከልን ነው የምናስተምረው፤ ሌላ መንገድ የለም። "ችግኝ ትከሉ" ብቻ ሳይሆን "ችግኝ እንተከላለን"፤ እኛ ስናስተምር የሚያውቁን ሰዎች፣ እኛ በተለያየ ነገር ስማችንን ከፍ አድርገው የሚያነሱ ሰዎች፣ መከተል ስለሚፈልጉ እያዩ እንዲከተሉን እናደርጋለን። በዚህ መንገድ የዘንድሮውን ክረምት በቂ ዝግጅት ስላደረግን ውጤታማ ስራ እንደምንሰራ ይጠበቃል። በተባበረ ክንድ የዘንድሮውን ዝናብ ወቅት ሳናበላሽ መጠቀም እንድንችል አደራ እላችኋለሁ።

**አመሰግናለሁ!!**





# ኢትዮጵያ፡- አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት

**ሰኔ 10፣ 2012 ዓ.ም.**

የአስር አመቱ እቅድ ዋነኛ እሳቤ እና አላማ ወጥ የሆነ ሃገራዊ ራእይ፣ ወጥ የሆነ ሃገራዊ እሳቤ እና ቋንቋ ኖሮን ያንን ለማሳካት እያንዳንዱ ክልል፣ እያንዳንዱ አካባቢ የራሱ ብልጫ ያለው ቢሆንም ያለውን ብልጫ ይበልጥ ተገንዝቦ እና አሳድጎ ሃገራዊ ራእይን ማሳካት እንዲችል ታስቦ፣ አመቱን ሙሉ ሲሰራ የነበረ ስራ ነው። የእቅዱ ዝግጅት እና አሁን ያለበት ደረጃ መጨረሻ የሰማሁት ክቡር አቶ አወል ያነሱት ሃሳብ ራሱ አስተቃቀዱ ያንን ችግር የሚፈታ ነው።

ከዚህ በፊት የነበረው ዓመታዊ የሀገር ውስጥ የምርት መጠን (GDP) እቅድ ዝግጅት፣ ልምምድ በፕላን ኮሚሽን ያሉ እቅድ የማዘጋጀት ልምድ ያላቸው ሰዎች እቅድን ካዘጋጁ በኋላ እንደ ሌሎች የፖለቲካ ሰነዶች አመራር ተሰብስቦ በገለጻ የሚነገረው እና ያንተ እቅድ፣ ያንተ ተግባር ይሄ ነው መባል አለበት። አለበለዚያ በባለቤትነት አይቀበለውም፤ ከእሱ የመነጩ አይደሉምና። በዚያ ምክንያት በስድስት ወርም በአስር ወርም ሲሰበሰብ እንደ አዲስ አስታዋሽ ነጋሪ ይፈልጋል። የራሱን ሴክተር እቅድ ሌላ የሚነግረው አካል ከሌለ በስተቀረ

የሞያተኞች ጉዳይ አድርጎ ስለሚወስደው እያንዳንዱ ተቋም እና ሴክተር በባለቤትነት አይረከበውም።

ያን ለመፍታት በዚህ አመት መጀመሪያ ያደረግነው የፕላን ኮሚሽን ለብቻ እቅድ እንዲያዘጋጅ፤ እነዚህ በዋና ዋና ያነሳናቸው የልማት ሴክተሮችም እቅድ እንዲያዘጋጁ ካደረግን በኋላ የአስር አመት የሚባለው የልማት ኮሚሽን እቅድ እና እያንዳንዱ ሴክተር ከራሱ ሁኔታ አንጻር ያዘጋጀው እቅድ የሚቀራረብ አልነበረም። ቅድም እንዳልኩት የሞያ፣ የቁጥር እና ጥቅል አይነት አካሄድ ይለካበት የነበረውን ልምምድ በመቀየር ከፕላን ኮሚሽን ሞያ እና የአስተቃቀድ ጥበብን ከነሱ አንጻር እንዲቃኙ፤ አቅማቸው ማደግ በሚገባው ልክ እና መደረስ የሚጠበቅባቸውን ደረጃ እንዲቃኙ አስር፣ አስራ አምስት ውይይቶች ከተደረጉ በኋላ ነው የአስር አመቱ የሃገራችን እቅድ የተዘጋጀው።

እቅዶቹ 5 ዋና ዋና ምሰሶዎች አሏቸው ማለት ሌሎች የሚያስፈልጉ እና ትኩረት የሚሰጣቸው የሉም ማለት አይደለም። ዋናው አምስቱ ምሰሶዎች ሌሎች በልካቸው ሚዛን የሚሰጣቸውን ጉዳዮች አቅፈው የምናስበውን እውነተኛ ብልጽግና ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ምሶሶዎች ናቸው ለማለት ነው። ለምሳሌ ከዚህ ቀደም ከግብርና ወደ ኢንደስትሪ፣ ከኢንደስትሪ ወደ ምናምን የሚባል የሌለን ነገር የማወዳደር ጉዳይ ነበር። ኢትዮጵያ ውስጥ ግብርና ካረስነው መሬት ያላረስነው፣ ከተጠቀምንበት ጉልበት ያልተጠቀምነው፣ ከተጠቀምንበት ውሃ ያልተጠቀምነው በልጦ እያለ ከግብርና ወደ ኢንደስትሪ የሚባለው ንግግር ውሃ አይቋጥርም። ምክንያቱም ግብርናው ስላልተሰራ ሽግግር የሚባለው ነገር የሚታሰብም የሚታለምም ነገር አይደለም።





ሁለተኛ ሽግግር ሳይሆን እያንዳንዱ ምሶሶ በከፍተኛ ሁኔታ አደገ ሲባል ማደግ የሚችለውን ልክ የሚያሳይም አይደለም። በዚህ ምክንያት ግብርና ስንል ግብርና የሚፈልገው ጉልበት፣ የሚፈልገው እውቀት፣ የሚፈልገው ካፒታል፣ የሚፈልገው ግብአት፣ የሚፈልገው መሰረተ ልማት ራሱን ችሎ ዘርዘር ብሎ መታየት የሚገባው እና የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው። በበረኻማ አካባቢዎች የጀመርናቸው ስራዎች፣ በኋላም በመሰረተ ልማት ያነሳችሁት መልሶ ግብርናው ራሱ የራሱ የሆነ መሰረተ ልማት ይፈልጋል። ግዙፍ የሆነ አውራ ጎዳና መንገድ ወይም የአየር ማረፊያ ግንባታ ሳይሆን የግብርና መሰረተ ልማቶች የሚባሉ አሉ። ሰፋፊ እርሻዎች ውስጥ የሚሰራው የመስኖ ሥራ የሚጠይቀው ኢነርጂ፣ የሚያልፍበት ቦይ፣ የሚፈልገው የግንባታ አይነት ከመንገድ ስራ ጋር አንድ እና ያው አይደለም። በመሆኑም ግብርናን ማሳደግ፣ ማሻሻል፣ ማዘመን ስንል በእሱ ሴክተር የሚጠበቀውን የመሰረተ ልማትና የፋይናንስ አቅርቦት፣ የእውቀትና የማድረግ አቅም በአጠቃላይ ታሳቢ ያደረገ ይሆናል።

ኢንደስትሪም እንደዚሁ ገና ዳዴ ያለ በጅምር ላይ ያለ፣ ቢሰራበት ትልቅ ዐቅም እንዳለ የሚያመላክት፣ ነገር ግን ከኢንደስትሪ አንጻር እዚህ ግባ የሚባል ስራ ሰራን ማለት የማያስችል ነው። ኢንደስትሪውን ከፍ ያደረገው የኮንስትራክሽን ሴክተር ነው። የኮንስትራክሽን ሴክተር ደግሞ በምን እድገቱን እንደምናይ አጠያያቂ ቢሆንም የኮንስትራክሽን ሴክተር መሰረታዊ እሳቤ እና አላማዎችን የሚያሳካ አይደለም። ለምሳሌ መንገድ ስንል ለሃያ ሰላሳ አመት የሚሰራ እንጂ ተሰርቶ በወሩ የሚፈርስ ማለት አይደለም። እድገት እንለዋለን፤ ነገር ግን አላማውን መልሶ የሚያሳካ መንገድ አይደለም።

ህንጻ ስንል ሁሉንም አገልግሎት መስጠት የሚችል፣ ንጹህ ሽንት ቤት ያለው፣ ውሃ ያለው፣ ቢዘንብ የማያንጠባጥብ፣ ድምጽ የማያሰማ ማለት

ነው እንጂ ፀሃይ ሲሆን ጥሩ ህንጻ፣ ዝናብ በሚሆንበት ጊዜ የሚያፈስ፣ አዳራሹ ውስጥ ሲገባ ምንም የማይል ግን ደግሞ ወደ መጸዳጃ ቤት ሲኬድ ውሃ የሌለው ከሆነ ህንጻ አይደለም። ግን እድገት ይባላል፤ እና የኮንስትራክሽን ሴክተሩ የሚጠበቅበትን አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ብቃት አልነበረውም። በተለይ ከጥራት አንጻር የመንግስት ፕሮጀክቶች ብቻ ሳይሆን የራሱን ቤት፣ የራሱን ህንጻ የሚገነባ ሰው ጭምር ለትውልድ የሚሸጋገር እና ጥራት የሚሻ ጉዳይ አድርጎ አይወስደውም። ይሄ መቀየር ይኖርበታል።

ከማእድን አንጻር ያው ይነገራል፤ ነዳጅ፣ ወርቅ፣ የማይነገር ነገር የለም። የትኛውም ሴክተር ወጥቶ በሃገር ኢኮኖሚ ውስጥ መጫወት የሚገባውን ሚና እንዲጫወት አላደረግንም። ነዳጅ ሳይወጣ የምንጣላው የማን ይሁን ብለን ነው፤ ፖታሽ ሳይወጣ የምንጣላው የማን ይሁን ብለን ነው፤ ወርቅ ሳይወጣ የምንጣላው የማን ይሁን ብለን ነው። እንጂ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በጂዲፒያችን ላይ በሚኖረው ትስስር "ሃገር ያድጋል? በእዚያ ውስጥ እንጠቀማለን?" የሚል እሳቤ ገና አልተገነባም።

ከቱሪዝም አንጻር ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያስፈልገው "አምስት ኮከብ ያለው ሆቴል እሰራለሁ እና ዲውቲ ፍሪ እቃ እንዳስገባ ፍቀዱልኝ" ለማለት ካልሆነ በስተቀረ ለአገልግሎት ባህሉ የሚያስፈልጉት ተቋማት ሪዞርትን ጨምሮ በአጠቃላይ ጥሩ አገልግሎት መስጫ የለም። የሚታይ ብዙ ነገር አለ፤ ዐቅም አለ፤ ስራው ግን ውስንነት አለበት።

አይ.ሲ.ቲም እንደዚሁ። አይ.ሲ.ቲ ሲባል ቴሌኮሚኒኬሽን፣ አንድ ሰው ከሌላ ሰው የሚገናኝበትን የስልክ ቁጥር ማሳደግ ብቻ ከሆነ፣ አይ.ሲ.ቲ በኢትዮጵያ ውስጥ በኢኮኖሚ ውስጥ ውጤታማ ስራ አይሰራም። እኛ አይ.ሲ.ቲ የምንለው ከትናንሽ ንግድ ጀምሮ እስከ ትላልቅ የኤክስፖርት





ስራዎች የሚያስተሳስር እና ሰው በቀላሉ የሚነግድበትን፣ የስራ የሚያገኝበትን፣ ስራ የሚፈልግበትን መንገድ የሚያቀራርብ አውድ እንዲሆን እንጂ የኮሚኒኬሽን ስራ ብቻ እንዲሰራ አይደለም። የኮሚኒኬሽን ስራ ከሰራ የቴክኖሎጂውን ውጤት እና አስፈላጊነት ሙሉ ነገር የሚያስገኝ አይሆንም።

ስለዚህ አይ.ሲ.ቲ አልተሰራም ሲባል፣ ጀማሪ የቢዝነስ ተቋማት ቨርቹዋሊ ትናንሽ ስራዎችን አቀናጅተው ለገበያ እያቀረቡ፣ ካፒታል ያለው ሰው እያገዛቸው፣ ፕሮቶታይፕ እየተሰራ፣ ያ ወደ ከፍተኛ ምርታማነት የሚወስድ እና በሃገር ውስጥም በውጪ ገበያም ላይ የሚጨበጥ ሃብት እንዲያመጣ ማስቻል ነው። ለዚያ መሰረታዊ የሆነ መሠረተ ልማት በመንግስትም በግልም እንዲገነባ፤ ባህሉም እንዲፈጠር፤ ልክ አሁን ፌስቡክ በከፍተኛ ደረጃ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈለግ እንደሆነው ቴክኖሎጂን በመሰረታዊ ነገሩ መጠቀም የሚያስችል የንግድ ስርአት፣ የፋይናንሻል ስርአት፣ ሌላው ቀርቶ የግብርናን ስርአት የሚያስተዋውቅበት መንገድ ከዛ ጋር ቢተሳሰር በብዙ መንገድ ኢኮኖሚያችንን ሊያሳድገው ይችላል።

በዚህ እቅድ ውስጥ በጣም አጓጊ የሚባል እና ለመተግበር የሚያሳስበው አንዱ ኢነርጂ ሴክተር ነው። የኢነርጂ ሴክተር እቅዳችን አጓጊ ነው ሲበዛ። እንግዲህ ይህን እቅድ በኢነርጂ ሴክተር ለማሳካት ከፍ አድርገን ያሰብንበት ዋነኛው ምክንያት አንደኛ - ያለንበት ቦታ ዝቅ ማለት ነው፤ ሁለተኛ በሴክተሩ ያለ ቴክኖሎጂ በመለወጡ ነው። ለምሳሌ ከፀሐይ ብርሃን የሚገኝ ኃይል (ሶላር) የዛሬ አስር አመት ከነበረው ዋጋ እና ውድነት ዛሬ በአንድ አስረኛ ቀንሷል። በከፍተኛ ደረጃ ቴክኖሎጂው አድጓል፤ ዋጋው ቀንሷል። ሶላርን በስፋት ለመጠቀም የሚያስችል ሁለንተናዊ ዐቅም ኢትዮጵያ ውስጥ አለ።

ከእንፋሎት የሚገኝ ኃይል (ጂኦተርማል) ለመጠቀም የሚያስችል አቅምም አለ። ሌላውን ሴክተር እንኳን የምታውቁት ነው። ከግድብ የሚገኝ ኃይልም (ሃይድሮ ፓወር) ቢሆን ቢያንስ ካለን አጠቃላይ እምቅ ዐቅም ሃምሳ በመቶ እንኳን ስንደርስ አሁን ካለን በብዙ እጥፍ የኢነርጂ አቅማችንን የሚያሳድግ ይሆናል።

መዋዕለ ንዋይ የማፍሰስ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች በሃይድሮ ውስን ፍላጎት የነበረ ቢሆንም በሶላር ከፍተኛ ፍላጎት አለ፤ በጂኦተርማል ከፍተኛ ፍላጎት አለ። አሁን አሁን ደግሞ በሃይድሮ ለመሳተፍ የሚታዩ ፍላጎቶች ስላሉ በመንግስትም በግልም ተረባርበን ከሰራን ከቴክኖሎጂው እድገት ጋር የኢነርጂ ፍላጎታችንን ማሳካት እንችላለን። ካላሳካንስ? ግብርናው ባልነው ልክ አይዘምንም።

የመስኖ ሥራ ኢነርጂ ይፈልጋል። ኢነርጂ ካላገኘ ውሃ ይቆራረጣል፤ ውሃ የሚቆራረጥ ከሆነ ግብርናው ይበላሻል። ኢነርጂ ከሌለ ኢንደስትሪ አይታሰብም፤ ኢነርጂ ከሌለ አይ.ሲ.ቲ አይታሰብም፤ ኢነርጂ ከሌለ ቱሪዝም አይታሰብም። ምሶሶ ያልናቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ሁሉ መንገድ ትራንስፖርት እንደሚፈልጉት ሁሉ፥ ኢነርጂ ደግሞ በጣም በከፍተኛ ደረጃ ይፈልጋሉ። እሱን ካላሟላን ሌላውንም ስለሚያበላሽብን ትንሽ የተጋነነና ሲያዩት የሚያማልል እቅድ ነው።

ከሰው ሃይል ልማት አንጻር የወሰድን እንደሆን በቁጥር ሰፊ ስራ ስንሰራ ቆይተናል። አሁን ጥራት ላይ ማሰብ የሚችል፣ መፍጠር የሚችል፣ ቀናኢ አስተሳሰብ ያለው፣ በማድረግ ዘመኑን የሚያጠፋ፤ ለሌብነት፣ ለጥፋት የማይነሳሳ ትውልድ ከፈጠርን ሰፊ ሕዝብ ስላለን ወደ ከፍተኛ ልማት ሊገባ ይችላል የሚል ነው።





## የተከበራችሁ የክልል አመራሮች፣

በአጭሩ እንድትገነዘቡ የሚያስፈልገው፥ እያንዳንዱ ሴክተር፣ እያንዳንዱ ኢንቨስትመንት የሁሉም ክልል ፕሬዝደንት ማየት ያለበት በጂዲፒ ላይ ምንድነው የሚያመጣው ውጤት? የሚለውን ነው። በጂዲፒ ላይ ውጤት የማይጨምር ኢንቨስትመንትም ይሁን፣ ልመናም ይሁን፣ ማንኛውም ስራ በማክሮ ደረጃ ምንም አስተዋጽኦ አይኖረውም። የሚመጣው ካፒታል በምን ያህል ጂዲፒያችንን ከፍ ያደርገዋል? የሚለውን እያንዳንዱ ክልል መገንዘብ ይገባዋል።

የእያንዳንዱ ክልል ጂዲፒ አበርክቶው መታወቅ አለበት። የተድበሰበሰ የሚባል የኢኮኖሚ ስርአት ለፌደራል ስርአት አይሰራም። ኦሮሚያ በኢትዮጵያ ጂዲፒ ውስጥ አበርክቶው ምንድነው? አፋር ምንድነው ያበረከተው? ሶማሌ ምንድነው ያበረከተው? ሁሉም የራሱ ክልል ጂዲፒ ማወቅ አለበት። ከዚያ ባሻገር ያለውን ደግሞ ለሀገር ያለውን አበርክቶ በግልጽ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚታወቅ መሆን አለበት። የተቀላቀለ፣ ዝም ብሎ በጀት ሲጸድቅ ብቻ የምንነጋገርበት መሆን የለበትም።

ሁለተኛው - እያንዳንዱ ክልል የሚያወጣው እቅድ በሃገር ደረጃ ካወጣነው እቅድ ጋር የሚናበብ መሆን አለበት። ወጥ መሆን አለበት፤ ሌላ ራእይ የለንም። ራእያችን **"በአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት የሆነች ሃገር"** መፍጠር ነው። አፋር በቱሪዝም፣ በግብርና፣ በማእድን የተቀመጡ ራእዮችን ካሳካ፣ ቤኒሻንጉል ካሳካ፣ ጋምቤላ ካሳካ፣ ያ ሲሰናሰል ኢትዮጵያ የብልጽግና ተምሳሌት የመሆን ፍላጎቷ እውን የሚያደርግ ይሆናል። በተለያየ እቅድ፣ የማናውቃቸው የቴክኒካል ሰዎች በአቀዱት እቅድ፣ ኢንቨስት ቢደረግም ባይደረግም በክልላችሁ ጂዲፒ ውስጥ ያለውን ሚና የማትገነዘቡ፣ በሃገር ደረጃ ያለውን ሚና

የማትገነዘቡ፣ በሃገር ደረጃ ያለውን የማትገነዘቡ ከሆነ የምንፈልገውን ነገር አናሳካም። ስለዚህ ጂዲፒ ላይ ያለው ውጤት በቃሉም ጭምር የሚያውቀው መሆን አለበት። ልክ ስራ አጥነትን ለማወቅ እንደምንሞክረው፣ ድህነት ቅነሳን ለማወቅ እንደምንሞክረው፣ የታረሰ መሬትን ስፋትን በሄክታር እንደምንገልጸው፣ የማዳበሪያ ስርጭትን ለመግለጽ እንደምንሞክረው፣ አመታዊ በጀታችንን እንደምንገልጸው ሁሉ፥ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ ውስጥ ለውጡን ማወቅ እና መምራት ይጠበቅብናል።

በዩኒፎርም የእቅድ ወይንም የሚቀራረብ የእቅድ ሰነድ ከመያዝ በተጨማሪ እያንዳንዱ ክልል ትኩረት ማድረግ የሚገባው ከምሶሶዎቹ በተጨማሪ ጥራት ላይ ነው። በግብርና ጥራት፣ በኢንዱስትሪ ጥራት፣ በቱሪዝም ጥራት፣ በኮንስትራክሽን ጥራት ከሌለ ለትውልድ አይሸጋገርም። ዘንድሮ መስኖ ብለን ኢንቨስት አድርገን ሁለት ዓመት ካመረተ በኋላ ሲስተሙ የሚበላሽ ከሆነ አዲስ ኢንቨስትመንት ይጠይቃል። እያንዳንዱ ፕሮጀክት የሚጠበቅበትን ጥራት የያዘ መሆኑን፣ ጥራቱ በየትኛውም የአይን መመዘኛ የሚስብ፣ የማያሳፍር መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ሁለተኛው - የፕሮጀክት አፈጻጸም ነው። በዚህ አመት መቶ ሺህ ሄክታር የበረኻ ስንዴ እናመርታለን ካልን ማምረት ነው ያለብን። ጊዜው ሲደርስ ዘጠና፣ ሰማኒያ፣ ሰባ አድርገን ላለመስራት፣ ላለማሳካት ምክንያት የምንደረድር ሳንሆን ለማሳካት እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን ሰብረን የምናልፍ ነው መሆን ያለብን። በቀላሉ የሚሳካ ምንም ነገር የለም። አድካሚ እና አስቸጋሪ ነው። ያንን ለማሳካት ሰበብ እንዳይኖር ማድረግ ያስፈልጋል።





ሶስተኛው አመለካከት ነው። እኛም፣ በየክልላችን ያሉ ሰዎችም ለልማት፣ ለብልጽግና፣ ለእድገት ያላቸውን እሳቤ ከፍ የሚያደርግ “ድህነትን እንዋጋለን፣ ድህነትን እናጠፋለን” የሚሉ ከድህነት ጋር የተቆራኙ ቋንቋዎች ተቀይረው “ወደ ብልጽግና እንሄዳለን፣ እንበለጽጋለን” በሚል መተካት አለባቸው።

አካባቢ ጥበቃን ብቻ ብንወስድ ዓለም ላይ ከሁለት መቶ ሃገራት በላይ ያሉ ቢሆንም ዓለም ላይ ያለውም የአካባቢ የደን ሽፋን ስንመለከት ግማሽ ገደማ ያለው በአምስት ሃገራት የተያዘ ነው። አሜሪካ፣ ካናዳ፣ ብራዚል፣ ቻይና እና ራሺያ የዓለምን ግማሽ ያክል የደን ሽፋን ይዘዋል። አፍሪካን የሚያክል ሰፊ፣ ከየትኛውም አህጉር የበለጠ መሬት ያለው፣ በንጽጽር ሲታይ እንዲሁ አረንጓዴ ተብሎ የሚነገር እንጂ ከነዚህ አካባቢዎች ጋር የሚወዳደር አይደለም።

ወደ ኢትዮጵያም ስትመጡ እያንዳንዱን ክልል ስናቋርጥ አምስት እና አስር ኪሎ ሜትር እየነዳን መሬቶቻችን በደን ተሸፍነው ማየት አንችልም። ያን መቀየር ያስፈልጋል። በአፍሪካ ውስጥ በደን ሽፋን በቂ ቦታ የያዙ፣ የዝናብ እጥረት የማይታይባቸው፣ አምርተው ከፍራፍሬውም፣ ከግብርናም፣ የሚያተርፉ ሃገራት ሲባል የምትጠቀስ ሀገር መሆን አለባት፤ መንገድ ሲባል የምትጠቀስ መሆን አለባት፤ ቴክኖሎጂ ሲባል የምትጠቀስ ሃገር መሆን አለባት። አሁን ያለው አመለካከት፣ ማንኛውም ነገር የምናደንቅ፣ የምንወድ፣ ፎቶ የምንነሳ ሆኖ እያለ ኢትዮጵያ ውስጥ ሲሆን ግን “ይሄማ ሃገር ውስጥ ሊሆን አይችልም፤ አይሰራም” የሚል ስነልቦና በከፍተኛ ደረጃ በኛ ዜጎች ውስጥ ይታያል። በቅርቡ እንኳን በሸገር ፕሮጀክት በወተር ሾው ያየነው በርካታ ሰዎች “ይሄ ኢትዮጵያ ሊሆን አይችልም፤ ዱባይ ነው እንጅ ኢትዮጵያ ውስጥ አይደለም” ብለው በግልጽ ለኔም አንስተውልኛል።

ስለዚህ ዱባይ የሚቻል ኢትዮጵያ እንደማይቻል የሚያስብ ትውልድ ነው ያለው። ዱባይ የሚቻለውን ነገር "አብልጠን እንችላለን" የሚለውን እሳቤ እንዲይዝ ስራ ይፈልጋል። ይሄን በድርጅት፣ በመንግስት ስንወያይበት የቆየን፣ አሁን ያጋጠመን አዲሱ የኮሮና አደጋ ተጨማሪ ነገሮችን መልሰን እንድንመለከት ያስገደደን ቢሆንም፣ ይህ ሃገራዊ እቅድ በአስር አመት ውስጥ ማንም ቢመጣ ነጻ፣ ገለልተኛ፣ የሚያቅደውን የሚተገብር ተቋም ፈጥረን ጂዲፒያችንን ከእጥፍ በላይ ማሳደግ ከቻልን፣ ድህነት መቀነስ ከቻልን እና ጥራት ያላቸው ነገሮችን ሃገራችን ውስጥ ማየት ከቻልን፣ ትውልድ ከዚያ በበለጠ አዘምኖ ሊሄድ ሊሰራበት ይችላል። እያንዳንዱ ክልል ሰፊ አቅም እንዳለው ያ አቅም በትክክል ካልተሰራ በሃገር ደረጃ ሊሳካ አይችልም።

ፕሬዝዳንቶች እቅዶቻችሁን በባለቤትነት ስሜት ተረክባችሁ፣ በፌደራል የሚደረግላችሁን ድጋፎች አሟጥጣችሁ መጠቀም፣ አጎራባች ክልሎችም እርስ በእርስ በጋራ መስራት፤ ቱሪዝም ቤኒሻንጉል ካለ ከአማራም ከኦሮሚያም ጋር መቀናጀት፤ ቱሪዝም አማራ ክልል ካለ ከትግራይም፣ ከኦሮሚያም ከቤኒሻንጉልም ጋር መቀናጀት እና ከአንዱ ወደ ሌላው እንዲሻገር ቱሪስትን የሚያቆይ ስራ መስራት፤ ግብርናም እንዲሁ ኩታገጠም በሆኑ አካባቢዎች ላይ የሚሻገር የጋራ የሆኑ ፕሮጀክቶች አብሮ መስራት ይጠበቅባችኋል። በኢንደስትሪ፣ በተለይ አግሮ ኢንደስትሪ ላይ ሊሠራ ይችላል። አንዱ ክልል ያለ የአግሮ ኢንድስትሪ አቅም ከአጎራባች እንደ ግብአት የሚወስዳቸው ነገሮች ካሉ ማስተሳሰር እና ሀገር አቀፍ አቅም መጠቀም ያስፈልጋል። በዓለም ላይ ያሉ ሃብቶችን እየለመንን፣ ባንኮችን በብድር እያስጨነቅን፣ እርስ በእርስ የማንተጋገዝ፣ እርስ በእርስ በትስስር የማንሰራ ከሆነ ውጤት ማምጣት ስለሚያስቸግር፣ ወጥ የሆነ፣ የእቅድ መናበብ እና ካስኬድ





ሲደረግ እያንዳንዱ ክልል ላይ የተበተነው ነገር ሰብሰብ ብሎ አንድ መልክ አንድ ቅርጽ የሚያሳይ መሆን አለበት።

ብልጽግና ኢትዮጵያ ውስጥ ማምጣት ያስፈልጋል። የብልጽግናን ጎዳና እንጀምር ስንል ደረጃ በደረጃ ድህነትን እንቀንስ፣ ክፋትን እንቀንስ፣ ስንፍናን እንቀንስ፣ ሌብነትን እንቀንስ ማለታችን ነው፤ ጭንቅላታችንን፣ ጉልበታችንን፣ የተፈጥሮ ሃብታችንን መጠቀም እና በየእለቱ ለዜጎቻችን ቀድሞ ከነበረው የተሻለ የኑሮ ስርአትን መፍጠር እንቻል ማለት ነው።

የፖለቲካ አመራር ሆነን ስንቀመጥ ብድር ቀንሰን፣ እዳ ቀንሰን፣ ጂዲፒ አሳድገን፣ የነፍስ ወከፍ ገቢ አሳድገን፣ የሰዎች በየቀኑ ማግኘት የሚገባቸውን መመገብ፥ ንጹህ ውሃ፣ መብራት፣ አልባሳት የመሳሰሉ ማሟላት ካልቻልን ከዚያ ውጪ ያለው የፖለቲካ ጨዋታ ትርጉም የለውም። ትርጉም ያለው በዜጎች ህይወት ላይ ለውጥ ማምጣት፤ ሃገርን ከድህነት እና ከልመና መገላገል፣ ፕሮጀክቶች መጀመር፣ ጀምሮ መሮከር ሳይሆን ጨርሶ ማሳየት፤ ገና ሲጀመር ብዙ የሚነገርላቸውን ጨርሶ መጨረስ እንደሚቻል ማሳየት፤ ያን እኛ እያደረግን ከሄድን የኢትዮጵያን ብልጽግናን ማረጋገጥ ይቻላል።

ይሄን ለማድረግ ደግሞ አሁን ባላችሁ ተነሳሽነት ባለው ዝንባሌ በትብብር መንፈስ ከሰራን የሚሳካ ስለሆነ አንዱ አንዱን እንዳይሸፍን የአረንጓዴ አሻራችን የክረምት የግብርና ስራችንን መሸፈን የለበትም። አረንጓዴ አሻራም ራሱን ችሎ የሚሰራ፣ የክረምት ግብርናችንም ራሱን ችሎ የሚሰራ፣ ለዚያም እንዲሆን ከሞላ ጎደል ወደ ሃምሳ ሚሊየን ነው የያዝነው።

በየክልሉ መንገድ ሲሰራ ያ እንዳይደናቀፍ በጥራት እንዲሰራ ማገዝ ይገባል። ከኢንቨስትመንት አንጻር ሰፊ ፍላጎት አለ። ብዙ ሃገራት፣

ግለሰቦች ጥያቄ እያቀረቡ ነው። ይሄ ራሱን አስችለን የምናየው ቢሆንም ከፍተኛ ማነቆዎች አሉ። በየክልሉ ኢንቬስተሮች የመሳብ ፍላጎት የለም። ኢንቬስተር መጣ ማለት ካፒታል መጣ ማለት ነው፤ እሱ ነው ጂዲፒ ላይ ውጤት ያለው። ያ እንዲቀየር ሰው በመስራት ብቻ መለወጥ-ማደግ እንዲችል የበኩላችሁን እንድታደርጉ። ይሄንን ማድረግ ከቻልን በየዓመቱ እቅዱን እያየን፣ ክለሳ እያደረግን ስለምንሄድ፤ ከዚህም በላይ ሰላም፣ ከዚህም በላይ የተቋማት ጥንካሬ ካለ ማሳካት የሚያስችል ሁለንተናዊ ዐቅም ኢትዮጵያ ስላላት፣ ይህ እቅድ እንዲሳካ እና የትውልድ የኑሮ ስርአት እንዲቀየር የበኩላችንን አሻራ አሳርፈን ለመሄድ ጥረት እንድታደርጉ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

የበለጠ ዝርዝር ቴክኒካል ጉዳዩን የፕላን ኮሚሽን ከየክልሉ የፕላን ቢሮ ጋር በዝርዝር በመነጋገር የሚናበብ እና የሚመጋገብ ይሆናል። ለምሳሌ "ግብርና በሃገር ደረጃ አስር በመቶ እናድጋለን" ብለን ካስቀመጥን፣ ቤኒሻንጉል "እኔ ሃያ በመቶ ማደግ እችላለው" ካለ ማስቀመጥ ይችላል። ያለውን ዐቅም አይቶ፣ አፋር "እኔ የምችለው አምስት ነው" ካለ ሲደመሩ ወደ አምስት ይመጣሉ ማለት ነው። በዚያ አይነት አካሄድ የቴክኒካል ስራዎቹ ከየቢሮዎቹ ጋር ይሰሩ። መናበብ ለአንድ ራእይ፣ ለአንድ ሃገር፣ ለአንድ ዓላማ ለሚያሰባስበን ነገር ደግሞ ወደ ትብብር መሄድ ያስፈልጋል።

ለአንድ ራእይ ስንሰራ ክልላዊ/ቀጣናዊ ራእይ ያስፈልጋል፤ ክልላዊ/ቀጣናዊ ጂዲፒ ያስፈልጋል፤ ክልላዊ/ቀጠናዊ የድህነት ቅነሳ ያስፈልጋል፤ ክልላዊ/ቀጠናዊ የመሠረተ ልማት ስራ ያስፈልጋል። እያንዳንዱ ክልል የራሱን ኢኮኖሚ እና በሃገር ደረጃ ያለውን አበርክቶ በግልጽ ማወቅ አለበት። ይሄ ቻይናም አለ፣ አሜሪካም አለ። ኢትዮጵያም፣ አሜሪካም የፌደራል ስርአት ነው። ግን አሃዳዊ መንግስት ያላቸው ሃገራትም በክልል ደረጃ ጂዲፒ ያውቃሉ። ያን እያደረግን





ብንሄድ ኢኮኖሚ ገብቶን እንድንመራ፣ ገብቶን ውጤታማ ስራ እንድንሰራ ስለሚያደርግ በዚሁ አግባብ የክልል አመራሮች ጉዳዩን ተገንዘባችሁ የቀጥተኛ አመራር እንድትሰጡ አደራ ለማለት እፈልጋለሁ። ለዛሬ በዚህ ይበቃናል በሚቀጥለው ጊዜ ደግሞ የነሱንም ጨምረን የምናይበት እና ግብአት የምንሰጥበት መድረኮች እየፈጠርን እንሄዳለን ለማለት ነው።

**አመሰግናለሁ!!**

# የሸገር ዳቦ ምርቃት ንግግር

ሰኔ 18፣ 2012 ዓ.ም.

**የተከበራችሁ የሃይማኖት አባቶች፣ እንዲሁም የሚድሮክ ሥራ አስኪያጅ እና የሥራ ሃላፊዎችና**

እዚህ ቦታ ለዚህ ውጤታማ ስራ የሪቫን ቆረጣ እና የማስጀመሪያ እለት ከእኛ ጋር በመሆን የአዲስ አበባን ነዋሪዎች ደስታ ለመጋራት የመጣችሁ ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ! እንኳን ለዚህ አበቃን ለማለት እፈልጋለው።

ይህ ፋብሪካ የዳቦ ፋብሪካ ብቻ አይደለም፤ ይህ ፋብሪካ በምግብ ራሳችንን የመቻል ፍላጎታችንን ከድህነት ለመገላገል እና ወደ ብልጽግና ለመሸጋገር ያለንን ጥማት ይሳካ ይሆን ወይ? የሚለውን ጥርጣሬ ላለን/ላላቸው ሁሉ የሚቻል የሚሳካ መንገድ መሆኑን አመላካች ነው። በአንድ በኩል ኢትዮጵያ ውስጥ በአስር ወር ፋብሪካ ጀምሮ መጨረስ የተለመደ አልነበረም። በተለይ ለሚድሮክ ደግሞ የሚታሰብ አልነበረም።





ሜድሮኮች የትናንትናውን ስንፍና እና ድካም ትተው በጠንካራ አመራር እና ፍላጎት ይህንን ፋብሪካ አሳክተው ማሳየታቸው ሁሉም እንደ እነሱ ከወሰነ እና ከቆረጠ የማይቻል ነገር እንደሌለ የሚያመላክት ነው።

በሌላ በኩል ስንዴ ከውጪ እያስገባን፣ ዘይት ከውጪ እያስገባን አብዛኛውን ለምግብ ፍጆታ የሚውሉ ፍላጎቶች ከውጪ እያስገባን አሁን ባለው የህዝብ ቁጥር ከችግር መውጣት ስለማይቻል አንዳንዱን ከውጪ የምናስገባቸውን ነገሮች በተለይ ከምግብ ጋር የሚያያዙትን በቀጥታ በሃገር ውስጥ ማምረት እና በምግብ ራሳችንን የመቻል ፍላጎታችን እንዲሳካ በአንድ በኩል በበረሃማ አካባቢዎች፥በአዋሽ ተፋሰስ፣ በኦሞ ተፋሰስ እና በሌሎች ተፋሰሶች፣ በአፋር፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ ኦሞ እና በሶማሌ ክልል ሰፋፊ የስንዴ እርሻዎች በዚህ አመት ተጀምረዋል። በዚህ አመት ሃያ ሺህ ሄክታር ማልማት እና ከእያንዳንዱ ሄክታር የተሻለ ምርት መሰብሰብ የሚያስችል ልምድ ቀስመናል። በሚቀጥለው አመት ከመቶ ሺህ ሄክታር በላይ እናመርታለን።

የኢትዮጵያ መንግስት ፍላጎት ቢበዛ በሚቀጥሉት ሁለት አመታት ስንዴን ከውጪ ማስገባት ማቆም ነው። ስንዴ ከውጪ ማስገባት ማቆማችን ብቻውን ግን ዳቦ አይሆንም። ወደ አግሮ ኢንድስትሪ መሸጋገር አለበት። ያንን ስንዴ ፕሮሰስ የሚያደርግ እና ወደ ምግብነት የሚቀይሩ ፋብሪካዎች ያስፈልጋሉ። በዚህ ምክንያት በያዝነው ዓመት መጀመሪያ አካባቢ ለሶስት አካላት ጥሪ አቅርበን ነበረ። አንደኛው ለግል ሴክተር፣ ሁለተኛው መርዳት ለሚያስቡ ልዩ ልዩ ተቋማት እና ግለሰቦች፣ በዚህ አግባብ የሚድሮክ ኩባንያ ባለቤት እና የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ ሼህ መሃመድ አላሙዲን ጥሪውን እንደሰሙ እሳቸው ያሉበት ሁኔታ ይሄንን ነገር ለመመለስ ይሄንን ነገር ለማሰብ የሚያስችል ባይሆንም ካሉበት ቦታ ሆነው ለዚህ ጥሪ ምላሽ መስጠት እንደሚፈልጉ

አሳወቁ። ማሳወቅ ብቻ ሳይሆን በቅርብ ክትትል ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ይሄንን ፋብሪካ በተባለበት ጊዜ ተጠናቆ ለህዝባችን ጥቅም መስጠት እንዲችል የሚያስችል ቁርጠኛ አመራር ስለሰጡ ሼህ መሃመድ አላሙዲን እጅግ በጣም የምናመሰግኖት እና ማመስገን ብቻ ሳይሆን ይሄንን ፋብሪካ በእግርዎ ተጉዘው አይተው ከህዝብዎ ጋር የሚቀላቀሉበት ጊዜ እንዲያጥር አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም የኢትዮጵያ መንግስት ከጎናቸው እንደሚቆም ዳግም ማረጋገጥ እንፈልጋለን።

ሁለተኛው - የካቶሊክ ቤተክርስቲያን በቫቲካን በነበረን ጉብኝት እኔም፣ የካቶሊክ እምነት የሚመሩት አባትም፣ እዚህ ከፊት ለፊታችን የሚታዩትም በጋራ በመሆን በቫቲካን ጥያቄ አቅርበንላቸው ነበር። መለስተኛ የዳቦ ፋብሪካዎች ካቶሊክ እንድታገዝ። እነሱም ቀና ምላሽ ሰጥተው በቅርቡ በአዲስ አበባ ሳይሆን በሌሎች ዋና ዋና ከተማዎች መለስተኛ የዳቦ መጋገሪያ ማሽኖች እንደሚያስገቡ ይጠበቃል። ለዚህም የካቶሊክ ቤተክርስቲያንን በእጅጉ ለማመስገን እፈልጋለሁ። ከዚህ በተጨማሪ የዱባዩ አልጋ ወራሽ በገቡልን ቃል መሰረት ተጨማሪ ትንሽ ከፍ ያለ ፋብሪካ በአዲስ አበባ ይቋቋማል።

እነዚህ ሁሉ ፋብሪካዎች የሚያስፈልጉበት ዋነኛው ምክንያት ትምህርት መማር እየፈለጉ መማር ያልቻሉ ህጻናት በዳቦ ምክንያት ትምህርት እንዳያቋርጡ፣ ቤት የሌላቸው ልጆች በውጭ መኖራቸው ሳያንስ በቀን ዳቦ በረከሰ ዋጋ አግኝተው መብላት እንዳይቸገሩ እንደ መንግስት ከህዝባችን ጋር ሆነን የነዚህን ሰዎች ችግር መፍታት ሃላፊነታችንም ጭምር በመሆኑ ነው። ይህ ፋብሪካ የብዙ ህልሞቻችን በር ከፋች፣ ፈር ቀዳጅ መንገድ ለማስጀመር ሳይሆን ለማስጨረስ የምንችል መሆናችንን፣ **"ተስፋ የማንቆርጥ ነገር ግን ሪቫን የምንቆርጥ"** መሆናችንን





በድጋሚ ያረጋገጥንበት ትልቅ ምላሽ በመሆኑ የሚድሮክ ኩባንያን ስራ አስኪያጅ፣ ባለቤት፣ የስራ ባልደረቦች እና ሃላፊዎች እንኳን ደስ አላችሁ። ይህ ልማዳችሁ ግን እዚህ እንዳይቋረጥ፤ በብዙ ፕሮጀክቶች እንዲደገም እና ደጋግመን ከእናንተ ጋር ሪቫን ለመቁረጥ ከፍተኛ ፍላጎት ያለን በመሆኑ በሁሉም ሴክተር ይህ እንዲደገም አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

## መለው የኢትዮጵያ ህዝብ፣

ኢትዮጵያ ካለችበት ወጥታ ወደ ብልጽግና እንደትጓዝ እና ቢያንስ በልቶ ማደር የሚያስጨንቀው ሰው እንዳይኖር የጀመርነው ጉዞ ይሳካ ዘንድ አንድ መሰረታዊ ነገር ከሁላችን ዘንድ ይጠበቃል፤ እሱም ወደፊት መመልከት። ወደፊት መመልከት እና የምንፈልገው ነገር ላይ ብቻ ማተኮር ጆሮዎችንን፣ ልባችንን፣ አእምሯችንን፣ ዐይናችንን ከምንፈልገው ነገር ላይ ከነቀልን በግራ በቀኝ የሚሰሙ ጩኸቶች ፍላጎታችንን እንዳይሳኩ ያደርጋሉ። ይሄን በብዙ ለውጥ ባመጡ ሃገራት ልምድ ማየት ተችሏል። በታላቁ መጽሐፍ ውስጥ ስለሎጥ ሚስት የተጻፈ አስደናቂ ታሪክ አለ። የሎጥ ሚስት ወደፊት መመልከት ሲገባት "ወደፊት ተመልከቺ" የተባለችውን ትእዛዝ ትታ ወደኋላ ስትመለከት የጨው ሃውልት ሆና ቀርታለች። ወደ ኋላ የሚመለከት ህዝብ ወደ ፊት መጓዝ ይቸገራል። ወደፊት መጓዝ የሚፈልግ ህዝብ ደግሞ ወደኋላ መመልከት ያለበት ዛሬን ለመስራት እንጂ በትናንትና ውስጥ ለመኖር መሆን የለበትም።

ቻይና የዛሬ ሃያ አመት በ2000 ዓ.ም. 1.2 ትሪሊየን ብቻ ጂዲፒ ያላት ሃገር ነበረች። ከሃያ አመት በኋላ 14.4 ትሪሊየን ዶላር ያላት ሃገር ሆናለች። ቻይና 1.4 ትሪሊየን ባላት የዛሬ ሃያ አመት ጊዜ ውስጥ

አሜሪካ 10 ትሪሊየን ኖሯት በአስር እጥፍ ከቻይና ትበልጥ ነበር። ነገር ግን ዛሬ በቻይና እና በአሜሪካ መሃከል ሁለት እጥፍ የማይሞላ የሃብት ልዩነት ነው ያለው። የዛሬ ሃያ አመት በ2000 ዓ.ም ህንድ 470 ቢሊየን ገደማ ጂዲፒ የነበራት ጊዜ ካናዳ በሁለት እጥፍ እንግሊዝ ደግሞ በአራት እጥፍ ትበልጣት ነበር። ዛሬ ህንድ 3.4 ትሪሊየን ጂዲፒ ይዛ ከእንግሊዝ፣ ከካናዳ በብዙ እጥፍ በልጣለች። ከካናዳ ከሞላ ጎደል ሁለት እጥፍ፣ ከእንግሊዝ ደግሞ በብዙ መቶ ቢሊየን ዶላር ትበልጣለች።

ኢትዮጵያ አሁን ያለችበት ሁኔታ ወደፊት ለመበልጸግ ካላት ፍላጎት ምንም አይነት ችግር መሆን አይችልም። እድል ነው የሚሆነው። ይህ እድል ግን ይሳካ ዘንድ ወደፊት መመልከት ያስፈልጋል። ሁሉም ሰው የታሪክ እና የትናንትና ተንታኝ ከሆነ ወደፊት መጓዝ አይቻልም። ሃኪሞች ወደፊት ጎበዝ ሃኪሞች መሆን አለባቸው፤ የሃይማኖት አባቶች ወደፊት ጎበዝ የሃይማኖት አስተማሪ መሆን አለባቸው። እነጀማል እነ አብነት ደግሞ ጎበዝ ፋብሪካ ሰሪ መሆን አለባቸው። ትንተናውን ለታሪክ ምሁራን መተው ያስፈልጋል። በተሰበሰበ አእምሮ ወደፊት እየተመለከትን ሁሉም ሴክተር አሁን በጀመረው መንገድ የሚሰራ ከሆነ ያለጥርጥር የዛሬ አስር አመት አብዛኛው ነገር ታሪክ ሆኖ ምግብ የማንለምን፣ ለሙብላት የማንጨነቅ፣ ያለውን የሚያበላ እና የሚያካፍልበት የምግብ ጉዳይ ዋና አጀንዳ ያልሆነባት ሃገር መፍጠር ይቻላል።

ለዚህ ዋናው ምስጢር ወደፊት ወደምንፈልገው ነገር መመልከት ነው። አዲስ አበባ ላይ አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ የማስመሰል እቅድ እና ትልማችን በሁሉም ግንባሮች የተሳካ ጉዞ እያመጣ ይገኛል። ለዚህም የከተማዋ ምክትል ከንቲባ እና አጠቃላይ የከተማዋ አመራሮች ምስጋና





ሊቸራቸው ይገባል። ይህ የጀመሩት ስራ እንዲጠናከር እና በዳቦና በዘይት ወይም በውሃ ብቻ ሳይሆን ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መልካም ዜና በትራንስፖርት ረገድም ለአዲስ አበባ ህዝብም እንደሚያሰሙ ያለኝን ተስፋ ከወዲሁ እየገለጽኩ፥ አዲስ አበባን እንለውጣለን፣ ሁሉንም ክልሎች እንለውጣለን። ኢትዮጵያ ያላት አቅም ከኢትዮጵያ በላይ ነው። ጎረቤት ሃገሮችን አስተሳስረን እንለውጣለን። አፍሪካን ከልመና እናወጣለን።

ይህን ህልም እና ራእይ ማቆም ማሰናከል የሚችል ኃይል የለም። ግለሰቦች ይወድቃሉ፤ ግለሰቦች ይነሳሉ፤ ኢትዮጵያ ግን ትበለጽጋለች። ድህነት የሰለቻት ሃገር ስለሆነች ለመበልጸግ ያላትን ፍላጎት ለማቆም የሚጮሁ ድምጾች እንጂ የሚያቆሙ ኃይሎች አይኖሩም። ይህ እንዲሆን መሰብሰብ፣ መደመር፣ ወደፊት መመልከት፣ የምፈልገውን ነገር "ሞያ በልብ!" እያልን ማሳካት ያስፈልጋል። በሁሉም ነገር መጮህ እና መሮከር አያስፈልግም፤ በሁሉም ነገር አድርጎ ማሳየት ነው የሚያስፈልገው። ኢትዮጵያ የጀመረቻቸውን ትልሞች በሙሉ ካለምንም ጥርጥር ታሳካለች በየአደባባዩ እየጮህች ሳይሆን ሪቫን እየቆረጠች።

## አመሰግናለሁ!!

# የጀሞ - ዊንጌት መንገድ ምርቃት ንግግር

ሰኔ 20፣ 2012 ዓ.ም.

**የተከበራችሁ የዚህ እጅግ አስፈላጊ ፕሮጀክት የማስጀመሪያ ፕሮግራም ላይ የተገኛችሁ ክቡራን እንግዶች፣**
**ከአዲስ አበባ ከተማ የሥራ ሃላፊዎች፣**
**ከሰበታ ከተማ የስራ ሃላፊዎች እና**
**የአካባቢው ነዋሪዎች፣**

በመጀመሪያ ለዚህ እጅግ አስፈላጊ ለሆነው ፕሮጀክት የማስጀመሪያ እለት እንኳን አደረሳችሁ! እንኳን አደረሰን ለማለት እፈልጋለሁ። በአንድ ከተማ ውስጥ እጅግ ወሳኝ ከሚባሉ ነገሮች መካከል የመጀመሪያው መሰረተ ልማት ነው። የመንገድ ወይም በጥቅሉ የትራንስፖርት፣ የመኖሪያ ቤት እና አንድ ሰው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተንቀሳቅሶ ለመስራት፣ ገቢ ለማግኘት፣ ለመኖር የሚያስችሉ መሰረተ ልማቶች እጅግ አስፈላጊ ናቸው። ወደ አንዳንድ ሃገራትም ስንሄድ የምናደንቀው በምናየው የመሰረተ ልማት ልክ ነው። ፎቅ





እናደንቃለን፤ መንገድ እናደንቃለን፤ እንደዚህ አይነት ፈጣን የባስ ትራንስፖርት መስጫ ስርአቶችን እናደንቃለን። ከዛ ውጪ ያሉትን እና የተደበቀውን ነገር በዝርዝር ለማወቅ እዚያ ከተማ ውስጥ መኖር ያስፈልጋል። በሄድንበት ሁሉ ከምናደንቃቸው አንዱ መሰረተ ልማት የሆነው ጎልቶ ስለሚታይ እና ለከተማ ውበትም እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ ነው። በዚህ የመንገድ፣ የቀላል ባቡር እና የፈጣን አውቶብስ ግንባታ አዲስ አበባ ላይ የተጀመረው ስራ እጅግ መጠናከር ይኖርበታል። የከተማችን ሰው እየበዛ ትራንስፖርት በእጅጉ እያስቸገረ ሰዎች ተንቀሳቅሰው ሠርተው ገቢ ለማግኘት እየተቸገሩ ስለሆነ ይሄንን መሰረተ ልማት መገንባት ቀዳሚ የከተማችን ተልእኮ ይሆናል።

ከመንገድ እና መሰል መሰረተ ልማት ባልተናነሰ በከፍተኛ ደረጃ የከተማችን ነዋሪዎች የሚቸገሩት በመኖሪያ ቤት ነው። መኖሪያ ቤትንም በዚሁ መንገድ አይቶ በዝቅተኛ ዋጋ ሰዎች መግዛት ባይችሉ እንኳን ተከራይተው መኖር ወደሚችሉበት መንገድ የሚያመቻች ስራ በመንግስት እና በግል ባለሃብቶች ቅንጅት ሊሰራ የሚገባው እጅግ አስፈላጊ ስራ ሊሆን ይገባል።

የቀላል ባቡር እና የባስ ትራንስፖርት ማሳለጫ መንገድ ሲሰሩ ግንባታው በራሱ አስፈላጊም ከመሆኑ ባሻገር ከተማችን ውስጥ ያለውን ስራ አጥነት በእጅጉ ይቀንሳል። ብዙ ሰዎች ከቀላል እስከ ከፍተኛ ስራ አግኝተው ኑሮዋቸውን ለማሻሻል እድል ይፈጥራል። በዛሬው በ19.2 ኪ.ሜ በሚሸፍነው መንገድ ውስጥ በርካታ ወጣት ኢንጂነሮች ስራ ያገኛሉ፤ ከስራ ባሻገርም ልምድ ያገኛሉ። ፕሮጀክቱን የሚሠራው የፈረንሳይ ኩባንያ ሲሆን የፈረንሳይ መንግስት ትብብር ያደርግልናል። ይኼን ፕሮጀክት በመሥራት ሂደት ውስጥ ልምድና ዐቅማችን እየጎለበተ መሄዱ ግልጽ ነው። በዚህ ምክንያት በፕሮጀክቱ ላይ

የሚሳተፉ ወጣት ሙያተኞች በሙሉ ለእለት ጉርስ ብቻ ሳይሆን ለወደፊት ለምንሰራቸው ስራዎች የሞያ ስንቅ ያገኛሉ። ለዚህ እንዲረዳ እያንዳንዱን ሂደት ፎቶ እያነሳችሁ፣ ማስታወሻ እየያዛችሁ፣ ድጋሚ መስራት ቢያስፈልገን እንኳን ሌላ ኃይል መለመን ሳይገባን ራሳችን ማድረግ እንድንችል አስባችሁ መሥራት ይኖርባችኋል።

በዚህ ፕሮጀክት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ እና የከተማው አስተዳደር በቅርበት እንዲከታተለው የምትሰሩ ሰዎች በአትኩሮት እንድታስተውሉ የሚያስፈልገው ግንባታው በተፈለገው ልክ በጊዜው መጠናቀቅ ካልቻለ መጀመር ብቻውን የምንፈልገውን ነገር አያመጣም። በጀመርነው ልክ በጊዜ መጨረስ ብቻ ሳይሆን በሚገባው ጥራት ልክ መጨረስ አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝበን የጥራት እና የጊዜ ጉዳይ ለድርድር ሳይቀርብ ቀን እና ማታ በመስራት ይሄንን መሰረተ ልማት ለህዝቡ ማዋል ይኖርብናል። በተጨማሪም የጥራትን ጉዳይ ስናነሳ በቀላል ባቡር የነበረውን ስህተት የሚያርም መሆን አለበት። የባስ ማሳለጫ መንገድ በቀኝ እና በግራ ያሉ ዜጎችን የሚያራርቅ ሳይሆን የሚያቀራርብ መሆን አለበት። መሃል ላይ ያለው ሰው ለማሽጋገር የማያስችል ሳይሆን አሁን ከተሰራው መንገድ ጋር ተስማምቶ ለባሱ ባስ በሌለበት ጊዜ ለሌላ አገልግሎት መዋል እንዲችል በሌላው ዓለም እንደምናየው ጥራት ብቻ ሳይሆን የሚያቀራርብ እና በቀላሉ የሚያገናኝ መሆኑን ማረጋገጥ እጅግ አስፈላጊ ነው።

በዚሁ አግባብ የከተማው አስተዳደር እየመራው ስለሆነ እስከመጨረሻው ክትትል የሚያስፈልገው በቀላል ባቡር ላይ ያጋጠመን ስህተት የሚደግም መሆን የለበትም። ይሄን እያደረግን በአካባቢያችን ዛፍ የማንተክል ከሆነ፥ አካባቢያችንን የማናጸዳ ከሆነ፥ አስፓልት፣ ግንባታው፣ መስታወቱ ሙቀት የሚጨምር ስለሆነ ለአንድ ሰው





የምኖር ፍላጎትን እና ጥራትን አያረጋግጥም። የተሟላ ጥራት እና ፍላጎት እንዲረጋገጥ ከምንገነባቸው ህንጻዎች እና መንገዶች በተጨማሪ የከተማ ጽዳት እና አካባቢ ጥበቃ ቢደረግ ጥሩ ነው። ንጹህ ውሃ፣ ዛፍ መትከል እጅግ አስፈላጊ ይሆናል።

በዚህ ስራ ለምትሳተፉ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ ያለኝ መልእክት ቁጥጥር ላይደረግ ይችላል፤ በየቀኑ ክትትል ላይደረግ ይቻላል። እያንዳንዳችሁ በዚህ ስራ የምትሰማሩ የስራ ሃላፊዎች እና ሙያተኞች ራሳችሁን በመቆጣጠር በከፍተኛ ሃላፊነት ብትሰሩ ዋጋውን መንግስት ባይከፍላችሁም አንድ ቀን በሚታወቅም ይሁን በማይታወቅ መንገድ ክፍያውን ልታገኙት ትችላላችሁ።

አንድ ወቅት ላይ የሰማሁትን ታሪክ ልንገራችሁ። ልጇ ወደ ውትድርና አገልግሎት የሄደባት አንዲት እናት ነበረች። ወጥቶ የቀረ ልጇ እንዲመለስላት ዘወትር ትመኝ ነበር። ይቺ እናት አንድ ልማድ አላት፤ በቤተሰቦቿ አባላት ቁጥር መሠረተ ዘወትር ዳቦ እየጋገረች ታበላለች። ጦር ሜዳ የዘመተው ልጇ በሌለበትም ዘመን በስሙ ዳቦ ስለምትጋግር ለተቀሩት ለልጆቿ አከፋፍላ ስታበቃ አንዱን ዳቦ በዚያ ልጅ ኮታ መሠረት በዳንቴል ጠቅልላ ወስዳ አንድ ቦታ ታስቀምጥ ነበረ፤ የቸገረው ሰው አንስቶ እንዲበላ። እዚያ ቦታ በየቀኑ ዳቦ እንደምታስቀምጥ የሚያውቅ አንድ አካሉ የተጎዳ፣ ወገቡ ላይ ጎባጣ ምልክት ያለው፣ በፍጥነት መጓዝ የማይችል ሰው በቀስታ ከሚኖርበት ስፍራ እየመጣ በየቀኑ ያንን ዳቦ እየወሰደ ይበላል። ነገር ግን ሴትየዋን "አመሰግናለሁ፤ እግዜር ይስጥልኝ" እንኳን አይላትም። በተቃራኒው "ሁሉም ሰው የእጁን የስራውን ያገኛል" እያለ ዳቦውን እያነሳ ይሄዳል።

ብዙ ጊዜ በዚያ መልክ ዳቦውን እያስቀመጠች ከሄደች በኋላ ያቺ እናት አንድ ቀን ይመርራታል። "ይሄን ሁሉ ዘመን በየቀኑ ሳላማርር እያስቀመጥኩለት እርሱም መጥቶ እየበላ አንድ ቀን እንኳን አመሰግናለሁ አይልም እንዴ? ምን አይነት ውለታ ቢስ ሰው ነው" ትልና በብስጭት በዚያ ዳቦ ላይ መርዝ ጨምራ ለማስቀመጥ ትወስናለች። በዚያ ጠዋት ተነስታ ዳቦ ጋግራ መርዝም ጨምራበት ልታስቀምጥ ካሰበች በኋላ ሆዷ ይሸበራል፤ ያው የእናት ሆድ እንደምታውቁት ስለሆነ። ሲሸበር ያንን ዳቦ ለዚያ እለት ታቆይ እና ነገር ግን በምትኩ የራሷን ድርሻ አንድ መርዝ የሌለውን ትኩስ ዳቦ በተለመደው መንገድ በዳንቴል ሸፍና ታስቀምጣለች። ያ ሰው እንደተለመደው መጥቶ ድርሻውን ወስዶ ይሄዳል። የዚያን እለትም "ሁሉም ሰው የእጁን ያገኛል" ከማለት ውጪ "አመሰግናለሁ" አላለም።

ነገር ግን ሴትየዋ የዚያን እለት የራሳቸውን ኮታ ከሰጡ መርዝ ያለበትን መጠቀም ስለማይችሉ ባዶ ሆዳቸውን ሆነው ለልጃቸው መጸለይ ጀመሩ። እየጸለዩም እያለ በር ይንኳኳል። እናት በሩን ሲከፍቱ ለረጅም ጊዜ የናፈቁት የሚጠብቁት ልጃቸው እጅግ በጣም ከስቶና ገርጥቶ እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ በር ላይ ቆሟል። እናት ልጃቸውን ካስገቡ፣ ካጠቡ፣ ካበሉ በኋላ ልጁ የጦር ሜዳ ውሎው ምን እንደሚመስል ይተርክላቸው ጀመር። በነበሩበት ቦታ ከፍተኛ የውሃ ጥም፣ ረሃብ፣ ችግር ያለ ቢሆንም በጦርነት ሳይሞት፣ ወደዚያች ወደሚኖሩበት ከተማ "እየመጣሁ እያለ ከተማዋ አፋፍ ላይ ስደርስ ረሃብ መቋቋም አቅቶኝ ወደቅኩ" ይላል። "ስወድቅ አንድ ወገቡ የጎበጠ ሰው፣ አንዲት ዳቦ ያያዘ ሰው ወደ እኔ ተጠጋና `በቀን አንድ ዳቦ ነው በልቼ የምውለው፤ ይቺን ዳቦ ከአንድ ስፍራ እያገኘሁ ነው የምበላው። ዛሬ ግን አንተ ከኔ በላይ ተጎድተህ እና





ከሞት አፋፍ ላይ ስላለህ እኔ በጾም ላይ ልዋል` ብሎ በደግነት እና በርህራሄ የራሱን ዳቦ ሙሉውን አብልቶኝ በዚያች ነው አንቺ ጋር መድረስ የቻልኩት እንጂ፣ ያ ደግ ሰው ያቺን ዳቦ ባያበላኝ ኖሮ ዛሬ እኔ እና አንቺ አንገናኝም ነበር። በጦር ሜዳ ባልሞትም በረሃብ እሞት ነበር" ብሎ ለእናቱ ሲነግራት እናቱ በነገሩ ተደንቃ "እውነትም ሰው የእጁን ነው የሚያገኘው" አለች ይባላል።

የእጃችሁን ታገኙ ዘንድ የሚያይ፣ የሚያመሰግን፣ የሚያደንቅ ሰው ባይኖርም በጥራት ለመስራት እና ለትውልድ የሚሸጋገር አሻራ ለማሳረፍ ሳትታክቱ መስራት ከእያንዳንዳችሁ ይጠበቃል።

በመጨረሻም ስናስመርቅ የምናየው ነገር አንደኛ በጊዜ መጠናቀቁን፥ ሁለተኛ በተገቢው ጥራት መጠናቀቁን፥ ሶስተኛ ከዚያ ማግኘት የሚገባንን በቂ ልምድ እና እውቀት ሞያተኞቻችን ማግኘታቸውን፥ አራተኛ አካባቢው የጸዳ፣ ዛፍ ያለው፣ ለዝውውር የሚመች መሆኑን ማረጋገጥ ይሆናል።

ይህ ሁሉ እንዲሳካ በዚህ ስፍራ የምትሰማሩ ሁላችሁም በሃላፊነት ስሜት እንድትሰሩ፣ የምትገነቡት ሃገራችሁን መሆኑን ተገንዝባችሁ እንድትሰሩ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። ይህ ስራ በአዲስ አበባ እና በሰበታ መካከል የሚሰራ ስራ እንደመሆኑ የሰበታ ከተማ አስተዳደር በርካታ ስራ ስለሚጠበቅበት አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

**አመሰግናለሁ!!**

# በታቦር ተራራ ላይ ስለ አረንጓዴ ዐሻራ የተላለፈ መልዕክት

ሰኔ 28፣ 2012 ዓ.ም

**የተከበራችሁ የፌደራል እና የክልል የስራ ኃላፊዎች፣**
**እንዲሁም የዚህን ታሪካዊ ቀን**
**አሻራችሁን ለማኖር ከያላችሁበት ስፍራ**
**እዚህ የተገኛችሁ ታዋቂ ግለሰቦች፣**
**የአረንጓዴ አሻራ አስተባባሪ ኮሚቴዎች**
**እንዲሁም ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ**

በመጀመሪያ ለዚህ ለተቀደሰ መልካም ለሆነ እና እጅጉን ለሚያስፈልገን አላማ የማብሰሪያ እና የመጀመሪያ ቀን እንኳን አደረሰን አደረሳችሁ ለማለት እፈልጋለው። ኢትዮጵያ ከባለፈው ዓመት ጀምሮ ለሚቀጥሉት አራት አመታት አምናን ጨምሮ ማለት ነው ከዚህ በኋላ ሁለት ይቀረናል። ሃያ ቢሊየን ችግኝ ለመትከል አቅዳ እየሰራች ትገኛለች።

የዚህ አጠቃላይ እቅድ የመጀመሪያው ዓመት ስራ ባለፈው ዓመት አራት ቢሊየን ችግኝ መትከል ተችሏል። ከዚህ አራት ቢሊየን ችግኝ እስካሁን ባለው ጥናት መሰረት እስካሁን ድረስ ባለው 84% አካባቢ





ጸድቋል። ይህ የሚያሳየው በትጋት ስንሰራ ተፈጥሮም እያገዘን ልፋታችን ፍሬ እንደሚያፈራ በቂ ማሳያ ሊሆን ይችላል። ዘንድሮ ሁላችሁም እንደታዘባችሁት አመቱን ሙሉ ማለት በሚያስችል ደረጃ ዝናብ ሳያቋርጥ መዝነብ ችሏል።

በተለይም በኢትዮጵያ ጠራራ ጸሃይ በመሆን የሚታወቀው የነበረው የግንቦት ወር በደቡቡ የሃገራችን ክፍል ብቻ ሳይሆን በመካከለኛው እና በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል ክረምት መስሎ እያለቀ ይገኛል።

ይህ ተፈጥሮ ለመልካም ሃሳባችን የሰጠችውን ትብብር ፈጣሪም ጸሎታችንን ሰምቶ የጀመርነውን የመልማት፣ የመለወጥ ሃሳብ እየደገፈ መሆኑን እንደ ማሳያ ሊወሰድ ይችላል። ዘንድሮ 5 ቢሊየን ችግኝ ለመትከል ማቀድ ብቻ ሳይሆን አመቱን ሙሉ የግብርና ሚኒስቴር፣ የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ ሌሎች የሚመለከታቸው የሙያ ክፍሎች ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል።

በፌደራል እና በክልል በሺህ የሚቆጠሩ ነርሰሪዎች የችግኝ ማፊያ ዝግጅት ሲያደርጉ እንደነበር በተደጋጋሚ ሁላችሁም በሚዲያ ለመታዘብ ችላችኋል። እኔም በርካቶቹን ማየት ችያለው።

ይህ ዝግጅት ውጤታማ እንዲሆን ፍሬ እንዲያፈራ ከዛሬ ጀምሮ እያንዳንዱ ቤተሰብ ባስቀመጥነው እቅድ መሰረት በጓሮ፣ በሰፈሩ፣ በየአካባቢው በተመረጠ ቦታ ችግኝ በመትከል ይህ ክረምት በዋዛ ፈዛዛ እንዳያልፍ በመጠቀም ሃገራዊ ትልሙን ማሳካት ከእያንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቅ ይሆናል። ይህን ስናደርግ ከአምናው በተለየ ሁኔታ ዘንድሮ የኮሮና ቫይረስ ፈተና ሆኖ በመምጣቱ ሰብሰብ ብለን ችግኝ ለመትከል የነበረንን መሻት በተወሰነ ደረጃ ሊፈታተን የሚያስችል ተግዳሮት ሆኖ

መጥቷል። ይሁን እንጂ ኮሮና ይፈታተነናል እንጂ ከፍላጎታችን፣ ከእድገታችን ሊያቆመን አይችልም። የሚጠበቅብንን ጥንቃቄ እና አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ እየወሰድን እና እየተጠነቀቅን ኮሮናም እንዳያጠቃን እና ከሃሳባችን እና ከህልማችን እንዳያደናቅፈን ማድረግ ይቻላል።

ዘንድሮ እንደምታስታውሱት በርካታ ተማሪዎች በቤት ቆይተዋል። ብዙ የመንግስት ሰራተኞች በቤት እንዲቆዩ ተደርገዋል። እንቅስቃሴ ከወትሮው ትንሽ ቀንሷል። ይህ የክረምቱን የችግኝ ተከላ ስራ ከተፈጥሮ ጋር እየተነጋገርን፣ ከራሳችን ጋር እየተመካከርን ፣አፈሩን እየነካን፣ ጭቃውን እየነካን፣ ተፈጥሮውን መልሰን ለማስተዋል፣ ለማጤን፣ እራሳችንን ለማድመጥ ልንጠቀምበት የሚገባ ሁነኛ ጊዜ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

በአንድ በኩል ቤት በመቀመጥ ስፖርት የሚያዘወትሩ ሰዎች፣ የሚንቀሳቀሱ ሰዎች የነበረባቸውን ፈተና አሁን በግል ወይም በጥቂት ቡድን ሆኖ በመራራቅ በመቆፈር፣ በመንከባከብ፣ በመትከል ለፊዚካል እንቅስቃሴያቸውም ጠቃሚ፣ ለአእምሮአቸውም ጠቃሚ እንዲሁም በሚሰራው ስራ እጅግ ውስጣዊ እርካታን የሚያመጣን ነገር ማድረግ ስለሚችሉ ጥንቃቄ እያደረግን በመትከል ይህንን ግብ ማሳካት ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የሚጠበቅ ይሆናል።

ሃያ ቢሊየን ችግኝ በአራት ዓመት ለመትከል ያቀድንበት ዋነኛው ምክንያት የኢትዮጵያ ደን እየተራቆተ በመሆኑ እና ሃያ ቢሊየን ችግኝ መትከል ካልቻልን የኢኮው ሲስተም ማስተካከል ስለምንቸገር ነው። ሁላችሁም ኢትዮጵያ በአካባቢው ካሉ ሃገራት ከፍ ያለ ቦታ ላይ የምትገኝ ሃገር ናት።





ደን እየተራቆተ ሲሄድ የሚዘንበው ዝናብ ማዳበሪያውንም፣ ለሙንም አፈር እያራቆተው በመሆኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ በድርቅ የመጠቃት ሁኔታ እያደገ የመጣ ሲሆን በዚህም ሁኔታ ለም የሆነው አፈራችን እየተራቆተ ያን ለመጠገን እና ለማከም የምንገዛው ማዳበሪያም በዝናብ እየተወሰደ ኢትዮጵያን በቀጣይነት የማራቆት እና የማድረቅ ችግር እያስከተለ በመሆኑ ችግኝ በመትከል እና በመንከባከብ እና በማድረቅ የመሬት መንሸርሸርን ለማስቆም እና የሚያጋጥመንን የርሃብ ችግር ለመከላከል በእጅጉ የሚጠቅመን ይሆናል።

ከኢትዮጵያ በላይ የደንን ጥቅም የሚገነዘብ ያለ አይመስለኝም። ደን ለእኛ መብራታችን ነው፣ የምንበላውም ምግብ ነው። እሱን ሸጠው የሚኖሩ እናቶች፣ የሚያስተምሩ እናቶች በርካቶች ናቸው። ዛሬም ድረስ በርካታ እናቶች ከጫካ እንጨት ተሸክመው የሚያኖሩ እናቶች ይህ የሚለቀመው እንጨት በቀጣይነት እየበዛ መሄድ ካልቻለ የሆነ ጊዜ ማለቁ እና የሚለቀም ነገር መጥፋቱ አይቀርም። ከኢነርጂም አንጻር፣ ከገበያም አንጻር ሁለንተናዊ ጥቅም በመገንዘብ ኢትዮጵያ ላይ ደን ማስፋት እጅግ ጠቃሚ መሆኑን ሞያተኞች ያስተምራሉ።

መንግስትም ይገነዘባል። አሁን በጣና ሃይቅ እያጋጠመን ያለው የእንቦጭ ችግርን ብትወስዱ መሰረታዊ እና ዋነኛው መፍትሄ እንቦጭን ለመከላከል ደንን ማብዛት ነው።

ጉና ተራራን በደን መሙላት ከቻልን ከጉና ተራራ የሚነሱ ወንዞች እና መጋቢ ጅረቶች ተከዜን እና ጣናን የሚሞሉ ስለሆነ እነሱን ይዘው የሚሄዱትን ማዳበሪያ ማስቆም ከቻልን እንቦጭን በመሰረታዊነት ለማስቆም በሃይቆቻችን ላይ እየደረሰ ያለውን ጥቃት ለመከላከል በእጅጉ የሚያስችል ስለሆነ፤ የዚህ ችግኝ ተከላ ጉዳይ ለውስጥ እርካታ

ብቻ ሳይሆን፣ ለአካባቢ ጥበቃ ብቻ ሳይሆን፣ ለኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን በጣም በርካታ ጠቀሜታ እንዳሉት ተገንዝበን ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ ለዚህ ቀና ስራ በአንድ ልብ፣ በአንድ መንፈስ ጥንቃቄ እያደረገ ቢተባበር፣ ቢሰራ እና ብናሳካው አዲስ ታሪክ፣ አዲስ አሻራ የምናሳረፍ እና ለልጆቻችንም መልካም ነገር የምናወርስ እንሆናለን።

በዚህ ጉዳይ ላይ በእምነት፣ በጾታ፣ በፖለቲካ አመለካከት ሳንለያይ የእምነት አባቶች ተከታዮቻችሁን በማሳመን ችግኝ እንድትተክሉ፣ የፖለቲካ ሰዎች የፖለቲካ አመለካከታችሁን ለጊዜው ወደጎን በማቆየት ተከታዮቻችሁን በማሳተፍ ችግኝ እንድትተክሉ፣ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አዛውንቶች፣ ሙሽሮች በሁሉም እለት በእለት በሚያጋጥመን እንቅስቃሴ ችግኝ በመትከል እራሳችንን ከምድር ጋር ከተፈጥሮ ጋር እያነጋገርን ክረምቱን ማሳለፍ አደራ እያልኳችሁ።

መሬት መንካት፣ መሬት መቆፈር፣ መጠየፍ እንደሌለብን እና ምናልባት በኮሮናም ይሁን በሌላ ምክንያት የሞት አደጋ ካጋጠመን የመጨረሻው ቤታችን መሬት ስለሆነ ለመኖር ብቻ ሳይሆን ስንሞትም መልካም የአየር ንብረት እንዲኖር ከወዲሁ የመጨረሻ ቤታችን ጋር ልምምድ ለማድረግ፣ ለማልማት፣ ጥላን ለማብዛት ለራሳችን እና ለትውልድ እንዲሁም ለሃገር የሚሰራ ስራ መሆኑን አውቀን በጋራ እንድንቆም አደራ እላለሁ።

ዛሬ የሁለተኛው ዓመት የአረንጓዴ አሻራ በደቡብ ብሄሮች እና ብሄረሰቦች ክልል በሃዋሳ ከተማ በይፋ የተጀመረ ሲሆን ከነገ ጀምሮ በያለንበት አካባቢ ይህንን የተቀደሰ ተግባር በመፈጸም ኢትዮጵያን ለም፣ ወደ ብልጽግና ማማ የምትወጣ፣ ለሌሎች አርአያ የምትሆን፣ በሁሉም ጉዳይ የምትከተል እና የምትለምን ሳይሆን በአንዳንድ ጉዳዮች





አርአያ ሆና የምታስተምር ጥንታዊት ወደፊትም ተስፋ ያላት ሀገር በጋራ እንደንገነባ አደራ እላችኋለው።

## አመሰግናለሁ ! !

# የምስጋና ንግግር

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በማራቶን ሞተርስ ለተበረከተላቸው ስጦታ ያደረጉት ንግግር**

**ሐምሌ 21፣ 2012 ዓ.ም**

የተከበሩ አቶ ኃይሌ ገብረ ሥላሴ፣ እጅግ የተወደዱ እና የተሳካላቸው ሯጭ የነበሩ፣ አሁን ደግሞ በሩቅ አሳቤ የኢትዮጵያን ብልጽግና ማረጋገጥ በሚቻልበት የቢዝነስ አውታር የተሳተፉ ጠንካራ የቢዝነስ ሰው ናቸው። እንዲሁም የተወደዱ እና የተከበሩ የኮሪያ አምባሳደር፣ የተከበራችሁ እንግዶች፣ ዛሬ እዚህ የተገኘነው የኢትዮጵያ የብልጽግና ጉዞ አይቀሬ መሆኑን፥ ያሰብናቸውን፣ ያቀድናቸውን እያሳካን በተለያየ መስክ ሪቫን እየቆረጥን የምንሄድ መሆኑን ያሳየንበት ጊዜ በመሆኑ ሁላችሁም እንኳን ደስ አላችሁ እንኳን ደስ አለን ማለት እፈልጋለው።

እንግዲህ የዛሬ አንድ አመት ገደማ ነው ኃይሌ የሃዩንዳይ ባለቤት እና ስራ አስኪያጅ ሲመጡ እንዳገኛቸው የጠየቀኝ። ያኔ በአጠቃላይ የምንፈልገው በኢትዮጵያ የመኪና ኢንድስትሪ እንዲሰፋ ነበር፤ “በተለየ ግን የኤሌክትሪክ መኪና እንደትጀምሩ እንፈልጋለን” የሚል ጥያቄ አቅርበን ነበር። እሳቸውም ኃይሌም ጥያቄውን በክብር ተቀብለው አንድ አመት ተኩል ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ይቺን የመሰለች መልካም፣ በብዙ መንገድ ዘመናዊ የሆነች መኪና አምረተውልናል።





ይሄ መኪና አንዴ ቻርጅ ተደርጎ ሶስት መቶ ኪሎ ሜትሮችን መጓዝ ይችላል። ከዚህ አዋሳ መሄድ ይችላል። ለነዳጅ ብቻ ሳይሆን ከነዳጅ ጋር ተያይዞ የሚያስፈልገው አብዛኛው እቃ በውስጡ ስለሌለ ወጪ ብዙ አያስወጣም።

በብዙ መልኩ ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ቴክኖሎጂ ነው። ጥገና ዋጋ ይቀንሳል፤፣ የነዳጅ ዋጋ ይቀንሳል፤ ከዚያ በላይ ግን አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ነዳጅ መጠቀም ብቻ ሳይሆን ድምጽም በጣም እየረበሸን ነው ያለው። ከድምጽም አንጻር ይሄ መኪና በጣም ጠቃሚ ነው። እና በሁሉም መልኩ ሲታይ ይሄ ቴክኖሎጂ ለኢትዮጵያ አስፈላጊ በመሆኑ ኢትዮጵያዊያን ይሄን መኪና እየገዙ መጠቀም ቢጀምሩ ከውጪ የምናስገባቸውን መኪናዎች ባለፈውም እንዳነሳነው የመንግስት ትኩረት አዳዲስ መኪና ላይ ስለሆነ በውጪ ምንዛሬ የምናስገባውን መኪና በሃገር ውስጥ የምንገዛ ከሆነ ለግብአትነት የሚውለውን ቁሳቁስ መጠቀም እንችላለን።

እንግዲህ የህዳሴው ጉዳይ እንደሰማነው ነው። በርካታ የኤሌክትሪክ ሃይል የማመንጨት አቅም አላት ይቺ ሃገር፤ ከወዲሁ ይሄን አይነት መኪና ኢትዮጵያ ውስጥ ማምረት እና መግጠም ከጀመርን የዛሬ አምስት እና አስር አመት የምንመኛትን የበለጸገች ሃገር ለማየት የሚቻል መሆኑን ያመላክታል።

እንግዲህ የኛ የብልጽግና ጉዞ በተደጋጋሚ እንዳነሳነው ላዳ ሹፌር አይነት ሳይሆን የባስ ሹፌር ጉዞ  አይነት ነው። የላዳ ሹፌር ከቤቱ ሲነሳ የት እንደሚሄድ አያውቅም። የት ጋር እንደሚቆም አያውቅም፤ መንገድ ከጀመረ በኋላ ተሳፋሪ ሲያገኝ ይቆማል። የት ጋር መሄድ እንዳለበት፣ በየት ጋር መታጠፍ እንዳለበት፣ የት ጋር መቆም እንዳለበት የሚነግረው

የሚመራው ደንበኛው ነው። የላዳ ሹፌር መሪ ቢይዝም ወዴት መጓዝ እንዳለበት ደንበኛው እስኪነግረው ድረስ መጓዝ አይችልም። የኛ ጉዞ ግን የባስ ሹፌር አይነት ጉዞ ነው። መነሻችንን እናውቃለን፤ መድረሻችንን እናውቃለን። በየፌርማታው የምንቆመው ለመጫን ነው፤ በየፌርማታው የምንቆመው ለማውረድ ነው።

የመጨረሻው መዳረሻችን የት እንደሆነ አስበን አቅደን የምንጓዝ በመሆናችን፣ የግሉ ሴክተር እንዲሁም የመንግስት አካላት በተባበረ ክንድ ከሁላችንም የሚጠበቀው የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን ማድረግ ነው። ብልጽግና ሳንደክም፣ ብልጽግና ሳንወድቅ ሳንነሳ፣ ብልጽግና ሳንቸገር፣ ብልጽግና ሳንፈተን፣ ስለምንፈለግ ብቻ፣ ስለምናልም ብቻ የሚሳካ ነገር አይደለም። በየመሃሉ የሚያጋጥሙን ፈተናዎች እያጠነከሩን፣ እያበረቱን የመጨረሻው መዳረሻችን የሆነው ሁለንተናዊ ብልጽግና ኢትዮጵያ ውስጥ እስኪረጋገጥ ድረስ በጋራ እንድንጥር እንድንሰራ አደራ ማለት እፈልጋለው። ኃይሌ ይህ ጉዳይ እንዲሳካ ላደረግከው ጥረት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት ስም ምስጋናዬን እያቀረብኩ፥ ምርቱ እንዲበዛ፣ ምርቱ እንዲያድግ፣ በሁሉም የኢትዮጵያ ከተሞች ኤሌክትሪክ መኪናዎች ማየት እንድንጀምር አደራ ማለት እፈልጋለው። እጅግ በጣም ደስ ብሎኛል። እንኳን ደስ አላችሁ።

**አመሰግናለሁ!!**





# የበጎ አድራጎት ገንዘብ ርክክብ

**ከመደመር መጽሐፍ ሽያጭ የተገኘውን ገቢ ለበጎ አድራጎት ሥራዎች እንዲውል ለቀዳማዊት እመቤት ጽ/ቤት ርክክብ በተደረገ ወቅት የተደረገ ንግግር**

**ነሐሴ 16፣ 2012 ዓ.ም.**

መደመር እንደ ሃሳብ ለኛ ለኢትዮጵያዊያን በጣም ጠቃሚ ሃሳብ ነው። ሚዛናዊነትን፣ መቀራረብን፣ መነጋገርን እናም ሃገራችንን ካለችበት ሁለንተናዊ ድህነት፣ ሰው ወለድም ሆነ መዋቅራዊ ወለድ ከሆኑ ስብራቶች አገግማ ወደ ብልጽግና እንድትሄድ የሚያደርግ ሃሳብ ነው። ሃሳቡም በመደመር እሳቤ የፈለቀ እና የደረጀ በመሆኑ፣ መጽሐፉም በሚያግዙ ሰዎች የታተመ በመሆኑ፣ ሙሉ በሙሉ ገቢው መልሶ ለልማት እና ችግር የሚፈታ መሆን አለበት።

በተገባው ቃል መሰረት ዛሬ እስካሁን የተሰበሰበውን መቶ ሚሊየን ብር ለቀዳማዊት እመቤት ቢሮ በማስረከብ በሚቀጥለው ዓመት፣ ማለትም በያዝነው በጀት ዓመት ይህ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ በክልሎች ትምህርት ቤት በማሰራት ቀደም ሲል የነበረውን ሃያ ትምህርት ቤት ቁጥር የሚጨምር እንደሚሆን ይታመናል። በሰጠነው ገንዘብ ልክ በቀዳማዊት እመቤት ቢሮ ሙሉ በሙሉ ስራ ላይ መዋሉን እንቆጣጠራለን።

ባለፉት ጊዜያት የመደመር መጽሐፍ በሀገር ደረጃ ከመቶ አስር ሚሊየን ብር በላይ ተሰብስቧል። ይህ መቶ አስር ሚሊየን ብር ሙሉ በሙሉ በተገባው ቃል መሰረት ለትምህርት ማሰሪያ እንዲውል፣ የቀዳማዊ እመቤት ዝናሽ ቢሮ ባለፉት ዓመታት ከተለያዩ አካላት ገንዘብ በማሰባሰብ ሃያ ትምህርት ቤቶች ኢትዮጵያ ውስጥ እያሰራ ነው። ከሃያ ትምህርት ቤት ውስጥ ሰባት ስምንት ተመርቀዋል። የተቀሩት በኮሮና ምክንያት የዘገዩ ቢሆንም ምናልባት እስከ መስከረም ባለው ጊዜ ውስጥ ተመርቀው አገልግሎት መስጠት ይጀምራሉ።

በሁሉም ክልሎች ነው ይህ ግንባታ የተፈጸመው። አሁንም በዚያ ልምድ መሰረት ሙሉ በሙሉ ገንዘቡ ለቀዳማዊት እመቤት ቢሮ ገብቶ በእነሱ መንገድ ትምህርት ቤት እንዲሰራበት ተወስኗል።

ከመጽሐፉ ሽያጭ የተገኘውን ገንዘብ መልሰን ለህዝብ ልማት ስናውል ከፍተኛ ደስታና ከፍተኛ ኩራት ይሰማናል። የገባነውንም ቃል በገባነው መሰረት ስንፈጽም እንዲሁ ደስታ ይሰማናል። መናገር ብቻ ሳይሆን የተናገርነውን ተግባራዊ ማድረግናመፈጸም መቻል እንደ ግለሰብም፣ እንደ ሃገርም በጣም ጠቃሚ ስለሆነ፣ ዛሬ ለህዝብ ጥቅም እንዲውል ስንፈጽምና ስናስረክብ ከፍተኛ ደስታ እየተሰማን መሆኑን እገልጻለሁ።

በየክልሉ ያልተሰበሰቡ ቀሪ ገንዘቦች አሉ። እነዚህ ገንዘቦች ክልሎች ሰብስበው በፍጥነት የሚያመጡ ከሆነ አሁንም ወደዚሁ ጽሕፈት ቤት በማዟዟር ትምህርት ቤት የሚሰራበት ይሆናል።

አንድም ብር ከመደመር ለግለሰብ ወይንም ለፓርቲ ወይንም ለመንግስት የሚሄድ የለም። የተለያዩ ስሞታዎች እንሰማለን ግን የመደመር ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ለህዝብ ልማት የሚውል ሃሳቡም





ህዝቡን የሚያለማ በሱ ምክንያት የሚገኝ ገንዘብም መልሶ ለህዝብ ልማት የሚውል መሆኑን ለማረጋገጥ እፈልጋለሁ።

# የገንዘብ ኖት ቅያሬን በማስመልከት የተደረገ ንግግር

**መስከረም 3፣ 2013 ዓ.ም.**

ዛሬ እንድንገናኝ የፈለግንበት ዋነኛው ምክንያት ላለፉት ጥቂት ጊዜያት ፕሮጀክት ኤክስ ብለን ስንሰራበት የቆየነው የኢትዮጵያን የብር ኖት የመቀየሩ ፕሮጀክት ተጠናቆ ዛሬ ለህዝቡም ለሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎችም ይፋ የሚሆንበት ቀን ነው። ዛሬ የካብኔ አባላት፣ የጸጥታ ሃላፊዎች እንዲሁም የሁሉም ባንክ "ሲኢኦዎች" እና ቦርድ ሰብሳቢዎች ባላችሁበት ለመጀመሪያ ጊዜ በመደበኛ መልኩ የብር ኖት መቀየሩን የምናበስርበት እና ለምን እንዳስፈለገ የምንወያይበት ቀን ይሆናል።

ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ስብራት በሃገራችን አጋጥሞ እንደነበር ይታወቃል። ይህ የኢኮኖሚ ስብራት በተለያየ ቴክኒኮች እንዲያገግም ከፍተኛ የሆነ ስራ እየተሰራ የቆየ ቢሆንም በዋናነት ከፍተኛ የሆነ ካሽ በወረቀት መልክ የተከማቸበት ሃገር ስለሆነ፣ የኖት ለውጥ ካላደረግን በስተቀረ የተሟላ ማስተካከያ ማድረግ ስለሚያስቸግር፣ ያ ደግሞ የተወሰነ ጊዜ ይጠይቅ ስለነበር ጊዜውን ጨርሶ ዛሬ ይፋ ሆኗል።





ዝርዝር የብር ኖቶችን በሚመለከት የብሄራዊ ባንክ ገዢ ዶ/ር ይናገር መረጃ ካቀረበልን በኋላ፣ ምናልባት የምንቀያየራቸው ሃሳቦች ካሉን ተቀያይረን እንዴት እንደምናስፈጽም አቅጣጫ ይቀመጣል። ለግል ባንኮች አቅጣጫ ይቀመጣል። ለሰኪዩሪቲ ተቋማሞች አቅጣጫ ይቀመጣል። ለካቢኔ አባላት አቅጣጫ ይቀመጣል። ይሄን አቅጣጫ በዲሲፕሊን መፈጸም ከእያንዳንዱ ይጠበቃል። ይሄን አቅጣጫ በተለመደው ልክ አለመፈጸም በዚያው ልክ በተቋምም በግልም ያስጠይቃል። እሱን በግልጽ ለመነጋገር እና አካሄዱን በሚመለከት በሚቀርበው ገለጻ ላይ የሚነሱ ጉዳዮች ካሉ መክረን፣ የብር ኖት ቅይይሩን እንዴት ስራ ላይ እንደምናውል የጋራ የሆነ አቅጣጫ ለማስቀመጥ እና በዚያው አግባብ እየገመገምን ለመሄድ እንድንችል ነው።

የብር ኖት የመቀየር ዋነኛው ፍላጎት የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ስብራት ነው። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በብዙ ምክንያቶች በሚፈለገው ልክ እያደገ የሚሄድና ኢትዮጵያን ከእዳ ጫና የሚገላግላት፣ እድገቷንም በፍጥነት የሚያረጋግጥ፣ የህዝቦች ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ መሆን አለመቻሉ ነው። ሀብት የምንሰበስብበትና የምናሰራጭበት መንገድ የራሱ የሆነ መዛባት ስላለው የኢኮኖሚ ስብራቱ ከለውጡ በኋላ በነበረው የማክሮ ኢኮኖሚክ ግምገማ ከፍተኛ የሆነ መዛባት ኢትዮጵያ ውስጥ መኖሬን ተገንዝቧል። ያ በመሆኑ ምክንያት እድገት ማስቀጠል ብቻ ሳይሆን በእለት ዕለት የዜጎቻችን ኑሮ ውስጥ በልተው ለመኖር የሚያደርጉትን ጥረት ማሟላት ስር ነቀል የሆኑ ለውጦች በሁሉም መስክ መውሰድ ይጠይቅ ነበረ። የብር ኖቱ የመጨረሻ እርምጃ ቢሆንም ከዚያ በመለስ ሊስተካከሉ የሚገባቸውን ነገሮች ማየት ማረም ይጠይቅ ነበር።

የመጀመሪያው ልክ ለውጡ እንደመጣ የኢኮኖሚው የቁልቁለት ጉዞ የምንለው “ኤክስፖርት” እየቀነሰ የመንግስት “የበጀት ዴፊሲት” በጣም ከፍተኛ ሆኖ፣ ደሞዝ መክፈል የማንችልበት ሁኔታ ደርሰን ነበር። ከውጭ የተበደርናቸውን እዳዎች መክፈል ባለመቻላችን ከፍተኛ የእዳ ጫና ውስጥ ያለች ሃገር፣ ብትበደር መክፈል የማትችል ሃገር የሚል ስም ተሰጥቶን፣ በሁሉም መንገድ የብሔራዊ ተቀማጭ እየወረደ በመሄዱ፣ የውጪ ምንዛሬ እጥረት በመኖሩ፣ ፍላጎቶች በጣም ሰፊ በመሆናቸው ለአንድ ዓመት ተኩል ገደማ በመስተካከል ኢኮኖሚውን የቁልቁለት ጉዞውን የማስቆም ስራ ነበር የተሰራው።

ብዙ ሊያግዙን የሚፈልጉ ሃይሎችን በማስተባበር እና በነበረውም የመነቃቃት ስሜት ከፍተኛ ሃብት ወደ ሃገር ውስጥ መጥቶ በተወሰነ ደረጃ ያ ጫና እንዲቃለል “ሪስትራክቸር” ማድረግ ያለብንን “ሪስትራክቸር” ለማድረግ አንዳንዱም ከዚያ ያለፈ ድጋፍ ማድረግ በመቻላቸው እንዲቆም ሆኗል።

ከአንድ ዓመት በኋላ በሀገር በቀል የኢኮኖሚክ ሪፎርም አጀንዳችን መቆም ብቻ ሳይሆን የእድገት ትራጀክተሪውን መልሰን መያዝ አስፈላጊ በመሆኑ፣ ቢያንስ አሥር ቢሊየን ዶላር ተጨማሪ ካፒታል ሃገር ውስጥ ማምጣት እና የነበረውን አለመረጋጋት ማስተካከል ያስፈልጋል የሚል ስራ ተሰርቷል።

ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ የሚሰራው ስራ ላይ የሚውለው የአሥር ዓመት ፍኖተ ካርታችን የብልጽግና ፋውንዴሽን የምንጥልበት ነው። አሁን ኢኮኖሚያችን ከሁለት ዓመት በፊት በነበረው ሁኔታ ላይ አይደለም፤ በብዙ መልኩ። እዳን ብቻ ብንወስድ 31 በመቶ ጂዲፒያችን እዳ ነበር። አሁን ወደ 25 በመቶ ዝቅ ማድረግ ተችሏል። በዚህ





ምክንያት ተጨማሪ ብድር ኢትዮጵያ በተለይ “ኮንሴሽናል ሎን” ለማግኘት ሰፊ እድል ያላት ሃገር ናት። ብዙ ለማበደር የሚፈልጉ ግለሰቦችም፣ ቡድኖችም፣ ሃገራትም ጥያቄ ያቀርባሉ። ከሁለት ዓመት በፊት ማበደር አስቸጋሪ ነበር፤ አደጋ አለው፤ “ተመልሶ አይመጣም” ከሚለው፣ አሁን ደግሞ ለማበደር ፍላጎቶች ይታያሉ። በሁሉም ስመጥር ባንኮችም፣ ከሌሎች የፋይናንስ ምንጮችም።

እንግዲህ ከወሰድናቸው እርምጃዎች ውስጥ አንዱ የእናንተን ሴክተር የሚመለከት ነው። የባንክ ሴክተሩን በአንድ በኩል ኢትዮጵያ የምትንከባከበው የምትጠብቀው፣ ሌሎች መጥተው እንዲያወጡት የምታደርግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እድገቱ ፈጣን እንዲሆን፣ በሌላ መመሪያ የታነቀ ነበር። ከዚህም ውስጥ አንዱ ቦንድ መግዛት የሚለው ጉዳይ በመጀመሪያው ቦርድ ሰብሳቢዎች፣ ከዚያ በፊትም በብዙ ጊዜ የሚነሳ ጥያቄ ነበር። በዚህ ሁለት ዓመት ውስጥ 27 በመቶ እንዲቆም ተደርጓል። ተጨማሪ “ሊኩዲቲ” የሚያስፈልጋችሁ ጊዜም በተለየ ውሳኔ፣ ከኮሮና ጋር ተያይዞ እኛ ጋርም ያላችሁ ገንዘብ ቀደም ብሎ እንዲለቀቅ እና የመንግስት የልማት አካል ሆነው፣ ታስበው፣ ታምነው እንቅስቃሴያቸውን ከሚገቱ ጉዳዮች በመቆጠብ እድገታቸውን ለማረጋገጥ የተወሰደ ውሳኔ ነበር።

ሶስተኛው እና መሰረታዊው ውሳኔ “ፊንቴክን” የሚወስን ዝቅ አድርጎ ሁሉም ሰው በባንክ ገንዘቡን ቢያስቀምጥ ጥሩ ነው። አንደኛ ኮሮና የመጣባቸው አገራት ቻይናን ጨምሮ በኮሮና ምክንያት ብቻ ብር ቀይረዋል። አንደኛ በጣም በወረቀት ገንዘብ ግብይት የሚያደርጉ ሀገራት በቀላሉ ለበሽታ ይጋለጣሉ። ሁለተኛ የሞባይል ባንኪንግ ቴሌ እየጀመረ ነው። ትናንሽ ግብይቶችን በሞባይል ማካሄድ ይቻላል። ከዚያ ከፍ ያለውን ባንኮች በቼክ እና ከአካውንት አካውንት ባለ

ዝውውር ዝቅ ያለ ካሽ ደግሞ ሲሆን በተወሰነ መንገድ ስለሚያስተናግዱ ሰዎች በተቻለ መጠን ገንዘባቸውን በእጅ ከመንካት ወጥተው ባንክ ማስቀመጥ ለምናስብም “ኦቶሜትድ” የሆነ “የሞደርን” ግብይት እድል ይሰጣል። በሌላ መንገድ ደግሞ ከበሽታም ይታደጋል።

ይሄ እንዲሆን ቴሌ ሞባይል ባንኪንጉን ማፋጠን አለበት። እናንተም በቀለጠፈ መንገድ በኤሌክትሮኒክስ የሚዘዋወሩ ገንዘቦችን ፈጠራ በማከል መስራት እንድትችሉ እና “ፋይናንሻል ኢንክሉዥን” ማረጋገጥ የሚያስችል እርምጃ እንዲሆን ሰፊ የሪፎርም ለውጦች በእናንተም ውስጥ ይጠበቃል። አላግባብ የተረጨ ሀብት ለዋጋ ግሽበቱ አንዱና ዋነኛው ችግር ነው።

ላለፉት ሁለት አመታት ይሄንን የምንፈታበት ምርት ከማምረት በተጨማሪ የብር ኖት መቀየር በከፍተኛ ደረጃ እድል ይሰጣል የሚል እምነትና እሳቤ አለው። ከዐይነ ስውራን አንፃር በተደጋጋሚ የሚነሱ አቤቱታዎች አሉ። በአሁኑ የብር ኖት ለውጥ በከፍተኛ ደረጃ የእነሱን ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል። ሁለተኛው የፋይናንሻል ሴክተሩ እንዲገነዘብ የምፈልገው ከፍተኛ ጥራት ያለው ኖት እንደሆነ ነው። ጊዜ ለመቆጠብ በአንድ ሀገር ሳይሆን በብዙ ኩባንያዎች ነው ያተምነው። ገንዘቡን በተቻለ መጠን ለፎርጂድ እንዳይጋለጥ ሆኖ የተሰራ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ በብር ኖቶች ላይ ከኋላ ያለው ትርክትአንደኛው ሰላም ነው። ለኢትዮጵያውያንም አስፈላጊው ነገር ሰላም ስለሆነ እሱን የሚያንፀባርቅ መሆን አለበት። እያንዳንዱ ህፃን፣ እያንዳንዱ ሰው፣ ርግብ ብቻ ሳይሆን የሆነ አበባ የያዘች ርግብ ናትና የምትታየው፣ እሷን





እያየ ለሰላም ያለንን ፍላጎትና ቁርጠኝነት የምናሳይበት እንዲሆን ተደርጓል።

ሁለተኛ ከአምስቱ በኢኮኖሚ ካስቀመጥናቸው ምሰሶዎች አንዱ የሆነውን ቱሪዝምን የሚገልጽ ነገር ተቀምጧል። እንደሚታወቀው ቱሪዝም የተዘነጋና ባለፉት ዓመታት ከዘርፉ ማግኘት የሚገባንን ጥቅም ሳናገኝበት የቆየንበት ዘርፍ ነው። አሁን “ኢንቨስት” እያደረግን ነው፤ እንቅስቃሴዎቻችን ቱሪዝምን የሚያንፀባርቁ መሆን አለባቸው።

ሌላው በአስር ዓመት እቅዳችን ውስጥ ምሰሶ የሆነው ግብርና ነው። ግብርናን ስናስብ በኩታ ገጠም ዘመናዊ ከማድረግ ጋር አያይዘን ስለሆነ ግብርናውን ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በአራተኛነት ኢንደስትሪው አለ። ከአምስቱ የኢኮኖሚ ምሰሶዎች በአዲሶቹ ገንዘቦች ላይ መግለጫ ያልኖረው የማዕድን ዘርፉ ብቻ ነው። እሱን እንዲወክልልን በሚል ወርቅ እንዳናስቀምጥ ወርቅ እኛ ሀገር ብቻ አይደለም ያለው። በዚያ ላይ ወርቁ ወጥቶ ብዙ ስላልጠቀመን ወደፊት በደንብ ከመጣ በምናሳትማቸው ብሮች ውስጥ እናየዋለን። እስካሁን ማዕድን ዘርፉ እዚህ ግባ የሚል ነገር አላመጣም በሚል አልገባም።

የመጨረሻው ትብብር ነው። ለምናስበው ማንኛውም የሰላም፣ የልማት፣ የእድገት ጉዞ ኢትዮጵያውያን መተባበር አለባቸው። እሱን ደግሞ ምናልባት የክርስትና ምልክት፣ ወይንም የእስልምና ምልክት፣ ወይንም የአንድ አካባቢ የባህል ልብስ ካደረግን ሁሉንም መጥቀስ ስለማንችል ኢትዮጵያውያን የሆኑ ሴት እና ወንዶች ቡናማ ዐይን ያላቸው በትብብር መንፈስ ቢታዩ በሚል እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚያሳይ ምስላቸው ተቀምጧል። የቡና ምስልም ተቀምጧል፡፡ ቡና ያው ቡና ነው እንደምታውቁት።

በተቻለ መጠን በዲዛይኑ በጥራቱ በጊዜው እና በምስጢርነቱ አስፈላጊ የሚባለውን ነገር ለማምጣት ጥረት ተደርጓል።

## ከቁጥጥር ጋር በተገናኘ

ሕግ አስከባሪ ተቋማት ቁጥጥራችሁን ልታጠናክሩ አጠናክሩ፡፡ አንደኛ ከጥቁር ገበያ፣ ሁለተኛ አየር መንገድ ላይ። ከዛሬ ጀምሮ ባስቀመጥነው አቅጣጫ መሰረት እያንዳንዱን ሕገወጥ ሻንጣ ማስወጣት ማስገባት እንዳይቻል በአየር መንገድ ጥብቅ ቁጥጥር ይደረጋል።

በድንበር አካባቢዎች ላይ፥ በተለይ ከጅቡቲ፣ ሱማሌ፣ ሱዳን ከፍተኛ ገንዘብ እንዳለ ይታወቃል። በነዳጅ ቦቴም ይሁን በምግብ መንገድ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ገንዘቡ እንዳይገባ ሕግ አስከባሪ ተቋማት በወጣው እቅድ መሰረት ከመነሻው ጀምሮ ሰፊ ጥበቃ ያደርጋሉ። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ይህ የብር ለውጥ በየቀኑ የሚያስቸግረውን የዋጋ ግሽበት ለማስተካከል እንደመጣ፣ እያንዳንዱ ፖሊስና መከላከያ ይሄንን ካላደረገ የእሱን ኑሮ መቀየር እንደማንችል ማሰብ አለበት። ዘራፊዎች እጅ የሚገኘው ገንዘብ መምከን የሚገባው መከኖ፣ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ስብራት ካልተስተካከለ በቀር የሰራተኛ ደመወዝ ጨምረን ኑሮ ማሻሻል አንችልም።

የባንክ ሰራተኞች አለቆቻችሁ ቢፈለጉ እንኳን ኢትዮጵያውያን ስለሆናችሁ ሕገወጥ እንቅስቃሴ ስትመለከቱብሔራዊ ባንክ ባዘጋጀው የኢንፎርሜሽን ሴንተር ወይም ለፖሊስ መረጃ እንድትሰጡ ይጠበቃል፡ ፡ ባንክ ተጠቃሚውም በተመሳሳይ መረጃ እንዲሰጥ ይጠበቃል።

የፀጥታ ተቋማት ባወጣችሁት እቅድ መሰረት ተባብረን ፎርጂድ ገንዘብና ህገወጥ ገንዘቦች ላይ በጣም ጠንከር ያለ እርምጃ እየወሰድን





ኢኮኖሚውን የምናረጋጋበት መንገድ እንከተላለን። ከባንኮች የምንፈልገው አሁን በመጣው መመሪያ መሰረት በውይይት የምናስተካክለው ካለ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚያ መመሪያ መሰረት ብቻ መፈፀም አለበት። ከዚያ ውጭ ያለ ማንኛውም ፈጠራ የታከለበት ሌብነት እንደርስበታለን፤ ስንደርስበትም ጠንከር ያለ እርምጃ እንወስዳለን።

ከባንኮች አንፃር ሁለት አይነት ግምገማዎች ነው ያሉን። አሁንም ህገወጥነትን የሚያስፋፉ ባንኮች አሉ፤ ፎርጅድ የሚሰበስቡ ባንኮች አሉ። አሁንም የኢትዮጵያ ባንኮች ሆነው። ከደህንነት ተቋማት ጋር ግልጽ እቅድ ነው ያወጣነው። በእያንዳንዱ ቅርንጫፍ የሚታይም የማይታይም የቁጥጥር ተቋማት አሉን። “ቨርቹዋሊ-ም” ክትትል እናደርጋለን። በአካልም ክትትል እናደርጋለን። አንድ ባንክ የኢትዮጵያን ሀምሳ ብር በዘር፣ በሃይማኖት፣ በሰፈር ሊያጭበረብር ከሞከረ በቀጣዩ ቀን ባንክነቱ ይቀራል። ይሄን እንድታውቁት።

ባንኮች በዚህ ተልእኮ ውስጥ ከመንግስት አቋምና ፍላጎት ጋር ተስማምታችሁ ጥራት ባለው መንገድ የምትሰሩትን ባንኮች መንግስት በተለየ መንገድ እውቅና ይሰጣችኋል፤ ያበረታታችኋል። ያጠፋውን ብቻ አይደለም የምንቀጣው። በደንብ ለሚሰሩት ማበረታቻ እናደርጋለን። የኢትዮጵያ ህዝብም ለእሱ እድገት የቆሙትን ባንኮች አውቆ አሰላለፉን እንዲያስተካክል እናደርጋለን። በጥሩ ለማትሰሩ ባንኮችና አሁንም አንዳንድ በፋይናንስ ኢንተለጀንስ መረጃ እያገኘንባቸው ያሉ ባንኮች ላይ ጠንከር ያለ እርምጃ እንወስዳለን። በእነዚህ ባንኮች ያለ ሥራ አስኪያጅ ሁለተኛ በኢትዮጵያ ባንክ ውስጥ አይሰራም። ባንኩም አይቀጥልም። ማጭበርበር የሚባል ነገር በፍጹም ስለማንታገስ ጥንቃቄ አድርጉ።

ቦርድ አባላት የጠራንበት ዋናው ምክንያት በኋላ እንዳትጮሁና አሁን በትክክሉ እንድትመሩት ለማሳሰብ ነው። ይሄንን ጉዳይ የቦርድ አባላትና “ሲኢኦዎች” በቅርበት ምሩት። በቅርበት ካልመራችሁ በጉዳዩ ባትኖሩበትም ስላልመራችሁ ትጠየቃላችሁ። ብዙ ገንዘብ ነው ያወጣንበት። በጣም ብዙ የደከምንበት ስራ ስለሆነ በቀላሉ የማናልፈው መሆኑ ታውቆ በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት ይሄንን ስራ ካሳካን፣ የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ስብራት በከፍተኛ ደረጃ ለማስተካከልና በሌቦች እጅ፣ ብር ባከማቹ ሰዎች እጅና በሙሰኞች እጅ የነበረው ገንዘብ ይመክናል። ከአሁን በኋላ ደግሞ እንዳይንቀሳቀሱ በባንክ ተብሏል። ሙስናውን እንኳን ከቀነሰልን ቀላል አይደለም። እሱ ከቀነሰ የኢትዮጵያ ህዝብ እፎይታ ስለሚያገኝ በትብብር መንፈስ ይሄን ፕሮጀክት እንድናሳካ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። ባንኮች ባገዝናችሁ ልክ አግዙን!!





# ግብር ከፋይነት ያሸልማል

## ለታማኝ ግብር ከፋዮች የሽልማት መርሃግብር ላይ የቀረበ ንግግር

መስከረም 7፣ 2013 ዓ.ም.

**የተከበራችሁ የዚህ እጅግ አስፈላጊ ፕሮጀክት ታማኝ ግብር ከፋዮች፣**
**የተከበራችሁ የሐይማኖት አባቶች እና የዚህ ክብረ በዓል ታዳሚዎች፤**

ከሁሉም በላይ ሁለት መቶ ታማኝ ግለሰቦችና ኩባንያዎች ማግኘት ስለቻልን እንኳን ደስ ያላችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

ግብር መክፈል አንድ ሰው መስራቱን እና ከሰራው ለእሱ የማይገባውን፣ ለሀገሩ ለወገኑ መስጠት የሚገባውን፣ በህግ አግባብ መስጠት ማለት ነው። ያን አለማድረግ ከስርቆት የሚስተካከል ወንጀል ነው። እናንተ “ስርቆት ተገቢ አይደለም” ብላችሁ በታማኝነት የሚጠበቅባችሁን ግብር መክፈል በመቻላችሁ፣ ዛሬ እዚህ ያለን ሰዎች ብቻ ሳንሆን በታሪክ ውስጥ ሁሌም የምትመሰገኑ፣ የምትታወሱ፣ ለሌሎችም አርአያ የምትሆኑ፤ አንዳንዶች በጦር አውድማ ጀግኖች እንደሚባሉት

እናንተም ባለመስረቅ የኢትዮጵያ ጀግኖች ስለሆናችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

ከግብር ጋር የሚያያዘውን አብዛኛውን መልዕክት ክቡር አቶ ላቀ ስላስተላለፉ ሁለት ነገር ላይ ብቻ ማተኮር እፈልጋለሁ። ዛሬ መሸለም የሚገባቸው ሰዎች በሺህ የሚቆጠሩ መሆን ነበረባቸው። ሁለት መቶ በቂ አይደለም። ይሄ የሆነበት ምክንያት ከዚህኛውም ከዚያኛውም ወገን ሌቦች አሉ ማለት ነው። ሁለቱን ሌቦች መቀነስ ማጥፋት እስካልቻልን ድረስ ብልጽግናን ማረጋገጥ አይቻልም፤ ልማትን ማረጋገጥ አይቻልም። የተሻለ ነገር አገራችን ውስጥ ማየት የምንፈልግ ከሆነ፥ ሰላም እንዲኖር የምናስብ ከሆነ፥ በትክክል ሰርተን፣ ካለችግር ከፍለን፣ በዚያ ልክ "አገልግሎት እናግኝ" የምንል ከሆነ፥ ታማኝ ግብር ከፋዮች ሊበራከቱ ይገባል።

በእናንተ ወገን ያሉ ሌቦች ግብር ሳይከፍሉ "መንግስት ሰላም ያስከብር" የሚሉ ሰዎች ግዴታቸውን ሳይወጡ የሚገባቸውን መብቶቻቸውን ይጠይቃሉ። በትክክለኛው የመንግስት ስርዓት ውስጥ ግብር የማይከፍል ሰው፣ ግዴታውን የማይወጣ ሰው የመብት ጥያቄ ማቅረብ ተገቢ አይደለም።

በሌላ መንገድ እንደ እናንተ ደግሞ በታማኝነት የሚከፍል ሰው በዓመት አንድ ቀን የሚሸለም ብቻ ሳይሆን የገቢዎች ሚኒስቴር ከአየር መንገድ ጋር፣ ከኢትዮ-ቴሌኮም፣ ከፖሊስ፣ ከሁሉም መስሪያ ቤት ጋር በመነጋገር እነዚህ ሁለት መቶ ሰዎች ዓመቱን ሙሉ በሄዱበት አገልግሎት ሲፈልጉ ቅድሚያ የሚያገኙበት፣ የሚከበሩበት፣በተለያዩ ተቋማት ከተለየ አክብሮት ጋር የሚያስተናገዱበትን ነገር ማመቻቸት ያስፈልጋል። አንድ ታማኝ ግብር ከፋይ አየር መንገድ ሲሄድ ግብር





ከማይከፍሉ ሰዎች እና በኮንትሮባንድ ብር ከሚያወጡ ሰዎች ጋር እኩል መሰለፍ የለበትም። ይህንን ባህል እያዳበርን ከሄድን ብቻ ነው ሰዎች በታማኝነት መክፈል የሚለማመዱት።

ፖሊሱም፣ አቃቤ ህጉም ሌሎች በየደረጃው ያሉ የመንግስት ሰራተኞችም፣ ደሞዝ የምንከፍልላቸውም ሆነ ደሞዝ የምናሻሽልላቸው ታማኝ ግብር ከፋይ እየበዛ ሲመጣ ስለሆነ፣ የታመኑትን በማክበር፣ ያልታመኑት እንዲታመኑ አርዓያ የሆነ የተለየ አገልግሎት በመስጠት፣ ታማኝ ግብር ከፋይነትን ማለማመድ ይጠበቅብናል። ይህን የገቢዎች ሚኒስቴር እንደሚያመቻችና በሄዳችሁበት ሁሉ ቅድሚያ አገልግሎት እንደሚሰጣችሁ፣ ይሄንን ባህል እንደምናደርግ፣ በዚህም አግባብ የሌባ ቁጥር እየቀነስን፣ የታማኝ ግብር ከፋይ ቁጥር እያደገ እንደሚሄድ፣ ዛሬ በአዲስ መልክ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ።

በእኛ አሰራሮች ይካተታሉ። ግብር የከፈለ የሚከበር ከሆነ የማይከፍል ሁሉም ክብር ስለሚፈልግ ወደመክፈል እንዲመጣ በመንግስት በኩል ይህ ተግባር ይቀጥላል። በሌላ በኩል በመንግስት ቤት የሚተጉ የሚለፉ እንዳሉ ሁሉ፣ አሁንም ከዚች ደሀ አገር የሚሰርቁ ሰዎች ተሰግስገው ይገኛሉ። እነዚህ ሰዎች እንዲቀንሱ፣ ወደፊትም ሌብነትን የሚጠየፍ አገልጋይ እንዲፈጠር ከእናንተ እና ከሌሎች ግብር ከፋዮች የሚጠበቅ አንድ ነገር አለ። በእኛ ወገን ሆነው እጅ መንሻ ለሚሹ ግለሰቦች እጅ ከፍንጅ ለመንግስት ጥቆማ ሰጥቶ የሚያስይዙ ግብር ከፋዮች የገቢዎች ሚኒስቴር በተለየ መንገድ የታክስ ቅናሽ ያደርግላቸዋል።

እንዲህ ሌብነትን ካልተዋጋን በስተቀረ በምትከፍሉት ገንዘብ ብቻ የሀገር ልማት ሊረጋገጥ አይችልም። ምክንያቱም ከከፈላችሁም በኋላ የሌብነት ባህል ባለበት የመንግስት ስርዓት ውስጥ የተከፈለውም

በትክክል ስራ ላይ ስለማይውል መክፈልና ስርቆትን መዋጋት እኩል መሆን አለበት። ይህ እንዲሆን ልክ ለሚረዱ ተቋማት ረድታችሁ ሃያ በመቶ ቅናሽ እንደምታገኙት ሁሉ፣ አንድ ሌባን ያስያዘ ግብር ከፋይ ፐርሰንቱን አሁን መናገር ቢያስቸግረኝም ገቢዎች በማጥናት አጠቃላይ ከሚከፍለው ክፍያ ቅናሽ እንዲያገኝ ማድረግ ይኖርብናል። ይህን እያደረግን ስንሔድ በውስጣችን ያሉ ሌቦች እየቀነሱ በዚያኛው ወገን ያሉ ሌቦች እየቀነሱ፣ ሌብነት ወንጀልና የሚጠሉት የማይፈለግ ነገር መሆኑን እያመንን ስንሄድ ያኔ ልማት ይመጣል።

ሰዎች ስለጃፓን ስለኮሪያ ልማት በስፋት ሲናገሩ ይደመጣል። በጃፓን እና በኮሪያ አንድ የመንግስት ሹም "ሌባ ነህ" ቢባል፣ ቢገመገም፣ ቢነገርበት ማታ ገብቶ እራሱን ይገላል። በሌብነት መጠርጠር በጣም አስቀያሚ ነገር ስለሆነ። እኛ ሀገር የሌብነት ባህል መቆም አለበት።

ሰሞኑን የገንዘብ ኖት ቅያሬ ከአደረግን በኋላ "በከፍተኛ ደረጃ የእንቅልፍ ኪኒን አዲስ አበባ ውስጥ ጨምሯል" ይባላል። "ብዙ ሰዎች መተኛት ይቸገራሉ" ይባላል። እስካሁን የእንቅልፍ ኪኒን በመጠየቅ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው በመንግስት ሹማምንቶች አካባቢነው የሚል ጭምጭምታዎች እየሰማን ነው።

በህገ ወጥ መንገድ ገንዘብ የምናከማች ሰዎች፣ የሚገባ ግብር የማንከፍል ሰዎች የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀረ ቀና ብለን መሄድ ስለምንቸገር በመንግስት ወገን ያለን ሰዎች ለማገልገል ወድደንና ፈቅደን የተቀጠርን በመሆናችን፤ የሚሰጠን ደሞዝ የማይበቃን ከሆነ በስውር ከመስረቅ በይፋ ለቅቀን ወደ እዚያኛው ወገን መቀላቀል ይቻላል። እዚህ ሆኖ በአንድ በኩል ሰርቪስ የሚሰጥ በሌላ በኩል የሚሰርቅ መሆን አስቸጋሪ ነው። በዚያ በኩልም ያላችሁ ሰዎች በእናንተ





የሚያምረው ሰርታችሁ፣ የሚገባችሁን ሰርቪስ አግኝታችሁ መክፈል የሚገባችሁን መክፈል ነው እንጂ፣ እዚያ ሆናችሁ እዚህ እያጎረሳችሁ ህግ የምታወጡ ከሆነ፣ እዚያ ሆናችሁ እዚህ ያለውን የምታሾሙ ከሆነ፣ አብሮ አይሄድም።

ነጋዴዎች የሚነግዱ፣ "ኢኖቬተርስ" የሚፈጥሩ፣ የመንግሰት ሰራተኞች ደግሞ የሚያገለግሉ ብቻ መሆን አለባቸው። ይሄ በከፍተኛ ደረጃ ኢትዮጵያ ውስጥ ተቀላቅሏል። ባለሀብቶች ከእኛ ጋር በመታየት፣ ከእኛ ጋር ፎቶ በመነሳት፣ ከእኛ ጋር በመደዋወል፣ መሬት የሚያጭበረብሩ አሉ። እኛ ጋር መዋል መሬት ማጭበርበሪያ መንገድ መሆን የለበትም። ይህን የምታደርጉ ባለሀብቶች እናንተን ከመቅጣት ወደኋላ እንደማንል ማወቅ ይኖርባችኋል። ዘመድ ጓደኛ መስላችሁ ቀርባችሁ፣ ከሹማምንት ጋር እየታያችሁ፣ በሪልስቴት ስም የምትዘርፉም ሁኑ በሌላ መንገድ የምትዘርፉ፣ መንግስት እያጣራ እርምጃ ይወስድባችኋል። መንግስት ሌቦች ይጠየፋል። በእኛ በኩል እንጨክናለን፤ በእናንተ በኩል ጨክኑ። ሁለታችን ከጨከንን አትጠራጠሩ ኢትዮጵያን ባልነው ጊዜ ውስጥ ካለችበት ከፍታ ማላቅ ይቻላል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ችግር የሆነው በዚህም በዚያም ወገን ተባብሮም ሳይተባበሩም የሚሰርቁ ሰዎች በመብዛታቸው ስለሆነ፣ ግብር በመስጠት ልክ ሌብነትን የምትዋጉ እንድትሆኑ፣ የሌብነትን ባህል ለመቀነስ በሚደረግ ውጊያ ውስጥ ከመንግስት ጎን ሆናችሁ እንድታግዙን አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

እንኳን ደስ ያላችሁ! ይልመድባችሁ!!

በሚቀጥለው ዓመት ክቡር አቶ ላቀ፣ ከአንድ ቢሊየን በታች ለሚከፍሉ ሰዎችን “ፕላቲኒየም” ማለት አያስፈልግም። እውነተኛ ወርቅ ወይም የማይጣል ነገር፣ ሻል ያለ ሽልማት መስጠት ይሻላል። በመቶ ሚሊየን ብር የሚቆጠር ግብር የሚከፍሉ ሰዎች ወደ ቢሊየን ደረጃ ከፍ ካላሉ በሽልማት ወቅት  ወደ ሚቀጥለው ደረጃ ዝቅ እንዲሉ፣ አስፈላጊ ከሆነ ነሐስ ተጨምሮ በዚያ ደረጃ የሚገኙ ሰዎች በዚያ አግባብ እንዲሸለሙ በዚሁ አጋጣሚ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። መልካም ጊዜ!

ዛሬ ከድግሱ በኋላ ዩኒቲ ፓርክ በነፃነት ወክ ማድረግ ትችላላችሁ፤ ማታ ማታ አይፈቀድም፤ ለእናንተ ግን የእናንተ ውጤት ስለሆነ ተፈቅዶላችኋል።





# የፌዴራል ፖሊስ ትርኢት ላይ የተደረገ ንግግር

መስከረም 19፣ 2013 ዓ.ም.

**ክቡር አቶ አደም ፋራህ የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈጉባኤ፣**
**ክብርት ወ/ሮ መአዛ አሸናፊ የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝደንት፣**
**የተከበራችሁ የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች፣**
**ክቡራን ሚኒስትሮች፣**
**ከሁሉ በላይ የኢትዮጵያን የሁልጊዜ ኩራት የሆናችሁ የፌደራል የፖሊስ አባላት፣**

ከሁሉ አስቀድሜ ላለፉት ሁለት አመታት ስንሰራ የቆየነው ሪፎርም ሃገር ወዳድ፣ ህዝብ አክባሪ፣ ራሱን ለሃገሩ እና ለህዝቡ አሳልፎ የሚሰጥ፣ ከሚመጣውና ከሚሄደው ጋር የሚሄድ ሳይሆን ሁሌም ከኢትዮጵያ ባንዲራ ጋራ የሚጸናውን፣ ፕሮፌሽናል ፌደራል ሰራዊት ለመገንባት ስናደርግ የነበረውን ጥረት ማሳኪያ የሆነውን ትርኢት ዛሬ ስላሳያችሁን በመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ስም የተሰማኝን ክብርና ኩራት ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።

የፌደራል ፖሊስ ሰራዊት የራሱን ህይወት፣ የራሱን የመዝናናት ጊዜ ሰውቶ፣ ኢትዮጵያችንን እና ህዝቦቿን በሰላም ወጥተው እንዲገቡ፣ ሰርተው እንዲያተርፉ፣ ማለም መትጋት እንዲችሉ፣ የሚተማመኑበት ሰራዊት እንዲሆን ከፖለቲካ ፓርቲዎች ገለልተኛ ሆኖ ራሱን ሁልጊዜ ከባንዲራው እና ከመለዮው ጋር በመርህ የሚሰራ ሰራዊት ለመገንባት የጀመርነውን የሪፎርም ስራ አጠናክረን እንድንቀጥል ጉልበት የሚሆን ማሳያ ሳምፕል ዛሬ ስላየን፣ የፌደራል መንግስት በሰራችሁት ስራ እና እየፈጠራችሁ ባላችሁት አቅም ከፍተኛ የሆነ ኩራት እየተሰማው መሆኑን ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ።

ሰራዊታችን በሚመች ሁኔታ ውስጥ ሳይሆን በዝናብ፣ በጸሃይ፣ በሃሩር፣ ግዳጁን ሊወጣ እንደሚችል የዛሬው ትርኢት ራሱ አመላካች ስለሆነ ዝናብ የማይሞክረው፣ ዓመት በአል የማይበግረው፣ ደስታ እና ሃዘን የማይበግረው፣ ትኩረቱ ሁልጊዜ ኢትዮጵያ እና ህዝቦቿን መታደግ የሆነ፣ ከመላው የኢትዮጵያ ህዝብ የተውጣጣ፣ ኢትዮጵያን የሚጠብቅ ሰራዊት እንድትሆኑ። የጀመራችሁት ሪፎርም ከኋላ ከታሪክ የሚማር፣ ዛሬን አጥርቶ የሚያይ፣ ለነገ ደግሞ ራሱን ያዘጋጀ፣ የኮራና የሚያኮራ ሰራዊት እንድትሆኑ። በዚህ ጉዳይ ከባለፈው የዓለም ታሪክ ውስጥ የጥንታዊ ባቢሎን ህዝቦች እና የጥንታዊ ባቢሎን መንግስትን ታሪክ ማየት ጠቃሚ ይሆናል።

በጥንት የባቢሎን ዘመን ጠንካራ መንግስት "የስኳት" አመለካከት ያለው፣ ሃገሩን የሚጠብቅ ሰራዊት ከመገንባቱም ባሻገር መላው ሃገሩን በግንብ አጥር የዘጋ እና ያጠረ፣ አልፎ አልፎም ሊያሳይ የሚችል ማማ የገነባ፣ በዚያም አማካኝነት ጠላቶቹን ከርቀት የሚያይ እና የሚከላከል ሰራዊት ገንብተው ነበር። ይሁን እንጂ ይህ ሰራዊት በእነሱ ባህል በባቢሎን ህዝብ የሚከበር የደስታ ቀን ሲመጣ ጥበቃውን እየተወ ከህዝቡ ጋር ያከብር ነበር።





ይህን ሁኔታ ያጠኑ የፈሪሳዊያን ጠላቶቻቸው አንድ ቀን መላው ህዝብ እና ሰራዊቱ በደስታ በሚዝናናበት ቀን ፈሪሳውያኑ በመግባት ባቢሎንን ታሪክ አደረጓት።

የእኛ ሰራዊት ስናንቀላፋ የማይተኛ፣ ስንዝናና የማይዝናና፣ የበዓላት ጊዜውን እኛን በመጠበቅ የሚያከብር፣ ሲሰራ የማይመሰገን፣ ሲያጠፋ የምንወቅሰው ነው። ከሶስት መቶ ስድሳ አምስት ቀናት ውስጥ ሶስት መቶ ስድሳ አራት ቀናቱን ሰላም ቢሆን ለማመስገን ብዙ ሰዎች አይነሳሱም። አንድ ቀን ቢጠፋ ግን ብዙ ወቃሽ፣ ብዙ ረጋሚ ይኖራል። የኛ ሰራዊት የራሱን ፍላጎት ረትቶ፣ የራሱን መሻት አስታግሶ፣ እኛ በዓል እንድናከብር፣ እኛ እንድንተኛ፣ ኢትዮጵያ ሰላም እንድትሆን ለሚያደርገው ሁለንተናዊ ጥረት የፌደራል መንግስት ሁሌም ከጎናችሁ በመሆን አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ የተጀመረውን ለውጥ የምናጠናክር መሆኑን እገልጻለሁ።

ይህ ፖሊስ፥ እንደ ህግ አስከባሪ ህግ ጠንቀቆ የሚያውቅ፣ እንደ ወንጀለኛ መርማሪ የወንጀል ምርመራ ክህሎት ያለው፣ የስነ ባህሪ ጥናት ያጠና፣ "ቢሄቪየራል ሳይኮሎጂን" ጠንቀቆ የሚያውቅ ነው። እንደ ሰራዊት ወታደራዊ ብቃት ያለው ነው። እንደ አድማበታኝ የተሟላ ተክለ ሰውነት ያለው፣ እንደ ደህንነት ተቋም መረጃ መሰብሰብ ና መተንተን የሚችል፣ ዘመኑን ለመዋጀት የቴክኖሎጂ ብቃትና ግንዛቤ ያለው፤ አሻራ፣ ዲኤንኤ፣ ዲጂታል ሲግኔቸር እንዲሁም ዲጂታል ፎረንሲክን በወጉ መተንተን የሚችል ዘመናዊ ሰራዊት መሆን እንዲችል የጀመርነውን ሪፎርም አጠናክረን የምንቀጥል መሆኑን እና የፌደራል መንግስት ሁለንተናዊ ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ፖሊስ ዋነኛ ዓላማው የሆነው ዜጎችን ከጥፋት የመጠበቁን ስራ በሁሉም ሁኔታ ውስጥ እየጠበቀ የኢትዮጵያን ሰላምና ብልጽግና

ለማረጋገጥ ቢዘንብ፣ የጸሃይ ሃሩር ቢወጣ፣ ቢተኮስ፣ ጠላት ቢያጓራ ሁሌም ጸንቶ የሚቆምና ራሱን መስዋእት በማድረግ ኢትዮጵያችንን የሚያሻግር በመሆን፣ ዋናው ተልኳችሁ የሆነውን ዜጎችን ከመጥፎ ዜጎች የመጠበቅ ስራ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

ፖሊስ መጥፎ ዜጎችን ከሰላማዊ ዜጎች የመጠበቁን ስራ ልክ እንደተለየ ጠላት ምሽግ ቆፍሮ ተኩሶ የሚገድል ወይንም ምሽግ ቆፍሮ የሚከላከለው ሳይሆን በዘመናዊ መንገድ አደጋዎችን የሚያስቀር መሆን አለበት። በህዝብ ውስጥ ተሰግስገው ያሉ፣ መብት ያላቸውን፣ ነገር ግን የሚያጠፉትን የመለየት ተግባር እጅጉን ውስብስብ ስለሆነ፣ ራሱን በህግ ምያተኞች፣ በሳይኮሊጂስቶች በቴክኖሎጂስቶች መጽሐፍት ማደራጀት፣ ማንበብ፣ ራሱን ማብቃት እና ለኢትዮጵያችን ኩራት እንዲሆን አደራ እላለሁ።

ዛሬ ባሳያችሁት ትርኢት እጅጉን እየኮራሁ፣ እራስን ለማብቃት የወትሮው ዝግጁነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣ ኢትዮጵያችን ለማንም ጠላት ሸብረክ ሳትል የጀመረችውን የብልጽግና ጉዞ አጠናክራ እንድትቀጥል፣ ለራሱ ኩራት ለአካባቢው ሃገራት ደግሞ የኩራት ምንጭ የሆነ ሰራዊት የመገንባት ስራ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን በድጋሚ አረጋግጣለሁ። እንኳን ደስ አላችሁ!!

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና**
**ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**





# የባህር ዳር ኢንደስትሪያል ፓርክ ምርቃት ላይ የተደረገ ንግግር

**መስከረም 26፣ 2013 ዓ.ም.**

**የሃገር ሽማግሌዎች፣**
**የሃይማኖት አባቶች፣**
**የባህር ዳር ከተማ ነዋሪዎች፣ እንዲሁም**
**የአማራ ክልል ፕሬዝዳንት እና**
**ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች፣**

በዚህች ውብ ከተማ አንድ ሳይንስን፣ እውቀትን፣ ሃብትን ሊያክል የሚችል ፓርክ በመመረቁ እንኳን ደስ አላችሁ፣ እንኳን ደስ አለን ለማለት እፈልጋለሁ።

ባህር ዳር በተፈጥሮ ውብ ናት፤ ሳቢ ናት፤ ለምለም ናት። ብዙዎች በተፈጥሮ ያልተሰጣቸውን ውበት በሰዎቻቸው ጥረት አስውበው እኛን ሲያስደንቁን፣ ሲያስደምሙን በብዙ ሃገራት ማየት ችለናል። ውብ ሆና በተሰራች ከተማ ውስጥ ያለን ሰዎች ትንሽ ጥረት አድርገን ከተማችን የኛ ብቻ ሳትሆን ብዙዎችን መሳብ የምትችል፣ ለብዙዎቻችን ድምቀት

መሆን የምትችል፣ ለልጆቻችን የስራ እድል መፍጠር የምትችል፣ ህይወት የምታሻሽል ማድረግ ይቻላል። ይህን ለማድረግ የኢፌዴሪ መንግስት ከአማራ ክልል መስተዳድር ጋር በመተባበር በጎርጎራ በቅርቡ የሚጀመረው የቱሪስት መስህብ ስራ ቱሪስቶች ወደ ባህር ዳር እንዲመጡ እና የተፈጥሮ ውበቷን እንዲያደንቁ፣ የህዝቧን ሰላምናሰው ወዳድነት በአይናቸው እንዲያዩ፣ ከዚያም በመነሳት ሃብታቸውን፣ እውቀታቸውን በዚህ ከተማ "ኢንቨስት" እንዲያደርጉ የሚያነሳሳ ነው።

ባህር ዳር ላይ የጀመርነው የቱሪስት፣ የኢንደስትሪ በእርሻም በተለይ አቡካዶን አስመልክቶ ጣና አከባቢ የምንሰራቸው ስራዎችን በሙሉ የነዋሪዎቿን ህይወት የሚያሻሽሉ ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ወደ ከተማችን ለማገዝ የሚያስችሉ ናቸው።

የባህር ዳር ከተማ ነዋሪዎች እንደተለመደው ጨዋነት፣ እንግዳን የማስተናገድ ባህል የተላበሱ ናቸው። እዚህ ስፍራ ተቀጥረን የምንሰራ ደግሞ በትጋት በመስራት ስራ ወዳድ መሆናችንን ማሳየት ይኖርብናል። ሰው የምንስበውም የምንገፋውም እኛ ነን፤ በግልፍተኝነት፣ በስሜት፣ በአንድ ቀን ጥፋት የባህር ዳር ስም ሊበላሽ ይችላል። በትዕግስት፣ በማስተዋል፣ በጥበብ ደግሞ በጣም በርካታ እውቀት እና ሃብት ልንስብ እንችላለን።

ይህ እንዲሆን የመጀመሪያው መልእክቴ በዚህ ኢንደስትሪያል ፓርክ ውስጥ የምትሰሩ ወጣቶች በእድሜ ወጣት ስለሆናችሁ ስራ መልመድ፣ "ዲሲፕሊንድ" መሆን፣ አሰሪዎቻችሁን ማክበር፣ ከተቻለም ባጠረ ጊዜ ውስጥ እነሱን መተካት የሚያስችል ብቃት መፍጠር ይኖርባችኋል። ይህ እንዲሆን መቀጠር ብቻ ሳይሆን የባህር ዳር ከተማ እና የህዝቦቿን





አደራ እና ስም የያዛችሁ መሆናችሁን አውቃችሁ በከፍተኛ የሃላፊነት ስሜት በጥሩ ስነ ምግባር እንድትሠሩ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ሁለተኛ የባህርዳር ከተማ ከንቲባ፣ ይህ ፓርክ የኢንደስትሪ ፓርክ ብቻ አይደለም። ይህ ፓርክ ለከተማው ሰዎች መዝናኛ መሆን የሚችል፣ የተሟላ መሰረተ ልማት ያለው፣ ለባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የምርምር ቦታ መሆን የሚችል፣ ባህር ዳር ላሉ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዐይን መክፈት የሚችል፣ የምርምር ቦታ መሆን የሚችል አውድ ይፈጥራል። ከሃገር ውስጥም ይሁን ከውጭ የምንጠራቸውን ኢንቨስተሮች በመቀበል ጥሩ የእድገት ማዕከል ይሆናል ። ይህ እንዲሆን ግን እሳቤያችን መቀየር አለበት። ይህ መልካም ቦታ፥ ፊት ለፊት አካባቢ ላይ አንድ አስር ሬስቶራንቶች፣ ቡና የሚሸጡ ቤቶች፣ የተወሰኑ መገበያያ ሱቆች ቢታከሉበት ቅዳሜ እና እሁድ ሰዎች የሚዝናኑበት ስፍራ ይሆናል። እግረ መንገዳቸውንም ኢንደስትሪውን እንዲጎበኙ፣ በዚህ ፓርክ ውስጥ ያሉትን ቴክኖሎጂ የእውቀት ብቻ ሳይሆን ከአቀማመጥ አንጻር ያለውን ውበትም እንዲያዩ እድል ይፈጥራል፤ ስለዚህ ፓርኩ ይኼንን አጋጣሚ ችላ ብሎ መተው የለበትም።

ኢንደስትሪያችን ለህዝቡ ክፍት መሆን አለበት። ገብቶ የሚያይ፣ የሚማር፣ ሃሳብ የሚያክል፣ ሃሳብም ጨልፎ የሚሄድ ወጣት እንዲፈጠር፣ ኢንደስትሪውን ለቱሪስት መስህብ ጭምር እንዲሆን፣ በአካባቢው ላይ መጠነኛ ኢንቨስትመንት እንዲኖር፣ ሰዎቻችን ቅዳሜ እና እሁድ መጥተው እንዲዝናኑ፣ ተማሪዎቻችን የምርምር ስራዎቻቸውን መስራት እንዲችሉ ልዩ ልዩ ነገሮችን ከዚህ ኢንቨስትመንት ጋር ማስተሳሰር ያስፈልጋል። ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና ከኢንደስትሪያል ፓርክ ጋር በመተባበር ለባህር ዳር ከተማ አንድ

የመዝናኛ ስፍራ እንዲሆን፣ የከተማው ከንቲባ በከፍተኛ የሃላፊነት ስሜት ቢሰሩበት መልካም ነው።

ጎርጎራ ላይ ከምንሰራው ስራ የሚያንስ ስላልሆነ እዚህ ያለውንም ለቱሪስቶች መዝናኛ እንዲሆን አክሎ መስራት ያስፈልጋል። ሰዎች ካላዩት አይጠብቁትም። ካላዩት አይማሩበትም። እየዘጋን ማደግ አንችልም። እየከፈትን፣ እየተማማርን፣ እየሰጠን፣ እየተቀበልን ስለሆነ፥ ይህ ፓርክ ለተቀጠሩበት ሰዎች ብቻ ሳይሆን እዚህ መስራት ያልቻሉም ቢሆኑ መጥተው የሚያዩት፣ የሚማሩበት፣ የሚመራመሩበት እንዲሆን ከተማው እና የኢንደስትሪ ተቋማት በትብብር አስበው መሥራት አለባቸው። ቦታውን ሌላ የመስህብ ቦታ እንዲያደርጉት አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ባህርዳር ብዙ አቅም አላት፤ ብዙ ቦታዎች አሉ። ይሄን አስተባብሮ በመስራት ለቱሪስት የሚመች፣ ለኢንደስትሪ የሚመች፣ ለኤክስፖርት የሚመች ዘመናዊ ከተማ ለማድረግ ተፈጥሮ የሰጣትን ጸጋ ጭንቅላት በማከል መስራት ይገባል። ከተማችንን ከአፍሪካ ከተሞች አንዷ እንድናደርጋት የባህር ዳር ከተማ የተለመደውን የጽዳት ዘመቻና ችግኝ መትከል ባህል ሆኖ መቀጠል አለበት። ይሄ ግቢም ከፍተኛ የሆነ የዛፍ እጥረት ይታይበታል። ብዙ ዛፍ መተከል አለበት። መዝናኛ መሆን የሚችለው አረንጓዴ ሲሆን ነው። እንደነዚህ አይነት ተግባራት በተለመደው መንገድ እንድትፈጽሙ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ከዚህ የተነሱ አርሶ አደሮች አሁን ባነሳሁት መንገድ ለቱሪስት፣ ለምግብነት፣ ለሱቅ በሚውሉ ግንባታዎች ጭምር እንዲሰሩ ማድረግ ብንችል ኑሮአቸው ይሻሻላል። ነገሩ "ተነሱ" የሚል ሳይሆን፣ "መጣንባቸው" የሚል ሳይሆን፣ "መጣንላቸው" እንዲሆን ማድረግ





ስለሚቻል፤ የአካባቢውን ህዝብ ያቀፈ፣ ልማት የሚያፋጥን፣ ኑሮ የሚያሻሽል፣ ከተማችንን ውበቷን የሚያስጠብቅ እና ተፈጥሮአዊ ጸጋዋን የሚጸና እንዲሆን የሁላችንንም ትብብር ይጠይቃል። በዚሁ መንፈስ የኢንደስትሪ ፓርክ ለከተማችን ጸጋ ስራ የምንፈጥርበት፣ ለሃገራችንም የውጪ ምንዛሬ የምናስገኝበት፣ የሚስፋፋበት እንዲሆን በትብብር መንፈስ መስራት ይገባል። ከዚህ አካባቢ የወጡ ዲያስፖራ እና ሻል ያለ አቅም ያላቸው ምሁራን ካሉ በመተባበር እዚሁ አካባቢ ሁለት ሶስት "ሼዶችን" በመስራት ለዜጎቻቸው ስራ መፍጠርና የነዋሪውን ኑሮ ማሻሻል ስለሚችሉ፣ ለእነሱም ተጨማሪ እድል እንደፈጠረ ታሳቢ ተደርጎ በር የሚከፍት ኢንደስትሪያል ፓርክ እንዲሆን አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

በተሰራው ስራ፣ ባየነው ነገር በጣም ደስተኞች ነን። ኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉም ኢንደስትሪ ፓርኮች አልቀዋል። 13ቱ ስራ ያልጀመሩትን በፍጥነት ማስጀመር ነው የሚቀረን። ይሄንን ከአግሮ ኢንደስትሪ ፓርክ ጋር በማስተሳሰር አካባቢውን ከተለመደው የግብርና አሰራር ባሻገር ወደ ዘመናዊነት የሚቀይር ስራ ፈር የሚቀድ ስለሆነ ሁላችንም በተባበረ ክንድ የጀመርነውን የሰላም፣ የብልጽግና፣ የልማት ጉዞ አጠናክረን እንድንቀጥል አደራ እያልኩ፤ ዛሬ የባህር ዳር ኢንደስትሪያል ፓርክ በይፋ መመረቁን በዚሁ ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

**አመሰግናለሁ ! !**

# ለገበታ ለሀገር የተደረገ ድጋፍ ምስጋና

**ጥቅምት 19፣ 2013 ዓ.ም.**

በኢትዮጵያ ያሉ የፋይናንሻል ሴክተሮች በድምሩ ለገበታ ለሃገር ፕሮጀክት 1.5 ቢሊየን ብር ያዋጡ ሲሆን፥ ከዚህ ውስጥ የኢትዮጵያ የሁልጊዜ ኩራት የሆነውና የኢትዮጵያን የንግድ እንቅስቃሴና ኢንቨስትመንት፣ በእጅጉ እየለወጠ ያለው የንግድ ባንክ 1.1 ቢሊየን ብር አዋጥቷል። የእነሱ መነሻ “ባንኩ የህዝብ ነው፣ የሚሰበሰበው ከህዝብ ነው፣ ለእንደዚህ አይነት ለህዝብ ጥቅም የሚውል ልማት ላይ በከፍተኛ ደረጃ ውሳኔ ላይ መሳተፍ ያስፈልጋል” የሚል ውሳኔ ወስነዋል።

ከፋይናንሻል ሴክተር በተጨማሪ የመንግስት ሠራተኞች በሙሉ የአንድ ወር ደሞዛቸውን እየለቀቁ ዲያስፖራው፣ የንግዱ ማህበረሰብ፣ አቅማቸው የቻለ ዜጎች በሙሉ በተለያየ መንገድ ለገበታ ለሀገር የሚችሉትን እያዋጡ ይገኛሉ። ይህ ስራ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፤ ባህልም መሆን አለበት።





የሰላሙ መደፍረስ ዋነኛው መንስኤ እነዚህ ስራዎች እንዳይሰሩ ነው። ሀገራዊ ፕሮጀክቶች እንዳይከናወኑ መንግስት ዐይኑን ከልማት አንስቶ ወደ ሌሎች ጉዳዮች እንዲያተኩር ስለሆነ፣ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለሰላም ቅድሚያ ሰጥቶ፣ ብልጽግናን በሚያረጋግጡ ጉዳዮች ላይ ደግሞ ተግቶና ተደምሮ እንዲሰራ ጥሪዬን እያቀረብኩ፤ ገበታ ለሀገር ከአንድ ወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ በመጨረሻ ፕሮግራሙ በአራት ይጠናቀቃል።

# የሶማሌ ክልል መንገድ ምርቃት ላይ የተደረገ ንግግር

**ጥቅምት** 20፣ 2013 **ዓ.ም.**

ከጥቂት ዓመታት በፊት በገለልሻ በተለይም መልቀቃ በምትባል ቀበሌ በአንድ ቀን ከሰማንያ ሰው በላይ የሞተባት፣ የጦር ካምፕ የውጊያ ሰፈር ነበረች። የልማት ጉዳይ አይነሳባትም ነበር። አሁን በሱማሌ ክልል በቢሊየን ብር የሚቆጠር ፕሮጀክቶች በየቦታው እየተጀመሩ፣ እየተሰሩና እየተመረቁ ነው።

ይኼን መንገድ ለማስመረቅ ከእናንተ መካከል መገኘት በመቻላችን እጅግ ከፍተኛ ክብርና ደስታ ይሰማናል። ከመንገድ ስራ በተጨማሪ፣ በዚህ ዓመት ባለፈው ጊዜ በነበረው ግጭት የተፈናቀሉ ሰዎችን ወደ ቀዬአቸው መልሰናል። የመጠጥ ውሃ በየከተማው ፕሮጀክት ተጀምሯል። እዚህም እየተሰራ ይገኛል። በዚህ ሥፍራ ሃይስኩል፣ ጤና ጣቢያ እየተሰራ ይገኛል።





እዚህ ቦታ ላይ የሰማነው አዲስ ዜና ቤአዬካ (BAEKA) የሚባለው ሀገር በቀል ፕሮጀክት፣ ከዚህ ቀደም ሲጓተት የነበረውን “መገጭ” የሚባለ ግድብ እና መጠጥ ውሃ በአጭር ጊዜ ሰርቶ ያጠናቀቀ ሃገር በቀል ኩባንያ በመሆኑ፤ ሰርቶ የሚጨርስ አስተማማኝ ኩባንያ በመሆኑ ደስታዬን እጥፍ ድርብ አድርጎታል። ይህ ኩባንያ ከመንገድ በተጨማሪ ከመጠጥ ውሃና ግድብ ጋር የሚያያዙ ሥራዎች፣ እንዲሁም ከባቡር ጋር የተያያዘ ሥራ በሰፊው የሠራ እና ያሳካ ስለሆነ፣ እንዳለውም በአንድ ዓመት ሰርቶ ሲጨርስ እኛም መጥተን የምናስመርቅ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ቃል እየገባሁ፤ ከገባው ቃል በአንድ ሳምንት ከተራዘመ ግን ራሱ ቢአዬካ (BAEKA) ያስመርቀዋል። እኛ ሩቅ ሆነን እንሰማለን ማለት ነው።

# በሶማሌ ክልል የስንዴ ማሳ ጉብኝት ላይ የተደረገ ንግግር

**ጥቅምት 20፣ 2013 ዓ.ም.**

አንዱ የሰርቬይ እና አንበጣን የማጥቃት “ቤዝ” በምስራቅ ያለው እዚህ የሚገኘው ነው። የግብርና ሚኒስትሩ ቅድም እንደገለጹልን በርካታ ዝግጅቶች እየተደረጉ ነው። ኬሚካሎች ገብተዋል፤ አውሮፕላኖች ጥናት እያደረጉ ነው። በተጨማሪም በርካታ ዩኤቪዎች (UAV) እያስገባን ስለሆነ የሚያሰጋን ነገር ካለ ፈጥነን እርምጃ እንወስዳለን። እስካሁን ባለው ሁኔታ ግን ምርት ለመሰብሰብ የሚያስችል ብቃት እንዳለ አይተናል። የተጠቃው ከማሽላ ውጪ ያለው በተለይ ስንዴው በቅርብ ጊዜ ውስጥ መሰብሰብ የሚቻልበት እድል አለ።

በጅጅጋ አቅራቢያ በዝናብ የሚመረተው ስንዴ በተለይ ዘንድሮ ሰፋ ብሎ ተሰርቷል። እስከ መቶ ሺህ ሄክታር ነው እቅዱ፤ ግን በሚቀጥለው በጣም መስፋት አለበት። በሄክታር እስከ 35 ኩንታል ነው እያገኘን ያለነው። ይኼን እያሰፋን ከሄድን ሶማሌ ክልል አብዛኛው ሴፍቲኔት የሚታገዘው ቀንሶ፣ ራሱን በራሱ መመገብ የሚችል፣ ከዚያም አልፎ ኢትዮጵያን መመገብ የሚችል አቅም አለው።





ዋናው ከክልሉ አመራር የምንፈልገው በመንገድ፣ በጤና፣ በመጠጥ ውሃ በመስኖ በእርሻ የተጀመረውን ስራ እንዲያፋጥን ነው። የሶማሌ መፍትሔ፣ የኢትዮጵያ መፍትሔ ልማት ብቻ ነው። ልማት የሚረጋገጠው ደግሞ ዋናው ባለን አቅም ላይ ነው። አሁን ያለው አቅም አንደኛው እርሻ ነው። ቅድም እንዳያችሁት ይኼን የመሰለ መሬት፣ ይኼን የመሰለ አፈር ይዘን፣ ውሃ ይዘን፣ በርካታ ወንዞች እየፈሰሱ፣ ስንዴ መለመንም መራብም የለብንም። ይህ እንዲሆን የክልሉ አመራር ከፍተኛ የሆነ ስራ እየሰራ ነው ያለው።

የፌደራል መንግስት በመስኖም፣ በመንገድ ስራም ሰፋፊ ኢንቨስትመንት በዚህ ክልል እያፈሰሰ ይገኛል። ይኼንን በማጠናከር የክልሉ ልማት በተሟላ ሁኔታ ቢያንስ የራሱን ፍላጎት መልሶ ወደ ሌላ ለመሸጥ፣ ለመርዳት የሚያስችል፣ ብቃት እንዲይዝ ማድረግ ያስፈልጋል።

አጠቃላይ ስራው እንደ መጀመሪያ ዓመት አመርቂ ነው ማለት ይቻላል። ግን በሚቀጥለው ዓመት መስፋት አለበት። ሶማሌ ሙሉ በሙሉ ከማንም ሳይፈልግ ራሱን መመገብ አለበት። ስንዴ ካለ እዚችው ዱቄት ፋብሪካ ካደረግን፣ እዚያ ዳቦ ፋብሪካ ካደረግን ዳቦ ርካሽ ይሆናል። የሶማሌ ህዝብ ዳቦ ካገኘ፣ መኮሮኒ ካገኘ፣ ፓስታ ካገኘ የምግብ ፍላጎቱ 90 በመቶ ተመለሰ ማለት ነው። ይኼ እንዲመለስ የመስኖ ስራ፣ የስንዴ ስራ ላይ ማተኮር አለብን። እስካሁን በተሰራው ላይ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን። በቅርበት እንከታተላለን።

# ከመከላከያ መኮንኖች ጋር የተደረገ ውይይት

**በመቀሌ ከተማ ከከፍተኛ የመከላከያ ሠራዊት መኮንኖች ጋር የተደረገ ውይይት**

**ታህሳስ 3፣ 2013 ዓ.ም.**

የመከላከያ ሰራዊት ልክ እንደ አባቶቹ በሀገሩ ሉአላዊነት የማይደራደር፣ የተሰጠውን ሀገራዊ እና ህጋዊ ሚሽን በብቃት የሚፈጸም፣ ጠንካራ ቁመና ያለው፣ ለሀገር ኩራት የሆነ ተቋም ነው። በውስጡ ስላለፍን ኮርተን ለልጆቻችን ልንናገር እንችላለን። እንዲህ የሚያኮራ ተቋም እንዲሆን አድርጋችሁታል። ለዚህ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የኢትዮጵያ መንግስት በእናንተ ከፍተኛ ኩራት እና ክብር የተሰማው መሆኑን እዚሁ መቀሌ ላይ ብገልጽላችሁ ብዬ ነው ዛሬ የመጣሁት።

በመጀመሪያ የቀድሞ የሃገር መከላከያ ሚኒስቴር ያደራጁ፣ የመሩ በብዙ ነገር ውስጥ ያለፉ አራት ጄነራሎች በመካከላችን አሉ። ጄነራል አበባው ታደሰ፣ ጄነራል ባጫ፣ ጄነራል ዮሃንስ፣ ጀነራል ዓለም እሸት ሁኔታው እንዳጋጠመ "ኢትዮጵያ ትፈልጋችኋለች፤ ሞያችሁ አልነጠፈም፤ እንተማመንባችኋለን፤ ሰራዊቱም ይተማመንባችኋል፤ ኑ እና አገልግሉ" ሲባሉ አራቱም በከፍተኛ ሞራል እና ደስታ ተቀላቅከዋክ። የተሰጣቸውንም ግዳጅ ተወጥተዋል። ይኼ ለወጣት ጄነራሎች ትልቅ





ትምህርት ይሆናል። ከዚህ ቀደም ብያችሁ ነበር፤ "ወታደር ጡረታ አይወጣም"። ታስታወሱ እንደሆነ ስልጠና ላይ። ጡረታ የማይወጣ ብቻ ሳይሆን ተመልሶ ሲመጣ የበለጠ ጥበበኛ፣ የበለጠ ጀግና፣ የበለጠ ድል የሚያሳካ መሆኑን ያሳዩ ጀግኖች ናቸው። እኛ በጣም ኮርተንባችኋል፤ እናንተንም እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

በማእከላዊ ትእዛዝ "በሲቹዌሽን ሩም" (በአፍሪካ ዘመናዊ የሚባል ሲቹዌሽን ሩም ገንብተን) ውጊያውን በቀጥታ በዐይናችን እያየን ነው የመራነው። ይህ ስራ እንዲከናወን ጄነራል ብርሃኑ ጁላ አጠቃላይ ለሰጡት አመራር እና ላሳዩት ቁርጠኝነት ሊመሰገኑ ይገባል። ያው እንደምታውቁት "በሲቹዌሽን ሩም" የሚገኘው አዲስ አበባ ቢሆንም ያው እኛም አልተኛንም፤ ቀንና ማታ ከእናንተ ጋር ነበር የነበርነው። በየእለቱ በሚሰሩ ሥራዎች ለሰጡት አመራርና አብሮአቸው ለነበረው ቡድን የበለጠ ምስጋናና ክብር እናንተ ባላችሁበት ማቅረብ ተገቢ ይመስለኛል።

ብዙዎቻችሁ ስማችሁን ላልጠራ እችላለሁ። በተለይ ሶስቱን ጄነራሎች፣ ሦስቱን ክፍለ ጦር ከነቡድናቸው ይዘው ታላቅ ጀብዱ ፈጽመዋል። ባለፈውም እንደሰማችሁት ስማቸውን አንስቼ ነበር። ነገር ግን የስም ነገር አልፎ አልፎ ሊዘነጋ ይችላልና ስማችሁ ሳይጠራ የቀራችሁ ደሞ እንዳትቀየሙኝ ዛሬ ደግሜ አልጠራም። ግን ሦስቱ ጄነራሎች ኢትዮጵያ ለዘላለም የምታከብረው ገድል ሰርታችኋል። ክፍለ ጦሮቻችሁን አድናችኋል፤ ጀግና መሆናችሁን በሁለት ሦስት ቀን ተደራጅታችሁ፣ ተዋግታችሁ አሸንፋችኋል። ለዚህ ለእናንተ የሚሰጠው ክብር፣ በእናንተ ላይ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ያለው ኩራት ከፍተኛ መሆኑን ሳልገልጽ አላልፍም። ብዙዎች የእናንተን አርአያ እንዲከተሉ የፈጸማችሁትን ገድል በቀላሉ የማናይ መሆኑን በዚሁ

አጋጣሚ ልገልጸላችሁ እፈልጋለሁ። ኮርተንባችኋል፣ ኢትዮጵያም ኮርታባችኋለች። ይኼ ጀግንነት የሁሉም ወታደር ትርጉም ከፍተኛ ነው።

እንግዲህ ጦርነቱ እንደተጀመረ ባለፈውም እንዳነሳሁት ወደ ኤርትራ ተጉዘን ነበር። ከጥቂት ጄነራሎች ጋር እዚያ በነበረው የወታደሩ ሞራል ዝግጅት ካየን በኋላ ውጊያው በሁሉም አቅጣጫ መሆን እንዳለበት ከጄነራል ብርሃኑ ጋር በተግባባነው መሰረት ነው የአሰራር እቅዱ የተሰራው። ባጠረ ጊዜ ውስጥ እንጨርስ የሚለው እቅዳችን የማንም ሀገር ወታደር ቢሆን በእናንተው ልክ በእቅድ የሚያሳካ የለም። ሀብታም ሊሆን ይችላል፣ በቁጥር የበዛ ሊሆን ይችላል።

በሁለት ሳምንት ኦፐሬሽን እንጨርሳለን ብሎ ነው ጄነራል ብርሃኑ ያቀረበው። ሦስተኛውን ሳምንት እኔ ነኝ የጨመርኩባችሁ። ይኼ ትልቅ ጀግንነትና ብቃት ነው። “ለምን ተጨመረ ያ ጊዜ?” የሚለው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያነሳው ጥያቄና እናንተ ጥያቄያችሁ አንድ እንደማይሆን ተስፋ አደርጋለሁ። እናንተ ከወታደራዊ ዐይን ታዩታላችሁ፣ ከፖለቲካ፣ ከዲፕሎማሲ ዐይን ይታያል። የሆነው ሆኖ ስድስቱ ቀን የተጨመረበት የራሱ የሆነ መልክ፣ ብዙ ምክንያት ያለው የተጨመረ ቀን ቢሆንም፣ መከላከያ ባቀደው እቅድ መሰረት ጦርነቱን በድል ማጠናቀቅ ችሏል።

ይህ ጦርነት ስንጀምረው ብቻ ሳይሆን፣ ስንጨርስ ብቻ ሳይሆን፣ በየአንዳንዱ አውደ ግንባር ውስጥ ከፍተኛ አቅም ገንብተናል። ከፍተኛ የማድረግ አቅም ገንብተናል፤ ወታደራዊ ቋንቋ መነጋገር ብቻ ሳይሆን ቴክኖሎጂያዊ ቋንቋ መነጋገርም የሚችሉ ኮማንዶች ተፈጥረዋል።





ጄነራል አበባው ሽራሮን ከያዘ በኋላ አዲገዘሞ ላይ በነበረው ውጊያ ከዚህ ቀደም የነበረው አይነት ዘፈን እንዳይደገም ዋነኛውን ማጥቃት ሳይፈጸም ቦታዎቹን በትክክል ካሳየን በኋላ በቴክኖሎጂ አማካኝነት ጠላትን ማፍረስ ችለናል። እንደምታውቁት በፈረሰ ጠላት ላይ እግረኛው፣ ሜካናይዝዱ ምን አይነት እርምጃ ወስዶ ሰፋፊ ድሎች ማስመዝገብ እንዳለበት በተናበበ መንገድ መፈጸም ተችሏል። አብዛኛው ኪሳራ እንዲቀንስና ጦርነቱ እንዲያጥር የሆነበት ምክንያት የመከላከያ አቅማችን ድሮ ሰዎች እንደሚያስቡት በነበረበት ሁኔታ ሳይሆን በስትራቴጂያችን እንዳስቀመጥነው በአራተኛ እና አምስተኛ ትውልድ ጦርነት የተቀናጀ እግረኛውን ከአመራሩ ጋር አቀናጅቶ መምራት የሚያስችል ብቃት ስለፈጠርን ነው።

ከሁሉ በላይ የሚያስደንቀኝ እና በጣምም የሚያኮራኝ አንድ ሺህ የሚጠጉ የኛ መኮንኖች ተይዘው፣ ጠላት ይዟቸው ሲንቀሳቀሱ እንደነበር ታውቃላችሁ። ማታ ማታ በምናደርገው ኦፐሬሽን በርከት ያለ ሰው በማይኖርበት ሰዓት “ይህ ኃይል የኛ መኮንን ሊሆን ይችላል” ብለን ያቆየናቸው ሚሳኤሎችና ቦንቦች ዛሬ ያኮሩኛል። በተቃራኒው ሆኖ ቢሆን ዛሬ እነ አዳምነህን መሃላችን አናያቸውም ነበር።

ይህ ብቃት ኢትዮጵያን የመታደግ፣ ኢትዮጵያን የማኩራት፣ የተሰጠንን ግዳጅ በአጭር የመፈጸም ብቃት የተቋማችን የሁልጊዜም አርማ መሆን አለበት። በተደጋጋሚ እንዳልኩት ይህ መከላከያ ሰራዊት የብልጽግና ሰራዊት አይደለም። ይህ ሰራዊት የዐቢይ ሰራዊት አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብ ክብርና ኩራት የሆነ ሠራዊት ነው። እኛ ከእናንተ የምንፈልገው ሀገር ወዳድ ጠንካራ እንደትሆኑ እንጂ ለአንድ ፓርቲ የሚወግንና የሚገዛ እንዲሆን ትላንት እንዳልኳችሁ ዛሬም እደግምላችኋለሁ አንፈልገም።

ኢትዮጵያ ከብልጽግና በላይ ናት፤ ከፓርቲ በላይ ናት። ትልቋን ሃገር የመታደግ ሃላፊነት ተጥሎባችኋል። ፖለቲካው የተበላሸ ነው፤ የማያውቀውን የደም ስር፣ የደም ሃረግ እየፈለገ የሚቧደን ነው። እናንተ ግን ጀግኖች ብቻ ሳትሆኑ ንጹህ ኢትዮጵያውያን ናችሁ። በየእንዳንዱ የጦር ግንባር ኦሮሞው አማራን ለማዳን፣ አማራው ወላይታን ለማዳን፣ ወላይታው ሲዳማን ለማዳን፣ ሶማሌውን ለማዳን ያሳያችሁት ጀግንነት ለመላው ፖለቲከኛ እና አመራር አርአያ የሚሆን ስራ ሰርታችኋል። ይኼ መቀጠል ይኖርበታል። ይህ ሁልጊዜ ከእናንተ መወሰድ የለበትም። አንድ ሆናችሁ ሀገር አንድ የምታደርጉ መሆን አለባችሁ።

በእርግጥ ጀግንነታችሁ በውጊያ ብቻ አይደለም። በውጊያ ካሳያችሁት ጀግንነት በላይ አሁን የሚያኮራኝ መብራት እንዲመለስ፣ መንገድ እንዲጠገን፣ ቴሌኮም እንዲገባ በትግራይ ያለው ህዝባችን በወያኔ ስርዓት የደረሰበት መከራ፣ የደረሰበት ስቃይ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲቆምና ወደ ልማት፣ ወደ ሰላም እንዲገባ እያደረጋችሁ ያላችሁት ጥረት በእጅጉ የሚያኮራ ነው።

ሁላችሁም እንደምታውቁት ጦርነቱን ስንጀምር በጣም ብዙ ሰዎች ባጠረ ጊዜ ውስጥ ብቻ ሳይሆን "ማሸነፍ ይከብዳል" የሚል ግምገማና ግምት ይናገሩ ነበር። ይኼ የሆነበት ምክንያት እኛን የሚዋጉን ሰዎች ዘመናዊ ጦርነት አያውቁም፤ የጦርነት ሳይንስ አያውቁም፤ የሚያውቁት የሽምቅ ውጊያ ነው፤ እሱ የሽፍቶች ውጊያ ነው። እሱ በተተኳሽ ቁጥርና በሰው ሃይል ቁጥር ብዛት ማሸነፍን የምናረጋግጥበት ውጊያ ነው።

ሁላችሁም የተሳተፋችሁበት እኔም በደንብ የማውቀው የኢትዮጵያና ኤርትራ ጦርነት ስንት ሺህ ወጣት እንዳስከፈለንና ምን ያህል ጊዜ እንደወሰደብን ታውቃላችሁ። ይኼን የአሁኑን ኦፐሬሽን ደሞ ምን





ያህል ባነሰ የሰው ሃይል መስዋእትነት ለድል እንደበቃን ታቃላችሁ። ከሁመራ መቀሌ በእግር መጓዝ ማለት ብዙዎች አዲስ አበባ ሆነው ዝም ብለው ጀግና እንደሚሉት ብቻ አይመስለኝም። በዚህ መልከአ ምድር፣ በዚህ በረሃ፣ በዚህ ሙቀት፣ ትጥቅ፣ ስንቅ ተሸክሞ ይኼን የሚያክል ጉዞ መጓዝ የማንም ዓለም ወታደር አያደርገውም።

ይኼን ጀግንነታችሁን በአንድ ነገር መድገም አለባችሁ። አሜሪካ ከኢራቅ ጋር ስትዋጋ ኢራቅን አሸንፋ ከያዘች በኋላ ሳዳምን ለመያዝ ወራት ፈጅቶባታል። ስምንት ወር ገደማ። ድልን ግማሽ የሚያደርገው ጦርነቱን ካሸነፉ በኋላ ወንጀለኞቹን መያዝ ሲዘገይ ተጨማሪ ወጪ፣ ተጨማሪ ኪሳራ ያስከትላል። ይኼ ሰራዊት የተሰጠውን ተልእኮ የመጀመሪያውን ተልእኮ መቶ በመቶ አሳክቷል። ነገር ግን ወንጀለኞች መያዝ አለባቸው። ሲያዙም በህግ አግባብ ለህግ ቀርበው መጠየቅ አለባቸው። ከዚህ አንጻር የትግራይ ህዝብ ከፍተኛ ሃላፊነት እንዳለበት ይሰማኛል።

የተደበቁ ሰዎች አሁን በአሃድ መልክ የሉም። በቡድን መልክ የሉም። በግለሰብ ደረጃ ከመኪና ወርደው የተበተኑትን ሃይሎች ካሉበት ቦታ ለትግራይ ክልል አስተዳደር እና ለሃገር መከላከያ ሚኒስቴር ማቅረብ ይጠበቃል። ከሁሉም ዜጎች ያ ካልሆነ በስተቀር ወታደሩ ሀገር የመገንባት ጊዜውን፣ መንገድ የመጠገን ጊዜውን ወንጀለኛ እያሰሰ ጊዜ ይባክናል። እዚያ ውስጥ ዜጎች ይጎዳሉ።

ከኢትዮጵያ መንግስት ልማት፣ ከኢትዮጵያ መንግስት ድጋፍ መጠየቅ ለዜጎች ተገቢ ነው። ነገር ግን ዜጎቹ ግዴታ አለባቸው። ወንጀለኞች ካሉበት አሳልፎ መስጠት። ይኼ ስምምነት ካለ ብቻ ነው፤ ባጠረ ጊዜ ጨርሰን ወደ ልማታችን የምንገባው። ይኼ እንዲሆን ለህዝባችን አደራ

እያልኩ፣ እናንተም ባጠረ ጊዜ ውስጥ ወንጀለኞችን ይዛችሁ፣ በርካታ ሰዎችን እየያዛችሁ እንደሆነ መረጃ አለኝ። ብዙዎች ያሉበት አካባቢ መታወቁም መረጃው አለኝ። ባጠረ ጊዜ ጨርሰን ወደ ዋናው የሀገር መከላከያ ሰራዊት ግንባታ ስራችን እንድንመለስ ኦፕሬሽኑ ማጠር አለበት።

ከዚያ በኋላ በጋራ እያንዳንዱን ክስተት እንገመግማለን። በዚህ ውስጥ ማን ጀግና ነበር? ማን ጀግንነትን ከእውቀት ጋር አዳብሎ ሰራ? እውቀት እና ጀግንነት ብቻ ሳይሆን ማን ጉዳት ቀነሰ? እንዴት ሊያሳካው ቻለ? የሚለውን እንማማርበታለን፤ እንገመግማለን፤ እንወያያለን። በጥቅሉ ግን የሃገር መከላከያ ሰራዊት የኢትዮጵያ ህዝቦች ኩራት በዚህ ቀጣና የሚነሳ ማንኛውንም አደጋ በሚፈለግበት ጊዜ የመመከት ብቃት ያለው ጦር መሆኑን በድጋሚ አረጋግጧል። የጁንታው ሃይል ከሰማኒያ ሺህ በላይ ይገመታል በቁጥር። የጁንታው ሃይል አዳዲስ ትጥቆች ታጥቋል። ከፍተኛ የተተኳሽ ዴፖዎች ነበሩት። ከኮማንዶ፣ ሜካናይዝድ ሮኬት መተኮስ የሚችሉም ሰዎች ከእኛ አስኮብልሏል።

ያው ሁላችሁም እንደምታውቁት መቀሌ እስከገባንበት ቀን ድረስ እኛ ሮኬት አልተኮስንም። በኛ እና በጁንታው መካከል ያለው ልዩነት ይኼ ነው። እኛ ሮኬት የተጠቀምነው ጁንታው መቀሌን ለቆ በረሃ ለበረሃ ለማምለጥ ሲሞክር ብቻ ነው። ይኼ የህዝባዊነትና የእውነት ልዩነት፣ ይኼ የፍትሃዊነት ልዩነት እኛን አሸናፊ አደርጎናል እንጂ፤ "ትጥቅ አለን" ብለን ከተማው ላይ ተኩሰን ቢሆን ኖሮ፣ ውጊያውን እዚህ አካሂደን ቢሆን ኖሮ፣ ዛሬ በዚህ ሞራል መቀሌ ውስጥ አንወያይም ነበር።

እናንተን እንድናከብርና እንድንኮራባችሁ ከሚያደርገን ነገር አንዱ በእያንዳንዱ ከተማ በሁመራ፣ በአክሱም፣ በሽሬ፣ በአድዋ፣





በአዲግራት፣ በመቀሌ በጦርነት ምክንያት ሊደርስ የሚችል ጥፋት በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ በጥበብ የተሞላ አመራር ሰጥታችኋል።

ባግዳድ ፈርሳለች። ባግዳድ የፈረሰችው ዘመናዊ ወታደር እየተዋጋ ነው። ሲሪያ ፈርሳለች። ዘመናዊ ወታደር እየተዋጋ ነው። እናንተ ግን ህዝባዊ ስለሆናችሁ አንድም ከተማ ላይ ጥፋት ሳይደርስ፣ ጉዳት ሳይደርስ፣ ሁሉም ባለበት ሆኖ ማሸነፍ መቻላችሁ የወታደራዊ ጥበብ ብቃት ብቻ ሳይሆን ህዝባዊነት ያለው ሰራዊት መሆኑን ያሳያል። አንድነታችሁ ይጠበቅ። የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት መከላከያን ከነበረበት ሁለንተናዊ አቅም ለማጠናከር አስፈላጊው ስራ ይሰራል። ነገር ግን ኢትዮጵያን የመታደጉ ጉዳይ በአንድ ጊዜ ድል፣ በአንድ ጊዜ የጦር አሸናፊነት የሚጠናቀቅ አይደለም። ሁልጊዜም ወትሮም ዝግጁ የሆነ ወታደር ትጥቁም የቡድን መንፈስም ያለው፣ የአመራር ጥበቡን የሚያውቅ፣ የሚከባበር፣ የሚዋደድ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

አደራ ልላችሁ የምፈልገው በብዙ ሃገር የጦርነት ታሪክ ውስጥ የእኛን ጨምሮ ያለው ወድቀት ከድል በኋላ የሚመጣ መከፋፈል ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ መኢሶን እና ደርግ ወደ ሶማሌ ሲሄዱ አንድ ነበሩ። "በኢትዮጵያ ጉዳይ አንለያይም" ብለው አብረው ዘመቱ። አሸንፈው ሲመለሱ ግን አብረው መቀጠል አልቻሉም። የጁንታው ሃይል ታውቃላችሁ። ወደ ኤርትራ ለውጊያ ሲሄድ አንድ ነበር። ከኤርትራ ጦርነት በኋላ ወደ አዲስ አበባ ግን ሲመለስ አንድ ላይ መቀጠል አልቻለም። አንጃ ተፈጠረ። መማር አለብን። በጦርነት ያገኘነው አንድነት እና ወንድማማች ስሜት መቀጠል አለበት።

በዚህ ጦርነት ለብቻው "ከበደ ጀግና፣ ተሰማ ፈሪ" የሚባል የለም። ሁላችንም ተዋግተናል። ሁላችንም በተሰጠን ተልእኮ ማድረግ

የሚገባንን አድርገናል። አየር ሃይላችን የሰራውን ስራ ታውቃላችሁ። ልዩ የሰራውን ስራ ታውቃላችሁ። ሎጅስቲክስ የሰራውን ስራ ታውቃላችሁ። እዚህ የነበሩት መጋዘኖች ተይዘው ጠላት እኮ ሲል የነበረው "ከሁለት ቀን በኋላ ጥይት የላቸውም" ነው። ጥይት እዚህ እንዳለ ስለሚያውቅ "ጥይት የላቸውም" ይል ነበር። እናንተን "ተዋጉ" እያልን ጥይት ባናዘጋጅ ኖሮ የተሟላ ድል አናመጣም። ሎጂስቲክስ እንደምታውቁት አቅም በፈቀደ መጠን የተሟላ እንዲሆን፣ የተናበበ እንዲሆን ተሰርቷል።

ይህ ነገር በልማት መደገም አለበት። የትግራይ ህዝብ ህዝባችን ነው። "ነጻ ወጣ" ስንል ቀልድ አይደለም። አይታችኋል፤ የታፈነ ህዝብ ነው። ብዙ አምባገነን መንግስታት በአፍሪካ ያሉ "ህዝብ ከኛ ጋር ነው ይደግፈናል" ይሉና ከወደቁ በኋላ ነው የህዝብ ቁጣ የሚታየው። እዚህ እንደሚታየው ማለት ነው። አንዳንድ አባላት፣ ቤተ ዘመድ አሁን ላይገባቸው ይችላል። ለትግራይ ህዝብ አሁን የተፈጠረው አስተዳደር ባጠረ ጊዜ ውስጥ የትግራይ ህዝብ የራሱን ልጆች በፈቀደው መንገድ መርጦ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ሲቋቋም ይኼ ነጻነት ከማንም በላይ የእሱ መሆኑን ያውቃል። ልክ ለማሸነፍ ብዙዎች እንደጠረጠሩን ሁሉ አሁን የምንናገረውን የልማትና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የመገንባት ጉዳይ ሁሉም በአንዴ የሚያምነውና የሚቀበለው ጉዳይ አይደለም። ጊዜ ይጠይቃል። እሱን በተግባር እናሳያለን። የኢትዮጵያ መንግስት የሚናገር ብቻ ሳይሆን የሚተገብር መሆኑን በተደጋጋሚ አሳይቷል።

እናንት ጀግኖች፣ የምለምናችሁ አንድ ነገር ነው። ጀግና አይፎክረም፥ እንዳትፎክሩ። ጀግና አይኩራራም፥ ጀግና ያደርጋል እንጂ፣ አይፎክርም። ጁንታው ጉድ የተሰራው በምላስ ሃይል ማሸነፍ የሚቻል መስሎት ነው። እኛ መዘጋጀት አለብን፤ መሰልጠን አለብን፤ ማንበብ





አለብን፤ መድከም አለብን። ጉራና ፉከራ ውስጥ ግን መገኘት የለብንም። ከገጠምን እናሸንፋለን። እስከምንገጥም ግን አንፎክረም። ይህንን ልምምድ የጦር መሪዎች በደንብ ከልባችሁ መኖር አለባችሁ። ጀግና የሚፎክር ከሆነ፣ ጀግና "አሸንፋለሁ" እያለ ቀድሞ የሚናገር ከሆነ ነገር ይበላሻል።

ጀግና ይራራል፤ ያዝናል፤ ያለቅሳል፤ ይስቃል፤ ሲዋጋ ደግሞ ህይወቱ እስኪያልፍ ይዋጋል። ይኼን ነው ስፔሻል ፎርስ ያሳየን። ጥይት ጨርሰው መሸሽ፣ እጅ መስጠት ሳይሆን፣ በእጃቸው ጠላት ማነቅ የሚችሉ ስፔሻል ፎርሶች የፈጠርነው "ጀግና አይፎክረም" በሚል ብሂል ነው። ሳትፎክሩ፣ ሰራዊቱ ሳይፎክር የተሰጠውን ግዳጅ የሚፈጽም መሆኑን ካሳያችሁ ለአፍሪካ ኩራት ይሆናል።

ስትመለሱ ዘርዘር ያለ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ ውጊያ የተመራበትን መንገድ ከሞላ ጎደል ሰፋ ባለ ጊዜ ውይይት እናደርጋለን። አሁን በነበረው ሁኔታ ይበልጥ አንድ ሆናችሁ፣ ተዛዝናችሁ፣ ተዋዳችሁ፣ ተከባብራችሁ፣ ይቺን ታላቅ ሀገር፣ ይቺን ታሪኳ ከብዙዎች በላይ የሆነ ሀገር መጠበቅ ከቻላችሁ በሚቀጥሉት አስር እና ሃያ ዓመታት ኢትዮጵያን ከልመና አውጥተን ረጂ እናደርጋታለን። የምትለምን ሃገር አናደርጋትም። ይኼን ልክ እንደ ጦርነቱ በተግባር እናሳያለን። ከእናንተ የሚጠበቀው አንድ መሆን፣ ራስን ስሜትን መግዛት፣ ራስን ማሸነፍ የጓድ ፍቅርና የጓድን ፍላጎት ማስቀደም በወታደር እውቀት ውስጥ ያለውን ልምምድ ማጠናከር ነው። ይህንን ካደረጋችሁ በበጀት፣ በስልጠና፣ በእውቀት እንደግፋለን። ጥሩ ጥሩ አመራሮች አግኝተናል። በጦርነት ተፈትነው ያሸነፉ አመራሮች አግኝተናል።

እነ ጄነራል ብርሃኑ ጁላ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ የሁለት ሳምንት የአሰራር እቅድ ማዘጋጀት የሚያስችል ብቃት አሳይተዋል። ጦርነት የሚመራበት ብቃት አሳይተዋል። እነ አበባው እቅዶቻችንን በየሁኔታው፣ በየመድረኩ ከመልከአ ምድሩ ጋር ማናበብና መቀያየር የሚያስችል ብቃት አሳይተዋል። እነ ዓለም እሸት የተኩስ ጥበብ ለእኛም ለጠላትም አስተምረዋል። የተኩስና "የሞቢሊቲን" አቅም አሳይተዋል። እነባጫ በነበሩበት መድረክ፣ ጀን ቀን ቀን የተሰጠውን የማደራጀት ስራ እየሰራ ማታ ማታ በእያንዳንዱ ቀን የእናንተን ድል ይከታተል ነበር።

እነዚህ ሰዎች ትልቅ እሴት ናቸው። እንኳን ተመለሱልን፤ ያስፈልጉን ነበር። በቂ ልምድ አልወሰድንም። ከእነሱ እነዚያን ልምዶች መቀመር አለብን። ከእነሱ ደግሞ የምንፈልገው ቋሚ እና ዘላለማዊ ነገር የለም። የእድሜ ጉዳይም ስለሚያሳስብ ሰራዊቱን ቶሎ ቶሎ መገንባት ከእናንተ ይጠበቃል። ቶሎ ገንብታችሁ፣ አቅማችሁን አጋርታችሁ፣ በቀጣይነት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተከብራችሁ የምትጠሩ እንድትሆኑ በዋናነት ይኼን ሠራዊት መገንባት ይገባል። ይኼን ስራ እንደሚያሳኩ ሙሉ እምነት አለኝ በተሰራው ስራ በጣም ደስተኞች ነን። መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ትልቅ ኩራት ይሰማዋል።

አሁን ግን በድል ስካር ውስጥ ካለን ከፊታችን ያለው ግዳጅ ከፍተኛ ስለሆነ ድልን በልኩ አስተናግደን ወደሚቀጥለው ምእራፍ እንድንሄድ አደራ እላችኋለሁ። ጄነራል ጌታቸው ጉዲና ኤርትራ በነበርንበት ጊዜ ውስጥ "ጦሬ ተመቶ አልመለስም" ብሎ እንባውን ያፈሰሰበት፣ አበባው "ከጦሩ ጋር ነው" የምሄደው ያለበት፣ የቆሰሉ ጀግኖች "አንመለስም" ያሉበት ወዘተ ታሪክ ሆኖ ይጻፋል፤ ገድሎቻቸው ወደፊት ስናንሰለጥን ሠራዊቶቻችንን የምንገነባበት ይሆናል። እንደ ተራ ታሪክ ተነግሮ





የሚያልቅ አይደለም። እና ብዙዎቻችሁ የሚያኮራ ነገር አድርጋችኋል። ጻፉት፤ አዘጋጁት፤ በግምገማ አዳብሩት።

አሁን አዲሱን የትግራይ ክልል አስተዳደር አግዙ፣ ጠንክሮ ራሱን ችሎ፣ ፖሊስ አቋቁሞ፣ እናንተ ወደ ዋናው ስራችሁ እንድትገቡ አድርጉ።

በዚህ መንገድ የኢትዮጵያን መጻኢ ጉዞ የምናሳምር፣ ልማቷን የምናመጣ፣ ሰላሟን የምናረጋግጥ፣ ሊነኳት የሚፈልጉ ሰዎች ሁለት ሶስቴ ደጋግመው እንዲያስቡ ማድረግ የምንችል መሆናችንን ዳግም ለማረጋገጥ በአንድ ልብ በአንድ መንፈስ እንስራ። ወታደር በመሆኔ በጣም ኮርቻለሁ። በእናንተ ውስጥ በማደጌ በጣም ኮርቻለሁ። ከጀግና መገኘት ይቅርና በአጠገባችሁም ያለፈው ይኮራል፤ እንኳን ከእናንተ ጋር ያሳለፈ። በጣም ደስታ የተሰማኝ መሆኑን እየገለጽኩ፤ ተባብረን ሀገራችንን እናሳድጋት፤ እንጠብቃት፣ በርቱ ለማለት እወዳለሁ።

**በጣም አመሰግናለሁ!!**

# የብልጽግና ፓርቲ ማኒፌስቶ

የካቲት 9፣ 2013 ዓ.ም.

**አቶ ታገሰ ጫፎ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈ ጉባኤ፣**
**የተከበሩ አደም ፋራህ የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈ ጉባኤ፣**
**የተከበራችሁ የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች፣**
**የተከበራችሁ ሚኒስትሮች፣ እንዲሁም**
**የብልጽግና ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች**

ለዚህ ብልጽግና የቆመለትን ዓላማና ሃሳብ ለህዝባችን የምንገልጽበት ስናበስር ደስ እያለን ነው፤ እዚህ የተገኛችሁ እንግዶች ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ፤ እንኳን ደስ አለን ለማለት እፈልጋለሁ።

የመጀመሪያ ሃሳብ፣ ይህ የብልጽግና ማኒፌስቶ አይደለም፤ በእኛ እና በህዝባችን መካከል የምንገባው ውልም አይደለም። ይልቁኑም ይኼ ሰነድ በእኛና በህዝባችን መካከል የምንገባው ቃልኪዳን ነው። ቃል ኪዳንና ውል እጅግ የተለያየ ትርጉምና ሃሳብ አላቸው። ውል ማለት መሰረቱ አለመተማመን ነው። በሚሸጥና በሚገዛ፣ በሚሰጥና በሚቀበል ወገን መካከል ያለመተማመን ኖሮ "ይኼንን ባታሟላልኝ ይኼን አልፈጽምም" ተብሎ የሚታሰር ውል ነው። ያ ውል ባለመተማመን፣





አንድ ቀን ጉዳዩ ባይፈጸም፣ ወደ ህግ ብንሄድ፣ "የትኛውን ወገን አሸናፊ ያደርጋል" ከሚል እሳቤ የሚነሳ ነው።

እንደምታውቁት፣ ውል ሰጪና ተቀባይ የመጀመሪያውን ውል ለመፈጸም ለምሳሌ "30 በመቶ የምከፍለህ ይኼን ያህል ስትሰራልኝ ነው" ይላል። ያ ስራ አልተከናወነም ብሎ ሲያስብ ክፍያውን አይሰጥም። አለመተማመን ላይ ስለሚመሰረት ብዙ ጊዜ እንደ አጀማመሩ ፍጻሜው አያምርም። ቃል ኪዳን ግን ቁርጠኝነት ላይ ይመሰረታል።

ሰው ሲጋባ ባል ብቻ የሚፈጽመው ወይንም ሚስት ብቻ የምትፈጽመው ጉዳይ የለም። አንዳንዴ ባል ሲጎድልበት ሚስት እየሞላች፤ ሚስት ሲጎድልባት ባል እየሞላ ነው ያ ምሶሶ የሚቆመው። እንደዚሁ ሁሉ በእኛ እና በህዝባችን መካከል የገባነው ቃል ኪዳን በቁርጠኝነት ላይ የተመሰረተ ነው። የኢትዮጵያን ብልጽግና፣ ጠኢትዮጵያ ልእልና በጋራ፣ በርብርብ፣ በፍቅር፣ በወንድማማችነት የምናሳካው እንጂ፣ ብልጽግናዎች ምንም ያህል የጠራ ሃሳብ ቢኖረን፣ ምንም ያህል ቀን ከለሊት ብንጥር፣ ህዝባችን በዚያ ልክ በቁርጠኝነት ከእኛ ጋር መቆም ካልቻለ የኢትዮጵያን ብልጽግናና ኃያልነት ማረጋገጥ አይቻልም።

በመሆኑም ይህ ቃል ኪዳን የእያንዳንዱን የብልጽግና አባል በገንዘብ የማይተመን፣ በኮንትራት ህግ የማይጠየቅ በፍቃደኝነትና በወዳጅነት ራስን መስጠት እና ማገልገል ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል። ያንን በማድረግ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከኛው ኮሚትመንት ወስዶ በሚሰራው ስራ የምናስባትን ኢትዮጵያ ማምጣት፣ የምናስባት ኢትዮጵያን ለትውልድ ማውረስ እንችላለን። በመሆኑም ይህ ትውልድ

በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ ከህዝባችን ጋር ሳይናወጥ በመጠየቅ ስሜት ሳይሆን በማድረግ እና በመርካት ስሜት የምንፈጽመው መሆኑን ሁላችሁም እንድትገነዘቡ እፈልጋለሁ።

ሁለተኛው ሃሳብ ይህ ሰነድ ድርሰት አይደለም። የሚፎካከሩን ፓርቲዎች ድርሰት እያዘጋጁ ነው። ፖሊሲ ድርሰት መሆን አይችልም። ማኒፌስቶ ድርሰት መሆን አይችልም። ከአንድ ዓመት በላይ ዝርዝር ዳታ ሲሰበሰብ ከምሁራን፣ ከወጣቶች፣ ከተለያየ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ስንወያይበት ቆይተን ለአምስት ዓመት የምንገባው ኪዳንና ለአስር ዓመት የሚኖረን የብልጽግና ፍኖታችን ተናበውና ተመሳክረው ይቺን ሀገር ካለችበት ሁኔታ ወደሚቀጥለው ማሸጋገር የሚችሉ ትላልቅ ሃሳቦች የያዘ ነው።

አሁን ከአንድ ወር በኋላ "እኔም የትምህርት ፖሊሲ አለኝ፤ እኔም የጤና ፖሊሲ አለኝ" የሚል ሃይል ካለ ያ ድርሰት እንጂ ፖሊሲ ሊሆን አይችልም። ፖሊሲ፥ በሰፊ የመረጃ ማሰባሰብ፣ ትንተና ማድረግ፣ የባለፈውን ችግር መገምገም፣ መመርመርና ከዚያም መማር እንዲሁም ነገን በብሩህ ተስፋ መሰነቅና መንደፍ ይጠይቃል። ስለሆነም እኛ ያዘጋጀናቸው ፖሊሲዎች፣ በብልጽግና የውድድር ማኒፌስቶ የተቀመጡ ሃሳቦች በእያንዳንዱ እቅዳችን ውስጥ ያሉ፣ መላው አባላችን የሚያውቃቸው፣ ከህዝባችን ጋር እንደ አስፈላጊነቱ የተወያየንበት፣ እየተወያየን የምናሰፋው፣ የምናሳድገው እንዲሁም የምንተገብረው ሰነድ ነው።

ሁላችሁም እንደምታውቁት ብልጽግና ጆሮ አለው፤ ብልጽግና ዐይኑ የንስር ዐይን ነው፤ ብልጽግና አፉ ቁጥብ ነው። ብልጽግና አፉ ቁጥብ የሆነበት ዋናው ምክንያት ሼክስፒር እንዳለው፣ እንደ ሳንቲም





ከመቅጨልጨል እንደ ብር ዋጋችን ከፍ ማለቱን አውቀን በዝምታ ቁም ነገር ለመስራት ነው፡፡ አሁን በኪሳችን ውስጥ የሚገኝ ሳንቲም ድምጹና ክብደቱ አያስቀምጥም ይንኮሻኮሻል፤ ይረብሻል። ድፍን ሁለት መቶ ብር ግን በዝምታ እና በሞገስ ይቀመጣል። በሳንቲሙና በሁለት መቶ ብሩ መካከል ልዩነት የሚታየው ገበያ ሲወጡ ነው። የሚንጫጫው ሳንቲም አንዲት ዳቦ አይገዛም። ባለግርማ ሞገሱ ኖት ግን ባይናገርም፣ ባይንጫጫም፣ ባይረብሽም ሲወጣ በገበያ ላይ ትርጉም ያለው ነገር ያደርጋል። እኛ አፋችን ቁጥብ ሆኖ የምንናገረውን የምንፈጽም ስብስቦች መሆን አለብን።

ባለፉት ሦስት ዓመታት የኢትዮጵያ ህዝብና የዓለም ህዝብ የሚገነዘበው ብልጽግና የተናገረውን የሚያደርግ፣ የጀመረውን የሚጨርስ መሆኑን ነው። ለማመን የሚከብዱ ስራዎችን ጨርሰናል። ለምሳሌ የህዳሴን ግድብ ብንወስድ፣ በነበረበት የለውጥ ጉዞ ሁኔታ በባለፈው ዓመት ውሃ ሸክፈን ለወዳጅም ለጠላትም ግልጽ የሆነ መልእክት እንደምናስተላለፍ የሚያምን ብዙ ሰው አልነበረም። ነገር ግን ቃል ገብተናል። በቃላችን መሰረት የህዳሴን ግድብ ለኢትዮጵያ አርሶ አደሮች፣ ሴቶች፣ እንዲሁም የነገ ተስፋ የሆኑ ወጣቶችን በብሩህ ብርሃን መፍጠር እንዲችል፣ አምፖላችን ከብርሃን መሻታችን ጋር የሚያያዝ ስለሆነ፣ ባልነው ቃል መሰረት ህዳሴን ለኢትዮጵያ ህዝብ የዚያኑ ዓመት ከንውን በገባነው ቃል መሰረት ፈጽመን ማሳየት ችለናል።

ከሕዳሴ በተጨማሪ አንድነት ፓርክን ስንጀምር ያልቃል ያለ አልነበረም። እንጦጦን ስንጀምር ያልቃል ያለ አልነበረም። የወንድማማችነት ፓርክን ስንጀምር ያልቃል ያለ አልነበረም። አብዮት አደባባይ ላይ የሰራነውን ፕሮጀክት ስንጀምር ያልቃል ያለ አልነበረም። እኛ መጀመር ብቻ ሳይሆን መጨረስ የምንችል፤ መሰረተ ድንጋይ

ማስቀመጥ የምንችል ብቻ ሳይሆን ቀን ከሌሊት ተከታትለን በመጨረስ የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን ለማድረግ የምንተጋ መሆናችን ባለፉት ሦስት ዓመታት በተግባር አሳይተናል። እናም ብልጽግና ከብዙ ፈተና የተማረ ፓርቲ መሆኑን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚገነዘበው ይመስለኛል።

ከዚህ ውጪ ከደቡብ ክልል ብቻ በከንባታ፣ በሃዲያ፣ በሃላባ፣ በዳውሮ እንዲሁም በከፋ ዞኖች በነበረን ውይይት የሚነሱ ጥያቄዎች የመንገድ፣ የጤና፣ የውሃ ጥያቄዎች ብልጽግና በምን ፍጥነት መመለስ እንደሚችል በተግባር ያሳየ ድርጅት ነው። ወደ ሰሜን ብንሄድ በተለይ ወሎ ለረጅም ጊዜ የመንገድ እጦት የሚታይበት አካባቢ ነው። ባለፉት ሁለት ዓመታት ብቻ በወሎ ከአፋር፣ ከትግራይ፣ ከተለያዩ ዞኖች የሚያገናኙ እጅግ ለልማት ወሳኝ የሆኑ የሚጠየቁ መንገዶች ተሰርተዋል። በሰሜን ሸዋም እንደዚሁ። በባህር ዳር ጣናን የሚያሻግር እና ከጎንደር ጋር የሚያገናኘው ድልድም እንደዚሁ፤ በብዙ ቦታ የህዝብ ጥያቄዎችን በማድመጥ መመለስ የቻለ ፓርቲ ነው። በሁሉም ዘርፍ የኢትዮጵያን ፍላጎት እና የኢትዮጵያን ልእልና ማረጋገጥ የሚችልበትን አቅጣጫ በነደፈው የስራ ልክ እና አግባብ የሚችል፣ ያንንም ማሳየት የቻለ፣ ፓርቲ መሆኑን ለሁላችሁም መግለጽ እፈልጋለሁ።

ብልጽግና ከልማትና ከፕሮጀክቶች ውጪ "ኢህአዴግን አፍርሶ ህብረ ብሄራዊ ፓርቲን ይፈጠራል" ብሎ ያሰበ አልነበረም፤ ግን ማድረግ ችለናል። ብልጽግና ከመፈጠሩ በላይ እጅግ የሚያስደስተኝ እና ህዝብ እንዲገነዘበው የምፈልገው፣ ብልጽግና "ፓርቲ" ከመሆን በላይ የኢትዮጵያን ህዝብ "ከአይዲዮሎጂ እስራት ነጻ ያወጣ" ፓርቲ ነው። የማናውቀውንና ለውጥ ያላመጣንበትን ኮሚዩኒዝም፣ ሊበራሊዝም፣ ሶሻል ዲሞክራሲ ወዘተ ህዝቡም ፖለቲከኛውም ሳይገነዘባቸው ከበድ





ከበድ ባሉ ቃላት የሚከራከርባቸውን አውዶች ሰብረን፣ ከሌሎች ሃገራት የምንማረውን ተምረን፣ የእኛን የመደመር መንገድ መፍጠር ችለናል። በዚህም መላው የኢትዮጵያ ህዝብና ፖለቲከኞች ከአይዲዮሎጂ እስራት ነጻ ወጥቷል።

ከኢኮኖሚ አንጻር ብዙ ችግር የነበረብን ቢንሆንም በዚያ ውስጥ በማለፍ የገንዘብ ኖቱም ቀይረን፣ አብዛኛውን የኢኮኖሚ ችግር በመቅረፍ በእዳ ጫና ምክንያት "መበደር የማትችልና ሃይ ሪስክ ተብላ የተፈረጀችውን ኢትዮጵያ" ጫናውን ማቃለል ችለናል። የውጪ ምንዛሪ ክምችታችንን ማሳደግ፣ ኤክስፖርታችንን ማሳደግ፣ ገቢዎቻችንን ማሳደግ፣ አንዳንድ ሴክተሮቻችን ላይ ያሉብንን ድካሞች ቀንሰን፣ በተለይ በማዕድን ዘርፉና በግብርና አካባቢ ወጣ ያሉ ስራዎችን በመስራት ከፍተኛ የገቢ ምንጭ እንዲሆኑ ማድረግ እንችላለን። በቱሪዝም እንደ ሌሎች አዲስና ያልነበሩ ትርክቶች የምንፈጥር ሳይሆን የሚነገር፣ የሚታይ፣ የሚሸጥ እንኳን ለውጪው ለእኛ የሚያጓጓ፣ በርካታ ሃብት ያለበት ሃገር ነው። ያንን እናወጣለን ስንል ያመነን አልነበረም። የገንዘብ ኖት መቀየር ተችሏል፤ የእዳ ጫናን በተወሰነ ማቃለል ተችሏል፤ ከሃይ ሪስክ ውስጥ ኢትዮጵያን ማስወጣት ተችሏል፤ በኮሮናም ጊዜ ቢሆን ዓለም የኢኮኖሚን እድገት የማይታሰብ ባለበት ወቅት የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ለውጥ በእድገት ትራጄክተሪ ማስቀጠል የቻለ ፓርቲ ነው። ከዚህም አንጻር የጀመርናቸውን የተግባር ልምምዶችና የቀሰምነውን እውቀት ካሰፋን እና ወደ ላቀ እድገት ከተንደረደርን ኢትዮጵያን ያለጥርጥር ትበለጽጋለች፤ ይኼንን በትንሹም ቢሆን ማሳየት የቻለ ድርጅት ነው።

ከሁሉ በላይ "ኢትዮጵያ አትፈርስም የሚያፈርሳት ይፈርሳል እንጂ" ባልነው መሰረት ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚፈልጉ የፈረሱበት፣

የኢትዮጵያን ህልውናና ቀጣይነት በግልጽ የታየበት፣ ባልነው ልክ አፍራሾችን ማፍረስ እንጂ ሃገራችንን ለማፍረስ የሚችሉ ኃይሎችን ለመሸከም ዝግጁ ያልሆንን መሆናችንን በተግባር ያሳየንበት ነው።

ብልጽግና እንደተባለው ለሁሉም፣ በሁሉም፣ ከሁሉም የሆነ ፓርቲ ነው። ብልጽግናን ኢትዮጵያ ውስጥ ማረጋገጥ ከፈለግን፣ ኢትዮጵያን በልእልና ማማ ላይ ማቆም ከፈለግን፣ ኦሮሞም፣ አማራም፣ ትግሬም፣ ሲዳማም፣ ሶማሌም፣ አፋርም፣ ወላይታም፣ ስልጤም፣ ጉራጌም፣ ሌሎችም በእኩልነት የሚሳተፉበት፣ በእኩልነት የሚጠቀሙበት ማድረግ ካልቻልን፣ ቢብዛ የሃያ አምስት ዓመታት ብልጠት እንጂ ዘላቂ ድል ማምጣት አንችልም። መላው የብልጽግና አባላትና የፓርቲያችን ደጋፊዎች መገንዘብ ያለባቸው ኢትዮጵያ ወደ ብልጽግና ማማ መውጣት የምትችለው ሁሉም ኢትዮጵያዊያን በእኩልነት፣ በፍቅር፣ በወንድማማችነት ተከባብረው፣ ተፈቃቅደው፣ ተዋደው መትጋት ሲችሉ ብቻ ነው:: ተረኝነት ብሎ የሚያስብም፣ ተረኝነት ብሎ የሚያውጅም ካለ የኢትዮጵያን ህልውና በአጭር የሚያስቀር ስለሆነ እኛ ብልጽግናዎች መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድ ልብና መንፈስ ተሳስረን ሁሉንም የምንጠቅም፣ ሁሉንም የምናገለግል፣ ሁሉንም የምንወድና ለሁሉም የምንቆም መሆን ይጠበቅብናል።

ይኼንን ማድረግ ከቻልን በኢኮኖሚው ዘርፍ ብዘሃ ዘርፍ፣ ብዘሃ ተጠቃሚ በሚል የተገለጸው፣ በተለይ በግብርናው የምንፈልገው ነገር በቀላል ቋንቋ በማኒፌስቶ ተቀምጧል። ሦስቱን "መ" ዎች የመጀመሪያው "መ" ኢትዮጵያ ራሷን "መመገብ አለባት" የሚል ነው፤ በቂ ውሃ አለን፣ በቂ መሬት አለን፣ በቂ የሰው ሃይል አለን። የሌለንን ትራክተር፣ የሌለንን ፓምፕ፣ የሌለንን እውቀት በማከል ራሳችንን





ለመመገብና ለምግብ እጃችንን ወደ ሌላ ቦታ መዘርጋት ማቆም የሚያስችል ስራ መስራት ይኖርብናል።

ሁለተኛው "መ" መዋቅራዊ ሽግግር ነው። በቡሬ እንዳያችሁት "አግሮ ኢንደስትሪ" አሁን በሲዳማ ክልል የሚታየው፣ ቀጥሎም በኦሮሚያ በሁሉም ክልሎች እና አካባቢዎች "የአግሮ ኢንደስትሪን" አስፋፍተን የግብርና ምርቶችን ወደ ኢንድስትሪ ግባቶች የሚሸጋገሩበት እና ለሃገር ውስጥ ምርትም፣ ለውጪ ገበያ የሚውሉበትን አቅም መፍጠር ይኖርብናል።

ሶስተኛው "መ" ምንዛሬ ነው። ግብርና ገንዘብ እንደሚያመጣ ከኢትዮጵያ በላይ የሚያውቅ የለም። በአንድ በኩል ቡና እየላክን ገቢ እናመጣለን። በሌላ በኩል ስንዴ እያስገባን የውጪ ምንዛሬ እናጣለን። ግብርና ከውጪ የምንገዛውን ማስቀረት የሚችል፣ በውስጥ ያመረትነውን ደግሞ ልከን ተጨማሪ ሃብት ሊያስገኝ የሚያስችል ሴክተር ስለሆነ በዘንድሮ በበጋ "የኢሪጌሽን" ግብርናችን በብዙ ሄክታር የሚቆጠሩ ስንዴዎች ማልማት ጀምረናል። ይህን በሁሉም ቦታ በማጠናከር በማስፋት የሚመግበን፣ መዋቅራዊ ሽግግር የሚያመጣና መዋቅራዊ ሽግግር የሚያመጣ ማድረግ አለብን።

ሁላችሁም እንደምታውቁት ሰፋፊ ግድቦች እየሰራን ነው። ማብዛት ይኖርብናል። "ይህንን ካላደረጋችሁ አስር ብር አንለቅላችሁም፤ ይኼንን ካልፈጸማችሁ እንዲህ አናደርግላችሁም" የሚሉ ሰዎችም ትንሽ ሰብሰብ ብለው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን የሚያከብሩበት ሁኔታ መፍጠር ስለሚቻል፣ ግብርና በሶስቱ "መ" ታጅቦ ዘላቂና የብልጽግና ጉዞአችንን የሚያረጋግጥ አንዱ ግብአት መሆን ይጠበቅበታል።

ከከተማ አንጻር በሦስት "I" ነው ያስቀመጥነው። የመጀመሪያው "I" "ኢንፍራስትራክቸር" ነው። ከተማ ውስጥ መሰረተ ልማት ችግር አለ፣ ከፍተኛ የቤት ችግር አለ፤ የመንገድ ችግር አለ፤ የውሃ ችግር አለ፤ የጤና ችግር አለ። እነዚህን ችግሮች መፍታት የሚያስችል "ኢንፍራስትራክቸር" ላይ ያተኮረ ስራ በከተሞች መስራት ይኖርብናል።

ሁለተኛው "I" ኢንደስትሪ ነው። ከተሞች በየዘርፉ ምርታማነት ላይ ካላተኮሩ በስተቀረ የተከማቸውን ሥራ አጥ ወጣት ስራ አስይዘው፣ ገንዘብ አምጥተው፣ ቀጣይነት ያለው እድገት ማምጣት ያስቸግራል። በመሆኑም ከተሞቻችንን "ኢንደስትሪያላይዝ" ማድረግ፣ ሁለተኛው "I" የሚይዘው ስራ ይሆናል።

ሦስተኛው "ኢንኪዩቤሽን" ነው። የፈጠራ ስራዎች እንዲያድጉ፣ ወጣቶች ተደራጅተው ስራ መስራት እንዲችሉ፣ ስራ እንዲያገኙ፣ የፈጠራ ስራዎች ለሃገር ውስጥና ለውጪ ጥቅም እንዲውሉ፣ "የኢንኪዩቤሽን" ማዕከላትን በማስፋት በከተሞቻችን ላይ አተኩረን እንሰራለን። ይኼን በምናደርግበት ሰዓት ስራ አጥነት ይቀንሳል፤ የኑሮ ሁኔታችን ይሻሻላል፤ ገቢያችን ያድጋል፤ በከተሞች ያለው የኑሮ መስተጋብር የተሳለጠ ይሆናል።

በገጠር የምንሰራው ስራ በተለይ በቱሪዝም መስክ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተን አደረጃጀቱን ቀይረን ከሰሜን እስከ ምእራብ፣ ከደቡብ እስከ ምስራቅ ኢትዮጵያ ውስጥ ታይተው የማይጠገቡ የተፈጥሮና የታሪክ ሃብቶች ስላሉ እነዚህን እያወጣን መጀመሪያ እኛ ኢትዮጵያዊያኖች የኢትዮጵያን ልክ እንድናውቅ፣ ቀጥሎ ደግሞ ገንዘብ እንድናገኝበት በትኩረት እንድንሰራበት መስክ ይሆናል።





በሚቀጥለው ስድስተኛው ሃገራዊ ምርጫ የብልጽግና ማኒፌስቶና እሳቤ በግልጽ የተቀመጠ ቢሆንም ዋናው ፍላጎታችን ግን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያንን አሸናፊ የሚያደርግ ምርጫ ማድረግ ነው። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያንን አሸናፊ የሚያደርግ ምርጫ ማድረግ ማለት ሰላማዊ፣ ዲሞክራሲያዊ፣ ሁሉም በነጻነት የሚሳተፍበት፣ በሃሳብ ልእልና የሚወድቅበት፣ ወይም የሚመረጥበት ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል። የሚፎካከሩት ፓርቲዎች ከወዲሁ ምርጫ ማድረግ ተስፋ የለውም። "ከምርጫ መውጣት ይሻላል" ብለው የሚያስቡ ይኖራሉ። ለእነሱ ያለኝ ምክር በምርጫ መወዳደርና ሃሳባቸውን መሸጥ ይሻላል። ምክንያቱም መንግስትም ብልጽግና እንደ ከዚህ ቀደሙ ዓይነት ምርጫ የማድረግ ፍላጎት ስለሌለው፣ ለህዝብ በሰጠነው ሃሳብና ተስፋ ልክ ህዝባችን መርጦን በፓርላማ መንግስት፣ በተለያየ ስፍራ ልዩ ልዩ ድምጾች እንዲሰሙ ማድረግ ከሁሉም ይጠበቃል። ስለዚህ ሁሉም አሁን የሚታያቸውን ችግርና የመሸነፍ ስሜት አሸንፈው በምርጫው እንዲወዳደሩ፣ በእኛ በኩል ደግሞ በተቻለ መጠን የትብብር እና የፉክክር መንፈስን እንዳናበላሽ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች መታገዝ የሚገባቸውን ነገር ማገዝ ይኖርብናል። አግዘን፣ ደግፈን፣ ወደ ምርጫው እንዲሳተፉ ማድረግ ይጠበቅብናል።

ምርጫው ዲሞክራሲያዊ ካልሆነ፣ ምርጫው ሰላማዊ ካልሆነ፣ ምርጫው ነፃ ካልሆነ ኪሳራ ነው። ምርጫው እነዚህን ካሟላ ከሁሉ በላይ አሸናፊ የምትሆነው ኢትዮጵያ ናት። ብልጽግና ቢያሸንፍም ባያሸንፍም ኢትዮጵያን አሸናፊ የሚያደርግ መንገድ ከያዘ በድምሩ በኢትዮጵያ ድል ውስጥ ተጠቃሚ ይሆናል። ኢትዮጵያ ሳታሸንፍ እኛ ግን አጭበርብረን ምርጫውን ብናሸንፍ ዘላቂ ድል ስለማይሆን በተቻለ መጠን ሰላማዊ፣ ዲሞክራሲያዊ፣ ሁሉ የሚሳተፍበት፣ በሃሳብ ልእልና

ብቻ በልጠን የምንገኝበት ምርጫ እንዲሆን፣ ሁሉም ተሳታፊ የበኩሉን እንዲያደርግ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

በዚህ ማኒፌስቶ የተቀመጡ ሃሳቦች በሙሉ በርብርብ፣ በሚቀጥለው አምስት ዓመት ተተግብረው፣ የኢትዮጵያን "ጂዲፒ" ቢያንስ በእጥፍ እንደያድግ የምናደርግበት አንድ "ተርም" ስለሚሆን፣ ከዚህም አንጻር ሃብት በማፍራት የሚታወቁና ብቃት ያላቸው ሰዎች፣ ምሁራን አርሶ አደሮች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች ሁሉም የሚሳተፉበት፣ ለሁሉም የሚሆን፣ ከሁሉም የሚመጣና ኢትዮጵያን ወደሚገባት የብልጽግና ማማ የሚያወጣት ምርጫ እንዲሆን ሁላችሁም ባላችሁ አቅም ርብርብ እንድታደርጉ። በውስጣችን ያሉ ድካሞች፣ ስንፍናዎችና ያለማድረግ ውስንነቶች እየታረሙ፣ እየተቀረፉ ኢትዮጵያን ወደሚገባት ብልጽግና ማውጣትና አሁን ከትናንሽ ሃብታሞች ከትናንሽ ጉልበተኞች ቁጣ እና እርዳታ መገላገል የሚጠበቅ መሆኑን ማሳሰብ እፈልጋለሁ።

በመጨረሻ ረዳት ፕሮፌሰር ቅድም ያነሳው ባለ ጸጋ የሚለው ሃሳብ ከገንዘብ ጋር መያያዝ የለበትም። እኛ ብልጽግና ስንል ሁለንተናዊ ብልጽግና ነው። በአእምሮ የታደሰ፣ መስጠት የሚችል፣ ያገኘውን ማካፈል የሚችል፣ መውደድ የሚችል፣ በፍቅር ውስጥ ማበብ የሚችል ማህበረሰብ ስለምንፈልግ፣ "ባለ ጸጋ" ሲሏችሁ "ባለ ገንዘብ" እያላችሁ እንዳታስቡ። የእናንተ ስራ ብዙ ባለ ጸጋዎችን መፍጠር ነው። የገንዘብ ባለ ጸጋ፣ የእውቀት ባለ ጸጋ፣ የሃሳብ ባለ ጸጋ፣ የፍቅር ባለ ጸጋ መፍጠር ስለሆነ "ባለ ጸጋዎች" ሲላችሁ "ባለ ገንዘብ" ማለቱ እንዳልሆነ እንዲታሰብ።

ለምሳሌ ለእኛ "ጓድ" ለሚለው አባባል በነበረው ልምምድ ብዙ ጥላቻ የለንም፤ ነገር ግን ባለፉት ሦስት አመታት በነበረው ሂደት የተሰዉ





ጓደኞቻችንን "እነ ዶክተር አምባቸውን" ስናስብ የምንመርጠው ቃል "ወንድማለም" ነው። "ወንድማለም" የሚለውን ቃል በጣም እንወደዋለን። አንደኛ "ወንደማማችነት" እያልን ስለሆነ እኛ ውስጥ የሌለ ወንደማማችነት ለህዝብ ሊደርስ ስለማይችል ነው። እኔ ብናልፍን "ወንድማለም" እለዋለሁ፤ ብናልፍም ታገሰን "ወንድማለም" ይለዋል። ጓድም አልፎ አልፎ ካመለጠን ችግር የለውም።

ከሁሉ በላይ ግን በርትታችሁ ባለጸጋዎች እንድትፈጥሩ አደራ እላለሁ።

**አመሰግናለሁ!!**

# ሀገርን እና ሕዝብን ማገልገል ያኮራል!

**የካቲት 27፣ 2013 ዓ.ም**

**አፈ ጉባኤ አደም ፋራህ፣**
**ሚኒስትር ሙፈሪያት ከሚል፣**
**የተከበራችሁ እንግዶች፣**
**ከሁሉ በላይ ያለፉትን ለማሳረፍ፣ ለመጪዎች ተስፋ ለመሆን፣ ለኢትዮጵያ ምሶሶ ለመሆን በመወሰን የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች የሆናችሁ በጎ ፍቃደኞች፤**

በዚህ ሁኔታ በመገናኘታችን የተሰማኝን ልዩ ክብርና አድናቆት ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ። ፈቅዶ፣ ወድዶ በነጻ መስጠት መታደል ነው። ለሁሉም የተሰጠ ነገር ቢሆንም ሁሉም መልሶ ሊሰጥ አይቻለውምና እናንተ ከመቶ ሚሊየን መካከል በነጻ የተሰጣችሁን እድሜ፣ ጉልበትና የማድረግ አቅም ለሃገራችሁ ድጋፍ ለሚሹ ዜጎች በነጻ ለመስጠት ስለወሰናችሁ ከፍ ያለ ክብር ሊሰማችሁ ይገባል። ይኼም ስጦታ ደግሞ ፍሬ እንደሚያፈራ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ።

ዛሬ የምንቀናባቸው ያደጉ ሃገራት ዋና ዋናዎቹ ቢያንስ በወር አንድ ቀን በነጻ የሚያገለግሉ ዜጎች አሏቸው። እነዚያ ዜጎች ራሳቸው ከማገልገል በተጨማሪ ለሌሎች ተስፋ በመሆን፣ አረአያ በመሆን፣ ሃገር





እንድትገነባ፣ ሃገር በጸና አለት ላይ እንድትቆም፣ አላፊ አግዳሚው እንዳይነቀንቃትን ምሳሌ በመሆን ሃገራቸውን ገንብተዋል። ለሁላችንም የሚያስቀና የህልም ምድር መሆን ችለዋል።

እኛ ኢትዮጵያዊያን ከላይ የተሰጠን ከሁሉም የሚሻል የጠገበ፣ የሚያምር፣ የሚያረካ ታሪክ ያለን መልከአ ምድራችን ታይቶ የማይጠገብ ነው። ጀግኞች አባቶቻችን በደምና በላብአቸው ነጻነቷ የተጠበቀናና ኮርታ የምትኖር ሃገር አስረክበውናል። አሁን ያለን ትውልዶች በነጻ መስጠትን፣ ዝቅ ብሎ ሀገር ማገልገልን ከተለማመድን ኢትዮጵያ የምታስቀና ሀገር ናት፤ ብዙዎች አርአያ የሚያደርጓት ሃገር እንደምትሆን ቅንጣት ጥርጣሬ የለኝም።

ዜጎች ሃገር ትቀየር ዘንድ ልናስበው የሚገባ አንድ ቁልፍ ቁም ነገር አለ። ድል የምናስብ፣ እድገት የምናስብ፣ መለወጥ የምናስብ ከሆነ ድል እና ስንፍና ተጋብተው አብረው መኖር አይችሉም። ስንፈና ባለበት ድል የለም፤ ስንፈና ባለበት ብልጽግና የለም፤ ስንፍና ባለበት መሻገር የለም። የሩሲያ ምሁራን እንደሚሉት "ድል እና ስንፍና ለአንድ አፍታ እንኳን ቢገናኙ ተጋብተው የሁልጊዜ ኑሮን በጋራ ማድረግ አይችሉም።"

እናንተ መሻሻል፣ ማደግ፣ መበልጸግ፣ መለወጥ የምትሹ ወጣቶች "ከስንፈና ጋር አንጋባም" ብላችሁ፣ በነጻ ለማገልገል ፈቅዳችሁ፣ ከቤተሰባችሁ ወጥታችሁ፣ በማገልገል መቆየታችሁ የሚያሳየው ስንፈናን የምትጠየፉ፣ ለድል፣ ለለውጥ፣ ለመሻገር እና ለማሻገር ዝግጁ መሆናችሁን ነው። እንደ እናንተ አይነት ያሉ ወጣቶች እንዲበራከቱ፣ በነጻ ማገልገል ክብር መሆኑን እንዲያውቁ፣ ማገልገል ብቻ ሳይሆን ቀጣዩን ስልጠና ማስተማርም ጭምር ከእናንተ የሚጠበቅ መሆኑን ከወዲሁ ላሳስባችሁ እፈልጋለው።

ዜጎች ትንሽ ጉልበት፣ ጥቂት ጊዜ፣ ትልቅ ልብ ካላቸው ሃገር ይገነባሉ። እንደ እናንተ በአፍላ እድሜ ላይ ያለ ወጣት ያለው ትንሽ ጉልበትና ጊዜ ለሀገሩ ቢሰጥ ብዙ ነገር ይለውጣል።

አዲስ መኪና ቀለሙ ያምራል፤ መስታወቱ ያምራል። ጎማው ጠንካራ ነው። ውስጥ ብትገቡ መቀመጫው ይመቻል። ሙዚቃ ብትከፍቱ፣ ሬዲዮ ብትከፍቱ ስፒከሩ ጥርት አድርጎ ያሰማል። መብራት ብታበሩ ቁልጭ አድርጎ ማመላከት ያስችላል። ከዚያም በላይ ሞተር ብታስነሱ ሞተሩ በከፍተኛ ድምጽ አይረብሽም። አዲስ መኪና ብዙ የሚያምር ነገር አለው። ነገር ግን ይህን የሚያምር መኪና ቆጥባችሁ፣ ሰስታችሁ፣ "አልነዳም ብላችሁ" ለሁለት፣ ሶስት ዓመታት ባለበት ብታቆሙት ጎማው ባለበት ይተኛል፤ ቀለሙ ይለቃል፤ ላስነሳህ ብትሉት መኪናው አይነሳም። ምክንያቱም መኪና እየሰራ፣ ዘይት እየተቀየረ፣ ውሃ እየተጨመረለት ካልሆነ በቀር አዲስ መሆኑ ብቻ ዋስትና አይሆንም።

እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ መስቀል ፍላወር አካባቢ ብትሄዱ ከዚህ ቀደም በስፋት አሮጌ መኪና የሚታይባቸው የመሸጫ ቦታዎች ዛሬ መንገድ ላይ ስትጓዙ በአዲሱ ህግ መሰረት አዳዲስ መኪናዎች ቢያንስ አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት የሚሆኑ ቦታዎች ላይ ማየት ትችላላችሁ። እነዚህ አዲስ መኪናዎች በዱባይ እንደምናያቸው፣ በለንደን እንደምናያቸው የአዲስ መኪና መሸጫ ቦታዎች አያምሩም። ምክንያቱም መኪኖቹ አዲስ ናቸው እንጂ፣ ያሉበት ቦታ በመስታወት ያሸበረቀ አይደለም። እነዚያን ቦታዎች ሻል ወዳለ ደረጃ ማሻሻል ብንችል፣ በመስታወት ውስጥ ማቆየት ብንችል፣ የመኪናዎቹን ውበት ለገዥ፣ ለሚመኝ በተሻለ መንገድ ማሳየት ይቻላል። አዲስ መኪና ማምጣት ስለቻልን ለሚገዛውና ለሚሸጡ የባንክ ስርዓት ማመቻቸት





ስንችል፣ ብዙዎች እያዩ የሚያማርጡበት፣ ሲፈልጉም ተበድረው የሚገዙበት ሁኔታም የሚመቻችባት ሃገር ትሆናለች ማለት ነው።

ዛሬ ግን የመጀመሪያው ደረጃ የሆነው መኪና የገባ ቢሆንም መሸጫው በትክክል ባለመቀየሩ ገገሮች በቀላሉ ተበድረው መግዛት ባለመቻላቸው አዲሱን መኪና ከነውበቱ፣ ከነግርማው ማየት አይቻልም። እና ወጣቶች ይህን አዲስ መኪና ሲያዩት የሚያምር፣ ሲሳፈሩበት በፍጥነት የሚያደርስ፣ ጉልበት ያለው ሆኖ ሳለ ይኼን በማይመጥን ስፍራ በመገኘቱ ብቻ ውበትና ፍጥነቱ ይኮስሳል። ወጣትም እንደዚያው ነው፤ ጉልበቱን ተሸክሞ ቢቀምበት፣ ቢጠጣበት፣ ቢያማበት ልክ መስቀል ፍላወር እንዳለው አዳዲስ መኪና ለአይን የማይሰብ ይሆናል።

እናንተም ጉልበታችሁን በጥቂቱ ለመስጠት ፈቅዳችሁ ለኢትዮጵያና ለህዝቦቿ ኩራት ስለሆናችሁ ስለፈቀዳችሁ "እንኳን ደስ አላችሁ" ማለት እፈልጋለሁ። ያልኳችሁም ዜጎች ጥቂት ጉልበት፣ ጥቂት ጊዜና ትልቅ ልብ ካላቸው ትገነባለች ነው። የመጀመሪያውን ጉልበት በመኪና መስዬ ገልጬዋለው።

ሁለተኛው "ጊዜ" ነው። ጊዜ እንደ ባለቤቱ ፍቃድና ሁኔታ ይወሰናል። ለሁሉም የተሰጠው ሃያ አራት ሰዓት ቢሆንም ሁሉም ሰው እኩል አይጠቀምበትም። አንዳንድ ጊዜ የምንጠብቀው ነገር ካለ ጊዜ ሲበዛ ይዘገያል። ሰው ቀጥረን ቁጭ ብለን ስንጠብቅ አምስት ደቂቃ ትላንትና የምናውቀው ዓይነት ሳይሆን እንደ አምስት ሰዓት የረዘመ ይሆናል። ወይም ባስ ስንጠበቅ ሰልፍ ላይ ስንሆን እያንዳንዱ ደቂቃ የረዘመ ይመስለናል። በሌላ በኩል ደስተኛ በምንሆንበት ሰዓት ጊዜ ያጥራል። ጊዜ ራሱ ሳይሆን የእኛ ደስተኛነት፣ ጊዜ ራሱ ሳይሆን የእኛ ጠባቂነት

ያጠረ እና የረዘመ ያደርገዋል። እንዲሁም በጣም ስናዝን፣ በሃዘን ስሜት ስንሆን ለሊቱ የማይነጋ፣ ያ የጭለማ ጊዜ የማያልፍ እስኪመስለን ድረስ ጊዜ ይንፏቀቃል። ጊዜን የሚያፈጥነው፣ ጊዜን የሚያዘገየው፣ ጊዜን የተንፏቀቀ የሚያስመስለው ራሱ ጊዜ ሳይሆን የእኛ ሁኔታ ነው። እኛ ያለንበት ሁኔታ የጊዜውን ፍጥነት በተለያየ መንገድ እንድንመለከት ስለሚያደረግ፣ ጊዜያችሁን ለመጠቀም ወስናችሁ በጥቂቱ ለሃገራችሁና ለህዝባችሁ መስጠት የወሰናችሁ ወጣቶች፣ ጊዜን መጠቀም የማይችል ሰው፣ ጊዜን መስጠት የማይችል ሰው፣ መሻሻል፣ ማደግ፣ ሃገሩን ማሳደግም አይችልም። ጊዜን ለመጠቀም መወሰናችሁና በጥቂቱም መስጠታችሁም በእጅጉ እንድትመሰገኑ ያደርጋችኋል።

ሦስተኛው እና ዋነኛው ሃሳብ “ልብ” ነው። ለሀገር ግንባታ ትልቅ ልብ ያስፈልጋል። ትልቅ ልብ የሌለው ሰው፣ ትልቅ ልብ የሌለው ማህበረሰብ፣ ሃገርን መገንባት፣ ራሱን መገንባት፣ ቤተሰብ መገንባት ይቸገራል። ትልቅ ልብ ሲባል በአጠረ መንገድ ለማስቀመጥ የማትጀምሩትን ነገር አትመኙ። የማትጨርሱትን ነገር ደግሞ አትጀምሩ። መመኘት ብቻውን ዋጋ የለውም። ከተመኘን በኋላ ለመጀመር አንድ ደረጃ መሄድ አለብን። ስለሆነም የማትጀምሩትንን አትመኙ። የማትጨርሱትንን ደሞ አትጀምሩ። ከጀመርራችሁ በኋላ እንደምትጨርሱ እርግጠኛ ካልሆናችሁ መጀመር ዋጋ የለውም። እንደምትጀምሩ ደግሞ ካላወቃችሁ ማለም ዋጋ የለውም። እናንተ ህልመኞች ናችሁ፤ ህልማችሁን ለመፍታት ጉዞ ጀምራችኋል። በዚሁ መንገድ እንደምትጨርሱ ያለኝን ሙሉ እምነት በዚሁ አጋጣሚ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።





ወጣቶች የሦስት **”ጉ”** መርሆዎችን መከተል አለባችሁ። የሦስቱ “ጉ” የሚባለው የመጀመሪያው የ“ጉ” መርህ “ጉጉት” ሲሆን፣ ሁለተኛው “ጉልበት”፣ ሦስተኛው ደግሞ “ጉብዝና” ነው።

“ጉጉት” ማለት ቅድም እንደገለጽኩት መመኘት፣ ለማደግ ለመለወጥ መሻት፣ ለማደግ ለመለወጥ አብዝቶ መፈለግ ነው። ጉልበት ደግሞ አሁን ባለንበት ሁኔታ ለሚያልፉ ወላጆች፣ ለታላላቅ ሰዎች፣ እረፍት መሆን ስንችል፤ ለሚያድጉ፣ ለታዳጊዎች ተስፋ መሆን ስንችል፤ ያ ጉልበትን አቅምን በትክክለኛው ቦታ መጠቀምን ያሳያል። አንድ ሃገርኛ አባባል አለ “ልጆች አያቶቻቸውን ሲጦሩ በረከት ነው” ይባላል። አያቶች ልጆቻቸውን ሲጦሩ መዓት እንደሆነም ይታሰባል። “ከመዓት ያድነን” እንደሚባለው ሁሉ፣ ወጣቶች የሚያሳርፉ የሚደግፉ እንጂ፣ ቁጭ ብለው ጡረታ ጠባቂ ከሆኑ የቤተሰብ ውድቀት፣ ከዚያም የሃገር ውድቀት ያስከትላል።

ሦስተኛው “ጉብዝና” ነው። ጉብዝና በብዙ መንገድ ሊተነተን ይችላል። ዋናው ለእናንተ የሚያስፈልጋችሁ ግን የእናንተ የጉብዝና ልክ የሚታይበት ዋናው መንገድ የማጥራት መንገድ ነው። በሃገራችን በገጠሩ ክፍል ውሃ ከጉድጓድ ይቀዳል። እንዳለ የሚጠጣ ከሆነ በሽታ አለው። ውሃን በሁለት መንገድ ማጥራት ይኖርባችኋል። አንደኛው ውሃውን በማፍላት በውስጡ ያሉ ጀርሞች መግደል እና ራስን ከጥቃት መከላከል ነው፤ ወይም በሰለጠነው መንገድ በተለያየ ኬሚካልና የማጥሪያ መንገድ ውሃን ማጥራት ነው። ውሃን ሳያጠራ ስለጠማው ብቻ የሚጠጣ ሰው ለጊዜው ከጥም እርካታ ቢያገኝም ውሎ ሲያድር በሽተኛ መሆኑ አይቀርም።

እናንተም እንዲሁ የምትሰሙትን የምታዩትን ማጥራት፣ ፊልተር ማድረግ ካልቻላችሁ ወደ ውስጣችሁ የሚገባ ውሸት፣ ወደ ውስጣችሁ የሚገባ የቅናት አነጋገር፣ ወደ ውስጣችሁ የሚገባ ጥላቻ፣ ወደ ውስጣችሁ የሚገባ አልባሌ ሃሳብ ሁሉ ወሎ አድሮ ውስጣችንን ይጎዳል። ያ እንዳይሆን ከምትሰሙትና ከምታዩት ነገር መጠበቅ ያለባችሁ “ፊልተር” በማድረግ ነው፤ በማጥራት ነው።

የሰማችሁት ሁሉ እውነት አይደለም። ኦሮሞዎች ወደ አማራ ሃገር ስትሄዱ በሃገራችሁ ሆናችሁ የሰማችሁት ነገር ሁሉ እውነት አይደለም። ወላይታዎች ወደ ሲዳማ ስትሄዱ፣ ሶማሌዎች ወደ አፋር ስትሄዱ፣ ትግራዮች ወደ ጉራጌ ስትሄዱ በየሄዳችሁበት የሚያስቀና ባህል፣ እጅግ ደግ የሆነ ህዝብ፣ እና የሚያምር መልከአ ምድር ታያላችሁ። ማጥራት ካልቻላችሁ ግን የሚነገረው ጥላቻ፣ የሚነገረው አሉባልታ እንኳን ልታገለግሉ፣ ልታዩም የሚያነቃቃ አይደለም። ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚነገሩ ብዙ የውሸት፣ የጥላቻ፣ የቅራኔ ሃሳቦች መጠበቅ እንድትችሉ ከጀርም ጋር ውሃ እንደማትጠጡት ሁሉ አልባሌ ሃሳብንም ወደ ውስጣችሁ ሳታስገቡ ማጥራት ይጠበቅባችኋል። ይህንን ካደረጋችሁ ውስጣችሁ ጤነኛ ይሆናል። ጤነኛ የሆነ ሰው ደግሞ መልካም ነገርን መስጠት ይችላል።

ሁለተኛው ከእናንተ ጋር እንዲቆይ የምፈልገው ሃሳብ የሶስቱን **“መ”** መርሆች ነው። የመጀመሪያው “መ” መርህ “ማረም” ነው። ሰው በጉዞው ይስታል፣ ያበላሻል፣ ያጠፋል። ጨርሶና በቅቶ የሚወጣ ሰው የለም። በሂደት ግን ማረምን፣ ማስተካከልን፣ ከጥፋት ራስን ማቀብን እየተማርን ከሄድን ወደ ሙሉነት እናድጋለን። ማረምን አትርሱ። በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ፣ በእያንዳንዱ ሂደት ውስጥ የሚታዩ ጥፋቶችን





ለማረም ዝግጁ ከሆናችሁ የበለጠ እያደጋችሁ፣ እየበሰላችሁ ትሄዳላችሁ።

ሁለተኛው “መ” ማስቀጠል ነው። እያንዳንዳችን አሁን ያለንበት ደረጃ የደረስነው በሌሎች ስራ፣ በሌሎች መሰረት ላይ ቆመን ነው። ትላንትናን ማራከስ ዛሬን ለመገንባት አያስችለንም። አይዛክ ኒውተን የተባለው ሰው ሲናገር “እርቄ ማየት ችዬ እንደሆነ ያለ ጥርጥር በሌሎች ሰዎች ትከሻ ላይ ቆሜ መሆኑን እወቁት” እንዳለው፤ አድገን፣ ተለውጠን፣ በልጽገን ከሆነ በአባቶቻችን ደምና ላብ፣ በነጻነት በቆመች ሃገር ላይ በመሆናችን እንደሆነ እንዳትረሱ።

ሦስተኛው “ማበልጸግ” ነው። ማላቅ፣ አሁን ያላችሁን የተቀበላችሁትን ነገር፣ የምታዩትን እንዳለ መቀበል ሳይሆን ማሻሻል። ለምሳሌ እዚህ እንዳለንበት ቦታ ማለት ነው። ይህን ቦታ እኛ አልሰራነውም። ይህ ቦታ ነበረ። ይህ ቦታ አሁን የያዘውን ቅርጽና ውበት ግን ለማላቅ፣ ለማሻሻል፣ ለማስበለጥ ፈቃድ ፍላጎት ስለነበረን ነው።

በዚያም ምክንያት ቀደም ሲል የነበሩ ሰዎች ያቆዩትን ቦታ እኛ አሻሽለን አሳምረን እንደዚህ ማቆየት ከቻልን ኢትዮጵያንም በነጻነት ያቆዩ አባቶች ስራዎች ሳይዘነጉ ይበልጥ ለማሳመር፣ ለማስዋብ፣ ለማሻሻል ከወሰናችሁ ማላቅ፣ ማሻሻል ይቻላል። ሦስቱን “መ” ማለትም፡- ማረም፣ ማስቀጠል እና ማላቅ ወይም ማበልጸግን በልቦናችሁ እንድታቆዩ አደራ ልላችሁ እፈልጋለው።

በመጨረሻም ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት ሁኔታ ከግራ፣ ከቀኝ፣ ከፊት፣ ከኋላ መገመት በሚያዳግት ሁኔታ ትልቁም ትንሹም በከፍተኛ ደረጃ ተረባርቦ የተነሳባት ጊዜ ላይ እንገኛለን። የዚህ የውሸት ፕሮፖጋንዳና

ጥላቻ ንግግር ዋና አላማ የዛሬ መቶ ምናምን ዓመት አልገዛም ብላ ለሌሎች አፍሪካ ሀገሮች ምሳሌ የሆነችው ሃገር አሁን ደግሞ “ድህነት አያስፈልገኝም ብልጽግናን እሻለሁ፤ መለመን አልፈልግም፤ መስጠትን እመኛለሁ እያለች ነውና ይቺን ሃገር ካላቆምናት፣ እዚህ ካልቀጨናት በስተቀር አሁንም ለጥቁር ህዝቦች አርአያ ትሆናለች” የሚል ስጋት በሰፊው ይናፈሳል።

ዛሬ ላረጋግጥላችሁ የምፈልገው ትልቅ ቢጮህ፣ ትንሽ ቢጮህ፣ ብዙ ውሸት ቢነገር፣ ብዙ ውሸት ቢነዛ፣ ትናንት አባቶቻችን ነጻነቷን የጠበቁትና ለጥቁር ህዝቦች ሁላ አርአያ ያደረጓት ሃገር በልጆቿ ጥረትና ትብብር በነጻ በሚሰጡ ጀግኖች ወጣቶች ታግዛ የብልጽግና ምሳሌ ትሆናለች። ለጥቁር ህዝቦች ሁሉ አርአያ ሆና ከልመና የምታወጣ ሃገር ለመሆን ምንም ምድራዊ ሃይል ሊያስቀራት የማይችል መሆኑን ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ።

የዓለም ሚዲያ በአንድ ድምጽ ቢጮህ እኛ ኢትዮጵያዊያን እይታችንን ከኢትዮጵያ ብልጽግና ላይ አናነሳም። ጆሮአችሁን፣ ልባችሁን፣ አእምሮአችሁን ጠብቃችሁ ኢትዮጵያን ማላቅ፣ ኢትዮጵያን ማበልጸግ፣ ኢትዮጵያን መውደድ እና ለኢትዮጵያ በክብር መስዋእት መሆን የኩራት ሁሉ ምንጭ እንደሆነ አውቃችሁ እንድታገለግሉ፣ እንድትጠብቋት፣ እንድታሻግሯት፣ ለሚመጡ ወጣቶች ተስፋ እንድትሆኑ፣ ላረጁት ደግሞ እረፍት እንድትሆኑ በድጋሚ አደራ ለማለት እፈልጋለሁ።

ዛሬ የሃገር መከላከያ ሰራዊት፣ የፌደራል ፖሊስ ብዙ ወጣቶች እንዲቀላቀሉት ይፈልጋል። ከቅርብና ከሩቅ ብዙ ኢትዮጵያን ለማጥፋት የሚፈልጉ ሃይሎች ስላሰፈሰፉ እራሱን ማጠናከር ይፈልጋል። ብዙዎች





ወጣቶች ግን ወደ መከላከያ ሄደው በፈቃድ ለማገልገል ዝግጁ ከመሆን ይልቅ በፌስቡክ ይዋጋሉ ያዋጋሉ። በፌስቡክ ነጻነታችንን መጠበቅ አንችልም። ዋጋ ከፍለን ራሳችንን ካልሰጠን በስተቀረ በያላችሁበት በምትናገሩበትና በምትጽፉበት፣ የኢትዮጵያን ህልውና ማስጠበቅ ስለማይቻል በጎ ፍቃድ፣ በበጎ በነጻ ማገልገል ጠቃሚ እንደሆነው ሁሉ፣ በመከላከያ በፖሊስ ሰራዊት ውስጥ ተሳትፈን ሃገራችንን መጠበቅና ህልውናዋን የሚገዳደሩ ሃይሎች የማይችሉ መሆኑን ማሳየት ይገባል። ይኽ ከመቶ አስር ሚሊየን ኢትዮጵያዊ የሚጠበቅ ኃፊነት መሆኑን እያሳሰብኩ፣ ውትድርና የስትራቴጂ፣ የታክቲክ፣ የሊደርሺፕ መገኛ መግለጽ እሻለሁ።

አድዋን ስናነሳ፣ ካራማራን ስናነሳ፣ ሌሎች ቦታዎችን ስናነሳ የምናወሳቸው ጀግኖች፣ መሪዎችን የፈጠረ በመሆኑ የምናፍርበት ሳይሆን ወደን፣ ፈቅደን የምንገባበት በመሆኑ፣ መከላከያችንን በማጠናከር፣ የፖሊስ ሰራዊት በማጠናከር እጅ ለእጅ በመያያዝ ለኢትዮጵያ ኩራት፣ ለጠላቶቿ ደግሞ የምታስፈሩ ሃይሎች እንድትሆኑ በዚሁ አጋጣሚ አሳስባለሁ።

እንኳን ደስ አላችሁ!!

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ደም እና ላብ፣**
**በልጆቿ አንድነት እና ጥረት ታፍራ**
**እና ተከብራ ለዘለዓለም ትኑር!**
**አመሰግናለሁ!**

# የጎጃም ስንዴ ማሳ ጉብኝት ላይ የተደረገ ንግግር

**የካቲት 28፣ 2013 ዓ.ም**

ዛሬ የምንገኘው በምእራብ ጎጃም በሜጫ ወረዳ ይኼ የቆጋ መስኖ የሚባለው ነው። ቆጋ መስኖ በዚህ ዞን ውስጥ እንደ ማሳያ የተወሰደ፣ በዚህ ከኋላዬ የበጋ ስንዴን በመስኖ የምናመርትበት፣ በዚህ ጋር ደግሞ አቦካዶ ለኤክስፖርት በሚመች መልኩ ከእስራኤል በመጣ ዝርያ ከተዘራበት፣ ብዙ አርሶ አደሮች በጋራ ሆነው የሚሰሩበት ቦታ ነው። ለኢትዮጵያ የግብርና ምርት እድገትና ለውጥ እንደ ጥሩ ማሳያ ይወሰዳል።

ያው እንደምታውቁት የበጋ ስንዴ በመስኖ የማልማት ልምድ ኢትዮጵያ ውስጥ አልነበረም። አሁን ነው የጀመርነው። ዘንድሮ በሀገር ደረጃ ያለው አጠቃላይ ምርት ከሁለት መቶ ሺህ ሄክታር በላይ ነው። ነገር ግን በየክልሉ ያለውን ጅማሮ እና እጥረቶች አውቀን ማስፋት ከቻልን ዋና አላማችን ስንዴን ከውጭ ለምግብ አገልግሎት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይገባ ማድረግ ነው። በምግብ ራሳችንን መቻል ነው።





አቦካዶን በሚመለከት ከፍተኛ ገበያ አለው። እኛ ጋር አቡካዶ በሚመረትበት ወቅት ሌላው ጋር ከሚመረትበት ወቅት ጋር ይለያያል። ያው እኛ ጋር እንደምታውቁት በጋ ሲሆን እነሱ ጋር ያለው አየር ንብረት ክረምት ይሆናል። ስለዚህ ወደ አውሮፓም ወደ መካከለኛው ምስራቅም ለመላክ ሰፊ እድል አለ።

አቦካዶ ማምረት እንችላለን። እንዳያችሁት የሚገርም ፍሬ ነው ያለው። እዚህ ያለው አቦካዶ ከምናውቀው የአቦካዶ ዝርያ የተለየ ነው። ረዘም ላለ ጊዜ ለሦስት ወር ገደማ ፍሪጅ ውስጥ መቆየት ይችላል። ተቆርጦ እስኪሸጥ ሁለት ሦስት ሳምንት መቆየት ይችላል። ገበያ ከሌለ ረዘም ላለ ጊዜ ዛፍ ላይ መቆየት ይችላል። አንዴ ካመረትነው የሚበላሽ አይደለም። ይኼን እያስፋፋን ሄደን አካባቢው ላይ "አግሮ ኢንደስትሪ" ማምጣት ከቻልን "ፕሮሰስ" እያደረግን ደግሞ ለሃገር ውስጥም ለውጪ ገበያም ማቅረብ እንችላለን።

ዋናው ነገር ኢትዮጵያ ይኼን የመሰለ መልክአ ምድር ይዛ፣ ውሃ ይዛ፣ መንግስት እና ህዝብ በተለይም አርሶ አደሩ በትክክል የግብርናን ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ጉዳይ ከሃገር ህልውና ጉዳይ ጋር የተያያዘ መሆኑን ኣውቆ፣ ሰርተን ራሳችንን መመገብ ካልቻልን ስንዴ እየለመንን ነጻነት የሚባል ነገር የለም። ስንዴ እየለመንን የሀገር ክብር የሚባል ነገር የለም። ስንዴን ከመለመን ነጻ መውጣት የሚያስችል ብቁ የሆነ መልከአ ምድር አለን። በጣም ሰፊ መስራት የሚችል ወጣት ዜጎች ያሉት ሀገር ነው። በእርግጥ ቴክኖሎጂ ያስፈልጋል፤ ትራክተር መስፋት አለበት፤ ፓምፖች ያስፈልጋሉ፤ የመስኖ ተደራሽነት ማስፋት ያስፈልጋል።

ከዚህ አንጻር መንግስት አቅም በፈቀደ መጠን ይሰራል። ይኼ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁሉም ዜጋ ማወቅ ያለበት ኢትዮጵያ ለምግብ የሚያስፈልጋትን ነገር መቶ በመቶ ራሷን መቻል አለባት። እየበላን ስለክብር እናወራለን፤ እየበላን ስለነጻነት እናወራለን፤ እዚህ ጋር ነጻነት ካልን መብላት የማንችል ከሆነ ግን ማስማማታችን አይቀርም።

አሁን የጀመርነው አካሄድ ምንድነው? የአቦካዶ በመስኖ መሆኑ ብቻ አይደለም። በአንድ የአቦካዶ ዛፍና በሌላኛው ዛፍ መካከል ሦስት ሜትር አካባቢ ስፋት አለ። እዚህ መሃል ሽንኩርት ማምረት ይቻላል፤ ጎመን ማምረት ይቻላል፤ ቃርያ ማምረት ይቻላል። ልዩ ልዩ ሰብሎች ማምረት ይቻላል። ይኼ ደግሞ እየበላን አቦካዶ እስከሚደርስ ባለው ጊዜ ውስጥ የምግብ እጥረት እንዳይኖር ሊያግዝ ይችላል። እዚህ ጋር አቮካዶ አለ። ሌሎች ነገሮች በመሃል ሊመረቱ ይቻላሉ።

ይኼን እያስፋፋን ከሄድን ኢትዮጵያ ራሷን በምግብ ችላ ለሌሎችም ኤክስፖርት የማድረግ አቅሟ ያድጋል። ክብራችንም፣ ነጻነታችንም እራስ ከመቻል ጋር ስለሚያያዝ አርሶ አደሩን ቀረብ ብለን እያገዝን ይኼንን ነገር ውጤታማ ማድረግ በጣም ያስፈልጋል።

በተለይ አሁን በደጋው በአንዳንድ አካባቢ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ ይኼ ነገር ተጀምሯል። በሚቀጥለው ዓመት ጅማሮው የሚታየውም በሶማሌ እና በአፋር ላይ ባለው ቆላማ የአየር ንብረት ላይ በከፍተኛ ደረጃ በተቋም ደረጃም አጠናክረህ ካስፋፋነው አቦካዶ በእኛ እምነትና እቅድ በሁለት ሦስት ዓመት ውስጥ የቡናን ኤክስፖርት ይተካል። ምርቱ፣ ተፈላጊነቱ ሰፊ ነው። ምርቱ ለእኛ ሃገር ምቹ ነው። ያን በማስፋት የቡናን ኤክስፖርት መተካት ይቻላል፤ ቢያንስ ይገዳደረዋል። አቦካዶ ኤክስፖርት ካደረግን፣ ቡና ኤክስፖርት





**Excellencies,**
**Ladies and Gentlemen,**

Finally, as we embrace disruptions and volatility as the new normal, we must build resilient institutions capable of implementing reforms to help us withstand the challenges of the future. However, unlike investments in the digital economy and in a climate resilient infrastructure, institution building is a pain staking, long and less tangible process. It requires reforms, consensus building, monitoring and course correction. It is the best anchor we can build as we prepare collectively for the next crisis.

We need continental institutions, regional institutions and national institutions to all stand together.

The African Union, the UNECA, the Africa CDC, the African Finance Ministers, are all part of this institutional fabric and have demonstrated the power of collective ambition and action. We must build on that to prepare for tomorrow's challenges and also tomorrow's promise of a brighter Africa.

With these insights, I would like to officially declare the conference open. I wish you all fruitful deliberations.

**Thank you for your attention!**





# Djibouti Speech

**Reconcilation of the Somalia and Somaliland**

**February 23, 2020 G.C**

**Your Excellency Ismail Omer Guelleh**
**Your Excellency Mohamed Abdullahi Mohamed**
**Your Excellency Muse Bihi Abdi**
**Distinguished Guests, ladies & gentlemen**

As-salamu alaykum, Malin Wanagsan

I am immensely delighted to be in this serene city of Djibouti to once again enjoy the generous hospitality of my elder brother and friend President Ismail Omer Guelleh. I am equally pleased to be with my dear brothers and neighbors, President Mohamed Abdullahi Farmajo and President Muse Bihi.

Today, this important gathering of the leaders of the Horn of Africa, gives me a good opportunity to reflect on the significance of peace, genuine reconciliation, mutually beneficial cooperation and security.

In fact, this is a family gathering more than anything else! I always say our countries are joined by one umbilical cord – we are blood brothers and we must be proud of that!

## Dearest brothers,

The Horn of Africa has experienced prolonged periods of bad governance and failed leadership. We are too familiar with the destruction, displacement and the decades of economic backwardness generated by senseless conflicts. We need to change course and start a new era. We need to cultivate hope and build a better future for our people.

As an integral part of the Cushitic family, the Somali people constitute one of the largest and most resilient people in the Horn of Africa. Somalis are largely energetic, dynamic, independent-minded, entrepreneurial and friendly.

After decades of conflict and despair, Somalis are yearning for a charismatic, visionary and unifying leadership that can galvanize their spirit, strength and resources and rally them to a future of prosperity and peace.





With a commitment to putting differences aside for mutual growth, that leadership is you!

As family and neighbors whose people have been pitted against each other for decades; whose people have been deprived of a stable environment for social and economic development and peaceful coexistence; whose people have been forced to endure in a state of perpetual poverty; we must understand that huge benefits are to be gained from investing in peace, reconciliation and integration.

My brothers, Mohamed and Muse, you have two choices to make today: to embrace the spirit of forgiveness, reconciliation and genuine healing and unleash the power of your people or perpetuate the suffering of your people and deprivation of opportunities for current and future generations.

The choices you make will also have profound impact on our region and set an example to other regions of Africa. A reconciled, peaceful and prosperous Somalia has the potential to become a formidable economic powerhouse.

Somalia is endowed with abundant natural resources; the longest coastline in Africa; rich marine resources; fertile productive agricultural lands; ample livestock assets and

untapped mineral deposits such as uranium, petroleum and gas.

Therefore, to fully harness the abundant human and natural resources, a reconciled, democratic, stable and peaceful Somali state is critical.

At the dawn of 21st century, the Horn of Africa cannot remain trapped in internal conflicts, ethnic divides, violence and poverty. The countries of the Horn of Africa combined possess immense natural and human resources, economic potentials and year-round favorable climate, which if positively exploited could enhance our geopolitical position. Together we can pool our resources to break the vicious cycle of poverty and despair and uplift the lives of our peoples.

This is why I believe your unity is the engine of our regional integration.

**Dear brothers Mohamed and Muse,**

This is your moment! Nations are transformed by visionary and courageous leaders. As leaders of this great nation, you have the power to shape the destiny of your people, the power to translate into achievable goals the big dreams and hopes of your fellow compatriots.





Your strength lies in your unity. Together you can rise as a nation and overcome monumental challenges. I urge you to seize the moment and look forward to a future of peace and prosperity for the Somali nation.

Both brother Ismail and I are genuinely interested to work hand in hand with our brothers and neighbors to finally settle their differences through genuine reconciliation, forgiveness and accommodation. This is what the traditional norms and regulations of heer demands from you. There is no any other way!

A reconciled, peaceful and prosperous Somalia that is at peace with itself and with its neighbors is in the interest of Ethiopia, Djibouti and the entire Horn of Africa region.

Guided by the virtues of the MEDEMER philosophy and in the spirit of good neighborliness, mutual cooperation, open borders, integrated economies, peaceful coexistence, we can certainly rise together to prosperity!

**I thank you once again for joining us here in Djibouti!**

# FT Meeting

**October 12, 2020 G.C**

**Ladies and Gentlemen,**
**Friends,**

It is a real pleasure to participate in the FT Africa Summit. I am grateful for the opportunity to share my thoughts with you.

The theme of the Conference "Getting Africa back to Business" following the Covid-19 pandemic is clearly a timely as well as most pressing theme.

There is now consensus that the health impact of the pandemic on Africa is not as severe as it was initially predicted. About 80% of people with the virus are asymptomatic in most African countries, including Ethiopia. And the fatality rate is below 1.6 per cent.





While the fatality rate from COVID19 remains fortunately low in Africa due to a combination of factors – including smart policies and structural factors such as demography and settlement patterns - the impact of the pandemic on the economy of the continent however, has been massive.

It has also become clear that COVID19 is unlikely to disappear anytime soon. This means we need to start opening up our economies with the knowledge that we are going to live with the disease for a while.

Yet we should not let our guards down but remain even more vigilant than before. We need to strengthen our infrastructure for managing and containing the consequences of the pandemic.

As we settle into this "new normal" of a post-pandemic world, we need to take stock, and reflect on its implications for our systems of governance, society, and the economy.

What will it take for Africa to build a more resilient society post-pandemic?

How can we build forward better and smarter?

How can we mobilize our collective resources — public and private, formal and informal, national, regional and

continental — to tackle our shared challenges and build a more sustainable Africa?

In my remarks today, I  focus on three major and interrelated considerations that I believe will help us in this exercise.

- **First: We need to rethink how our system of governance works.**

These are extraordinary times. Wherever we look, we face adaptive, complex and challenging realities in every domain — and not limited to COVID19. They include obvious global issues such as climate change, extreme poverty, widening income inequality, rising populism and nationalism, diminishing multilateralism, natural disasters such as the largest locust outbreak in decades in Africa, to name only a few.

And these and more adaptive challenges are highly interlinked precisely because our lives are interconnected and interdependent to an unprecedented degree.

They are complex because they have multiple and interrelated causes. Complex problems, by definition, do not have simple technical solutions, nor can they be solved





by a single actor or country. They require adaptive solutions.

To succeed, I believe we need a renewed approach to our systems of governance that is rooted in the politics of principled pragmatism.

The politics of principled pragmatism recognizes that complex challenges have no easy solutions. Making progress requires learning, innovation, trade-offs, and hard choices. It also demands of each of us to examine our deeply held assumptions and to change long-standing habits.

Put simply, it requires collective efforts—as we say in Ethiopia—Medemer-- based on deep and principled cooperation.

The politics of principled pragmatism conserves and builds on what works while discarding what is outmoded. In this way it creates the conditions for a resilient system for a sustainable future. It is about rolling-up-our sleeves, and providing realistic, and competent leadership with our eyes set on making steady progress.

A good part of the credit for Africa's relatively effective response to COVID19 lies in the recognition that the

solutions to collective challenges must come from many places, with everyone working together.

For example, in Ethiopia, our collaboration with the Jack Ma Foundation to distribute medical supplies to every African country soon after the outbreak of the pandemic through our national carrier Ethiopian Airlines, was motivated by the recognition that the pandemic was a collective challenge that called for shared responsibility. To survive, we had to work together, not against one another. And that is what we did.

Together with other African leaders, we collectively championed the cause for debt relief, for increased financing of the World Health Organization, and coordination in the search for vaccines and treatments. We are determined to continue on this course until the virus is defeated.

**Second, we need to build our capacity for resilience by investing in our productive capacity.**

As painful and costly as COVID19 is, it has only strengthened our resolve and taught us to plan smarter for an increasingly complex world.

I would highlight this by giving a few examples, drawing from Ethiopia.





This year, we redoubled our efforts for the Green Legacy Initiative, comfortably meeting our target to plant 5 billion tree seedlings.

Despite the COVID pandemic, we were able to mobilize millions of our citizens—young and old, in cities and villages across the country – in the call for climate-resilient reforestation, with the long-term goal of enhancing biodiversity, reversing land degradation, and developing nature-based solutions for prosperity.

We did that while fully observing appropriate protocols in terms of social distancing and other public health measures to ensure that we are still fully protected from COVID.

In these times of climate change and associated environmental disasters, initiatives such as our Green Legacy are an existential imperative. A green recovery can also be a job-rich recovery.

We are also investing in renewable energy. Our flagship project — the Grand Ethiopian Renaissance Dam — is making steady progress and we have achieved initial filling of the reservoir. When completed, it will be a source of sustainable energy for tens of millions both in Ethiopia and the sub-region.

In short, we are playing a vanguard role in accelerating a Green Recovery while contributing our share to the global fight against climate change.

- **The third important lesson is the need to invest in our overstrained healthcare system and to extend healthcare to the most vulnerable people who live in extreme poverty.**

In many African countries, healthcare is a neglected sector. This pandemic has exposed our dark underbelly in this regard and made clear the need for additional investments in personnel, equipment, and facilities.

For example, in Ethiopia, in a typical year what we spend servicing our external debt is twice the size of our annual health budget.

Following the COVID19 pandemic, healthcare has been our single most important priority this year. Compared to last year, our spending in healthcare in 2020 has gone up by 46%, making it the fourth largest sector in terms of budget spending.

**Ladies and Gentlemen,**





Before I conclude, let me say a few words about the investment opportunities here in Ethiopia. We are committed to bring our country firmly into the international marketplace of ideas, capital, technology and talent.

It is a new age of openness for Ethiopia. Our efforts to cut burdensome regulations and improve our investment climate are bearing fruit. We recently revised our investment laws to open our markets to investors in telecommunications, logistics, energy, and other industries. We have passed the arbitration law to facilitate dispute resolution.

I am pleased to report that, in the telecommunications sector, we have succeeded to elicit interest from some of the most recognizable global operators, which will help us deploy a modern, accessible, affordable connectivity and digital services to Ethiopians throughout the country.

Rest assured we intend to deliver a transparent licensing process based on objective rules and criteria before the end of the calendar year.

We are also building our productive capacity and diversifying the sources of growth. In the course of the past two years, and against all the odds, we conceived, planned, executed, and launched a number of projects—including

museums, parks, and public squares — that have transformed the face of our capital city — Addis Ababa – and will no doubt make Ethiopia an attractive tourist destination in the years to come.

We envision an integrated tourism package--one that presents natural wonders, our rich agricultural practices and our diverse cultures. My government is happy to have launched new projects in Gorgora, Koysha, and Wenchi—sites where Ethiopia's vast natural endowments intersect.

Come invest in Ethiopia, help us make these riches accessible, hospitable so that rest of humanity can come and have a world-class experience in Ethiopia.

We are now open to welcome our visitors once again with our traditional Ethiopian hospitality.

Let me conclude.

We live in extraordinary times. Our challenges are enormous. But we will not relent. We will not retreat. We will not rest.

Together, we will emerge from this crisis stronger and more resilient than before.

I invite you to visit Africa; to invest in Ethiopia; to invest in Africa.





**Thank you very much!**

# AU Video Conference



# ክፍል አራት

## የአማርኛ መልዕክቶችና መግለጫዎች

# የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመግታት የተወሰዱ እርምጃዎች

**መጋቢት 18፣ 2012 ዓ.ም.**

ላለፉት ሁለት ቀናት በዋናው “ሚኒስትሪያል” ኮሚቴ ስር የተደራጁ ንዑስ ኮሚቴዎች በልዩ ልዩ ሥራዎች ተጠምደው አሳልፈዋል። የሜዲካል እቃዎችን የሚያሰባስቡ፣ የጊዜያዊ ማቆያ ቦታዎችን የሚያዘጋጁ፣ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ሀብት የሚያሰባስቡ፣ እንዲሁም ኢኮኖሚያችን በከፋ ሁኔታ እንዳይመታ በዋና ዋና ኢኮኖሚ ሴክተሮች ዙሪያ እየተወያዩ ግብአት የሚወስዱ እና የመፍትሄ አቅጣጫ የሚያዘጋጁ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ተቋቁመው ስራቸውን ሲሰሩ ቆይተዋል። የሁሉንም ኮሚቴዎች ስራ ላለፉት ሁለት ቀናት በዝርዝር ስናይ እና ተጨማሪ አቅጣጫ ስናስቀምጥ ቆይተን አሁን የሚኒስትሪያል ስትሪንግ ኮሚቴው አጠቃላይ ያለውን እድገት ግምገማ አካሄዶ ተጨማሪ አቅጣጫዎች አስቀምጧል።

እስከ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በሞት አደጋ የገጠመን ባይሆንም፤ አስራ ስድስት ሰዎች በበሽታው መጠቃታቸው በምርመራ ተረጋግጧል። ይህ





ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እንዳያሻቅብ እና ወደ ሞት አደጋም እንዳይወስድ ከፍተኛ ርብርብ እና ጥንቃቄ የሚያስፈልገው መሆኑን በዝርዝር ለማየት ተሞክሯል። መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሚገነዘበው የኮሮና ቫይረስ ወይም ኮቪድ 19 የሚባለው ይህ ወረርሽኝ ድንበር የማያቆመው፣ ሀብታም ደሃ የማይል፣ ትልቅ ትንሽ የማይል፣ ሁሉን የሚያጠቃ፣ ሰዎች በበቂ ከተዘጋጁና ከተባበሩ ሊከላከሉ የሚችሉት፣ በተቃራኒው ያልተዘጋጀና የተዘናጋ ደግሞ በርካታ ዜጎቹን የሚያሳጣ አደገኛ ወረርሽኝ ነው። መላው የዓለም ህዝቦችና ኃያላን ሀገራት ጭምር እየተናጡበት ያለ ችግር መሆኑን ሁላችሁም ትገነዘባላችሁ።

በእንደዚህ አይነት ወሳኝ እና ፈታኝ ጊዜ ከህዝባችን የሚጠበቀው ትብብር፣ መደጋገፍ፣ በጋራ ሆኖ የዜጎች ህይወት እንዳይቀጠፍ የሚቻለንን ሁሉ ማድረግ ይሆናል። ከዚህ አንፃር በሽታው በመንግስት ብቻ መቋቋም የሚቻል ቢሆን ኖሮ ለህዝባችን ተጨማሪ ድጋፍ ባልጠየቅን ነበር። በህዝባችን ትብብርና ድጋፍ ብቻ የሚቆም ቢሆን የተቀረውን ዓለም የእርዳታ እጁን እንዲዘረጋ እና ከጎናችን እንዲቆም ማስቸገር ባላስፈለገ ነበር። ነገር ግን በሽታው የመላው ዓለም ትብብር የተቀናጀ አመራር መስጠት የሚጠይቅ በመሆኑ በሀገር ደረጃ ጉዳዩን የሚመራ ስትሪንግ ኮሚቴ ያቋቋምን ሲሆን፣ በአካባቢ ሀገራት ደረጃም የጋራ የመሪዎች ኮሚቴ ጉዳዩን መረጃ እየተለዋወጠ የሚመራበት መንገድ ተፈጥሯል።

በአህጉር ደረጃም ጥቂት አመራሮች፣ ጥቂት የሀገር መሪዎች ያሉበት ኮሚቴ ተቀናጅቶ በጋራ ሆኖ አፍሪካን የሚከላከልበትና ለአፍሪካ ተጨማሪ ሀብት የሚያመጣበት ስራ እየሰራ ሲሆን ኢትዮጵያ በሁሉም ኮሚቴ ውስጥ ትሳተፋለች። በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥቂት ታዋቂ ግለሰቦች፣ የዓለም ሃያላን መንግስታት እና ዓለም አቀፍ ተቋማት

ድጋፍ ማድረግ እንዲችሉ የተቋቋመ "ቨርቹዋል" ኮሚቴ አለ። እዚያም ውስጥ ኢትዮጵያ ትሳተፋለች። በሁሉም መስክ እየተደረገ ያለው ጥረት በዓለም አቀፍ ደረጃ ችግሩን መቀነስ መግታት የሚቻልበት ነው። በአህጉር ደረጃም ችግሩ የከፋና የብዙ ሰዎች ህይወት የሚቀጥፍ እንዳይሆን ለመከላከል የሚቻልበትን መንገድ እየተፈለገ ነው። በአካባቢ ሀገራት እና በኢትዮጵያም ይህንኑ ለማድረግ የተጠናከረ የጋራ አመራር ለመስጠት የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎች በየቀኑ እየተሰሩ ይገኛሉ።

እየተገኘ ያለው ውጤት አበረታች ቢሆንም ተጨማሪ ጥረት፣ ተጨማሪ ስራ፣ ተጨማሪ ትጋት የሚጠይቅ እና ሙሉ በሙሉ በሽታውን መቆጣጠር መከላከል የሚቻልበት ደረጃ የትኛውም ሀገር ያልደረሰ መሆኑን ማወቅ ይቻላል።

በኢትዮጵያ የጀመርነው ትብብር ተጠናክሮ ይቀጥላል። አሁን ላቋቋምነው የምግብ ባንክ ጤፍ ያለው ጤፍ፣ ከብት ያለው ከብት፣ ማር ያለው ማር፣ ያለውን ሀብት በማዋጣት ከፍተኛ ድጋፍ ማድረግ ተጀምሯል። በጉልበታቸው በርካታ ዜጎች የበጎ ፈቃድ ስራ እየሰሩ ይገኛሉ። በእውቀታቸውም ተጨማሪ ሀሳብ በማፍለቅ ሀገርን ለማገዝ የሚጥሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን እንዳሉ ማየት ተችሏል።

ይህ ትብብር፣ ይህ መደጋገፍ እና የጋራ ጠላትን በጋራ የማስቆም ስራ በሁላችንም ዘንድ ተጠናክሮ እንዲቀጥል መንግስት ጥሪ ያቀርባል። ከኢትዮጵያ አየር መንገድ አንፃር ሰላሳ ያህል መዳረሻዎችን ባለፈው አቁመን የነበረ ቢሆንም፤ ዛሬ ላይ ያቆምናቸው መዳረሻዎች ወደ 72 (ሰባ ሁለት) ይጠጋሉ። በሚቀጥለው ሳምንት እድገቱን እያየን ተጨማሪ ቦታዎች አስገዳጅ ሁኔታ ካለ ለማቆም እንገደዳለን።





አሁን ባለው ሁኔታ በቀን በአማካይ ከሃምሳ ሰው ያልበለጠ ወደ ኢትዮጵያ ይገባል። ለዚህም አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ፣ ይኼ ቁጥር እጅግ አስፈላጊ ተጓዦች (Essential Travelers) የሚባሉትንም የሚያካትት ይሆናል። ከእነዚህ ተጓዦች ውስጥ አቅም ያላቸውና መክፈል የሚችሉት በተዘጋጀላቸው ሆቴሎች በራሳቸው ወጪ ለሁለት ሳምንት በማቆያ ክትትል እየተደረገላቸው ይቆያሉ። ከእነዚህ በተጨማሪ ከአንዳንድ ሀገራት በእስር ላይ የነበሩ፣ "ህገወጥ ስደተኛ" በሚል በርካታ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገር ውስጥ እየተመለሱ ይገኛሉ።

እነዚህ ኢትዮጵያውያን በራሳቸው ወጪ በተዘጋጀላቸው ማቆያ ስፍራ መቆየት የማይችሉ በመሆናቸው አዲስ አበባ ላይ ባዘጋጀናቸው የማቆያ ቦታዎች ለማቆየት ሙከራ ተደርጓል። አንዳንድ ሊሟሉ የሚገቡ ነገሮች በበቂ ደረጃ ያልተሟሉ መሆናቸውን አረጋግጠን፤ በአዲስ አበባ ያሉ ከውጭ በተለያየ ምክንያት የመጡና ወጪያቸውን መሸፈን የማይችሉ ሰዎች ከዛሬ ከሰአት ጀምሮ "ASTU" ወደሚባለው ዩኒቨርሲቲ እንዲዘዋወሩ እና እዚያ የህክምና፣ የምግብ፣ የመኝታ እና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች አቅም በፈቀደ መጠን እንዲሟላላቸው ተወስኗል።

ከውጪ የምትገቡ ወገኖቻችን እንድትገነዘቡ የምፈልገው የመጣችሁት ወደ ኢትዮጵያ ነው። ኢትዮጵያ ደሀም ብትሆን፣ አቅሟ ውስን ቢሆን ዜጎቿን ለመቀበል ለመንከባከብ በምታደርገው ጥረት ውስጥ እንደነበራችሁበት ሀገር የተሟላ ነገር እንዳትጠብቁ። መንግስት አቅሙ በፈቀደ መጠን በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን አስተኝቶ፣ አብልቶና ህክምና ሰጥቶ ለማቆየት ከፍተኛ ወጪ ስለሚጠይቀው፣ ይኼን ተገንዝባችሁ በኛ በኩል አቅም የፈቀደውን ሁሉ የሚደረግላችሁ መሆኑን እየገለጽኩ፤ በእናንተ በኩል ግን ከአቅም በላይ የሆኑ ነገሮችን መጠበቅ እንዳይኖር ጥንቃቄ ቢደረግ መልካም ይሆናል።

በርካታ ሰዎች እየገቡ ስለሆነ ለዚህ ሁሉ ሰው ሆቴል ይዘን ማኖር የሚያስችል አቅም የለንም። ነገር ግን ዩንቨርሲቲዎች፣ "ሀይስኩሎች"፣ የወጣት ማዕከሎች እና ከግለሰቦች የምናገኛቸውን ቦታዎች፣ እንዲሁም አዲስ አበባ ላይ ሁለት የማምለኪያ ቦታዎች በገዛ ፈቃዳቸው ማምለኪያ ቦታቸውን ለዚህ ጉዳይ እንድናውል ስለፈቀዱልን፣ በእንደነዚህ ቦታዎች እናንተን የምናቆይ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገባ።

ከትምህርት ቤት ጋር ተያይዞ ባለፉት ሁለት ሳምንታት "ሀይስኩል" ዘግተን የቆየን ሲሆን፤ ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ ባሉበት ግቢ፣ ባሉበት "ካምፓስ" ቆይተው በርቀት እንዲማሩ ጥረት ሲደረግ ነበረ። ቢሆንም ያ ሙሉ በሙሉ በተለያየ ምክንያት ያልተሳካ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ወደየቤታቸው እየሄዱ ነው ያሉት። ለዚያ በጣም በርካታ ምክንያቶች አሉ፤ ነገር ግን አሁን ያን መዘርዘር አያስፈልገኝም።

ለሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት ተጨማሪ ሁሉም ትምህርት ቤቶች ዝግ ሆነው እንዲቆዩ ተወስኗል። ባለፈው ካደረግነው የሁለት ሳምንት ቆይታ ተጨማሪ ለሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታትም ትምህርት ቤቶች የተዘጉ ይሆናሉ ማለት ነው።

የማህበራዊ ርቀት ወይም "ሶሻል ዲስታንሲንግ" በምንለው ዘዴ ለውጦች የመጡና ብዙ ነገሮችን ያሻሻሉ ቢሆንም፤ አሁንም የተሟላ ሆኖ አላገኘነውም። የሀይማኖት ተቋማት፣ መገበያያ ስፍራዎች፣ እንዲሁም አልፎ አልፎ አንዳንድ ቦታ ላይ በርከት ያሉ ሰዎች ለወረርሽኙ ምንም አይነት ግንዛቤ ያልፈጠሩ በሚመስል መንገድ ተሰባስበው የሚታይበት ሁኔታ አለ። ይሄ በሽታ እስከ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ምንም ሰው ያልገደለ ቢሆንም ወደ ከፋ ችግር የገባን እንደሆነ





እንኳን እኛ ከእኛ የተሻለ ኢኮኖሚ፣ የተሻለ ዝግጅት ያደረጉ ሀገራት በከፍተኛ ደረጃ እየፈተኑ ነው። ስለሆነም ኢትዮጵያውያን በድጋሚ በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት ከመንግስት ጎን በመሆን ይህንን ወረርሽኝ በጥንቃቄ መከላከል ስለምንችል የበኩላችሁን ድርሻ እንድታበረክቱ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

በህገ መንግስቱ በግልጽ እንደተቀመጠው በአንቀጽ 27/5 እና በ93/4 ባለው መሰረት መንግስት የሐይማኖት ተቋማትን ጨምሮ እንደዚህ አይነት የበሽታ ወረርሽኝ ሲያጋጥም የመዝጋት ስልጣን የተሰጠው መሆኑን ይታወቃል። መንግስት ይሄን ስልጣኑን ተጠቅሞ ወደማገድ ያልገባው እነዚህ ተቋማት ዋና አላማቸውና ፍላጎታቸው ህዝባቸውን መጠበቅ፣ ህዝባቸውን ማስተማር፣ ህዝባቸውን ማንቃት፣ ስለሆነ በዚያ መንገድ ሳይሆን በንግግር እና በትብብር መስራት ይቻላል ከሚል እምነት የተነሳ ነው። ስለሆነም በርካታ ጥረት የሚያደርጉ የሀይማኖት አባቶችና ተቋማት እንዳሉ ሆኖ፤ የምትዘናጉ ተቋማት ጥንቃቄ እንድታደርጉ፣ ወደከፋ አስገዳጅ እርምጃዎች ከመግባታችን በፊት በኃላፊነት ስሜት ለተወሰነ ጊዜ ገታ መደረግ እንዳለበት የምታምኑትን በተግባር እንድታውሉ አደራ ማለት እንፈልጋለን።

ይህ ማለት "ጸሎት አያስፈልግም፣ ምልጃ አያስፈልግም" ለማለት አይደለም። እኛም በየኃይማኖታችን እየጸለይን ስለሆነ ህዝባችን እንዲጸልይ እና እንዲማልድ እንፈልጋልን። ነገር ግን ጸሎትና ምልጃው በሽታ የሚያመጣ፣ አደጋ የሚያስከትል ሳይሆን መወሰድ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎች ከግምት ያስገባ እንዲሆን ብቻ ነው። ጥያቄ እያቀረብን ያለነው ጸሎቱ ይቀጥል፤ ምልጃው ይቀጥል፤ ነገር ግን በሽታ በሚያመጣና አደጋ በሚያስከትል መንገድ እንዳይሆን ሁላችሁም የበኩላችሁን ኃላፊነት እንድትወጡ አደራ ማለት እንፈልጋለን።

ከዚህ በተጨማሪ የዚህ ወረርሽኝ አጋጣሚ ለፖለቲካ ፍጆታ የምታውሉ ግለሰቦች ኢትዮጵያዊ ማንነታችሁን እንዳትዘነጉ። በእንደዚህ አይነት ጊዜ በተቻለ መጠን በመደጋገፍ፣ እውነተኛ መረጃ በማቀበል፣ ህዝቡን ማንቃት እንጂ የፖለቲካ ቁማር መጫወት እምብዛም ጠቃሚ አይደለም። ህዝብ ከሞተ፣ ሀገር ከተጎዳ፣ ኢኮኖሚ ከወደቀ ምናልባት እድል ቀንቷችሁ መንግስት ብትሆኑ፣ ኃላፊነት ብትወስዱ፣ ጣጣው አሁን የሚቆም ሳይሆን ወደ እናንተ የሚሸጋገር ነው የሚሆነው። ይህን አገራዊ ችግር ከምንም የፖለቲካ ሀሳብና ፍላጎት በወጣ መንገድ ህዝባችን ለመታደግ፣ ሀገራችን ለመታደግ፣ ኢኮኖሚያችን ለመታደግ እንድንጠቀምበት አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ከህክምና ሞያተኞች አንፃር ምናልባት በጡረታ የተገለሉ ወይንም በስልጠና ላይ ያሉ የህክምና ሞያተኞች ልክ እንደ ወታደር ዝግጅት እንዲያደርጉ፣ መንግስት ከአቅም በላይ የሆነ ጉዳይ ከገጠመው ጥሪ እንደሚያቀርብላቸውና፣ እራሳቸውን ከሙያቸው ጋር በርቀት በማቀራረብ እንዲቆዩና ድጋፍ በሚያስፈልገን ጊዜ ጥሪ የምናቀርብ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ልገልጽ እፈልጋለሁ።

ከዚህ በተጨማሪ ባለፈው በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ከአራት ሺህ በላይ እስረኞች ተፈተዋል። ዋና የተፈቱበት ምክንያት የተጨናነቁ እስር ቤቶች ውስጥ በሽታው ከገባ በርከት ያለ ሰው እንዳይጎዳ በማሰብ ወንጀላቸው ዝቅተኛ የሆኑትን እንዲፈቱ ወስነናል። የተቀሩትን ደግሞ ዘርዘር ባለና ለአደጋ በማያጋልጥ መንገድ እንዲቆዩ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል። የወጡ እስረኞች ምርመራ እና አስፈላጊው ድጋፍ ተደርጎላቸው ወደ አካባቢያቸው እየተላኩ መሆኑን መግለጽ እፈልጋለሁ።





እንግዲህ አዲስ አበባ ላይ ከ134 በላይ የማቆያ ቦታዎች ከ44 ሺህ አልጋ በላይ መያዝ የሚችሉ ቦታዎች ተዘጋጅተዋል። የሚሊኒየም አዳራሽን ጨምሮ በርካታ ተቋማት ለዚህ ጉዳይ ተለይተው አደጋ ካጋጠመን፣ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካጋጠመን፣ ህዝባችንን መታደግ የምንችልበትንና ሞት የምንቀንስበትን መንገድ ለመፈለግ መንግስት ከፍተኛ ርብርብ እያደረገ ይገኛል። ይሁንና እነዚህ ቦታዎች በርካታዎቹ የውሃ ችግር፣ የመብራት ችግር፣ የአልጋ፣ የፍራሽ፣ የአልባሳት ችግር ያለባቸው በመሆኑ፣ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ መንግስት ከሚያደርገው ጥረት በተጨማሪ እነዚህ ቦታዎች ችግር ካጋጠመ ለመከላከል በሚያስችል ቁመና ለማቆየት እንዲቻል ድጋፍ እንዲያደርግ። የተጀመረውም የድጋፍ መንፈስ ተጠናክሮ እንዲቀጥል በዚሁ አጋጣሚ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ከኢኮኖሚ አንጻር የማክሮ ኢኮኖሚ ንዑስ ኮሚቴ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚያደርገው ጥረት በተጨማሪ በሀገር ውስጥም የሚሰራቸው ሥራዎች አሉ። የፋይናንሻል ዘርፉን በሚመለከት ከፍተኛ ታክስ ከፋዮች፣ የኢክስፖርት አድራጊዎች በተለይም የአበባ፣ የአልባሳት፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ የቁም ከብት የሥጋ የመሳሰሉትን በዝርዝር አወያይቶ፣ ኢኮኖሚያችን እንዴት በከፍተኛ ደረጃ ሳይመታ እና ሳይጎዳ መሻገር እንደምንችል ምክክር በማድረግ ግብአቶች ወስዷል።

በተገኘው ግብአት መሰረትም ሰፊ ውይይት በማድረግ የማክሮ ኮሚቴው ለውሳኔ የሚበጁትን ለሚኒስትሪያል ኮሚቴው አቅርቦ ዛሬ በሚከተሉት ዘጠኝ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ አሳልፏል።

ይህን አደጋ ለመከላከል ለተለያየ እቃ ግዥዎች፣ ምግብ ዝግጅትና የቦታ ዝግጅት የሚውል የመጀመሪያው አምስት ቢሊየን ብር ገደማ

በገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር በኩል ተወስኗል። በብሔራዊ ባንክ በኩል ደግሞ የአስራ አምስት ቢሊየን ብር ተጨማሪ ፈሰስ እንዲሆን ለግል ባንኮች ተወስኗል። ይህን ገንዘብ የግል ባንኮቹ እንዲያውሉት የሚጠበቀው ደንበኞቻቸው ያለባቸውን ችግር ተረጋግተው እንዲያስተናግዱና የብድር እፎይታ እንዲያራዝሙላቸው ነው። ተጨማሪ ብድር መስጠቱ ኢኮኖሚው እንዳይጎዳ ለመከላከል ይረዳል።

ሶስተኛው የኮሮና ወረርሽኝ ለመከላከል የሚያስፈልጉ የገቢ እቃዎች በሙሉ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ተወስኗል። ለምሳሌ ቬንትሌተር፣ የንጽህና እቃዎች፣ የሜዲካል እቃዎች፣ እንዲሁም የቴስት ኪት የመሳሰሉትን የሚያካትት ሆኖ ውሳኔው ተላልፏል።

አራተኛው የኮሮና ወረርሽኝ ለመከላከል የሚያስችሉ እቃዎች እና ግብአቶች ወደ ሀገር ለሚያስገቡ አስመጪ ባንኮች የውጪ ምንዛሪ ቅድሚያ በሚያገኙበት መንገድ እንዲያስተናገዱም ተወስኗል።

አምስተኛ በፋይናንስ አገልግሎት ዙሪያ፥ የብር ንክኪን ለመቀነስ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሞባይል አማካኝነት የሚደረገውን ክፍያና ገንዘብ የማስተላለፊያ ጣሪያ ከዚህ ቀደም ከነበረው ከፍ እንዲያደርግ ተወስኗል።

ስድስተኛ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለውጪ ገበያ በሚቀርብ አበባ ላይ የጣለው ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ ገደብ ለጊዜው እንዲነሳ ተደርጓል።

ሰባተኛ ኩባንያዎች የተሻለ ገንዘብ የገንዘብ ፍሰት እንዲኖራቸው የገቢዎች ሚኒስቴር የተጨማሪ እሴት ታክስ አመላለስ ሂደቱን በተለየ መልኩ እንዲያፋጥንላቸውም ተወስኗል።





ስምንተኛ የኮሮናን ወረርሽኝ ተከትሎ ሊከሰት የሚችለውን የሸቀጦች እጥረትና አላስፈላጊ ዋጋ ጭማሪን የመቆጣጠር እንቅስቃሴ በንግድና ኢንደስትሪ ሚኒስቴር በኩል ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተወስኗል።

በመጨረሻም በኮንትሮባንድ መልክ የሚወጡ እቃዎች በብሔራዊ ባንክ ማሻሻያ ተደርጎላቸው፣ በተለይም ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ የሚገባበት መንገድ የማሻሻያ ውሳኔ ተወስኗል። ወደ ውጪ የሚወጡ ሰዎች በሁሉም ድንበር እንዳይወጡ እንዲደረግና በቀጣይም አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን መገምገም ተጨማሪ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ጠንከር ያለ ስራ መስራት እንዳለብን ውሳኔ ላይ ተደርሷል። ይኽን ተከትሎ በሚቀጥሉት ቀናት ያለውን እድገት በማየትና በመገምገም ተጨማሪ እርምጃዎች እና ውሳኔዎች ለህዝብ የምናሳውቅ ይሆናል።

ከዓለም አቀፍ ሀገራት ያገኘናቸው ምላሾች በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ከዓለም ባንክ፣ ከአይ ኤም ኤፍ (IMF) እና ከአፍሪካ ባንክ፣ እንዲሁም ከአንዳንድ ሀገራት ድጋፎች ይጠበቃሉ። በነበሩን ንግግሮች በቅርቡ ተጨማሪ ድጋፍ የማድረግ እርምጃ እንደሚወስዱ ይጠበቃል። እነዚህን ድጋፎች ሳናባክን በከፍተኛ ጥንቃቄ አሁን የገጠመን አደጋ ለመከላከል እና ህዝቦቻችንን ታድገን በበሽታው ምክንያት የሚያጋጥም የኢኮኖሚ ጫና ለመከላከል እንድንጠቀምበት ከስምምነት ተደርሷል።

በመጨረሻም የሚኒስትሪያል ኮሚቴ አባላት የተሰጣችሁን ስራ በመስራት መንግስት የዜጎች ደህንነት ለመከላከል የሚያደርገውን ጥረት በመደገፍና በሚያኮራ መንገድ ኃላፊነታችሁን ስለተወጣችሁ በራሴና በኢፌዲሪ መንግስት ስም ለሚኒስትሮች ኮሚቴ፣ ለንዑስ ኮሚቴ፣ እንዲሁም ትብብር ለሚያደርጉ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

በቀጣይም ደከመን ሰለቸን ሳንል ተናበን፣ መረጃ እየተለዋወጥን፣ እውነተኛ መረጃ እየተቀያየርን፣ ተደጋግፈን ይህንን ወረርሽኝ በመከላከል የኢትዮጵያውያንን ህይወት ለመታደግ እና ኢኮኖሚያችን እንዳይንኮታኮት ለመከላከል የምናደርገውን የጋራ ርብርብ አጠናክረን እንድንድንቀጥል አደራ ማለት እፈልጋለሁ!

**አመሰግናለሁ!!**





# የኮሮና ወቅታዊ መግለጫ

**መጋቢት 21፣ 2012 ዓ.ም**

የኮሮና ቫይረስ ለመላው ዓለም አስጨናቂ ሊከላከሉት የማይችል አደገኛ ወረርሽኝ ከሆነ ሰንበትበት ብሏል። በዓለም ላይ ከ600 መቶ ሺህ በላይ ሰዎች በዚህ ቫይረስ መጠቃታቸው ተረጋግጧል። ከ30 ሺህ ያላነሰ ሰው ሕይወቱ አልፋል። አሁንም ብዙ ቦታዎች ጭንቀት፣ ስጋት፣ ፍራቻ ይስተዋላል። ይህንን ጭንቀት ፍራቻ ገንዘብ ሊመክተው አልቻለም። እውቀትም ሊያቆመው አልቻለም። “ኃያል” መባል ወይም “ብዙ፣ ትንሽ” መባል ሊያቆመው አልቻለም።

እስከ አሁን ባለው ልምድ ይሄንን ቫይረስ በተቻለ መጠን መቀነስና አደጋውን እንዳይከፋ ለማድረግ የቻሉ ሃገራት በትብብርና በሥነ ሥርዓት መሥራት የቻሉ ሀገራት ብቻ ናቸው። በሥነ ምግባር ያደገ ማህበረሰብ ያላቸውና በመረጃ ፍሰት ሕዝቡን፣ የየዕለት ሁኔታውን እያወቀ እራሱን እንዲጠብቅ፣ ሀገሩን እንዲጠብቅ፣ ማሕበረሰቡን እንዲጠብቅ ያደረጉ ሃገራት ወረርሽኙ በከፍተኛ ደረጃ ሊደርስባቸው ከሚችል አደጋ ራሳቸውንና ሀገራቸውን መታደግ ችለዋል። በእኛ ሁኔታ ቁጥሩ እየጨመረ መሆኑን የሚያመላክቱ ሪፖርቶች እየወጡ ነው።

ዛሬ ጠዋት ኢትዮጵያ ውስጥ በዚህ በሽታ ከመረመርናቸው ከ800 (ስምንት መቶ) ሰው በላይ እስካሁን ምርመራ የተካሄደ ቢሆንም 23 ሰው ገደማ በዚህ ቫይረስ መጠቃቱ ተረጋግጧል። ከነዚህ ውስጥ 2 (ሁለት) ሰው ያገገመ ሲሆን፣ ምንም ሰው እስካሁን የሞተብን የለም። ይሁንና በከተሞች እየታየ ያለው ጥግግትና ንኪኪ፣ የሚሰጠውን መመሪያ ለመቀበል ችላ ማለት ያሳስባል። ብዙዎች "ኢትዮጵያ ውስጥ በከፋ ሁኔታ ከተገለጠ አሁን ባለው ዲሲፒሊን እንዴት መከላከል ይቻላል?" የሚል ስጋት አላቸው።

ሁላችሁም እንደምታውቁት የተሻለ ሃብት፣ የተሻለ ሆስፒታል፣ የተሻለ አቅም ያላቸው ሀገራት በቀላሉ አደጋውን መከላከል ስላልቻሉ በእኛ ሁኔታ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዳይሆንብን ማህበረሰቡ ከምንም በላይ ሊተባበር ይገባል። ብቸኛው መከላከያ መንገድ በዲሲፒሊን ራስን ማሸነፍና ርቀትን መጠበቅ፣ ንጽህናን መጠበቅ፣ በተቻለ መጠን ከንኪኪ ራስን አርቆ ማስገኘት ነው።

ሁሉም ዜጋ በከፍተኛ ኃላፊነት ስሜት በመተግበር ኢትዮጵያን ከሚገጥማት አደጋ መከላከል እንድንችል በከፍተኛ ትህትና ለማሳሰብ እፈልጋለሁ። ይሄ እንዳለ ሆኖ በገጠመን ፈተና ላይ ስለ ብዙዎች ሲባል መስዋእትነት የሚከፍሉ በርካታ የቁርጥ ቀን ልጆች የቁርጥ ቀን ልጅነታቸውን በተግባር አሳይተዋል። መስዋዕትነቱ ጊዜን፣ እውቀትን፣ ጉልበትን፣ ገንዘብን፣ ከሁሉም በላይ ራስን መስጠት ሊሆን ይችላል።

ሰው ስላለው ወይም ስለተረፈው ብቻ አይሰጥም። መስጠት ለሕዝብ መስዋዕት ለመሆን ከመወሰን የሚመጣ ነው። በዚህ ፈታኝ ወቅት ገንዘባቸውን፣ ቤታቸውን መኪናቸውን፣ ሆቴላቸውን፣ ሕንፃቸውን፣ እህላቸውን፣ ያላቸውን ሁሉ የሚሰጡ የቁርጥ ቀን ልጆች ኢትዮጵያ እንዳሏት ማየት ችለናል።





በቂና ብቁ መሳሪያዎች ባልተሟሉበት ሁኔታ "እኔ ለወገኔ" ብለው ሕዝባቸውን ለመታደግ የሚሰዉ የሕክምና ባለሙያዎች አግኝተናል። ይህ ጊዜ ያልፋል። እናንተ ሁላችሁ ኢትዮጵያውያን ኮሮናን የሚከላከለው ሠራዊት አባል ናችሁ። ሁላችን ይሄንን ሠራዊት ከተቀላቀልን ኮሮናን በአጭር ጊዜ የከፋ ጉዳት ሳያስከትል ልናሸንፈው እንችላለን።

ኮሮናን የማሸነፊያው ብቸኛው መንገድ መደመርና ዲሲፕሊን መሆኑን ከዓለም፣ በተለይም ከቻይና መማር ተችሏል። የኮሮና ነገር ወደ ታሪክ መዝገብ ቤት ተልኮ ሀገር የጀመረችውን የብልጽግና ጉዞ እንድትቀጥል ሁላችንም የሚነገረን ማሳሰቢያ ተቀብለን መተግበር ይጠበቅብናል። ይህንን ማድረግ ከቻልን ትውልድ እኛን በኩራት የሚያነሳን የዚህ ዘመን ጀግኖች አድርጐና በትምህርት ቤት የሚማርብን ልንሆን እንችላለን።

እናም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተቻለ መጠን በሽታውን በአጭር ጊዜ አስቀርተን የጀመርነውን የብልጽግና፣ የእድገትና የሰላም ጉዞ ማስቀጠል እንድንችል፣ የበኩላችሁን መወጣት እንድትችሉ ደግሜ ደጋግሜ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። ያላችሁን ሁሉ ለሀገራችሁ በመስጠት፣ ለመስዕዋትነት የተሰለፉችሁትን ሁሉ ሀገራችን ታመሰግናችኋለች።

እንድታስብ አእምሮህን፣ እንድትፀና ጉልበትህን፣ እንድትወስን ልቦናህን፣ እንድትፈጽም መንገድህን ፈጣሪ ይጠብቅ። ፈጣሪ በነገር ሁሉ ኢትዮጵያን ሀገራችንን ሕዝባችንን ይጠብቅ። ባለን አቅም ሁሉ ተረባርበን የምንሰሥራ፣ በሚጐድለን ደግሞ እሱ የሚሞላበት ይሁን!

**አመሰግናለሁ!!**

# ያልፋል አትጠራጠሩ

መጋቢት 24፣ 2012 ዓ.ም.

## ክቡራትና ክቡራን ኢትዮጵያውያን ውድ የሀገሬ ሕዝቦች

የለውጡን ጉዞ ሁለተኛውን ዓመት የምናከብረው በአንድ በኩል ፈተናና ስጋት በሌላ በኩል የተስፋ ውጋጋን ከፊታችን እየታየን ነው። ሀገራችን ባለፉት ሁለት ዓመታት በለውጥ ሂደት ያገኘቻቸውን ተስፋዎች ለማፍካት፣ ያጋጠሟትን ሳንካዎች ደግሞ ለማስተካከል እየጣረች ባለችበት ወሳኝ ወቅት መላው ዓለምን በጥቂት ወራት ውስጥ በቁጥጥሩ ስር ያዋለው የማይታየው ጠላት የኮሮና ቫይረስ በእኛም አገር አሻራውን አሳርፏል።

በእስካሁን ጉዞው 200 የሚጠጉ ሀገራትን ያዳረሰው ይህ ወረርሽኝ ወደ ሀገራችንም ገብቶ 16 ሰዎችን የቫይረሱ ተጠቂ አድርጓል። ነገ ምን ያህል ዜጎቻችንን እንደሚያጠቃ በእርግጠኝነት ባናውቅም ሁላችንም ተረባርበን በዝቅተኛ ጉዳት እንደምናስቆመው ግን ሙሉ እምነት አለን።

ሀገራችን በፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ ስታልፍ ይኽ የመጀመሪያዋ አይደለም፤ የመጨረሻዋም ላይሆን ይችላል። በለውጡ ጉዞ





የመጀመሪያው ምዕራፍ ወቅት በሶማሌ ክልል የተነሳውና በመሳሪያም፣ በጭካኔም እስካፍንጫው ታጥቆ የነበረው ሀይል በስልጣን ጥም ታውሮ አጎራባች ክልሎችን ሰላም ከማናጋት አንስቶ ክልሉን እስከመገንጠል የተለጠጠ ፍላጎት የነበረው ሲሆን፤ የለኮሰው እሳት የአፍሪካ ቀንድን እስከመረበሽ ሊደርስ ይችላል የሚል ስጋት በብዙዎች ዘንድ መፈጠሩ አይካድም። ያም ሆኖ የለውጡ ዓላማ ኢትዮጵያን በፍትሕ የላቀች፣ በዴሞክራሲ የዳበረች፣ በሰብአዊ መብት ጥበቃ የተመሰገነች፣ በኢኮኖሚ የበለጸገች፣ በሰላምና በደኅንነት የተረጋጋች ሀገር ማድረግ ነበርና ከፈተናው ጎን ለጎን በተከናወኑ የተሃድሶ ተግባራት ያ መጥፎ አጋጣሚ አልፎ እዚህ ደርሰናል።

በተመሳሳይ የታጠቁ ኃይሎች በወለጋ እና በሌሎች የምእራብ ኦሮሚያ ክፍሎች ላይ የጥፋት በትራቸውን አሳርፈው ባንክ እየዘረፉ፣ ሰው እየገደሉ፣ ቤት እያቃጠሉ፣ መንገድ እየዘጉ፣ ትምህርት ቤት እየዘጉ ነዋሪውን እያማረሩ የነበረበት፤ ከገጠር ቀበሌዎች አልፎ እንደ ነቀምት፣ ጊምቢ እና ሻምቦ ባሉ ትላልቅ ከተሞች ውስጥ መንግስታዊ መዋቅርን ለማፈራረስ የተንቀሳቀሰበት፤ የእለት ተእለት እንቅስቃሴዎች ያለወታደራዊ አጀብ የሚያስቸግሩበት ጊዜያትን አስተናግደናል። የለውጥ ጉዞው ይሄንንም መጥፎ ጊዜ አልፎ አሁን የሕዳሴ ግድብ ግንባታችንን እያጣደፍን፣ ሌሎች ሜጋ ፕሮጀክቶቻችንን በማጠናቀቅ ተስፋችንን ሳይሆን ሪቫን እየቆረጥን ዛሬ ካለንበት ደርሰናል።

በአንድ ቀን በአማራ ክልል ጠንካራ ጓዶቻችንን በግፍ አጥተን፤ በአዲስ አበባ ተወዳጅ የጦር መሪዎቻችን ተገድለው፤ ውጥረቱ ለድፍን ኢትዮጵያ ተርፎ የነበረበት ጊዜ አልፏል። እዚህና እዚያ እሳት በተለኮሰ ቁጥር ጥፋተኛው ይህና ያኛው ቡድን ነው እየተባለ፤ በየአካባቢው

ሀያና ሰላሳ የታጠቀ ጦር ሠራዊት ያለ እስኪመስል ድረስ በየቦታውና በየጊዜው ሰዎች እየተገደሉ፤ አንድ ሰው አልበቃ ብሎ መንደር በሙሉ በእሳት ይጋይ የነበረበት፤ እልቂቱ በአንድ አካባቢ ሳይወሰን፣ ሁለትና ሦስት ክልሎችን ያነካካበት፤ ዜጎች "ኢትዮጵያ ልትበታተን ትችላለች" በሚል ስጋት ውስጥ እንዲቆዩ የሆነበት አስጨናቂ ጊዜን ተረማምደናል።

ኃላፊነት በማይሰማቸው ሰዎች ንግግር ወንድም እህቶቻችንን የተቀጠፉበት፤ በትንሽ በትልቁ የህግ የበላይነት ያበቃለት፣ ኢትዮጵያም ያከተመላት እንዲመስል ተደጋጋሚ የጥፋት ርምጃዎች የተካሄዱበት ወቅት አልፎ ከሞላ ጎደል ወደ ሰላማችን ተመልሰናል። የለውጥ ጉዞው በየጊዜው የሚገጥሙትን ጋሬጣዎች ከመሻገር ባለፈ የተለያዩ የሪፎርም ተግባራትን ለማከናወን የተንቀሳቀሰበት ወሳኝ ወቅትም ነበር።

በዚህም፣ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያችንን መሬት እንዲረግጥ ለማድረግ፤ ንግድን ለማሳለጥ የሚያስችል የ"ዱይንግ ቢዝነስ" ማሻሻያን በፍጥነት ለመተግበር፤ ከዓለም የንግድ ድርጅት ጋር ስኬታማ ድርድር ለማካሄድ፤ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ የብድርና የርዳታ ተቋማት ጋር ኢኮኖሚውን ለመደገፍ የሚያስችሉ ውጤታማ ስምምነቶችን ለማድረግ ችለናል። በባንኮች ላይ የነበሩ የአሠራር ጫናዎችን ለማቃለል፣ ለሰብአዊ መብትና ለጋራ ተጠቃሚነት ዕንቅፋት የሆኑ ሕጎችና አሠራሮችን ለማስተካከል፤ በተለያዩ አካባቢዎች ግጭቶች ሳይከሰቱ ለማምከን የሚያስችል አቅማችንን ለማደርጀት፤ ግጭቶችን የሚፈጥሩ ግለሰቦችን በሕግ ጥላ ሥር ለማዋል በሙሉ አቅማችን ተንቀሳቅሰናል። ወደ አስቸጋሪ ሁኔታ እያመሩ የነበሩ በዩኒቨርሲቲዎችን ወደ መልካም መማር ማስተማር ሂደት ማምራት የሚችሉበት አጋጣሚ





ተፈጥሮ፣ ስለ ምርጫ፣ ስለ ሀገራችን ብልጽግና እና ስለ ወደፊቷ ጠንካራ ኢትዮጵያ ማሰብ በጀመርንበት ወቅት እነሆ ሌላ ጋሬጣ ከፊታችን ቆሟል። ምንም እንኳ ፈተናው የመጣው ለመላው አለም ቢሆንም ከፊታችን የተደቀነውን ችግር ለመጋፈጥ እንደ ቀደሙት ጊዜያት ጉልበታችን ላፍታ ሸብረክ እንደማይል ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። ሁሌም እንደምናደርገው ሕዝባችንን አስተባብረንና ዐቅማችንን ደምረን በድል ከተሻገርነው በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ጀመርናቸው ሀገራዊ ሪፎርሞች ፊታችንን እንደምናዞር ጥርጥር የለኝም።

ሀገራዊ ለውጥን በጽኑ መሰረት ላይ የመትከል ትግላችንን ጊዜያዊ ፈተና አይገታውም። አሁን በዓለም ደረጃ የተከሠተውን ዓይነት ፈተና ወደፊትም ይገጥመን ይሆናል። "ስለ ነገ በትክክል ለመተንበይ የተሻለው ዘዴ ዛሬ ላይ ሆኖ የወደፊቱን መፍጠር ነው" እንዲሉ ለሚገጥሙን ፈተናዎች የዝግጁነት አቅማችንን እያሳደግን እንቀጥላለን።

ኢትዮጵያን ከፈተናዎች በላይ እንድትሆን አድርገን ለመገንባት የሁላችንም ርብርብ ይጠይቃል። እስካሁን ባለው ጉዟችን የሀገራችንን ኢኮኖሚ፣ ተቋማቶቿን፣ የፍትሕ ሥርዓቷን፣ ማኅበራዊ ደኅንነቷን፣ የሕግ አስከባሪ አካላትን፣ የጤናና የትምህርት ሥርዓቷን በማጠናከር ፈተናዎችን መቋቋም በሚችሉበት ደረጃ ለማደራጀት ጠንካራ የዐቅም መሠረት መጣል ጀምረናል። ዐቅም ግንባታ ስትራቴጂያዊ ዕይታን የሚጠይቅ፣ ተከታታይ ስራን የሚፈልግ እና ፈጽሞ የማያቋርጥ ረጅም ሂደት መሆኑ ግልጽ ነው። ይኽም ደግሞ እንደኛ ድሀ በሆኑ ሀገራት ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚ ግንባር ቀደም የሆኑትን ጭምር የሚመለከት መሆኑ የሰሞኑ ዓለም አቀፋዊ ፈተና ምስክር ነው።

በኮሮና ቫይረስ ምክንያት እንኳን እኛን ጠንካራ የጤና መሠረተ-ልማት የገነቡትን ምዕራብያውያን ምን ያህል እያስጨነቀ እንዳለ ሁላችንም እንገነዘባለን። በብዙ ሀገራት ትምህርት ቤቶች ከተዘጉ ሰነባብተዋል። በድንበሮች አካባቢ ከፍተኛ ቁጥጥር እየተደረገ ነው፤ የንግድና ስራ እንቅስቃሴዎችም በከፊል ተቋርጠዋል።

የዶላር ግኝት አለኝታችን የሆነው እና ከሀገራችን አልፎ የአፍሪካችን የኩራት ምንጭ የሆነው አየር መንገዳችን እንቅስቃሴው በከፊል ተገቷል። የአበባ ኤክስፖርት ንግዳችን የሚያንሰራራበት ጊዜ በውል ባልታወቀ አጣብቂኝ ውስጥ ተቀርቅሯል። በኤክስፖርት፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በፋይናንስ ዘርፎቻችን ላይ የተደቀነው ተግዳሮት በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ምንም እንኳ እየገጠመን ያለው ችግር ከዚህ በፊት እንዳየናቸው አደጋዎች የማያልፍ ቢመስልም ማለፉ ግን አይቀርም። ስለተመኘን ሳይሆን በትብብር ስለምንሰራ ይህ ጊዜ ያልፋል። ከወዲሁ እውቀታቸውን፣ ሀብታቸውን፣ ጊዜና ጉልበታቸውን በመስጠት የትብብር አቅማቸው ምን ያህል እንደሆነ እያሳዩን ያሉ ድንቅ ኢትዮጵያውያን ለዚህ ምስክር ናቸው።

## ውድ የሀገሬ ህዝቦች !

የለውጡን ጉዞ ሁለተኛ ዓመት ስንዘክር ምን ዓይነት ኢትዮጵያ እንገንባ የሚለውን እያሰብን መሆን አለበት። ኅብረ ብሔራዊ አንድነቷ የጠነከረ፤ ሁለንተናዊ ብልጽግናን ያረጋገጠችና ለዜጎቿ ምቹ የሆነች፤ ለኢንቨስትመንት ተመራጭ፣ የምሥራቅ አፍሪካ የቢዝነስና ኢኮኖሚ





ማዕከል የማድረግ ርዕይ በውስጣችን ልንሰንቅ ይገባል። ሰላሟና ደኅንነቷ የተረጋገጠ፤ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ከፍትሐዊ ተጠቃሚነት ጋር ያገናዘበች፤ በአፍሪካ ለቱሪስቶች ተመራጭ የሆኑ መዳረሻዎች ያሏት፤ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሀብቶቿን በሚገባ ማልማት የምትችል ሀገር መገንባትን ታሳቢ ማድረግ ይጠበቅብናል።

ይህችን ብሩህ ተስፋ የሰነቀች ሀገር ተሳክቶላት ለማየት ካለፉት ስሕተቶቻችን እየተማርን፣ ያሉንን ወረቶች ይዘን፤ ከሚያራርቁን ይልቅ ለሚያቀራርቡን ነገሮች ትኩረት እየሰጠን፤ ከትናንት ይልቅ ነገ ላይ እያተኮርን መጓዝ አለብን። ዓለም ከነገ ጋር ለመወዳደር እየሮጠ ነው። ተወዳድረን ማሸነፍ ከፈለግን መሮጥ ቀርቶ መራመድ፣ መራመድ ቀርቶ መቆም፣ መቆም ቀርቶ መተኛት ለእኛ ፍጹም አያዋጣንም። ያለችንን ጥቂት ጉልበት ይዘን ሽምጥ ለመፈትለክ መፍጨርጨር ነው ምርጫችን። ሙሉ ትኩረታችንን ታላቁ ሀገራዊ ዓላማ ላይ አድርገን ከተጓዝን ከወጀቡ ባሻገር በስኬት እንሸለማለን።

በመጨረሻም ቀጣዩ የለውጥ ዘመን ካሳለፍናቸው ሁለት የለውጥ ምዕራፎች የተሻለ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ። ሀገራችንን ወደሚገባት ምእራፍ እንደምናደርሳት አምናለሁ። ለዚህ ደግሞ የሁላችን የሥራና ጸሎት ሕብረት ያስፈልጋታል። ከቀበሌ እስከ ፌደራል ባሉ የተለያዩ የሀላፊነት እርከኖች፤ ከአርሶና አርብቶ አደር ማህበሮች እስከ ንግድና ኢንቨስትመንት ማዕከላት፤ በተለያየ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ሞያተኞች፤ ልሂቃን፤ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት፤ በውጭ የምትኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፤ በየግንባሩ የተሰለፋችሁ የሠራዊት አባላት፣ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ እጣ ፈንታ ይመለከተናል የምትሉ ሁሉ

ለሀገራችን ጉልበታችሁን ሳትሰስቱ እንድትሰጧት በዚሁ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

ተባበርን፣ ተደመርን፣ በአንድነት ወቅታዊ ፈተናችንን እንሻገራለን፤ የምንመኛትን፣ የምንጓጓላትን፣ የበለጸገች ኢትዮጵያን እንገነባለን። የተዘጉ ትምህርት ቤቶች፣ መስሪያ ቤቶችና ድንበሮች ይከፈታሉ፤ የተቀዛቀዘ ኢኮኖሚያችን ዳግም ያንሰራራል። ላልተወሰነ ጊዜ የምናደርገው መራራቅ በመቀራረብ ይተካል። እንቅስቃሴዎች ሁሉ ወደነበሩበት ይመለሳሉ። ሞትም በሕይወት ይሸነፋል።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**





# ኮቪድ 19 በተመለከተ የተላለፈ መልእክት

**መጋቢት 26፣ 2012 ዓ.ም**

## የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ሕዝቦች

ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ዓለምን የገጠመውን አዲሱን ቫይረስ በሚመለከት በየጊዜው መነጋገር፣ የእለት ተእለት አጀንዳችን መሆን ከጀመረ ውሎ አድሯል። ይህ ኮቪድ 19 የሚባለው ቫይረስ የኮሮና ቫይረስ አንዱ አካል ሲሆን በኮሮና ቫይረስ ምድብ ውስጥ ከፍ ባለ ደረጃ ስሙ የተጠቀሰ እና ጥቃትም እያደረሰ ያለ አደገኛ ወረርሽኝ ነው። የዚህ አደገኛ ወረርሽኝ ከበረታን፣ ከተደማመጥን፣ በጋራ ከሰራን፣ ከዚህ ቀደም የሰው ልጅ ተቋቁሞ እንዳሸነፋቸው በርካታ ፈተናዎች ተላላፊ በሽታዎች ሁሉ ለማሸነፍ ዛሬ ከትላንት ይልቅ የተሻለ እድልና ተስፋ አለ።

ቴክኖሎጂው፣ የህክምና ሳይንስ ጥበቡ፣ ዓለም ባጠረ ጊዜ የመተጋገዝ አቅሙ ከዚህ ቀደም ከነበሩት ወረርሽኞች እና ፈታኝ ወቅቶች፣ ዓለም በተሻለ ደረጃ ለመከላከል አቅም እንዳላት የሚያሳይ ነው።

ባለፉት ሺህ አመታት የሰው ልጅ በርካታ ፈተናዎች በተለይም ወረርሽኞችን አስተናግዷል። እነዚህ ወረርሽኞች ብዙዎቹ የተወሰነውን

የዓለም ክፍል ሲያጠቁ ጥቂቶቹ ደግሞ ዓለምን ያዳረሱ ነበሩ። የሰውን ልጅ በብዙ ቁጥር የጨረሱ፣ የታሪክን አቅጣጫ የቀየሩ፣ የሰው ልጅ እራሱን ለማዳን አዳዲስ ፈጠራዎች እንዲያደርግ እድል የከፈቱም ነበሩ። በአንዳንድ ወቅቶች የሰውን ልጅ ህልውናና ስልጣኔ ከነጭራሹ የሚደመስሱ እስኪመስሉ ድረስ አደገኛ ወረርሽኞች፣ ተግዳሮቶችን፣ የሰው ልጅ ተቋቁሞ ትውልድን ማስቀጠል ችሏል።

ከነዚህ አደገኛ ገጠመኞቹ መካከል ጥቂቶቹን ለመግለጽ እንዲቻል፦ በመጀመሪያ የዘርፉ ሞያተኞች እንደዚህ አይነት ወረርሽኞችን በሶስት ከፍለው ያስቀምጧቸዋል። የመጀመሪያው "ኢንደሚክ" (Endemic) የሚባለው በተወሰነ ቦታ ላይ በወረርሽኝ መልክ የሰውን ልጅ የሚፈታተን የሚገድል ሲሆን፣ እንደ ወባ ያለው በሽታ "ኢንደሚክ" ሊባል ይችላል። ውስን ቦታ በተደጋጋሚ እየመጣ የሚያጠቃ፣ የሰውን ልጅ ህይወት የሚቀጥፍ ሲሆን ኢንደሚክ ይባላል።

ሁለተኛው አይነት ከአንደኛው ከፍ የሚለው "ኢፒደሚክ" (Epidemic) የሚባለው ነው። ሰፋ ያለ ቦታ ከሃገር እስከ መሻገር የሚደርስ፣ በማጥቃት አቅሙም "ከኢንደሚኩ" ከፍ ያለ እንደ "ኢቦላ" (Ebola) ያለውን ወረርሽኝ "ኢፒደሚክ" ይሉታል።

ሦስተኛው ከአህጉር በመሻገር በርካታውን የዓለም ክፍል የሚያጠቃው እና ህይወት በመቅጠፍ የሚታወቀውን አይነት ወረርሽኝ ደግሞ "ፓንደሚክ" (Pandemic) ተብሎ ይከፈላል።

ይህ "ፓንደሚክ" የሚባለው ከአንድ ሃገር፣ ከአንድ አህጉር በላይ በርከት ያለ ቦታ የሚሸፍን እና ብዙዎችን የሚገድል፣ የሰው ልጆችን በአስከፊ ሁኔታ የሚፈታተን አይነት ወረርሽኝ ነው። እነዚህ ወረርሽኞች በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ያጋጠሙትን እንደ ምሳሌ ጥቂቱን ለማንሳት





ያህል አንደኛውና ተጠቃሽ ወረርሽኝ "ጥቁር ሞት" ወይም (Black Death) ይባላል። ይህ በሽታ በዓለም ላይ የተከሰተው እንደ እ. ኤ. አ 1346 አካባቢ ሲሆን የበሽታው መንስኤ የባክቴሪያ ኢንፌክሽን ነበር። የዚህ የባክቴሪያ ኢንፌክሽን ዋነኛ አስተላላፊዎች አይጦች እና ቁንጫዎች ሲሆኑ በሰው ልጅ ላይ ከፍተኛ አደጋ እንዲጋረጥ ምክንያት ሆነዋል። በጊዜው በባክቴሪያው ከተለከፈው ሰው ሰማኒያ በመቶ ያህሉ ይሞት ነበር። በበሽታው አለመያዝ እንጂ ከተያዝን ለመትረፍ ሃያ በመቶ ብቻ ማለት ነው። የተያዘ ሰው የመሞት እድሉ እጅግ የሰፋ ነበር።

በዚህ በሽታ በአውሮፓ ብቻ ከሃምሳ ሚሊየን በላይ ህዝብ ፈጅቷል። ይህም ቁጥር ማለት በወቅቱ የአውሮፓ ህዝብ ከነበረው የህዝብ ቁጥር ስድሳ በመቶ ገደማውን ይሸፍናል። እንግዲህ በዓለም ላይ ከነበሩ ሁለት ሰዎች አንዱን እንደ መግደል ያህል በጣም አደገኛ፣ በሰው ልጅ ላይ ጎልቶ የሚታይ ጥቃት የፈጸመ ወረርሽኝ ነበረ። በወቅቱ የሰው ልጅ በሽታውን የሚከላከልበት የህክምና ጥበብ በብዙ ስላልነበረው እያየ ያልቅ ነበረ። አባት ልጁን መታደግ፣ እናት ልጇን መታደግ፣ ሞያተኛ እና የተማሩ ሰዎች ዜጎቻቸውን መታደግ በፍጹም የማያስችል ነበር።

ይህም ሆኖ የሰው ልጅ በበሽታው እስከ መጨረሻው ተሸንፎ አልጠፋም። የሰው ስልጣኔና የሰው ዘር በርትቶ፣ ተደጋግፎ እያገገመ ትውልድን ማስቀጠል እና ከምድረ-ገጽ ሳይጠፋ ህይወት እንድትቀጥል ማድረግ ችሏል።

ከዚያ በኋላ የመጣው ወረርሽኝ "ፈንጣጣ" ወይንም (Small Pox) የሚባለው ነው። ይህ በሽታ በአውሮፓ በሰፊው የተከሰተው በ18ኛው ምእተ ዓመት አካባቢ ነው። የህመሙ መነሻ እንደ መጀመሪያው ሳይሆን ይሄኛው ደግሞ ቫይረስ ነው። ይህ በሽታ ክትባት

እስከተገኘለት ጊዜ ድረስ የአውሮፓን ዳታ ብቻ ስንመለከት በዓመት እስከ 400 ሺህ ህዝብ ይገድል ነበር። ይህ ከፍተኛ የሆነ ጥቃት ያደረሰ ሁለተኛው ወረርሽኝ በሰው ልጅ የተባበረ ክንድና ትጋት ተሸንፎ ህይወት ማስቀጠል ተችሎ ነበር።

ሦስተኛው በዓለም ታሪክ ውስጥ ጎልቶ የሚነገረው "ኢንፍሉዌንዛ" (Influenza) ወይንም "ስፓኒሽ ፍሉ" (Spanish Flu) የሚባለው ነው። ይህ በሽታ የዛሬ መቶ ዓመት ገደማ በ1918 እ.ኤ.አ የተከሰተ ሲሆን በሽታው የሚያጠቃው በአብዛኛው ጨቅላ ህጻናትንና በእድሜ የገፉ አዛውንቶችን ነበር። ይህ በሽታ በጣም ከመስፋፋቱ የተነሳ 500 ሚሊየን የሚጠጋ ህዝብ በዚህ በሽታ ተጠቅቶ እንደነበር በርካታ መረጃዎች ያመላከታሉ።

ይህ ማለት ከዓለም ህዝብ አንድ አራተኛው በዚህ በሽታ ተጠቂ ነበር ማለት ነው። በዚህ ህመም በወቅቱ የሞተው ህዝብ ቁጥር የተሟላ ዳታ ባይገኝም አንዳንድ ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት ከሃምሳ እስከ መቶ ሚሊየን ህዝብ ይገመታል። ይህ በሽታም ብዙ ህዝብ የፈጀ አደገኛ ወረርሽኝ ቢሆንም በመጨረሻ ከትባት ተገኝቶለት እና የሰው ልጅ የተፈጥሮ የመከላከያ አቅሙ ጎልበቶ ይህን ወረርሽኝ ማሸነፍ ችሏል።

ከነዚህ ሦስት "ፓንደሚክ" ከሚባሉ ወረርሽኞች ቀጥሎ በዓለም ጤና ድርጅት (WHO) "ፓንደሚክ" የሚል የተፈረጀው አደገኛ ቫይረስ ኮሮና ወይንም ኮቪድ-19 ነው።

ኮቪድ-19 ከተከሰተ ጥቂት ወራትን የፈጀ ቢሆንም ከአንድ ሚሊየን በላይ ህዝብ በዚህ በሽታ ተጠቅቷል። በዓለም ላይ በአጠቃላይ ያልደረሰበት ሃገር የለም፤ መላውን ዓለም ሸፍኗል። በአፍሪካ ብቻ ያለውን ዝንባሌ ስንመለከት ከአንድ ሳምንት በፊት አፍሪካ ውስጥ





ሦስት ሺህ ሰው ብቻ የተጠቃ ሲሆን ከአንድ ሳምንት በኋላ እጥፍ በመሆን ከሰባት ሺህ ሰው በላይ በበሽታው ተበክሏል። ከነዚህ ውስጥ ከ286 ሰው በላይ ህይወቱ አልፏል።

ይህ በአፍሪካ እየፈጠነ ያለው የወረርሽኝ ጥቃት ቁጥር ቀደም ሲል ከነበሩት የወረርሽኝ ጥቃቶች አንጻር ሲታይ በፍጥነት እየተዘረጋ ያለና መተሳሰር፣ መደጋገፍ፣ መደማመጥ በእጅጉ የሚጠይቅ ነው። ይህን ወረርሽኝ በከፍተኛ ደረጃ መጠንቀቅ የሚያስፈልግበት ምክንያት ወረርሽኙ በአንድ በኩል የሰዎችን ህይወት እየቀጠፈ፣ በርካቶችን እያራገፈ ያለ ሲሆን፣ በሌላ በኩል በአጭር ሁኔታ ማገገም በማያስችል ሁኔታ የዓለምን ኢኮኖሚ መትቷል።

በተለይም የአፍሪካ ኢኮኖሚ ከዚህ አንጻር ለሚቀጥሉት ዓመታት ማገገም እስኪያቅተው ድረስ በከፍተኛ ደረጃ ተመትቷል። እንግዲህ ይህ በሽታ በፍጥነት እየተዛመተ ያለ ሲሆን ኢኮኖሚውንና ሰዎች የመቅጠፍ አቅሙ ባላደጉ፣ ባልበረቱ መንግስታትና ሃገራት ብቻ ሳይሆን ጠንካራ ለሚባሉት ኃያላን ሃገራትም ጭምር አስከሬን ማስቀመጫ እስኪቸግራቸው ድረስ እጅግ አስከፊ የሆነ ጥፋት እንድንታዘብ፣ እንድናይ አድርጎናል።

በዚህ ዘመን የተሻለ ሕይወት የማትረፍ የህክምና አቅም በዓለማችን ደረጃ የተፈጠረ ቢሆንም፣ በንጽጽር የተሻለ መሰረተ ልማት እና የኢንፎርሜሽን ልውውጥ ያለ ቢሆንም፣ የተሻለ ዓለማዊ ትስስርና ትብብር ያለ ቢሆንም፣ የተሻለ ህዝባዊ እሴትና ጠንካራ መንግስታት ያሉ ቢሆንም እኛ በአፍሪካ የምንገኝ ገና በማደግ ላይ ያለን ሀገሮች ኮሮናን ተዋግተን አሸንፈን የአፍሪካ ህዝቦች ከዓለም ህዝቦች ጋር ትውልድ መቀጠሉን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ጥረትና በሃላፊነት መንፈስ መስራት ይጠይቃል።

እስካሁን በኢትዮጵያ ውስጥ በዚህ በሽታ ጥቃት የሞተ ሰው ባለመኖሩ በሽታውን ቀለል አድርጎ የማየት እና ገዳይ እንዳልሆነ የመመልከት ዝንባሌ ይታያል። በሌላ መንገድ መንግስት እንደ አንዳንድ ሃገራት "ሙሉ በሙሉ ገበያውንና እንቅስቃሴውን ለምን አይዘጋም?" የሚሉ ወገኖችም በስፋት ይደመጣሉ።

ኢትዮጵያን የተሻለ አቅም እንዳላቸው ሃገራት እንዳንዘጋ የሚያደርገን "ሁላችሁም ቤታችሁ ግቡ" ብንል ቤት የሌላቸው በርካታ ቁጥር ያላቸው ዜጎች እንዳሉን እናውቃለን። ቤት ያላቸውም ቢሆኑ በቀን ወጥተው የእለት ጉርሳቸውን ካልሰሩ መንግስት የእለት ጉርሳቸውን ማቅረብ አይችልም። እነሱ ደግሞ ካልወጡ የማይበሉ ከሆነ በአንድ መንገድ ህይወታቸውን ብንታደግም፣ በሌላ መንገድ ህይወታቸውን ስለምናጣ፣ ሌላ ሃገር ያየነውን ሁሉ እዚህ አምጥቶ መተግበር ያስቸግራል። ስለዚህም ከእኛ ሁኔታ አንጻር ተመካክረን፣ ተወያይተን፣ በአቅማችን ልክ ሞት ቀንሰን፣ በሽታውን መከላከል እንድንችል በርካታ ውይይቶች፣ የማስተማሪያ መንገዶች ስንከተል መቆየታችንን ህዝባችን ይገነዘባል።

አሁን ከአፍሪካ መሪዎችና ከዓለም ጤና ድርጅት (WHO) ጋር ባደረግነው ውይይት በሚቀጥሉት ሳምንታት በአፍሪካ ውስጥ ይሄ ወረርሽኝ አሁን በጀመረው አዝማሚያ ራሱን እያባዛ ከሄደና ወደ ማጥቃት ከተሸጋገረ የመከላከል አቅማችን በእጅጉ ሊፈተን እንደሚችልና አደጋውም ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል የመስጋትና ጥንቃቄ እንድናደርግ ምክር ለግሰዋል። ከዚህ አንጻር ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ ቢያንስ ቢያንስ በንክኪ እና በጽዳት ማነስ ምክንያት የሚያጋጥመውን አደገኛ የመጠቃት መንገድ ተከላክሎ እራሱን ማዳን ቢችል፣ መንግስት ወረርሽኙ መመከት የሚቻልበትን ቦታ ለማዘጋጀት ከመላው ህዝብ ጋር በመሆን ሰፊ ርብርብ እያደረገ ነው። በመሆኑም





"አደጋውን መቀነስ ይቻላል" የሚል ግምት ወስደን ነበር። ይሁንና ሕዝባችን ላይ የባህሪ ለውጥ እምብዛም መታየት ባለመቻሉ ስጋታችን ከፍተኛ ሆኗል።

በተለይ ህጻናት ታዳጊዎች ትምህርት ቤት እንዳትሄዱ በቤት እንድትቆዩ የተፈለገበት ዋናው ምክንያት ስትነካኩ፣ ስትጫወቱ ወረርሽኙ በቀላሉ ሊተላለፍባችሁና ከእናንተም አልፎ ወላጆቻችሁን ሊያጠቃ ስለሚችል መማራችሁን ብንፈልገውም ለመማር ብላችሁ ህይወታችሁ እንዳይቀጠፍ ካለን ጥንቃቄ የተነሳ በቤት እንድትቆዩ ለማድረግ ከተወሰነ ሰንበትበት ብሏል። ከእናንተ የሚጠበቀው የተሰጡ የጥንቃቄ ትምህርቶችን ማለትም መራራቅ እና መታጠብ አዘውትራችሁ መተግበር ይገባችኋል። በተጨማሪም ቤት በምታሳልፉት ጊዜ ብቃታችሁን በመጠቀም አዳዲስ ፈጠራዎችን ለማጎልበት እንድትነሳሱ ልመክራችሁ እፈልጋለው።

ይህ ተግዳሮት ያመጣብን ፈተና እንዳለ ሆኖ ለመፍጠር፣ ጭንቅላታችንን ለመጠቀምም የራሱ የሆነ እድል ስላለው "ትምህርት ፈትተን ተቀምጠናል" ብቻ ሳይሆን "እንዴት አድርገን ይሄንን ፈተና፣ ይሄንን ችግር በመመራመር ጭንቅላታችንን ተጠቅመን አዳዲስ ነገር ልንፈጥርና የማህበረሰቡን ችግር ልንቀርፍ እንችላለን" የሚለው ጉዳይ እንድታስቡበት፤ ጭንቅላታችሁን ለፈጠራ እንደትጠቀሙበት ላሳስባችሁ እፈልጋለው።

በትብብር ኮቪድ 19 የተባለውን ወረርሽኝ ማጥፋት ይቻላል። ታዳጊ ህጻናትንና ወጣቶችን መከላከል ትውልድ ማስቀጠል ስለሆነ፣ እናንተን ማዳን ሃገር ማስቀጠል ስለሆነ፣ ራሳችሁን የምትጠብቁ፣ ወላጆቻችሁን የምታስተምሩ፣ ጥንቃቄ የምታደርጉ እንድትሆኑ አደራ ለማለት እፈልጋለሁ።

ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሁለት ተማጽኖዎችን ማቅረብ እፈልጋለሁ። አንደኛው አንድ ቤተሰብ ለሌላ አንድ ቤተሰብ በቀን አንድ ምግብ ማካፈል የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ ይኖርብናል። ይህንንም ማእድ ማጋራት ብለን ልንጠራው እንችላለን። መንግስት በየቤቱ ምግብ ለማድረስ አቅሙም፣ የማድረጊያ መንገዱም ጠባብ ስለሚሆንበት፣ ወረርሽኙ ሰፋ ያሉ ሰዎችን እንዳያጠቃ እኛ በልተን ሌሎች በረሃብ እንዳይሞቱ ማድረግ ብንችል መልካም ነው። አንድ ቤተሰብ ለሌላ አንድ ቤተሰብ አንድ ምግብ በቀን የማቅረብ ዝግጁነት እንዲኖረው፣ በዚህም መድረክ ላይ ያላችሁት እንደ አንድ ቤተሰብ እንድትመካከሩና እንድትዘጋጁ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ሁለተኛው የዩኒቨርስቲ መምህራንና ተማሪዎች ትምህርት በመዘጋቱና ቤት በመቀመጣችሁ ምክንያት ጊዜ ትኩረት ስለምታገኙ ይኼንን አጋጣሚ በጥሩ እንድትጠቀሙበት አደራ እላለሁ። እንዴት አድርገን ከዚህ ችግር መሻገር እንደምንችል ልዩ ልዩ ምርምሮችን፣ ጥናቶችን እና የፈጠራ ስራዎችን በማዘጋጀት አዳዲስ ፈጠራዎችን እንድታሳዩ ይጠበቃል።

በተጨማሪም የጥበብ ሰዎች የተለያየ የጥበብ ስራ በመስራት ህዝቦቻችንን የምንከላከልበት፣ ተስፋን የምንሰንቅበት፣ የወደፊቱን ለማየት የሚይስችል መንገድ ለመፍጠር አጋጣሚውን እንድንጠቀምበት አደራ እያልኩ፤ ወረርሺኙ በሚቀጥለው ሳምንት ያለውን አካሄድ በማየት፣ ከሌሎች ሃገራት መሪዎች ጋር የምናደርገውን ውይይት በመቀጠል፣ ተጨማሪ እርምጃዎችን በመውሰድ፣ ሃገርና ትውልድን ለማስቀጠል ጥረት የምናደርግ ይሆናል።

ሃገር እና ትውልድ ማስቀጠል የግድ በሚባልባቸው ሁኔታዎች ሁሉ መንግስት አዳዲስ እርምጃዎችን እየወሰደ፣ ሃገርና ዜጎቹን የመከላከሉን





ሥራ አበክረን እንደምንሰራ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ። ይኸንን ወረርሽኝ በመደማመጥ፣ በመተባበር፣ በጋራ በመቆም፣ በመተጋገዝ የምናሸንፈው መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። ዛሬም እንደትላንቱ የሰው ልጅ ለወረርሽኝ የማይቆም፣ አሸናፊ መሆኑን ለማረጋገጥ እድል የሚሰጥ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን ነቅተን፣ ተባብረን፣ ከዚህ ጥቃት ሃገራችንንና ህዝባችንን እንድንከላከል አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

ፈጣሪ ህዝባችንን ሃገራችንን ይጠብቅ። በጸሎት በብርታት አብረን በመሆን ሃገራችንን እናሻግራለን፣ ኮሮና ቫይረስን እናሸንፋለን፣ ይህ እንዲሆን ህዝብ እና መንግስት በትብብር መንፈስ በጋራ እንድንቆም አደራ እላለሁ!!

**አመሰግናለሁ ! !**

# የፋሲካ በዓልን በማስመልከት የተላለፈ መልእክት

ሚያዚያ 9 ፤ 2012 ዓ.ም.

**እንኳን ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ በዓል አደረሳችሁ!**

የትንሣኤን በዓል ስናስብ ምንጊዜም በኅሊናችን የሚመጣ ነገር አለ። ከሕማማት በኋላ ደስታ፣ ከሞት በኋላ ትንሣኤ፣ ከጨለማ በኋላ ብርሃን እንደሚመጣ። ሕማማት፣ ሞትና ጨለማ ክርስቶስን አላሸነፉትም። ከሕማማቱ በኋላ ስለሚመጣው ደስታ፣ ከሞቱ በኋላ ስለሚመጣው ትንሣኤ፣ ከጨለማውም በኋላ ስለሚመጣው ብርሃን ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ አስቀድሞ ነግሯቸው ነበር።

ይህ ያለንበት ወቅት ለእኛ የተለየ ነው። ኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ - 19) ያለ ጦር መሳሪያ ዓለማችንን ወርሯል። ኃያላንን ለማንቀጥቀጥ ጊዜ አልፈጀበትም። በአጭር ወራት ውስጥ ሚሊዮኖችን ከመማረክ፣ መቶ ሺዎችን ከመቅጠፍ የሚያግደው ነገር አልተገኘም። በሀገራችንም ብዙ





ወገኖቻችን በቫይረሱ ተይዘዋል። አንዳንዶቹም ሕይወታቸው አልፏል። ወረርሽኙ እስካሁን በኢኮኖሚያዊ፣ በፖለቲካዊ፣ በማኅበራዊና በሐይማኖታዊ ሕይወታችን ላይ ካሳረፈብን ጫና ባልተናነሰ “ወደፊት ምን ዓይነት ፈተናና ችግር ይከተለን ይሆን” በሚል ስጋት የምናስተናግደው የስነልቦና ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። አሁን ከገጠመን የበለጠ ፈተና እንዳይገጥመን እንደ መንግሥትና እንደ ሕዝብ እስከምን ድረስ ራሳችንን ማዘጋጀት እንዳለብን ሁላችንም አንደ አንድ ልብ መክረን፣ ለተግባራዊነቱ መጽናት አለብን።

ከትንሣኤ የተማርናቸውን ትምህርቶች አሁን በኮሮና (ኮቪድ - 19) ምክንያት የገጠመንን ፈተና ለመወጣት ልንጠቀምባቸው ብንችል ውጤታማ እንሆናለን። የሕማማቱን ወቅት በሚገባ ተዘጋጅተው ካለፉት የትንሣኤውን ቀን እንደሚያዩ ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ነግሯቸው ነበር። አንዳንዶቹ እንደ ቅዱስ ዮሐንስ ለፈተናው በሚገባ ተዘጋጅተው ስለነበር ጽናታቸው ፈተናውን በድል እንዲወጡ አስችሏቸዋል። እኛም ዛሬ የሚጠበቅብን ይሄው ነው። ኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ -19) ለሚያስከትለው ሀገራዊ ፈተናና ችግር በሚገባ ከተዘጋጀን ያለ ከባድ ጫና ልንወጣው እንችላለን።

ፈተናውን የምናልፈው በዝግጅታችን መጠንና ለተግባራዊነቱ በምናሳየው ጽናት ልክ ነው። ዮሴፍ ከረሀቡ ዘመን በፊት በሚገባ ስለተዘጋጀ በሰባቱ የረሐብ ዘመናት ምግብ ለዓለም ለማከፋፈል በቅቷል። እኛም በተግባርም፣ በእምነትም ከተዘጋጀን ይሄንን ሕማማት አልፈን እስከ ትንሳኤው መጽናታችን፣ ብርሃኑንም ለማየት መብቃታችን አይቀሬ ነው። ያለጥርጥር አሁን ያለንበት የወረርሽኝ ጊዜ ያልፋል።

ሳንታገለውም ማለፉ አይቀርምና የምንታገለው እንዲያልፍ ብቻ አይደለም። የምንታገለው ወረርሽኙ በብዙ ሳይጎዳን እንዲያልፍ ጭምር ነው። የሕማማቱ ጊዜ ረዥም እንዳይሆን ነው። የትንሣኤው ጊዜ እንዲቀርብ ነው።

ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ለሐዋርያት የተገለጠላቸው በአንድ ቤት ውስጥ ዘግተው ተቀምጠው በነበረበት ጊዜ ነው። ዙሪያቸው በፈተና የተሞላ ስለነበር፣ በውጭ ፈታኞቻቸው ቆመው ስለነበር፣ ሁሉም በቤታቸው ውስጥ ዘግተው ተቀምጠው ነበር። ይህ ጊዜ እኛም እንደነሱ ዘግተን የተቀመጥንበት ጊዜ ነው። ፈታኙ ወረርሽኝ እንደ ሁልጊዜው ከወዲያ ወዲህ እንዳንል፣ እንደፈለግን ወጥተን እንዳንገባ፣ በሙሉ አቅማችን እንዳናመርት፣ ነግደን እንዳናተርፍ ጋሬጣ ሆኖብናል። ሐዋርያቱ በዚያ በፈተናቸው ወቅት በራቸውን ዘግተው በጸሎት ይተጉ እንደነበረው፤ እኛም በዚህ ወረርሽን ጊዜ አካላዊ ፈቀቅታን ጠብቀን፣ ከብዙ ንክኪና ወረርሽኙን ከሚያስፋፉ እንቅስቃሴዎች ተቆጥበን፣ የፈተናው ጊዜ እስኪያልፍ ድረስ በየቤቶቻችን ተወስነናል።

በተዘጋው የሐዋርያት ቤት ገብቶ ‹ሰላም ለእናንተ ይሁን› ያለው ጌታ የሰላሙን ጊዜ እንደሚያቀርበው እናምናለን። የሞቱን ዜና ቀርቶ ትንሣኤውን፣ የጨለማው ወሬ ቀርቶ የብርሃኑን፣ የሕማማቱ ነገር ቀርቶ የደስታውን ነገር የምንነጋገርበት ጊዜው ሩቅ አይደለም። ማድረግ ያለብንን ሁሉ ካደረግን፣ የመከራውን ጊዜ እናሳጥረዋለን። ማድረግ ያለብንን ካላደረግን ግን የመከራው ጊዜ ይረዝማል።





አሁን ያለንበት ጊዜ ከኀሙስ ምሽት እስከ ቅዳሜ እኩለ ሌሊት ያለውን ሰዓት ይመስላል። የችግር፣ የብዥታ፣ የጥርጣሬ ጊዜ ነው። ጽናትና ጥንካሬያችን፣ መልካምነትና ተባባሪነታችን፣ አንድነትና ወንድማማችነታችን የሚፈተንበት ወቅት ነው። አንዳንዶች እንደ ቶማስ የተነገራቸውን ይረሳሉ፤ አንዳንዶች ለሚያልፍ ጊዜ የማያልፍ ስሕተት ይሠራሉ፤ አንዳንዶች እንደ ዮሐንስ እስከ መጨረሻው ጸንተው ይገኛሉ፤ ሌሎቹ "የለንበትም" ብለው ጥለው ይሸሻሉ። አንዳንዶቹ የሚወራው ወሬ ከእውነታው በልጦ ይወስዳቸዋል፤ ሌሎቹ በሐሰተኛ ወሬዎች ሳይበገሩ ከእውነት ጋር ይቆማሉ። አንዳንዶች ጣት በመጠቆምና በጸያፍ ቃላት በማንቋሸሽ ሲጠመዱ፣ ሌሎቹ ከመከራው ቀንበር ለመሸከም ትከሻቸውን ያዘጋጃሉ፤ አንዳንዶች እንደ ይሁዳ ከእንግልቱ ለማትረፍ ይሞክራሉ፤ ሌሎች የሕዝቡን መከራ ለመካፈል እንደ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ይመጣሉ።

በየዓመቱ በምንዘክረው በዚህ የትንሳኤ ሰሞን ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት፣ ብዙዎች የዚያ ሁነት ተካፋዮች ነበሩ። አቅማቸው እየፈቀደ ባለመፈለግ እጃቸውን የሰበሰቡ ሰዎች ተረስተው ሲቀሩ፤ ተገቢውን ነገር በተገቢው ጊዜ ያደረጉት ሰዎች ታሪካቸው መልካም ይነሳል። ሌላው ቀርቶ ፀሐይ በተገቢው ጊዜ ጨልማ፣ ጨረቃም በተገቢ ጊዜ ደም በመልበሷ ስለትንሣኤው ሲነገር ተያይዞ ያ ታሪካቸው በመልካም ይወሳል። ለመልካም ተግባር እምቢታቸውን ላሳዩና አብዝተው ለከፉትም ታሪካቸው ክፉ ተግባራቸውን ጮሆ ይተርካል።

ዛሬ፣ በታሪክ አጋጣሚ ለዘመናት ስማችን ከመልካም ወይም ከክፉት ጋር ተያይዞ እንዲነሳ የሚያስገድድ ታላቅ የተጋድሎ አጋጣሚ ላይ

ደርሰናል። አሁን ያለንበት የወረርሽኝ ጊዜ፣ ወቅቱ የሚፈልገውን ሥራ በተገቢው ቦታና ሰዓት አከናውነን፣ ተጋድሏችንን በድል ለመወጣት መወሰን ያለብን ወሳኝ ወቅት ላይ ነን። ዛሬ መናገር ያለብንን ነገር እንደ ሮማዊው መቶ አለቃና እንደ ጲላጦስ ሚስት እንናገረው፤ ዛሬ ለሌሎች ማድረግ ያለብንን እንደ አልዓዛር እናድርገው፤ ዛሬ ደፍረን መወሰን ያለብንን ነገር እንደ መግደላዊት ማርያም እንወስነው። ይህን ማድረግ ተስኖን፣ ትክክለኛውን ተግባር በትክክለኛው ጊዜ መፈጸም ካልቻልን በታሪክ መዝገብ ላይ ጥላሸት የተቀባ ስማችን ታትሞ እንደሚኖር ምንም ጥርጥር የለውም። መልካም የሚሰራውን ሰው ጎትቶ ለመጣል የሚዘረጉ እጆች፣ ለማንጓጠጥ የሚያፈጡ ዐይኖች፣ ለመሳደብ የሚከፈቱ አንደበቶች ከድል ማግስት በታሪክ ሚዛን ላይ ትክክለኛ ዋጋቸው ሲሰፈር ይኖራል።

አሁን ተጋድሏችን ከዓርብ እስከ ቅዳሜ ሌሊት ያለው ጊዜ እንዲያጥር ነው። የትንሣኤው ዘመን ከመከራው ዘመን ይረዝማል። የመከራው ዘመን ቅዳሜ ሌሊት ሲደመደም፣ የትንሣኤው ዘመን ግን እስከ ዓለም ፍጻሜ ይኖራል። ከላይ እስከታች፣ በየተሠማራንበት መስክ፣ በተሰጠን ኃላፊነት፣ ባገኘነው ዕውቀት የሚገባንን ከሠራን፣ የችግሩ ጊዜ የከፋ ጉዳት ሳያመጣ በአጭሩ ያልፋል። የኢትዮጵያ የትንሣኤዋ ዘመንም ይረዝማል። በመከራዋ ዘመን ካጨደችው አበሳ በላይ በትንሳኤዋ ዘመን የምትሰበስበው ሀሴት ይበዛል፤ በጭለመዋ ወቅት የነገሰውን ጽልመት የሚሽር ደማቅ ብርሀን ይፈልቃል። የትንሳኤ ብርሃንዋ ሲፈነጥቅ በሕማምዋ ወቅት የታመሙ ይድናሉ፤ በድካሟ ወቅት የደከሙ ይበረታሉ፤ ጸንተው የታገሉ የድሉን ጽዋ ቀምሰው ይረካሉ።





ደግሞም እናምናለን። ፈጣሪ የሕዝባችንን ጸሎት ይቀበላል። ለሕክምና ባለሞያዎቻችን ጥበቡን፣ ግንባር ቀደም ሆነው ለተሰለፉ ጀግኖቻችን ኃይልና ብርታቱን፣ ትግላችንን እያገዙ ላሉ ደጋግ ልቦች ሁሉ በረከቱን፣ በቫይረሱ ለተያዙት ድኅነቱን፣ በወረርሽኙ ምክንያት ለተጎዱት ጽናቱን እርሱ ያድልልን። አሜን!

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና**
**ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# ለታላቁ የረመዳን ወር የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት

ሚያዚያ 14፣ 2012 ዓ.ም.

ስለ ታላቁ የረመዳን ወር ሲነሳ ተያይዞ የሚጠቀስ ነገር አለ። ረመዳን ከምግብና ከመጠጥ ቀኑን ሙሉ ራስን በመቆጠብ መንፈሳዊ ኃይል የሚገኝበት ድንቅ ወር ነው። ሙስሊሞች ከምንጊዜውም ይልቅ በረመዳን ወር ለፈጣሪያቸው ይቀርባሉ፤ አብዝተው ይጸልያሉ፤ ዘካት ይሰጣሉ። ጾበኞች አኡፍ ተባብለው ወሩን በመንፈሳዊነት ያሳልፉታል። በረመዳን ወር ከፋት ተንቆ መልካምነት ይነግሳል፤ ጭካኔ ጠፍቶ እዝነት ይበዛል። በሰው ልጆች ልብ ውስጥ ደግነት፣ ሩህሩህነት፣ ይቅር-ባይነትና አብሮነት በእጅጉ ይጠነክራል።

የረመዳን ወር፣ በሙስሊሞች የቀን መቁጠሪያ በዘጠነኛው ወር የሚውል የተቀደሰ፣ የጾም፣ የጸሎት እና የመንፈሳዊነት ወር ነው። ከአምስቱ የእስልምና መሰረቶች መካከል ሰላትን ከመስገድ፣ እምነትን ከማወጅ፣ ዘካ ወይም ምጽዋት ከመስጠት፣ መንፈሳዊ ጉዞ ‹ሀጅ› ከማድረግ ባለፈ በረመዳን ወር መጾም አንደኛው የእስልምና መሰረት





በመሆኑ፣ ዓለም ላይ የሚኖር ሙስሊም ሁሉ ረመዳንን በጾምና በጸሎት ያሳልፋል። ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንደ ተናገሩት በረመዳን ወር፣ የገነት በሮች ሁሉ ይከፈታሉ፤ የሲኦል በሮች ይዘጋሉ፤ ሰይጣኖችም ይታሰራሉ። ፈጣሪ፣ በዚሁ የረመዳን ወር ቅዱስ ቁርዐንን ለነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በቅዱስ ጅብሪል አማካኝነት ያወረደበት የተቀደሰ ወር ነው። ይህ ጊዜ ‹ላይላት አል-ቃድር› ይባላል። ‹የኃይል ሌሊት› እንደማለት ነው። መንፈሳዊነት የሚበረታበት፣ መልካምነትና ደግነት ጉልበት የሚያገኙበት፣ ሰዎች በጸጋና በጥንካሬ ወሩን የሚያሳልፉበት ወቅት ነው።

በዚህ ሰዓት ዓለም ላይ በኮሮና ወረርሽኝ (ኮቪድ -19) ብዙዎች አቅማቸው እየተዳከመ፣ ጉልበታቸው እየከዳቸው፣ በሞትና በህመም ጎርፍ ውስጥ እየተንገላቱ እንደሆነ ይታወቃል። በእኛም ሀገር ጥቂት የማይባሉ ወገኖቻችንን ቫይረሱ ቀጥፎብናል፤ የተያዙትም በመቶዎች መቆጠር ጀምሯል። የተቀረውም ሕዝባችን “ከዛሬ ነገ ወረርሽኙ እኔም ቤት ይገባ ይሆን” በሚል ስጋት እየተሰቃየ ነው። በዚህ አስቸጋሪ ወቅት የተቀደሰውን የረመዳን ወር ስንቀበል መልዕክቶቻችን ‹እንኳን አደረሰህ፣ እንኳን አደረሰሽ› በሚል ብቻ መወሰን የለባቸውም። ሁላችንም ከቁጥር ሳንጎድል ለመጭው የዒድ አልፈጥር በዓል መድረስ እንድንችል የጥንቃቄ መልዕክቶችንን መለዋወጥ ይገባናል።

ኮሮናን የመከላከያው የመጀመሪያው መንገድ ስለ በሽታው በቂ ግንዛቤ ማግኘት በመሆኑ በአራቱም አቅጣጫ የሚኖረውን የሀገራችንን ህዝብ ማሳወቅና ማንቃት ከእያንዳንዱ ሙስሊም ይጠበቃል። በተጨማሪም ከረመዳን ወር የምናገኛቸውን እሴቶችና ትምህርቶች በሚገባ

ከተገበርናቸው ወረርሽኙን ለመከላከልና ለማጥፋት የበለጠ ጉልበት እንደምናገኝ አልጠራጠርም።

የረመዳን ወር ከብዙ ነገሮች የምንታቀብበት፣ የጸሎትና የጾም ወቅት ነው። ከሥጋዊ ተግባራት ይልቅ ለመንፈሳዊ ተግባራት ትኩረት የምንሰጥበት፣ ሰፊው ቀናችንን በቤታችን ሆነን ቅዱሳን መጻሕፍትን በማንበብ፣ ዚክርን አብዝተን በማድመጥ የምናሳልፍበት ወር ነው። ይሄኛው እሴት የኮሮና ወረርሽኝን ለመከላከል ከተቀመጠው መፍትሄ ጋር በእጅጉ ይገጥማል። ብዙ ሰዎች ከሚሰበሰቡበት ቦታ፣ እንቅስቃሴዎች ከሚደምቁበት ሥፍራ ገለል ብለን ራሳችንና ሌሎችን ከዚህ ወረርሽኝ ለመጠበቅ እንችላለን።

የረመዳን ወር ሌላኛው ትልቅ እሴት ‹ዘካ› እና ‹ሰደቃ› ማድረግ ነው። ለሌሎች በማካፈል ከፈጣሪ ጸጋ የምናገኝበት ትልቁ እሴት ነው። ህዝበ ሙስሊሙ፣ በታወቀ ተመን ከሀብቱ ላይ ቀንሶ ለተቸገሩ ወገኖቻችን ዘካ የመስጠት ልማድ አለው።

ከዚህም ባለፈ በተለያዩ መንገዶች ሰደቃ ያደርጋል። ይህ በጎ ተግባር ለተቀባዩ ከሚሰጠው የኑሮ ድጋፍ በላይ ለሰጭው የሚያስገኘው መንፈሳዊ እርካታና ለማህበረሰባዊ ግንኙነት መጠናከር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እጅግ የጎላ ነው። የሀይማኖቱ ታላላቅ ሊቃውንት እንደሚነግሩን “ዘካን ከረመዳን ውጭም ልናደርገው እንችላለን፤ ረመዳንን ግን ከዘካ ውጭ ልናደርገው አንችልም።” ይህ ወቅት ዘካና ሰደቃ እጅግ የሚያስፈልጉበት ጊዜ ነው። በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት እንደልባቸው ሮጠው የእለት ጉርሳቸውን የማያገኙ፣ ቀኑን ሙሉ ጾመው አመሻሽ ላይ ለአፍጥር የሚቸገሩ አነስተኛ ኑሮ ያላቸው





ወገኖቻችን በዙሪያችን ሞልተዋል። ዐይናችንን ገልጠን ከተመለከትን ከወረርሽኙ ባልተናነሰ እንዳሻቸው መስራት ባለመቻላቸው ምክንያት ርሀብ የሚጎበኛቸው ድኩማን በየመንደራችን አሉ። ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) «ውኃ እሳትን እንደሚያጠፋ ሁሉ፥ ልግስናም ክፋትን ከልብ መደምሰሻ ናት» ብለው እንደተናገሩት፣ የዚህ ዓመት ዘካችንና ሰደቃችን ለእነዚህ ወገኖች በማድረስ የክፋትን እሳትና የበሽታን ሸክም እንደምስስበት።

ለሺህ ዘመናት የቆዩ መልካም እሴቶች እያሉን በዚህ አስቸጋሪ ወቅት አንድም ኢትዮጵያዊ መቸገር የለበትም። በረመዳን ወር፡ ንግዳቸው የቀዘቀዘባቸውን፣ ለቤት ኪራይ የሚከፍሉት ያጡትን፣ ልጆቻቸውን መመገብ የከበዳቸውን፣ የንጽህና መጠበቂያ መግዛት ያልቻሉትን የምናግዝበት ይሁን። ረመዳን የመጣው በሚያስፈልገን ጊዜ ነውና ለወቅታዊው ችግራችን መፍቻነት እንጠቀምበት።

የረመዳን ወር መንፈሳዊነት ብቻ ሳይሆን ማህበራዊነትም ጠንክሮ የሚወጣበት የተባረከ ወቅት መሆኑ ግልጽ ነው። ቤተሰቡ፣ ሠፈር መንደሩ፣ የቅርብ የሩቁ ሁሉ ለኢፍጣር ይሰባሰባል። ረመዳን ለብቻ ማፍጠር ሠርግን ለብቻ ከማድረግ በላይ ከባድ መሆኑ ሁሉም ሰው የሚገነዘበው ሐቅ ነው። በሌላ በኩል የኮሮና ወረርሽኝ (ኮቪድ -19) ለብዙ ነገሮች ተቃራኒ ሆኖ መጥቷል። መሰባሰብን፣ መጨባበጥን፣ መቀራረብን፣ እንደ ጥሩ መሳሪያ ተጠቅሞ ወረርሽኙ ከዓለም ጫፍ እስከ ጫፍ እየተስፋፋበት ይገኛል። ስለሆነም መልካም እሴታችንን በነጻነት እንዳንተገብር እንቅፋት የሆነብንን ወረርሽኝ በጥንቃቄና በመተባበር እንደምናሸንፈው አልጠራጠርም።

በዚህ የተቀደሰ የረመዳን ዋዜማ ላይ ቆሜ ሕዝበ-ሙስሊሙና የተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ በዚህ ወረርሽኝ ላይ የሚያደርገውን የጋራ ትግል አጠናክሮ እንዲቀጥል በድጋሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ። የመላ ኢትዮጵያውያን ጸሎትና የጋራ ጥረታችን የመከራችንን ጊዜ ያሳጥረዋል። ጾም፣ ጸሎትና ትብብር ለሚነግስበት የረመዳን ወር እንኳን አደረሰን!

**ረመዳን ከሪም!**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**





# በኮሮና ወቅት ስለምርጫ የተደረገ ንግግር

ሚያዚያ 29፣ 2012 ዓ.ም.

## ክቡራን እና ክቡራት ኢትዮጵያዊያን!

በዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ጎልተው ከወጡ የህዝብ ፍላጎቶች አንዱ ህዝብ የሚሳተፍበት እና የሚሰማበት የአስተዳደር ሂደት በሌላ አነጋገር “ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት” የመገንባት ፍላጎት ነው። ይህ ፍላጎት ከዘመን ወደ ዘመን እያደገ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ ዛሬ ላይ ደርሷል። በዚህ ባለንበት ዘመን እና ትውልድ ይህ ፍላጎት እውን ሆኖ ዲሞክራሲያዊ ሃገር እንድንገነባ ትልቅ ፋይዳ እንዲሮረው የሚያደርገው አንዱ ኩነት ቀጣዩ ጠቅላላ ሃገራዊ ምርጫ መሆኑ ግልጽ ነው። ለዚህም ነው ይህ ምርጫ በብዙዎች በጉጉት እየተጠበቀ የነበረው።

አንዳንድ ፓርቲዎች እና ልሂቃን “ምርጫው መደረግ የለበትም” የሚል አቋም በያዙበት ጊዜ መንግስት ምርጫው በጊዜው መደረግ እንዳለበት አምኖ በቁርጥ ሲዘጋጅ የነበረው የምርጫውን ሃገራዊ ፋይዳ በሚገባ በመረዳት እና በማመን ነበር። ሆኖም በኮቪድ 19 ወረርሽኝ መከሰት የተነሳ ይህ ምርጫ ቀድሞ በተያዘው ሰሌዳ ማካሄድ እንደማይችል በየደረጃው ላሉ ምክር ቤቶች የሚደረገውን የሃገሪቱን ምርጫ

ለማከናወን በህግ ብቸኛው ስልጣን የተሰጠው የምርጫ ቦርድ መጋቢት 22/2012 ዓ.ም መሰረት አስታውቋል።

በዚህም የተነሳ ምርጫውን ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ የግድ ሆኗል። ከኮቪድ የተነሳ የምርጫ መተላለፍ ደግሞ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም በብዙ ሃገራት እየተከሰተ ያለ እውነት ነው። ከዚህ በተቃረነ መልኩ ምርጫ ላለማስተላለፍ ወይንም ላለማሸጋገር ወስኖ ፕሬዝዳንታዊ ምርጫን ሙሉ በሙሉ በፖስታ ለማድረግ እንዲሆን የወሰነው የፖላንድ መንግስት ከሃገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ከፍተኛ ውግዘት ደርሶበታል። የሃገሪቱ የዲሞክራሲ ተቋማት፣ የአውሮፓ ህብረት እና ተፎካካሪ ፓርቲዎች የዜጎችን ደህንነትን ለማስጠበቅ እና የዜጎችን ነጻና ፍትሃዊ ለማድረግ መተላለፍ እንዳለበት እየሞገቱ ነው።

ከፖለቲካዊ ምርጫዎች በተጨማሪ በኮቪድ 19 ምክንያት የዓለም ከፍተኛ ስፖርት የሆነው እና ዘንድሮ በጃፓን የሚዘጋጀው ኦሎምፒክ ለአንድ ዓመት ተራዝሟል። ዘመናዊ ኦሎምፒክ ከተጀመረበት ከ1896 ጀምሮ ኦሎምፒክ ተቋርጦ የሚያውቀው በአንደኛው እና በሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች ምክንያት ብቻ ነበር።

ኮሮና በዓለም ላይ አሁን የደረሰበትን ደረጃ ይህ ሁኔታ በግልጽ ያመላክታል። እንዲሁም በዱባይ ሊደረግ ታቅዶ በብዙ ቢሊየን ዶላሮች የተዘጋጀው እና ለስድስት ወራት ይቆይ የነበረው የዓለም ኤክስፖም ለአንድ ዓመት ተሸጋግሯል።

የምርጫ ቦርድ ምርጫውን በተያዘለት ጊዜ ማካሄድ እንደማይችል ከገለጸበት ከመጋቢት መጨረሻ ጀምሮ መንግስት የተለያዩ አማራጮችን በታወቁና በበሰሉ ባለሞያዎች ሲያስጠና ነበረ። በሦስት ቡድን





ተከፋፍለው አንዳቸው ከሌላኛው የማይገናኝ ቡድን መስርተው ባለሞያዎቹ በዝርዝር አጥንተዋል። ከሪፖርቱ እንደተረዳነው የሃገሪቱ ህገ-መንግስትና ሌሎች ህጎች፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና የሌሎች ሃገሮች ልምዶችን በሚገባ ተመልክተዋል።

በመጨረሻም የተለያዩ አማራጮችን ይዘው በአንድነት በመገናኘት የተቀራረቡ የሃሳብ አማራጮችን አቅርበዋል። ባለሞያዎቹ ያቀረቧቸውን አማራጮች በመያዝ ምርጫው ሊተላለፍ የሚችልበትን ህጋዊ አግባብ በተመለከተ ከልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት እና ምክክር ተደርጓል።

የፌደራሉ መንግስት ከፍተኛ የስልጣን አካል የሆነው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ ህገ መንግስታዊ ትርጓሜ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለህገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ መርቶታል። በዚህ መልኩ በህግ አውጪው የሚቀርብ የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ በብዙ ሃገራት የተለመደ ህገ መንግስታዊ ሃሳቦችን ወደ መሬት ማውረጃ መንገድ ነው። ለምሳሌ በፈረንሳይ የህገ መንግስት ካውንስል የሚባለው የሃገሪቱ ህገ መንግስት ተርጓሚ ብዙ ጉዳዮችን የሚያየው በሃገሪቱ ፓርላማ እየተመራለት ነው። የኛም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያደረገው ይሄንኑ ነው።

በኮቪድ 19 የተነሳ 6ተኛው ሃገራዊ ጠቅላላ ምርጫ በታቀደለት ጊዜ ሊካሄድ እንደማይችል የምርጫ ቦርድ ካስታወቀ በኋላ ምላሽ የሚፈልጉ ህገመንግስታዊ ጉዳዮችን በተመለከተ የቀረቡ አማራጮች ለህዝብ ይፋ ሆነዋል። አማራጮቹ ይፋ ከሆኑ በኋላ ጉዳዩ የህዝብን አትኩሮት የሳበ መነጋገሪያ አጀንዳ ሆኗል። በዚህ ጉዳይ ላይ ከህዝቡ፣ ከህግ ባለሞያዎች እና ከተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰቦች የተለያየ አስተያየቶች

እየቀረቡ ይገኛሉ። በጉዳዩ ላይ የሚቀርቡት ዋና ዋና አስተያየቶች በሶስት ሊከፈሉ ይችላሉ።

- **አንደኛው** - ህጋዊ ወይንም ህገ መንግስታዊ መፍትሄ እንደሚቀበሉ፣ ነገር ግን ከህገ መንግስት ውጪ ያሉ ህገ መንግስታዊ አማራጮችን የሚያቀርቡ፤
- **ሁለተኛ** - ህገመንግስታዊ ትርጓሜን የተሻለ አማራጭ አድርገው የሚያቀርቡ፤
- ሦስተኛ - "በህጋዊ አካሄድ ሳይሆን በፖለቲካ መፍትሄ የሚፈታ ነው" የሚሉ፣ ለዚህም "የሽግግር መንግስት መቋቋም ወይንም ተፎካካሪ ፓርቲዎችን ያቀፈ መንግስት ፖለቲካዊ መፍትሄ ነው" ብለው የሚከራከሩ ናቸው።

የመጀመሪያውን ሃሳብ የሚያራምዱት የተወሰኑ የህግ ባለሞያዎች አንዳንዶቹ ምርጫን በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማራዘም እንደሚቻል እና የተሻለው አማራጭ ይህ እንደሆነ ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል። በዚህ መልክ ምርጫው በመተላለፉ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት እስከ ቀጣዩ ምርጫ በስራ ላይ የሚቀጥል እንደሆነ እነዚህ የህግ ባለሞያዎች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። በሌላ በኩል አንዳንድ ፓርቲዎች እና የህግ ባለሞያዎች ደግሞ ህገ-መንግስታዊ ማሻሻያ የተሻለ አማራጭ ነው ብለው መከራከሪያ ያቀርባሉ።

መንግስት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ብቻውን ብዙ ርቀት መሄድ እየቻለ ወይንም በቀላሉ ህገ መንግስታዊ ማሻሻያ ማድረግ እየቻለ ጉዳዩን ለምክክር እና ለውይይት ማቅረቡ አሳታፊ የሆነ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት





ለመገንባት ያለውን ቁርጠኝነት በግልጽ ያሳያል። በዚህ ሂደት ቀደም ተብሎ የተገለጹትን ዓይነት በህገ መንግስታዊ ማእቀፍ ውስጥ ያሉ ገንቢ አስተያየቶች፣ ግብአቶች እና ትችቶች እየቀረቡ ላሉ ሁሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

እንዲህ ያሉ ምክንያታዊና በህግ ላይ የተመሰረቱ ውይይቶች እና ክርክሮች ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ትልቅ አስተዋጽኦ አላቸው። የሃሳብ ፍጭት በጠረጴዛ ዙሪያ፣ በአንደበት እና በብዕር ከተደረጉ ሃገር ይገነባሉ። ለጥፋት መቀስቀሻ እና ለደም ማፍሰሻ ከዋሉ ግን የስልጣን ጥመኞችን ያፈራሉ። ወደ ሁለተኛው ሃሳብ ስንመጣ ህገ መንግስታዊ ትርጓሜ የተሻለ አማራጭ እንደሆነ ሃሳባቸውን በተለያዩ የመገናኛ ሚዲያ እየገለጹ ያሉ የህግ ባለሞያዎች እና ሌሎች ሃሳብ አቅራቢዎች አሉ።

ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ከሲቪክ ማህበራት ጋር በነበረን ውይይትም የህገ መንግስታዊ ትርጓሜ መጠየቅ በብዙ ፖለቲካ ፓርቲዎች የተሻለ ተቀባይነት ያገኘ አማራጭ እንደሆነ ለማየት ችለናል። "ይህ አማራጭ የተሻለ ነው" የተባለው ዛሬ በገጠመን ፈተና ብቻ አይደለም። "ለወደፊቱም ህገ መንግስታዊነትን በሃገራችን እንዴት ልናጎለብት እንችላለን?" የሚለውን በማሰብ ጭምር ነው።

ከእኛ ህገ መንግስት ተቀራራቢ እድሜ ያለው የደቡብ አፍሪካ ህገ መንግስት በህገ መንግስት ትርጓሜ ዳብሮ ከአፍሪካ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጠቃሽ ህገ መንግስታዊ ሥርዓት ሆኗል። በጎረቤታችን ኬንያ አስር ዓመት ብቻ ያስቆጠረው ህገ መንግስት በትርጉም እየደረጀ ለጥናት እና ምርምር የሚፈለግ ሥርዓት ሆኗል።

ይህ አጋጣሚ እኛም ህገ መንግስታዊ ሥርዓታችን በትርጓሜ የምናዳብርበት አዲስ ምእራፍ ይከፍትልናል። ጀርመን፣ ህንድ፣ አሜሪካ፣ ኮሎምቢያ፣ ካናዳ ግንባር ቀደም ህገ መንግስታዊ ሥርዓት ተደርገው የሚቆጠሩት በህገ መንግስት ትርጓሜ ህገ መንግስቶቻቸው እንደ ሰነድ ያሉባቸውን ክፍተቶች ለመሙላት ስለቻሉ ነው።

ወደ ሦስተኛው ሃሳብ ስንመጣ በዋነኛነት እንደ መፍትሄ ተደርጎ የሚቀርበው የሽግግር መንግስት አማራጭ ነው። አማራጭ ተደርገው የሚቀርቡት መከራከሪያዎች ደግሞ “የገጠመን ህገ መንግስታዊ ቀውስ ነው፤ ህገ መንግስቱ ለዚህ መልስ የለውም፤ ምንም ዓይነት ምርጫን የሚያራዝም መንገድ በህገ መንግስቱ የለም። ለህገ መንግስታዊ ትርጉም መነሻ የሚሆንና ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ህገ መንግስታዊ አንቀጽ የለም”።

“ህገመንግስታዊ ትርጓሜም ሆነ ማሻሻያ የብልጽግና ፓርቲ ሙሉ በሙሉ በሚቆጣጠራቸው ምክር ቤቶች የሚተገበሩ ስለሚሆኑ ገለልተኛ ባልሆኑ አካል ተግባራዊ ከተደረጉ ተቀባይነት የሌላቸው መፍትሄዎች ናቸው” የሚል, እንዲሁም “ገዢው ፓርቲ የሚቆጣጠራቸው የምክር ቤት ወንበሮች ነጻና ዴሞክራሲያዊ በሆነ ምርጫ ያገኘው አይደለም፤ ስለዚህም ከመጀመሪያውም ቅቡልና ያለው መንግስት አይደለም፤ ከመስከረም በኋላ ደግሞ ምንም አይነት ቅቡልነት እና ህጋዊ መሰረት የሌለው፣ ዓለም አቀፍ እውቅናም የማይኖረው፣ መንግስት ይሆናል” የሚል መከራከሪያ ነው።

እነዚህ መከራከሪያዎች መቅረባቸው እና የውይይት አጀንዳዎች መሆናቸው ለሃሳብ ፍጭቶች እና ለሰላ መፍትሄ መገኘት እጅግ ጠቃሚ ናቸው። የቀረቡት አማራጮች ግን በአግባቡ መመርመር





ይጠበቅባቸዋል። “ህገ መንግስቱ ለዚህ ጉዳይ የሚሆን መፍትሄ የለውም” የሚለው መከራከሪያ ያላየው ቁም ነገር አለ።

በመጀመሪያ ደረጃ እጅግ ብዙ ቁጥርና ሰፊ ልምድ ያላቸው የህግ ባለሞያዎችና ምሁራን አማራጮች አሉ። ወይም አማራጮች የራሳቸው የሆነ ውስንነት ያላቸው ቢሆንም አሉ። እያሉ በጉዳዩ ላይ ምንም ምርምርና ጥናት ያላደረጉ፣ ባለሞያም ያልሆኑ ሰዎች በድፍረት ህጋዊ መፍትሄ የሌለው ችግር ነው ማለታቸው ምኞታቸውን እንጂ እውነታውን አያሳይም። ከዚያም ሲያልፍ “ነገሩ መድሃኒት የለውም” ሲልህ “መድሃኒቱ እኔ ጋር ብቻ ነው” ማለቱ ነው እንደሚባለው ሆኖ እናገኘዋለን።

አስቀድመው ነገሩ በህገ መንግስታዊ አጣብቂኝ እንደተፈጠረ፣ ህጋዊ መፍትሄም የሌለው ቀውስ ያደርጉታል። ቀጥለውም ራሳቸውን መፍትሄና መድሃኒት አዋቂ አድርገው ያቀርባሉ። “ህጋዊ መፍትሄ የለም” ማለታቸው ህጋዊ መፍትሄን አንፈልግም ማለታቸው ነው። “ህጉ በአቋራጭ ስልጣን እንድንቆናጠጥ አያደርገንም” ማለታቸው ነው። እንደሚታወቀው ማንኛውም ህገ መንግስት ሰፊና ጥልቅ ሃሳቦችን የያዘ ነው።

ህገ መንግስቱ የያዛቸው አንቀጾችና አንቀጾቹ የተዋቀሩባቸው መሰረታዊ ሃሳቦች አሉ። “ህገ መንግስት እና ህገ መንግስታዊነት” ወይም (Constitution and constitutionalism) ሁለት የተሳሰሩ፣ ግን የየራሳቸው ትርጉም ያላቸው ጽንሰ-ሃሳቦች ናቸው። “ህገ መንግስት” የተጻፈ ነው፤ “ህገ መንግስታዊነት” ግን ሥርዓት ነው። “ህገ መንግስታዊ መፍትሄ” ማለት ከሁለቱም የሚገኝ መፍትሄ ነው። የህገ መንግስት ትርጓሜ ህገ መንግስታዊ መፍትሄ የማዋለድ ስራ ነው። ለምሳሌ

የደቡብ አፍሪካ ህገ መንግስት ስለሞት ቅጣት ምንም አያወራም። በዚህ ጉዳይ ላይ ህገ መንግስታዊ አቋም ምን እንደሆነ ሃገሪቱ ላይ ህገ መንግስታዊ ፍርድ በሰጠው ህገ መንግስታዊ ትርጓሜ ምላሽ ለማግኘት ችሏል።

በኮሎምቢያ “አንድ ፕሬዝዳንት ከአንድ የስልጣን ዘመን በላይ ማገልገል ይችላል” የሚለውን ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ “ማሻሻል ይቻላል ወይስ አይቻልም?” የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ በቀጥታ የሚለው ነገር ባይኖርም፣ ጉዳዩ በህገ መንግስት ትርጓሜ ምላሽ ማግኘት ችሏል። በሃገረ አሜሪካ ህገ መንግስቱ ስለጤና ኢንሹራንስ ወይም “ኦባማ ኬር” የሚለው ምንም ነገር የለም።

እንዲሁም ህገ መንግስቱን የመተርጎም ሥልጣን የማን እንደሆነ እንኳን ህገ መንግስቱ በቀጥታ የሚለው ነገር የለም። ነገር ግን እነዚህና ሌሎች መሰል ወሳኝ ጥያቄዎችን በትርጉም ምላሽ መስጠት ተችሏል።

በሰሞኑን ክርክር ለህገ መንግስታዊ ትርጉም መነሻ የሚሆን እና ይሄንን ጉዳይ በተመለከተ “ህገ መንግስታዊ አንቀጽ የለም” የሚለው መከራከሪያ ወሳኙ አካል ሊመልሰው የሚገባውን ጥያቄ ቀድሞ የሚመልስ ነው። አንደኛ “የሚተረጎም ነገር አለ ወይም የለም?” የሚለው የሞያ ውሳኔ ነው። “ትርጓሜ ያስፈልጋል? ወይስ አያስፈልግም?” የሚለውን በሞያዊ መወሰኛ አይቶ የመወሰን ስልጣን ለህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በህግ የተሰጠ ነው። መመለስ ያለበት እርሱ ነው። ሁለተኛ በጉዳዩ ላይ የተካኑት ባለሞያዎች የሚተረጎም ነገር እንዳለ ሞያዊ አስተያየታቸውን እየሰጡ ነው። ከሌሎች ሃገራት ልምድም ለእንደዚህ አይነት ህገመንግስታዊ አጣብቂኝ ህገ መንግስታዊ ትርጓሜ ሁነኛ መፍትሄ መሆኑን ያመላክታል።





ሶስተኛ እስካሁን በዚህ ጉዳይ ላይ ከአንዳንድ ወገኖች የታየው ብዥታ የትርጉምን አስፈላጊነት የሚመሰክር ነው። ማብራሪያ ከሌለው ስልጣንና ንትርክ ተቋማዊና ህገ መንግስታዊ በሆነ አካሄድ ለገጠመን ፈተና መፍትሄ መፈለግ የተሻለውና ወደፊት የሚያራምደን አማራጭ ነው።

አራተኛው “የሚተረጎም አንቀጽ የለም” የሚለው ክርክር አውቆ ላለማወቅ ከወሰነ ሰው ወይም ጥልቅ ከሆነ ያለአዋቂነት አረንቋ ውስጥ ከተዘፈቀ ሰው የሚጠበቅ መከራከሪያ ነው።

ስለ ህገ-መንግስታዊ ትርጉም በጥቂቱ እንኳን ለመረዳት በቅን ልቦናው ለሞከረና ጥረት ላደረገ ሰው ይህ ጉዳይ ትርጉም የሚያሻውና በትርጉም ሊፈታ የሚችል እንደሆነ በግልጽ ያሳያል።

ሌላም የተነሳ መከራከሪያ አለ። “ህገ መንግስታዊ ትርጓሜም ሆነ ማሻሻያ የብልጽግና ፓርቲ ሙሉ በሙሉ በሚቆጣጠራቸው ምክር ቤቶች የሚተገበሩ ስለሆኑ ገለልተኛ ባልሆነ አካል ተግባራዊ የሚደረጉ፣ ተቀባይነት የሌላቸው መፍትሄዎች ናቸው” የሚለው ጉዳይ ነገሩ ወንዝ ባያሻግርም፣ በህገ መንግስት ትርጉም የማይተካ ሚና የሚጫወተው የህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ኮሚቴ በዋነኛነት በገለልተኛነት የሚመራ ተቋም ነው።

በህገ መንግስቱ ይሄን ጉባኤ የተመለከቱ ድንጋጌዎች ፍርድ ቤቶችን ከተመለከቱ ድንጋጌዎች ጋር አብረው የተቀመጡ ናቸው። ጉባኤው ወደ ፍርድ ቤትነት የተጠጋ ህገ መንግስታዊ ተቋም ነው። ከዚህም በተጨማሪ የፌደሬሽን ምክር ቤት የሚመራው በብልጽግና ፓርቲ

አይደለም። ስለዚህ የትርጓሜው ሂደት በአንድ ፓርቲ ቁጥጥር ሥር ያለ ነው ማለት አይቻልም።

የትርጓሜውን የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርበው በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት እና በምክትል ፕሬዝዳንት የሚመራ ገለልተኛ አካል ነው። የህገ መንግስታዊ ትርጓሜ ሥርዓታችን ወደፊት መሻሻል ቢኖርበት እንኳን ለህገ መንግስታዊነት ተገዥ የምንሆነው አሁን ያለውንና በህገ መንግስቱ የተደነገገውን ሥርዓት አክብረን መሆን አለበት።

ዛሬ ያሉንን ተቋማትና ሥርዓት ማክበር ካልቻልን ህገ-መንግስታዊነት ስር ሊሰድ ፈጽሞ አይችልም። ለምሳሌ በሀገረ አሜሪካ ጥቁሮች እንደ ዜጋ ያላቸውን መብት ማስከበር ከነውስንነቱም ቢሆን በህገ መንግስታዊ ሥርዓት ማእቀፍ ውስጥ ተግባራዊ ያደረጉት ትግል ነው። እስከ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ድረስ ያቀረቧቸው የህገ መንግስት ጉዳዮች በመጨረሻ ዘላቂ እና ህጋዊ በሆነ መንገድ መብታቸውን እንዲያስከብሩ አስችሏቸዋል። ያሉትን ተቋማትና ሥርዓት እየተጠቀሙ እያዳበሩ መሄድ ብልህነትና ለሃገር እጅግ ጠቃሚ አካሄድ ነው።

የህገ መንግስታዊነት አንዱ መገለጫ ህገ መንግስቱን የተመለከቱ አለመግባባቶች ሲኖሩ "የመንግስት ውሣኔና ተግባር ህገ መንግስታዊ አይደለም" የሚል ቅሬታ ሲኖር፣ ጉዳዩን ህገ መንግስቱን የመተርጎም ስልጣን ሲኖር፣ በህገ መንግስት ለተሰጠው አካል ማቅረብ ነው። ከዚህ ውጪ ሁሉም ህገ መንግስቱን ተርጓሚ እና የህገ መንግስት ዳኛ እሆናለሁ ካለ ለዲሞክራሲና ለህገ መንግስታዊነት የማይበጅ ምስልቅል የሚያስከትል አካሄድ ነው። በህገ መንግስቱ የተቀመጠውን ሥርዓት እና የተቋቋሙ ተግባራትን አክብረን መንቀሳቀስ ጉድለታቸውን እየሞላን መሄድ የሁላችንም ግዴታ ነው።





ሌላም የተሰነዘረ መከራከሪያ አለ። "ገዢው ፓርቲ የሚቆጣጠራቸውን የምክር ቤት ወንበሮችን ነጻ እና ዴሞክራሲያዊ በሆነ ምርጫ ያገኘው አይደለም። ስለዚህ "ከመጀመሪያውም ቅቡልነት ያለው መንግስት አይደለም፤ ከመስከረም በኋላ ደግሞ ምንም አይነት ቅቡልነትና ህጋዊ መሰረት የሌለው፣ ዓለም አቀፍ እውቅናም የማይኖረው መንግስት ይሆናል" የሚል ነው። ይህ አስተያየት መመለስ ያለበት በህግ ነው። ስለ 2007 ምርጫ መከራከር ሳያስፈልገን አሁን ያለው መንግስት ህግ የሚያወጣ፣ ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶችን የሚፈርም በጀትና እቅድ የሚያጸድቅ ህጋዊ መንግስት ነው።

ብልጽግና ፓርቲ በመላው ሃገሪቱ አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም መዋቅር ያለው፣ ሃገራዊ ለውጦችን በመምራት የብዙዎችን ድጋፍ ያገኘ ግዙፍ ፓርቲ ነው። ህጋዊ በሆነ አግባብ የኮቪድ 19 ስጋት እስኪወገድ ድረስና ቀጣይ ምርጫ እስኪካሄድ ደግሞ ሃገር የማስተዳደር ኃላፊነት ያለበት ፓርቲ ነው። ከጥቂት አካባቢ ያልዘለለ ድጋፍ ያላቸው ፖለቲከኞች በህግም፣ በፖለቲካም ሆነ በሞራል መስፈርት ከእነርሱ በብዙ እጥፍ የተሻለ ቅቡልነት ያለው ፓርቲና መንግስት ሃገሪቷን እየመራ መሆኑን መረዳት ይኖርባቸዋል።

የቀድሞውን የምርጫ ሰሌዳ የተወካዮች ምክር ቤት ሲያጸድቅ ያልተነሳ የህጋዊነትና የቅቡልነት ጥያቄ ምርጫው እንዲራዘም እና ሌላ ለመራዘሙ ህገ መንግስታዊ መፍትሄ እንዲገኝለት ሲወስን የህገ መንግስታዊ ቅቡልነትና የህጋዊ ጥያቄ ማንሳት በአንድ ነገር ላይ ሁለት አቋም መያዝ ነው።

የመጨረሻው ነገር ግን በቀላል የማይታየው ሃሳብ ድግሞ መፍትሄው "የሽግግር መንግስት ነው" የሚለው ነው። ይህ መንገድ በህገ

መንግስቱም ያልተደነገገ፣ ህገ መንግስታዊም ያልሆነ ሃሳብ ነው። ያለ ምርጫ እንዲሁ ተጠራርቶ ስልጣን የሚከፋፈልበት ምንም አይነት ህጋዊም ሆነ ህገ መንግስታዊ አካሄድ የለም። "የፖለቲካ ፓርቲ ስለሆንኩ ስልጣን ይገባኛል" የሚለው ፈሊጥ ዲሞክራሲያዊም ሆነ ህገ-መንግስታዊ አይደለም።

ህገ መንግስቱ ስልጣን በምርጫ ብቻ እንደሚገኝ ይደነግጋል። ይህን መሰረታዊ መርህ በጣሰ ሁኔታ "ስልጣን እንደ ድግስ ቱሩፋት ለሁላችንም ይዳረስ" የሚለው አካሄድ በሃገራችን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የምናደርገው ጥረት ወደ ኋላ የሚመልስ፣ ከህዝብና ከሃገር ይልቅ የስልጣንን ፍላጎት የሚያስቀድም አስተሳሰብ ነው። በመሆኑም የተመረጠ መንግስት እያለ ያልተመረጡ ፓርቲዎች ተሰባስበው መንግስት የሚመሰርቱት በየትኛው የሞራል፥ የህግ እና የሥርዓት አካሄድ ነው? የሀገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ በይሁንታ በአንድም በሌላም መልኩ ሳይኖረው በፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ብቻ እንዲወሰን ስልጣን የሚሰጠው የትኛው የህግ መሰረት ነው? ከሙቶ በላይ ፓርቲዎች ተደራድረውና ተስማምተው ወደ ፖለቲካዊ መፍትሄ እስኪመጡ ድረስ ምርጫው የሚራዘምበት ችግር ተፈትቶ ከህጋዊ ምርጫው ቀን እንደርስ የለም ወይ? ለወራት ምርጫን ማራዘም ወይስ ለአመታት ለሽግግር መንግስት ብሎ የብጥብጥና የንትርክ መንግስት መፍጠር ነው፤ ኢትዮጵያን ለአደጋ የሚያጋልጠው?

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የቆየ ተሳትፎ ያላቸው ማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የሲቪክ ተቋማት መሪዎች አሉ። እነዚህን ሁሉ ወይ እንዲደራደሩ፣ ወይም በመራጭነት፣ አልያም በተመራጭነት ያገለለ፣ የፓርቲዎች የሽግግር መንግስት እንዴት አሁን ካለው መንግስት በተሻለ ቅቡልነት ይኖረዋል? የሽግግር መንግስት





የተመሰረተባቸው ሃገራት እና አጋጣሚዎች ብዙውን ጊዜ ከወታደራዊ ወይም አምባገነናዊ የጥቂቶች አስተዳደር ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሽግግር ማድረግ የፈለጉ፣ እና ተሰናባቹ ቡድን እየተንደረደረ ያለ የህዝብ ድጋፍ ያለው ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እስኪያካሂዱ ድረስ አዲስ ህገ መንግስታዊ ማእቀፍ እስኪዘጋጅ ተግባራዊ የሚያደርጉት አማራጭ ነው።

ለምሳሌ በደቡብ አፍሪካ የነጮች ብቻ የሆነው ፓርቲና የአፓርታይድ መንግስት የብዙሃን ድጋፍ ላለው የአፍሪካን ናሽናል ኮንግረስ በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ስልጣን እስኪያስረክብና አዲስ ህገ መንግስት እስኪጸድቅ በጋራ የሽግግር መንግስት መስርተዋል።

በፖርቹጋል፣ በፖላንድ እና ሌሎችም በመሰል የሽግግር ሂደት ያለፉ ሃገራት ልምድም ተመሳሳይ ነው። የደቡብ አፍሪካን፣ የደቡብ እና የምስራቅ አውሮፓን፣ እንዲሁም የላቲን አሜሪካን የሽግግር ተሞክሮ ስናይ አብዮታዊ ሊባል የሚችል ለውጥ፣ ሙሉ የህገ መንግስት ለውጥ የሚካሄድበት፣ በስልጣን ላይ ያለው ኮሙኒስት ፓርቲ ወይም ወታደራዊ አገዛዝ ከስልጣን ለመውረድ በሚንደረደርበት ሂደት ውስጥ ነው የሽግግር መንግስት የመሰረቱት።

በዚህ አጋጣሚ በግልጽ መታወቅ ያለበት ነገር አለ በኢትዮጵያ ያለው ለውጥ "ተሃድሶ" እንጂ አብዮት አይደለም። ህገ መንግስት ቀይረን አዲስ ህገ መንግስታዊ ሥርዓት እየገነባን አይደለም። አዲሱ ገዢ ፓርቲም ታድሶና የህዝብ ተቀባይነቱንም ጨምሮ ገና ጀምበሩ እየወጣ ያለ አዲስ ጉልበትና አቅም ያለው በቀጣዩም ምርጫ እጅግ ሰፊ የማሸነፍ እድል ያለው ፓርቲ እንጂ፣ ተሰናባችና ጀምበሩ ያዘቀዘቀ ስብስብ አይደለም።

ስለዚህ የሽግግር መንግስት የሚለው ሃሳብ ከህግ አንጻር ብቻ ሳይሆን ካለንበትም ነባራዊ ሁኔታ በንድፈ ሃሳብም ሆነ ከሽግግር ተሞክሮ አንጻር ለኢትዮጵያ የሚሆንና የሚበጅ አይደለም።

በተለይም የኮቪድ 19 ስጋት ባለበትና የቀጠናችን ሁኔታ ሉአላዊነት ስጋት በደቀነበት ወቅት "የሽግግር መንግስት እንመሰርታለን" ብሎ መቋጫ የሌለው ውይይት አይባል ድርድር መጀመር፣ ሃላፊነት የጎደለው ተግባር ነው። ህገ ወጥ ብቻም ሳይሆን አደገኛም ነው። መገንባት የምንፈልገው ህገ መንግስታዊ ዲሞክራሲ ነው።

ይህም ማለት ህገ መንግስታዊነት የሰፈነበት፣ የህገ መንግስት የበላይነት የሚከበርበት ሥርዓት ነው። ህገ መንግስቱ ከደነገገው ሥርዓት ውጪ ያለምርጫም ህገ መንግስታዊ እውቅና በሌለው ህገወጥ ምርጫ ስልጣን ለመያዝ የሚደረግ እንቅስቃሴ ፍጹም ተቀባይነት የለውም። እንዲህ ያለው እንቅስቃሴ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ን ህገ መንግስት ብቻ ሳይሆን ሌሎች የሃገራችንን ህጎችና ዓለም አቀፍ ህጎችን የሚጥስ ነው።

በዚህ ረገድ ኢ-ህገ መንግስታዊ በሆነ መንገድ ስልጣን መያዝን አጥብቆ የሚያወግዘውና የሚከለክለው፣ እንዲሁም በግለሰብ ደረጃም ሆነ በሃገር ላይ ቅጣት የሚደነግገው የአፍሪካ የዲሞክራሲ የምርጫ እና የአስተዳደር ቻርተር (African Charter on Democracy Election and Governance) ተጠቃሽ ነው። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ ሃምሳ የፌደራል መንግስትና ስልጣን ሲዘረዝር ቁጥር አንድ አድርጎ ያስቀመጠው ህገ መንግስቱን የመጠበቅና የመከላከል ኃላፊነት ነው።





ይህንን ሃላፊነት ለመወጣት አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ ነን። ይህንን ማድረግ የማንደራደርበት ህገ መንግስታዊ ግዴታችን ነው። በህገ መንግስቱ እና በህገ መንግስታዊ ሥርዓቱ ካልሆነ በስተቀር የጨረባ ምርጫ ለማድረግ መነሳት ሃገርንና ህዝብን ለከፋ አደጋ የሚዳርግ በመሆኑ መንግስት የሃገርንና የህዝብን ደህንነት ለመጠበቅ ሲል ወሳኝ እርምጃ ለመውሰድ ይገደዳል።

ስልጣን የሚፈልጉ የፖለቲካ ሃይሎች የሃሳብ ክርክሮቻቸው መላው ህብረተሰብብ በማይጎዳ መልኩ እንዲያደርጉት ይመከራሉ። ፖለቲከኞች ስልጣን እንዲይዙ ወጣቶች ማለቅ፣ እናቶች ማልቀስ፣ ቤቶች መፍረስ፣ ህዝቦች መፈናቀል የለባቸውም። የኢትዮጵያዊያን ጫንቃ ይሄንን ከሚሸከምበት አልፏል።

የኮሮና ቫይረስ ስጋት ተጋርጦብን የሃገር ሉአላዊነት እና ደህንነት ለአደጋ ተጋልጦ ባለበት ጊዜ ስልጣንን ያለ ምርጫና ከህግ አግባብ ውጪ በሁከትና በብጥብጥ ካልሰጣችሁኝ "ሀገር አተራምሳለው" የሚለውን ማንኛውንም ኃይል እንደማንታገስ ከወዲሁ በግልጽ ለመንገር እንፈልጋለን። ለዚህም በሁሉም ረገድ በቂ ዝግጅት ያለን መሆኑም እንዲታወቅ እንፈልጋለን።

በአጠቃላይ የሚኖረን የመፍትሄ ሃሳብ ሁላችንንም በፍጹምነት የሚያረካ ባይሆንም ከህግና ከህገ መንግስታዊነት ያልወጣ፣ ሃገሪቱን ያለ መንግስት የማያስቀር፣ በቀጣይ ምርጫውን የማድረጊያ ጊዜውን አጭርና ምቹ የሚያደርግ፣ ኮቪድ 19ኝን ለመከላከል ያለንን አቅምና እድል የማያበላሽ፣ የህዝቡን ዴሞክራሲያዊ መብት ለጥቂቶች አሳልፎ የማይሰጥ አካሄዱ ለወደፊቱ ሌሎች ችግሮችንም እንድንፈታ መንገድ የሚከፍት መሆን እንዳለበት መንግስት ያምናል። ለዚህም ነው ህገ

መንግስታዊ ትርጉም የገጠመንን ፈተና ከሌሎች በተሻለ መልኩ ይፈታዋል ብለን የምናምነው።

ይሄንንም በውይይት፣ በክርክር፣ በጥበብና በእውቀት ለኢትዮጵያና ለህዝባችን የሚበጀውን ለማድረግ፣ እንደወትሮው የሚጠበቅብንን ለማድረግ ዝግጁ መሆናችንን እየገለጽኩ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ይሄንን ጉዳይ በትኩረት እና በጥሞና እንዲከታተል አደራ ማለት እፈልጋለው።

**አመሰግናለሁ!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያን እና**
**ህዝቦቿን አብዝቶ ይባርክ!**
**ያሻግርም!!**





# ለዒድ አልፈጥር የተላለፈ መልእክት

ግንቦት 16፣ 2012 ዓ.ም.

**ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች እንኳን ለ1441ኛ ዓመተ ሂጂራ ዒድ አልፈጥር አደረሳችሁ፣ አደረሰን! ዒድ ሙባረክ!**

የረመዳን ወር ስጋዊ ፍላጎትን በመንፈሳዊ ጽናት መርታትንና ራስ ማስገዛትን የመማሪያ ወር ነው። “ሰው ከምድራዊነቱ ባሻገር ያለውን ሰማያዊ ዓለም በጥቂቱ የሚቀምስበት ወቅት ነው” ይባላል። ብዙዎች ረመዳን ሲገባ በከፍተኛ ደረጃ ደስታ ይሰማቸዋል። በአንጻሩ ሲወጣ ግን ያዝናሉ። ከአንዳች ከፍታ የወረዱ መስሎ ይሰማቸዋል።

በተለይ እንደ ዘንድሮ ባለ ወቅት የሚጾም የረመዳን ጾም የመጣውን ወረርሽኝ የማሸነፊያ ትልቅ መሳሪያ ነው እና ጾሙ ከአእምሮ የሚጠፋ አይሆንም። ምክንያቱም የጾሙን ወር የምንቀበለውም የምንሸኘውም የኮሮና ወረርሽኝ ከከፈተብን ጦርነት ጋር ፊትለፊት የተጋጠምንበት በዚህ አስቸጋሪ ወቅት በመሆኑ ነው። ሙስሊሞች ታላቁን ረመዳን ከመስኪድ ሳይለዩ ለማሳለፍ ዓመቱን ሙሉ በጉጉት ይጠብቁታል።

ዘንድሮ ግን ይሄን ማድረግ አልቻሉም። ብዙዎች ጾሙን ያሳለፉትና ስግደቱን የሰገዱት በየቤታቸው በመሆን ነው።

ይሄን ወቅት በትዕግስት፣ በታዛዥነት እና በአርቆ አሳቢነት ላሳለፉ ሙስሊም እህትና ወንድሞቼ ምስጋና ለማቅረብ እወዳለሁ። ህዝባችን ሳይጎዳ ወረርሽኙን እንድናሳልፈው ሲሉ መራር የሆነውን ውሳኔ ያሳለፉትን የሃይማኖት አባቶችንና የእነርሱን ትእዛዝ ያከበሩትን ሙስሊም ወገኖቻችንን የኢትዮጵያ ታሪክ በኩራትና በአድናቆት ሲያስታውሳቸው ይኖራል።

የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመከላከል የእኛንም፣ የወገኖቻችንንም ህይወት ለመጠበቅ የረመዳን እሴቶች ቱሩፋት የላቀ መሆኑን አምነን ነው ጾሙን የጀመርነው። እስከ ዒድ አልፈጥር ዋዜማ የነበሩትን ጊዜያት ብዙዎች ንጽህናቸውን በመጠበቅ ከመጨባበጥ በመቆጠብ፣ አካላዊ ርቀትን በማክበር እርስ እበርስ በመተጋገዝ በቤታቸው በመቀመጥና ማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ በመሳተፍ የሚቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል።

ጾሙን በሰላም አሳልፎ ያደረሰን ፈጣሪ የወረርሽኙንም ወቅት አሳልፎ እንደሚያደርሰን ሙሉ እምነት አለኝ። ዒድ ሲባልም በየዓመቱ መመላለስ ነው። እና ቀጣዩን ዒድ ከኮሮና ወረርሽኝ በጸዳ መልኩ እንደምናከብረው ተስፋ አደርጋለሁ። ዒድ አልፈጥር ሙስሊሞች በረመዳን ሙስሊሞች በረመዳን ወሩን ሙሉ ጾመው ሲፈቱ የሚከበር የጾም ፍቺ በዓል ነው። በዓሉ በውስጡ ታላላቅ ጥበቦችንና አላማዎችን እንደያዘ የእምነቱ ሊቃውንቶች ያስተምራሉ።





በዒድ ሰላት እና በተክቢራ አላህን ከፍ በማድረግንና በማመስገን፣ ሃይማኖቱ በሚፈቅደው መንገድ መደሰትና ሌሎችን በማስደሰት፣ ችግረኞችን በመርዳት ማህበራዊ ትስስርን በማጠናከር እና የመሳሰሉትን በዓሉ ከሚታወስባቸው ድንቃ ድንቅ በዓላት መካከል በምሳሌነት ይጠቀሳሉ። በረመዳን ወር ጾመኛን በማስፈጠር፣ ሰደቃ በመስጠት የተጀመረው የመተሳሰብ ጉዞ በዒድ ዋዜማ በዘካትል ፈጥር እንደሚጠናቀቅ ሊቃውንት ይናገራሉ። የዘካትል ፈጥር አካፋዮች ወይንም ሰጪዎቹ እና ተቀባዮቹ በተለያየ አንጻር የሚታይ ትርጉም ይሰጠዋል።

ዘካተል ፈጥር ከሰጪዎቹ አንጻር ሲታይ የረመዳንን ጾም ሲጾሙ ሰው በመሆናቸው የፈጸሟቸውን ጥቃቅን ስህተቶች እና ጉድለቶች እንዲሽርላቸው በማሰብ የሚፈጸም ነው። ከተቀባዩ አንጽር ሲታይ ደግሞ ችግረኛ ሙስሊሞች በዓሉን ከቤተሰቦቻቸው ጋር በደስታ እንዲያሳልፉ እንዲያግዝ የተደነገገ ነው።

የኢስላም ሊቃውንት እንደሚያብራሩት “ዘካትል ፈጥር” ለበዓሉ ጊዜ ከሚመገበው ውጪ ትርፍ ምግብ ባለው ሙስሊም ላይ በግዴታነት ተደንግጓል። ከዚህ ድንጋጌ እንደምንረዳው የእለት ጉርሱን ሳያገኝ በዓልን የሚያሳልፍ ወገን እያለ በዓልን በበዛ ቅንጦት ማሳለፍ፣ ወገን ዛሬ ተርቦ ሳለ ለነገዬ ብሎ ማከማቸት ዘካትል ፈጥርን እንደ አለማውጣት አድርጎ ይቆጠራል።

ዘካትል ፈጥር ጾም እንዲጾሙ ግዳጅ የሌለባቸውን ህጻናት እና ሌሎች የቤተሰብ አባላቶች ጭምር አካትቶ በእያንዳንዳቸው የቤተሰብ ብዛት በነፍስ ወከፍ በአንድ ሰው አንድ ቁና ወይም ሁለት ኪሎ ተኩል ገደማ

ያህል ያወጣል። ወይም በአካባቢው በተለምዶ ከሚመገቡት የእህል አይነት ወይንም የዚያን ተመን ገንዘብ ተሰልቶ ይሰጣል።

ዘካትል ፈጥር የሚሰጠው የዒድ ማሳለፊያ ላጣ ችግረኛ ሰው ነው። ተቀባዩም በተራው የተቀበለው ዘካ ከበዓሉ እለት ፍጆታው የሚተርፍ ከሆነ እርሱም በተራው ለሌሎች ዘካትል ፈጥርን የመስጠት ወይንም የማካፈል ግዴታ አለበት። ይህ ልማድ ከእምነታዊ ጸጋው ባለፈ ማህበራዊ ኑሮን በማጠናከር በኩል ለሃገር የሚኖረው ፋይዳው እጅግ የጎላ እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም።

ሌላው የዒድ ውበት ዘመድ ከዘመድ፣ ጎረቤት ከጎረቤት ጋር መጠያየቅ፣ መመራረቅና አቅም በፈቀደ መጠን ደስታን በመግለጽና ቤት ያፈራውን መቋደስ ነው። አማኙ ስጦታ ይቀያየራል። በተለይ ለበዓሉ ማረድ የማይችሉ ችግረኛ ጎረቤቶች ካሉ እነርሱን በስጦታው ማሰብ ግዴታው ነው። የምንሰጠው ስጦታ አነስተኛ ቢሆንም እንኳ ዋናው እነርሱን ማሰባችን ነው። ቡካዩና ሙስሊም እንደዘገቡት ነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ መክረዋል፤ "እናንተ የሙስሊም ሴቶች ሆይ፥ የፍየልን ሸኮናን የሚያክል አነስተኛ ቢሆንም እንኳን ጎረቤት ለጎረቤት ስጦታ ማበርከትን አትናቁ" ብለዋል።

ይህን መሰል ኢስላማዊ እሴቶችን በመጠቀም የኮሮና ወረርሽኝ የከፈተብንን ጦርነት በመከላከል፣ ጥረታችን ጎን ለጎን እርስ በእርስ የመደጋገፍ ባህላችንን አጠናክረን እንቀጥል ለማለት እወዳለሁ። አቅም በፈቀደ መጠን ማእዳችንን እናጋራ፤ ችግረኛ ወገኖቻችንን በእውቀት፣ በገንዘብ እና በቁስ እንደግፍ። አንድነትን የማጠናከር ተግባሮቻችንን ወደ ተቀሩት አስራ አንድ ወራትም እናዝልቃቸው።





ለአንድ ወይንም ለሁለት ዓመት ብቻ ሳይሆን በእድሜ ዘመናችን ሁሉ የሚከወን የጽድቅ መንገድ እናድርጋቸው። ነብዩ መሐመድ (ሰ. ዐ. ወ) ማእድ ስለማጋራት ሲያስተምሩ ቡካዩና ሙስሊም በዘገቡት ሃዲስ፣ "ለሁለት ሰዎች የተዘጋጀ ምግብ ለሦስት ሰዎች ይበቃል። ለሦስት ሰዎች የተዘጋጀ ምግብ ደግሞ እንዲሁ ለአራት ሰዎች ይበቃል" ብለዋል። ይህን የነብዩን አስተምህሮ ብንተገብር በምግብ እጥረት አንድም ሰው ወደ ጎዳና እንደማይወጣ ምንም ጥርጥር የለውም።

ኮሮና በዓለም ላይ ብርቱ ክንዱን በማሳረፍ አደጋ እያሳረፈ ያለው ሰዎች ራሳቸውን በመቆጣጠር የመከላከያ መንገዶች ላይ ሳይዘናጉ መተግበር ስላልቻሉ ነው። ነብዩ መሃመድ (ሰ.ዐ.ወ) በእሳቸው ምልከታ ራሳችንን መቆጣጠር መቻል ታላቅ ቦታ ከተሰጣቸው ተግባራት መካከል አንዱና ዋነኛው ጉዳይ መሆኑን እንዲህ ሲሉ አስተምረዋል። "ጀግና ወይንም ብርቱ ማለት ሰዎችን ታግሎ የጣለ ሳይሆን በንዴት ጊዜ ራሱን የተቆጣጠረ ሰው ነው" ሲሉ ራስን ለመቆጣጠር መቻል ጀግንነት እና ብርታት መሆኑን አስተምረዋል።

ከኮሮና ወረርሽኝ ጋር የገጠምነውን ትግል በድል የምንወጣው በሽታው የሚተላለፍባቸውን መንገዶች ሁሉ ራሳችንን በመቆጣጠርና በመግራት ከዘጋናቸው ብቻ ነው። የኮሮና በሽታ ለኃያላኑ እንኳን ያልተበገረ ክፉ ወረርሽኝ እንደሆነ ሁላችንም አይተናል። ራሳችንን ለሃይማኖት አባቶችና ለጤና ባለሞያዎች ምክር፣ ትእዛዝ ተገዢ ካደረግን፣ በጾሙ ጊዜ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ያሳዩትን ብርታትና ቁርጠኝነት ካስቀጠልነው፣ ኢትዮጵያ ወረርሽኙን በመቋቋም የምትመሰገን ሃገር ትሆናለች።

የሚቀጥሉትን የዒድ በዓላት ከአሁኑ በተሻለና የዘንድሮውን ገድል በሚዘክር መንገድ እንደምናከብራቸው ተስፋ አደርጋለሁ። ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ከሌሎች እምነት ተከታዮች ጋር እያደረጉት ካለው ትብብር፣ ትግግዝና መተሳሰብ ከቀጠልን ወረርሽኙ ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን መማሪያ እንጂ መማረሪያ እንደማይሆንብን አምናለሁ።

በዘመን መቁጠሪያ ምክንያት የጾምና የጸሎት ጊዜው አሁን ቢወጣም እኛ ግን ከጾም እና ከጸሎት እንደማንወጣ ተስፋ አለኝ። ከጥሩ ምንጭ የቀዳችውን ውሃ በጀርባዋ አዝላ እንደምትጓዝ እናት በጾም ወቅት ያገኘናቸው እሴቶች በልባችን ይዘን እንደምንጓዝ አልጠራጠርም።

በድጋሚ እንኳን ለ1441 ዓመተ ሂጂራ የረመዳን ወር ጾም ፍቺ፣ የዒድ አልፈጥር በሰላም አደረሳችሁ፣ አደረሰን።

**ዒድ ሙባረክ!**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ እና ተከብራ ለዘለዓለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያን እና ህዝቦቿን ይባርክ ያሻግራትም!**





# ትናንትን በነገ መነጽር

**ሰኔ፣ 2012ዓ.ም.**

‹ወደኋላ አርቆ ለማየት በሚገባ ወደፊት መጓዝ ያሻል› ይባላል። ዓለም የጥንቱን ታሪክ በሚገባ መመርመር የቻለው በሥልጣኔ ወደፊት ስለተራመደ፤ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ከፍ ስላለ ነው።

የተቀበሩ ከተሞች ያሉበትን ሥፍራ፣ የተቀበሩ ቅርሶች ያላቸውን እድሜ፣ የእጅ ጽሑፎች የተጻፉበትን ዘመን፣ ቀደምቶቻችን የነበራቸውን ዕድገት፣ አኗኗርና ሥልጣኔ፣ ቋንቋችን ከየት ወዴት እንደመጣ፣ ዋሻዎች በሆድቃቸው ውስጥ ምን እንዳዘሉ ዛሬ በሚገባ ለማወቅ ችለናል። በዚህ ደረጃ ያወቅነው ግን ዓለም በዕውቀትና በክህሎት መጥቃ ወደፊት ለመሄድ በመቻሏ ነው። ለዚህ ነው ‹አርቀን ወደኋላ ለማየት በሚገባ ወደፊት መጓዝ ያሻል› የተባለው።

ታሪካችንን በሚገባ ለመመርመር፣ ለማወቅና በትናንታችን ላይ ለመግባባት የተሻለው መንገድ የድሮው ላይ ተቸንክሮ በመቅረት ሳይሆን ወደፊት በመገሥገሥ ነው። የተሻሉ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች፣ የአጠናን ዘዴዎች፣ የመመርመሪያ መሣሪያዎች ሲኖሩን የበለጠ በትናንቱ ታሪካችን ላይ እንግባባለን። ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮቻችን እየተፈቱ ሲሄዱ ይበልጥ በትናንቱ ላይ እንግባባለን፤ ወይም ደግሞ ባለመግባባት ተግባብተን እንቀጥላለን።

ወደኋላ ያለውን ለማየት በሚገባ ወደ ፊት መራመድ የሚያስፈልገን ነገሩን በቅጡ ለመረዳት የሚያስችል እውቀትና ቴክኖሎጂ ስለምናገኝ ብቻ አይደለም። በቅጡ ለመረዳት ሙሉ ስእሉን ማየት ስለሚያስፈልገን፤ የእይታ አድማሳችን ሰፊ መሆን ስላለበት፤ መረጃዎቻችን መብዛት ስለሚኖርባቸው ጭምር ነው። የነገሮችን ትስስርና ውጤታቸውን፣ የሁኔታዎችን ግንኙነትና መሰናሰል በወግ በወጉ መመልከት ስንችል ያኔ ምን እንደተፈጠረ ይገለጽልናል። አርቀን ለማየት ከነገሩ ከፍ ብለን መገኘት አለብን። በእውቀት ከፍ ማለት፣ በመረጃ ከፍ ማለት፣ በመተንተን ችሎታ ከፍ ማለት ይጠበቅብናል። ምርምራችን እየደረጀ ሲመጣ እውቀታችን ይደረጃል፤ የእይታ አድማሳችን ሲደረጅ መረዳታችን እንደሚያድግ ምንም ጥርጥር የለውም። በጊዜ፣ በእውቀትና በቴክኖሎጂ ታግዘን የማንፈታው የችግር ቁልል፣ የማንገፋው የመከራ ዳገት አይኖርም። እንደ ሀገር የሚያዋጣንም ይሄው ነው።

ትናንታችን ከድህነት በተላቀቀ አእምሮ መታየት አለበት። ትናንትን ከፖለቲካ ማፋታት፣ ከብሔር ልዩነት ማፋታት፣ ከመዋጊያነት ማፋታት የምንችለው ትናንትን በብልጽግና ድልዳል ላይ ሆነን ካጠናነው ነው። ትናንትን በብሶትና በቁዘማ ማጥናት ትናንትን በሚገባ እንድንረዳው አያደርገንም። የትናንት ጥያቄዎችን በዛሬ ዕውቀትና አሁን እጃችን ላይ ባለ ጥበብ መመለስ ብልህነት ነው። የዛሬ ጥያቄዎችን በትናንት ታሪክ ለመመለስ መጣጣር ግን ከንቱ ድካም ነው።

ታሪካችን ገና ተሰርቶ ያለቀ አይደለምና ዛሬ ላይ ሆነን የምናበጃጃቸው ብዙ ነገሮች አሉን። ገና ቤቱ ሙሉ ሆኖ አልቆመም። ስለ ትላንታችንን





ሙሉ መረዳት እስኪኖረን ድረስ ቀዳደን መጣል ሳይሆን ስዕሉ ሙሉ የሚሆንበትን መፍትሄ እየፈለግን፣ የበኩላችንን ጡብ አስቀምጠን ማደረጀትና ሙሉ ቁመናውን እንዲይዝ ማድረግ ከእኛ ይጠበቃል። ተሰርቶ አለማለቁም አንድ መልካም አጋጣሚ ነው። ተሠርቶ ካለቀ ቤት ይልቅ ለመሠራት በሐሳብ ላይ ባለ ቤት ላይ የምንፈልጋቸውን የዲዛይን ሐሳቦች ማካተት እንችላለን። ተሠርቶ ያለቀው ቤት ግን የምንፈልገውን ሁሉ ለማደረግ ማፍረስ ይኖርብናል። ያ ደግሞ ኢኮኖሚያዊ፣ ታሪካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ብሎም ፖለቲካዊ ቀውስ እንጂ ምንም የሚፈይደው ነገር የለም።

ሌላው መረዳት የሚገባን ትላንታችንን በሚገባ ማወቃችን ነጋችንን ለማቆንጀት እንጂ ለማጠልሸት ከሆነ ጥቅም የለውም። ሰውን ጠቢብ የሚያስብለው ስለነገ ጭለማውን ሳይሆን መልካም ተስፋውን ሲሰንቅ ነው። ስለሆነም ታሪክ ባትሪ ሆኖ ከፊታችን የተዘረጋውን መንገድ ቀለል አድርጎ ሊያሳየን እንጂ ግርዶሽ ሆኖ ሊያጨልምብን አይገባም። ነጋችን የሚጎዳው በትላንት ታሪካችን ሳይሆን ታሪክን በምናይበት መነጽር ነው። መነጽሩ ከደበዘዘ አሻግረን የምናየው ነገ ደብዛዛ፣ ጥላሸት ተቀብቶ ከሆነም እንደዚያ ጥላሸት መሆኑ አይቀርም።

ሀገርና ሕዝብ ሩቅ ተጓዦች ናቸው። ‹ዜጎች› ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እሴቶችን እየተቀባበሉ በትውልድ ጅረት ላይ ወደ ፊት ይጓዛሉ። የነገው ትውልድ የጉዞ ርቀት የሚወሰነውም የትላንቱና የዛሬው ትውልድ ባዋጣው ልክ ነው። መጭውም እንደዚያው ለቀጣዩ ጉዞ እርሾ እያስቀመጠ እንደሚሄድ ምንም ጥርጥር የለውም። ጉዞው

ልክ እንደ ዱላ ቅብብል ነው። የመጀመሪያው ሯጭ ባፈጠነው ልክ ቀጣዩ እንደሚፈጥነው ሁሉ ባዘገየው ልክ ይዘገያል።

እናም በተቻለን አቅም ወደፊት እንገስግስ፤ እኛ በሚገባን ልክ ወደፊት ከሄድን እንደ ሀገር ወደኋላ ያለውን ታሪክ አጥርተን የምናይበት መነጽር ለመፍጠርና በብሩህ ነጋችን ውስጥ ተወዳዳሪዎቻችን በልጠን መገኘታችን አይቀሬ ነው።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**





# በወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የተላለፈ መልዕክት

ሃምሌ 10፣ 2012 ዓ.ም

**ውድ የሃገሬ ህዝቦች፤**
**የተከበራችሁ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣**
**ሲቪክ ማህበራት እና የሃገር ሽማግሌዎች፣**
**ከቡራት እና ክቡራን**

ባለፉት ጥቂት ወራት በዓለም ተሰራጭቶ በሃገራችን ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ሃገራዊ እንቅስቃሴዎችን ባስተጓጎለው የኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት ወቅቱን የሚመጥኑ ተግባራት በየአቅጣጫው ሲከወኑ መቆየታቸው ይታወቃል። ውሳኔ ከሚሹ ጉዳዮች መካከል ሰደስተኛው ሃገራዊ ምርጫን የተመለከተው አጀንዳ አንዱ እና ዋነኛው ሲሆን ወራትን በፈጀ ሂደት ውስጥ አልፎ ከውሳኔ ላይ ደርሷል።

እንደሚታወቀው ህገመንግስታችን ምርጫ በየአምስት አመቱ መደረግ እንዳለበት ደንግጓል በሌላ በኩል ወረርሽኙ ምርጫውን ለማካሄድ

የሚያስችሉ የዝግጅት ስራዎችን አስተጓጉሏል። ለዚህ ሁኔታ መፍትሄ ለመስጠት ህገመንግስታዊ አካሄድ ተከትሎ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የቀረበለትን የህገመንግስትን ትርጉም ጥያቄ ተመልክቶ ምላሽ ሰጥቷል።

ምላሹን ተከትሎ የመመልከት ሰልጣን ያለው ይህ ምክር ቤት ምርጫውን ያራዘመው ወረርሽኝ ተገትቶ ቀጣይ ምርጫ እስኪደረግ ድረስ ሁሉም የፌደራል እና የክልል ምክር ቤቶች ስራቸውን እንዲቀጥሉ እና ከዘጠኝ እስከ አስራሁለት ወራት ባለ ጊዜ ውስጥ ምርጫ እንዲካሄድ ወስኗል።

ለገጠመን ህገመንግስታዊ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ያሉንን ተቋማት፣ ያሉንን ህግጋት እና ያሉንን ባለሞያዎች በአግባቡ እንድንጠቀም ከዚህ በፊት ባልታየ መልኩ በር የከፈተ ሲሆን የሃገራችን ዲሞክራሲ እራሱን በራሱ እያጎለበተ የሚሄድ መሆኑን በግልጽ አመላክቷል። ይህ ክስተት የወቅቱን ፈተና ለማለፍ ከማገዝ ባለፈ ነገሩን በትክክል ካጤነው አጋጣሚውን እንደ ሀገር ዴሞክራሲን ለመለማመድ እንድንችል አንድ እርምጃ ወደፊት የገፋን ትልቅ እድል ነው ማለት ይቻላል።

የኮሮና ወረርሽኝ በአሁኑ ሰአት የማያስጨንቀው ሀገር የለም። በኢትዮጵያም አደጋው እየሰፋ መጥቷል። በየጊዜው የሚመጡት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከሆነ በኮሮና የሚጠቁት እና የሚሞቱት ዜጎቻችን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። በተለይም በመጪው ክረምት ቁጥሩ ከዚህ በላይ ሊያሻቀብ እንደሚችል ይገመታል።





እንደሚታወቀው በሽታው በተወሰኑ አካባቢዎችን ለይቶ ወይም ጥቂት ሰዎችን ብቻ መርጦ የሚያጠቃ አይደለም። ለሁላችንም የመጣ እያንዳንዳችንን ሊያጠቃ የሚችል አደገኛ ወረርሽኝ ነው። ፈተናው የመጣው ለሁላችንም እንደመሆኑ መጠን መዋጋት የሚገባንም በጋራ እና በሁሉም አቅጣጫ መሆን ይገባዋል። በአንድ ግምባር ተዋግተን ኮሮናን እናሸንፋለን ማለት ዘበት ነው። ቢያንስ ቢያንስ በሶስት ግምባሮች ያለንን አቅም አሟጠን መታገል ይጠበቅብናል።

አንደኛ በጤናው ዘርፍ የጀመርናቸውን እንቅስቃሴዎች አጠናክረን በመቀጠል የበሽታውን መስፋፋት እንዲቀንስ ከማድረግ በተጨማሪ ታማሚዎች እንዲያገግሙ ማስቻል ይኖርብናል።

ሁለተኛ በኢኮኖሚው ዘርፍ የተጋረጠብንን አደጋ በመቀነስ ወረርሺኙ የፈጠረውን ዓለም አቀፋዊ ስጋት ምክንያት ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች በመቀዛቀዛቸው ምክንያት ምጣኔ ሃብታችን ላይ ከፍተኛ ጫና እንዳይፈጥርብን ከበፊቱ ለይተን ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ቀይሰን በመንቀሳቀስ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ እድገታችንን ማስቀጠል ይኖርብናል።

ሶስተኛ ከታሪክ እንደምንማረው ከወረርሽኝ በኋላ  ረሃብ የመከሰት እድሉ ከፍተኛ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በወረርሽኙ ዓለም አቀፋዊ ምክንያት ከውጪ የሚመጡ ዓለም አቀፍ ድጋፎች ሊቀዛቀዙ፣ በውጪ ምንዛሬ እጥረት ምክንያትም የምግብ ግዢዎች ሊቀንሱ ይችላሉ። ስለሆነም ወረርሺኙ የአርሶ እና የአርብቶ አደሮቻችን አቅም በማዳከም የምግብ ምርቶች ላይ ማሽቆልቆል እንዳያጋጥመን ምን መደረግ እንዳለበት ስልቶች መንደፍ ያስፈልጋል።

ለአርሶ እና አርብቶ አደሮቻችን አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት የተለየ ድጋፍ ሰጥተው ምርታማነታቸውን ለመጨመር ለማስቻል ከወዲሁ እገዛዎች መደረግ ይኖርባቸዋል። ከነዚህ ጉዳዮች አኳያ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሰሞኑን ያሳለፈው ውሳኔ በአንጻራዊነት ትኩረታችንን ለብዙዎች ችግሮቻችንን እምብርት ወደሆነው ወደ ኮሮና እንድናደርግ ያግዛል። ማንኛውም ሀገራዊ ነገር የሚደረገው ለህዝብ ነው ህዝብ ሳይኖር ለህዝብ የሚደረግ ነገር ደግሞ አይኖርም።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት በምርጫ እና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ የሰጠው የእፎይታ ጊዜ ለህዝብ ደህንነት የተሰጠ ጊዜ እንጂ ለፓርቲዎች የተሰጠ ጊዜ አይደለም። ውሳኔው ያስፈለገው ለህዝብ ደህንነት እንጂ ለመንግስት አይደለም።

ምርጫውን ማራዘም ያስፈለገው ለምርጫ ሲባሉ በሚከናወኑ ኩነቶች ምክንያት የሚፈጠር አደጋን ለመቀነስ ነው። በኢትዮጵያ ወስጥ ዲሞክራሲ እንዲያብብና ሀገራዊ መግባባት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ገዥው ፓርቲ በቀጣይ ጊዜያት በዋና ዋና ሃገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በውይይት እና በምክክር መስራቱን ይቀጥላል።

ምንም እንኳ በተለያዩ ሃገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚኖረን ኣመለካከት አንድ አይነት ባይሆንም ያለችን ሀገር ግን አንድ ናት። ለአንዲቷ ሀገራችን ስንል በሰከነ፣ በሰለጠነ እና ነገን አርቆ በሚያይ በሳል ስሜት ውይይት እና ምክክር ማድረጋችንን አናቋርጥም። በተለይም የሀገራችንን መጻኢ እድሎች በሚወስኑ ዋና ዋና ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ መግባቢያ ላይ እየደረስን ነገሮችን ማስተካከል ይጠበቅብናል። አሁን





የትኛውም ተግባር ለአንድ የተወሰነ አካል ተጠቅለሎ የሚሰጠበት ወቅት አይደለም።

ኮሮና በኢኮኖሚው ዘርፍ ላይ እያሳደረ ያለውን ጫና የመቀነስ ሃላፊነት የሁላችንም ይሆናል። የስራ ፈጠራን መደገፍ፣ አዳዲስ የልማት እድሎችን መጠቀም ግብርናችን ከዚህ በፊት ባልተጓዘባቸው መንገዶች ሄዶ ምርት እና ምርታማነትን እንዲጨምር ማስቻል፣ አምራች ኢንዱስትሪው ከውጪ የሚመጡ ሸቀጦችን ሊቀንስ በሚችልበት መንገድ አቅምን አሟጦ እንዲያመርት መደገፍ፣ አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን ማፈላለግ የእያንዳንዳችን የቤት ስራ በመሆኑ በሃሳብ፣ በስትራቴጂ እና በልዩ ልዩ መንገዶች የየበኩላችንን ማበርከት ይጠበቅብናል።

ይህ ጉዳይ ሃገርን እንደ ሃገር ህዝብንም እንደ ህዝብ ለማኖር የሚሰራ ሀገራዊ ስራ በመሆኑ ሁሉም የፖለቲካ ሃይሎች ሊሰሩበት የሚገባ ሀገሪቱን ከፈተና የሚያወጣ መንገድ በመሆኑ በሁላችንም ሃላፊነት ለወሰድ ይገባል።

አሁን ዳር ቆሞ የመመልከቻው ጊዜ እና ጣት የመጠቋቆሚያ ጊዜ ላይ ባለመሆናችን የጋራ ክንዳችንን አጠናክረን መፍትሄ መፈለግ ይኖርብናል። ከዚህ ጎን ለጎን መጪውን ምርጫ ነጻ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ሰላማዊ እና ተአማኒ ለማድረግ በጋራ በቂ ዝግጅት ለማድረግ እያደረግን እንቆያለን አንዱ ዋናው አላማችን መጪውን ምርጫ ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያዊያን የሚመጥን ማድረግ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

በዚህ ረገድ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከሲቪክ ማህበራት፣ ከሃይማኖት ተቋማት፣ ከታዋቂ ሰዎች፣ ከሚዲያ ልሂቃን፣ ከሃገር ሽማግሌዎች እና ከጎሳ አባቶች እና ከሚመለከታቸው ሁሉ ጋር የኮሮና ቫይረስን የመከላከል እርምጃችንን በማያውከ መልኩ በመወያየት እና በመመካከር እንሰራለን። ሁላችንም በታሪክ ፊት ጎላ ብሎ የሚናገረው በአንደበታችን ሳይሆን በተግባራችን ነው። ስለሆነም እያንዳንዳችን ለተግባራዊነቱ ከወዲሁ ቆርጠን እንነሳ ስል ጥሪዬን አቀርባለሁ።

በመንግስት በኩል ይሄንን አጋጣሚ ሃገርን እና ህዝብን ለማዳን ግዳጅ እንደተሰጠው፣ ሃላፊነት እንደተጣለበት አድርጎ ይቀበለዋል። እንደገዢ ፓርቲ ይሄንን ጊዜ እንደ ተጨማሪ የሃላፊነት ጊዜ እናየዋለን፤ የፌደሬሽን ምክርቤት ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች ሁላችንም በዚህ መልኩ ከተቀበልን ምክር ቤቱ የህዝብን ደህንነት በበቂ ሁኔታ ለማስጠበቅ በማለም እንዳሳለፋቸው አድርገን ካመንን በእርግጥም ከፊታችን መልካም ተግባር የምንፈጽምበት ጊዜ ተዘርግቷል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች የኢኮኖሚ ተዋንያን፣ ሲቪክ ማህበራት፣ የሚዲያ ልሂቃን፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የሃገር ሽማግሌዎች እና በየዘርፉ ጠቃሚ አስተዋጾችን የምታበረክቱ አካላት በሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ጉዳዮች ዙሪያ የሚጠበቅባችሁን ለመወጣት ዝግጁ እንድትሆኑ እጠይቃለሁ።

አንደኛ የኮሮናን ወረርሽኝ በቁጥጥር ስር ለመዋል፣ ሁለተኛ ከፊታችን የተጋረጠውን የኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ቀውስ ከፍተኛ ቀውስ ሳያደእርስብን በብቃት ለመሻገር፣ ሶስተኛ ሊደቀንብን የሚችል የረሃብ እና የምግብ ምርት እጥረት ሊያስከትልብን የሚችልባቸውን አደጋዎች





እና ከሉአላዊነት ጋር የተገናኙ ጥቃቶችን በቁርጠኝነት ለመመከት፣ አራተኛ ቀጣዩን ምርጫ ሰላማዊ፣ ዲሞክራሲያዊ፣ ነጻ እና ተአማኒ ለማድረግ በጋራ እንድንሰራ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ እና**
**ተከብራ ለዘለዓለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያን እና ህዝቧን ይባርክ**
**ያሻግራትም! አመሰግናለሁ!**

# የሕዳሴ ግድብ የመጀመሪያ ዙር ውኃ ሙሌትን በማስመልከት የተላለፈ መልእክት

**ሃምሌ 16፣ 2012ዓ.ም.**

## የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ሕዝቦች
## ክቡራትና ክቡራን

ዛሬ ሀገራችን በታላቅ ጉጉት የምትጠብቀውን ብሥራት የምትሰማበት እለት ነው። የዓመታት ልፋታችን ወሳኝ ምዕራፍ ላይ የደረሰበት፣ የሕዳሴው ግድባችን የመጀመሪያ ዙር የውሃ ሙሌት የተጠናቀቀበት ታሪካዊ እለት ነው። በጋራ ጥረታችን ግድባችንን እዚህ ደረጃ ስላደረስነው መላው የሀገራችን ሕዝቦች እንኳን ደስ አለን፣ እንኳን አላችሁ ለማለት እወዳለሁ።

በዚህች እለት እኛ ኢትዮጵያውያን ዳግም «አሸናፊነት» ምን እንደሆነ አውቀናል፤ ድል ማድረግ የሚያስገኘውን ደስታ በድጋሚ ማጣጣም ጀምረናል። ይበልጥ የሚያስደስተው፥ ማንም ባልተማመነብን ወቅት በራሳችን አቅም ላይ እምነት ኖሮን ማሳካት በመቻላችን ነው። አንዳንዶች ሕዳሴው ግድብ ላይ ሙጭጭ ማለታችን ምስጢሩ





አይገባቸውም። የታችኛው የአባይ ተፋሰስ ሀገራትን ለመጉዳት አልመን የነደፍነው ተንኮል ይመስላቸው ይሆናል፤ እውነታው ግን ያ አይደለም።

ሕዳሴ ግድባችን የዚህ ትውልድ መለያ ማህተም፣ የዳግም አሸናፊነት ምልክት ነው። የዘመናት ቁጭታችን መልስ ማግኘት መጀመሩን የምናበስርበት የድል ነጋሪት ነው። አንገታችንን ሊያስደፉ ሲከጅሉ ለነበሩት ሁሉ የጫኑብንን የድህነትና ኋላቀርነት ሸክም ወዲያ ልናሽቀነጥር መቁረጣችንን ጮክ ብለን የምንናገርበት ድምጻችን ነው። ከእንግዲህ “ግድባችን” በሁለት እግራችን መቆም እንደማይሳነን በተግባር የምንጠቁምበት፣ ወደ ከፍታው ለማቅናት የመታጠፊያ ነጥባችን መሆኑን ዓለም በትክክል ይረዳል ብዬ እገምታለሁ።

እነሆ እንደተናገርነው ማንንም ሳናስቸግርና ማንንም ሳንጎዳ ባቀድነው ልክ የመጀመሪያውን ዙር ውኃ ሞልተናል። መስከረምን ጨምሮ፣ ክረምቱ ገና ሁለት ወር ተኩል ይቀረዋል። የዝናቡ መጠንም እየጨመረ ነው። እኛም ፈጣሪ ረድቶን ከታቀደለት ጊዜ ቀድሞ የግድቡ ውኃ ሞልቶ መፍሰስ ጀምሯል። ግድባችን እንኳንስ ጉዳት ይቅርና በተቃራኒው ለታችኛው ተፋሰስ ሀገሮች ጥቅም ሊያስገኝ እንደሚችል የተናገርነውም አሁን በተግባር ይረጋገጣል።

## ውድ ኢትዮጵያውያን፣

ይሄን እኛ ያየነውን ግድብ ለማየት፣ የሰማነውን የግድቡን ዜና ለመስማት፣ መዋጮ ማዋጣቱ ላይ ለመሳተፍ ብዙ ትውልዶችና ብዙ መሪዎች ተመኝተው ነበር፤ ዳሩ ግን አልቻሉም። እኛ እዚህ ዘመን ደርሰን ዓባይ ከዘፈንና ከማስፈራሪያነት አልፎ፣ ማንንም ሳይጎዳ

ተገድቦ፣ ግድቡም ውኃ ይዞ ለማየት በቃን። ይሄን ያዩ ዓይኖቻችንና ብስራቱን የሰሙ ጆሮዎቻችን ምንኛ ዕድለኞች ናቸው?

በሕዳሴው ግድብ ስም የግል ጥቅማቸውን ሲያሳድዱ የነበሩ ጥቂቶች የመኖራቸውን ያህል ግድቡ እውን እንዲሆን ብዙዎች ለፍተዋል፤ ሳይሰስቱ ጉልበታቸውን፣ ገንዘባቸውን፣ ጊዜና እውቀታቸውን ሰጥተዋል። ከምንም በላይ አይተኬ ሕይወታቸውን ለሕዳሴው የገበሩለትም አሉ። በተከፈለው ዋጋ እነሆ የዘመናት ሕልማችን እውን ሆኗል። ዛሬ የምንወቃቀስበት ጊዜ ሳይሆን የምንመሰጋገንበት እለት ነው። ግድቡን ያቀዱ አመራሮች፣ ፕሮጀክቱን ሲያስተዳድሩ የነበሩ መሪዎች፣ ሌት ተቀን በግድቡ ሥራ ተሠማርተው የደከሙ ሠራተኞች፣ በየመድረኩ ኢትዮጵያን ወክለው ስለ ግድቡ ሲደራደሩ የነበሩ የቁርጥ ቀን ልጆች ይሄን እለት እንድናይ አድርገዋል። ከእለት ጉርሳቸው ቀንሰው መዋጮ ያዋጡ ዜጎቻችንና በእውቀታቸው ሲያግዙ የነበሩ ባለሙያዎችን ስም እንዘርዝር ብንል ቀናት ይፈጃል። እንዲሁ ባጠቃላይ የቀድሞዎቹን ጠቅላይ ሚኒስትሮች እና በግድቡ ግንባታ ሂደት ላይ ቀጥተኛም ተዘዋዋሪም ተሳትፎ የነበራቸውን አካላት በሙሉ፣ በዲፕሎማሲውም መስክ ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረጉትን ጭምር ከልብ ሳላመሰግን አላልፍም። እኛ እንደሀገር የመውቀስና የመኮነን እንጂ የምስጋና ባሕል በመጠኑ ይጎለናል። ትልቁ ወንዛችን ዓባይ ጭምር የዘመናት ወቀሳችን ሰለባ ነበር። በእርግጥ ወቀሳው ያለምክንያት አልነበረም፤ እኛን ትቶ ሌሎችን ሲጠቅም ኖሯል። ከእንግዲህ ዓባይም ለእናት ሀገሩ መልካም አስተዋጽኦ ለማበርከት ከጫፍ ደርሷልና አፍ አውጥተን ልናመሰግነው ግድ ይለናል።





ኢትዮጵያውያን ዓባይን በተመለከተ ሲመኙ ከኖሩበት ረዥም ዘመን አንጻር፣ የሕዳሴው ግድብ ቢያንስ የዛሬ ሁለት መቶ ዓመት መገደብ ነበረበት። መሪዎቻችንና ሕዝባችን ፍላጎት ነበራቸው። ሁኔታዎች ግን አልሠመሩላቸውም። እኛ ግን እነርሱ ያሰቡትን አደረግነው፤ የተመኙትን አየነው፤ የናፈቁትን አሳካነው።

ድል ያስፈነድቃል። በድል ላይ እየፈነደቁ ተንጠልጥሎ መቅረት ግን ሁለት ጉዳት አለው። አንድም የተያዘውን ድል ያስነጥቃል፤ ሁለትም ለሌላ ቀጣይ ድል በር ይዘጋል። ለዚህ ደግሞ ሁነኛ መፍትሔው ያገኙትን ድል አድንቆና አመስግኖ፤ ወደሌላኛው ምዕራፍ ተሻግሮ ማለፍ ነው - ልክ ደረጃ እንደመውጣት። የደረስንበትን የደረጃ እርከን ለቅቀን ወደ ቀጣዩ የደረጃ እርከን ካልወጣን፣ ወደ ኋላ መመለሳችን አይቀሬ ነው። ወደ ከፍታ መጓዝ የሚቻለው ከሚናፍቁት የደረጃ እርከን ለመድረስ በመጓዝ፤ ሲደርሱበት ደግሞ እርሱን ትቶ ወደቀጣዩ በማለፍ ነው።

## የተከበራችሁ የሀገራችን ሕዝቦች፣

ታላቁ የሕዳሴው ግድብ በትልቁ እንዳስተማረን አምናለሁ። የማሸነፍ ምስጢሩ ተስፋ አለመቁረጥ መሆኑን፣ ሀገራዊ ስኬት የሚመዘገበው በትብብር መሆኑን፣ ብልጽግና የትውልድ ቅብብሎሽ ያለበት ተከታታይ ሥራ መሆኑን፣ ዋጋ ሳይከፍሉበት የሚሳካ አንድም ተወዳጅ ነገር አለመኖሩን ግድባችን አሳይቶናል፤ በሚገባ አስተምሮናል። በአስተዳደርና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታው ሂደትም አሸናፊነት ሊመዘገብ የሚችለው በትብብር፣ በትውልድ ቅብብሎችና ተስፋ ሳይቆርጡ ትግል በማድረግ መሆኑ ግልጽ ነው። በተበታተነ አቅምና

እርስ በእርሱ በሚሳሳብ የገመድ ጉተታ ተያይዞ መውደቅ እንጂ ተያይዞ ማደግና መገንባት እንደማይቻል ሕዳሴ ግድባችን ሕያው ምስክር ነው።

ለሚለያዩን ዕድል ካልሰጠን፣ ለሚያጋጩን በር ካልከፈትን፣ ለሚያጋድሉን ፊት ከነሣን ገና ብዙ ድሎችን በስኬት እንፈጽማለን። ከሕዳሴው ግድብ የሚስተካከሉ ብቻ ሳይሆን፣ ከእርሱ የሚበልጡ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችንም አስበን፣ ዐቅደን፣ ሠርተንና አጠናቅቀን ብልጽግናችንን እውን እናደርጋለን። ሁሌም አባቶቻችን የሠሩትን ታሪክ በመናገር ሳይሆን የራሳችንን አሻራ ጥለን በሠራነው ታሪክ መኩራት እንችላለን። ለዚህም ቁርጠኝነታችንን በተግባር ማሳየት ይኖርብናል።

ማሳካት ከሚገቡን ጉዳዮች መካከል ግድባችን አንዱ ቢሆንም ከፊታችን ገና ብዙ የቤት ሥራዎች አሉ። ሌላው ቀርቶ የግድቡ ጉዳይ ሙሉ ለሙሉ ያለቀና የደቀቀ ጉዳይ አይደለም። ገና ብዙ የዲፕሎማሲ ሥራዎች ይቀሩናል። ገና ሐይል ማመንጨት አልጀመረም። አሁን ያሳካነው የመጀመሪያውን ዓመት ውኃ ሙሌት ነው። ይሄም በመጪው ዓመት ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ተርባይኖች ሐይል እንድናመርት ያስችለናል። በቀጣይ ሁለት ዓመታት ትኩረት ሰጥተን ከሠራን በ2015 ዓ.ም ግድቡ ሙሉ በሙሉ ሐይል ማምንጨት በሚያስችል ደረጃ ላይ ይደርሳል። እስከዚያው ቀሪ ግንባታዎችን በፍጥነት ማከናወን፣ ለግድቡ የሚሆነውን ገንዘብ ባለማቋረጥ ማሰባሰብ፣ ዲፕሎማሲያዊ ትግላችንን በበቂ ሁኔታ መወጣት ይጠበቅብናል። ሌላው ወሳኝ ተግባር በዝናብ እጥረትም ይሆን በደለል ምክንያት ወደፊት ግድባችን በሙሉ አቅሙ ጥቅም እንዳይሰጠን የሚያደርጉ እንቅፋቶችን ከወዲሁ ገለል ለማድረግ መረባረብ ነው። ለዚህም ‹‹ባንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ›› መምታት





የሚያስችለውንና ቀደም ብለን የጀመርነው የአረንጓዴ አሻራችንን በስኬት ማጠናቀቅ ያስፈልጋል።

ወንዞቻችን እንዲጠቅሙን ከፈለግን የደን ብርድ ልብስ መልበስ አለባቸው። አይናችን እያየ ወንዞቻችን ለም አፈራችንን ተሸክመው እንዲሄዱ መፍቀድ የለብንም። አባቶች ሲናገሩ “ችግኝ የመትከያው ምርጡ ጊዜ የዛሬ ሀያ ዓመት ነበር፣ ሁለተኛው ምርጥ ጊዜ ደግሞ አሁን ነው” ይላሉ። እውነት ነው። በዝናብ ማጠር ምክንያት ግብርናችን በያመቱ የድርቅ ስጋት ሲደቀንበት ኖሯል። አሁን ደግሞ ስጋቱ ከግብርናችን አልፎ ወደ ኤሌክትሪክ ሐይል ምንጫችን ብሎም የአምራች ዘርፉ መሸጋገሩ አይቀርም። ስለዚህ የሕዳሴውን ግድባችንን ሙሉ ለሙሉ ከማጠናቀቃችን በፊት በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ችግኞችን ተክለን፣ ተንከባክበን፣ አጽድቀን ዛፍ ማድረግ አለብን። የችግኞች ዘመን አልፎ የደኖች ዘመን መምጣት አለበት። የሐምሌ ወር ሳይጠናቀቅ እያንዳንዱ ቤተሰብ አረንጓዴ አሻራውን ማሳረፍ አለበት።

## ውድ ኢትዮጵያውያን፣

ይሄ ዓመት  የሕዳሴ ቤተሰብን የምንመሠርትበት ዓመት ቢሆን መልካም ነው። የዚህ ዓመት የሕዳሴ ቤተሰብ ሦስት ነገሮችን ማሳካት ይጠበቅበታል። ቀሪ ግንባታዎችን ለማከናወን የሚያስችል ገንዘብ ማሰባሰብ፤ አረንጓዴ አሻራውን ማሳረፍ እና የሕዳሴውን ዘመን ለማየት ራሱን ከኮሮና የሚከላከል መሆን አለበት።

ሁላችሁም እንደምታውቁት በኮሮና ቫይረስ የሚያዙና የሚሞቱ ወገኖቻችን ከእለት ወደ እለት ቁጥራቸው እየጨመረ ነው። ከሦስት

ወራት በፊት በቀን የሚያዙ ሰዎች በጣት ይቆጠሩ የነበሩ ሲሆን አሁን ቁጥሩ በቀን ወደ ሰባት መቶና ከዚያ በላይ አሻቅቧል። ኮሮና ከባድ አደጋ ይደቅንብናል ሲባል ውሸት አይደለም። በሀገራችን ኮሮና ሰዎችን እየገደለ ነው፤ ብዙ ሥራዎችን አስተጓጉሏል። ከእውነታው መሸሽ እውነታውን አያስቀረውም። በሁሉም መስክ ተጋፍጠን ኮሮናን ማሸነፍ እስካልቻልን ድረስ ሸክማችንን ይበልጡኑ እያጠነከረብን ይመጣል። ወረርሽኙን ከሀገራችን እስካላጠፋነው ድረስ የምንጠፋባቸውን አያሌ ችግሮች ይፈለፍልብናል። ባግባቡ ካሰብንበት ከኮሮናና ወረርሽኙ ከሚያስከትለው ችግር ለመውጣት መፍትሔው እጅግ ከባድ አይደለም። የጥንቃቄ ሕግጋትን ባግባቡ እስከፈጸምን፣ የተቸገሩ ወገኖቻችንን እስከደገፍን እና ምርትና ምርታማነትን መጨመር እስከቻልን ድረስ የከፋ ፈተና ላይገጥመን ይችላል። በተቃራኒው ችላ ብለን ለበሽታው መስፋፋት ምክንያት የሚሆኑ ተግባራትን ከፈጸምን ውጤቱን በጥቂት ወራት ውስጥ ባይናችን እናያለን።

በብዙ ምክንያቶች የዘንድሮው ክረምት ከዚህ በፊት እንዳለፉት ክረምቶች አይደለም። መደበኛ ሥራዎችን ተዝናንተን የምንፈጽምበት ወቅት አይደለም። ጊዜ የማይሰጠውን ግብርናችንን ነጥለን እንኳ ብንመለከት በተለየ ስትራቴጂ ወሳኝ ተግባራትን ለመፈጸም መንቀሳቀስ ይገባናል። አንድም መሬት ጦም እንዳያድር፤ አንድም አርሶ አደር ግብአት አጥቶ እንዳይቸገር፤ አንድም የግብርና ባለሞያ ቁጭ ብሎ እንዳይውል ማድረግ ይኖርብናል። ወቅታዊው ወረርሽኝ የምግብ እጥረት እንዳያስከትል ቀድመን ነው መሥራት ያለብን። እንኳን ገጠሩ ይቅርና ከተማው ለግብርና ትኩረት መስጠት አለበት። በየግቢያችን የሚገኙ መሬቶች ቢያንስ የጓሮ አትክልት ሊይዙ ይገባቸዋል።





በተመሳሳይ በማኑፋክቸሪግ ዘርፍ፣ በቱሪዝም ዘርፍ፣ በማዕድንና ቁፋሮ ዘርፍ እና በሌሎችም ጥንቃቄ ሳይጓደል ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው። እንዲህ ካደረግን ያለ ጥርጥር ኮሮናን ብቻ ሳይሆን ወረርሽኙ ጥሎት የሚያልፈውን ጠባሳ ከማንም ሀገር በተሻለ እኛ መሻገር እንችላለን። ከኮሮና ጋር የምንገጥመውን ትግል በተግባር እንጂ በምኞት ልንወጣው አንችልም፤ ችግሩ ቀላል እንዲሆንልን በመጨነቅ ሳይሆን እኛ ተሽለን ስለምንገኝባቸው መንገዶች በማሰብ ነው እያንዳንዱን እንቅፋት መሻገር የምንችለው። ለዚህ ደግሞ ከሕዳሴ ግድባችን የበለጠ ጥሩ ማሳያ ከየትም አይመጣም። በድጋሚ እንኳን ደስ ያለን! አመሰግናለሁ!!

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና**
**ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# የዒድ አል - አድሐ በዓልን በማስመልከት የተላለፈ መልእክት

**ሃምሌ 23፣ 2012ዓ.ም.**

ለመላው ሙስሊም ወገኖቼና ለተቀረው ኢትዮጵያዊ ሁሉ፣ እንኳን ለ1441 ኛው ዓመተ ሒጅራ፣ ለታላቁ የዒድ አል-አድሐ / የዐረፋ በዓል በሰላም አደረሳችሁ፣ አደረሰን ለማለት እወዳለሁ። ዒድ ሙባረክ!

የዘንድሮው የዐረፋ በዓል በተለያዩ ምክንያቶች ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ለየት ያለ ትርጉም አለው። ከዓመታት ግንባታና የዲፕሎማቲክ ትግል በኋላ፣ የመጀመሪያውን የሕዳሴ ግድብ የውኃ ሙሌት ባሳካንበት ጊዜ የሚከበር በመሆኑ በዓሉን በከፍተኛ ሐሴት ውስጥ ሆነን ነው የምንቀበለው። ሙስሊሙ ወገናችን ከአረቡ ዓለም ጋር ባለው የሐይማኖት፣ የባህልና የቋንቋ ትስስር ምክንያት ከመካከለኛው ምስራቅና ከአረብ ሀገራት ጋር በተያያዘ ሀገራችን ኢትዮጵያ ለሚገጥሟት ልዩ ልዩ የዲፕሎማሲ ትግሎች ወሳኝ ሚናዎችን ሲጫወት ቆይቷል። የሕዳሴ ግድባችን እውን እንዲሆንም ገንዘብ ከማዋጣትና ጠቃሚ ሐሳቦችን ከማበርከት ባለፈ በዲፕሎማሲያዊ ተጋድሎው ሒደት ግንባር ቀደም በመሆን የሁላችንም የሆነችው





ሀገራችንን ለማኩራት በሀገር ውስጥና በውጭ የሚኖሩ ሙስሊሞች መሥዋዕትነት መክፈላችሁን እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በክብር ያየዋል። ላበረከታችሁት አስተዋጽኦ በኢፌዴሪ መንግስትና በመላው ኢትዮጵያዊ ስም ሳላመሰግን አላልፍም።

ዒድ አል አድሓ፣ በዓረብኛ “የመሥዋዕት በዓል” ማለት ሲሆን፣ ነቢዩ ኢብራሂም ለጌታው የነበረውን ፍጹም እምነት፣ በቆራጥነት ያሳየበት ልዩ ቀን ነው። ፈጣሪ አላህ፣ (ሱብሀነሁ ወተአላ) ልጅህን መሥዋዕት አቅርብልኝ ብሎ በጠየቀው ጊዜ ኢብራሂም አንድዬ ልጁን፣ እስማኤልን ወደ መሠዊያው ወስዶታል። ፈጣሪም የኢብራሂምን ፍጹም እምነት ተመልክቶ፣ ሙክት እንደሰጠውና በልጁ ምትክ ሙክቱ እንደተሠዋ ሙስሊሞች ያምናሉ። የገዛ ልጁን ለመሠዋት ዝግጁ ከመሆን የበለጠ ቆራጥነት የለምና፣ ዒድ አል-አድሐ “የመሥዋዕት በዓል” እየተባለ ይጠራል።

ከልጅ በላይ የቀረበና የሚወደድ ነገር እንደሌለ የወለደ ሰው ሁሉ ያውቀዋል። እንደ ኢብራሂም ያሉ መልካምና ቆራጥ ሰዎች፣ ለእምነታቸው ሲሉ አንድዬ ልጃቸውን መሥዋዕት ለማድረግ ይዘጋጃሉ። መልካም ሰዎች እንደ ኢብራሂም ናቸው። ለመልካም ዓላማ ሲሉ እጅግ ውድ የሆነ ሀብታቸውን፣ ልጃቸውን ሲሰጡ ቅር አይላቸውም። በተቃራኒው ክፉዎች ለእኩይ ዓላማቸው ወንድማቸው ላይ በትር ያነሳሉ። እህታቸው ላይ፣ ልጃቸው ላይ፣ እናትና አባታቸው ላይ ሲጨክኑ ዐይናቸውን አያሹም። ከእኛም መካከል አንዳንዶች ለተራ ቁሳዊ ሀብቶች፣ ለትንንሽ የፖለቲካ ድሎችና ለሥልጣን እኩይ ተግባራትን የሚፈጽሙ አሉ። ለሆዳቸው ሲሉ ቤተሰባቸውን፣ ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ሀገርና ወገናቸውን ለመሸጥ ሲዘጋጁ እንደማየት

የሚያሳዝን ነገር የለም። እንዲህ የሚያደርጉ አካላት ከክፉ ሥራቸው እንደሚለሱ ሕዝበ ሙስሊሙ በጥበብ እንዲያስተምራቸው አደራ ለማለት እወዳለሁ።

**የተከበራሁ ሙስሊም ወንድምና እህቶቼ፣**

እንደሚታወቀው የዒድ አል-አድሐ በዓል፣ ከአምስቱ የእስልምና መሠረቶች መካከል አንዱ የሆነውና ማንኛውም ሙስሊም የገንዘብና የጉልበት ዐቅሙ እስከፈቀደ ድረስ በሕይወት ዘመኑ ቢያንስ አንዴ ሊያከናውነው የሚገባው፣ የሐጅ ሥርዓት የሚፈጸምበትም ቅዱስ በዓል ነው። ያም ሆኖ የዘንድሮው የዐረፋ በዓል የሚከበረው ዓለምን እየፈተናት ያለውን የኮሮና ወረርሽኝ በምንዋጋበት ወቅት ነው። በዚህም ምክንያት በዓሉን ከዚህ ቀደም ካየናቸው በዓሎች ለየት ባለ መልኩ እንድናከብረው የሚገፋፉ ብዙ ምክንያቶች አሉ። ለወትሮው በዐረፋ በዓል ሕዝበ ሙስሊሙ በጋራ ሆኖ ለማክበር ዘመድ ወደ ዘመዱ፣ ልጆች በወደ ቤተሰቦቻቸውና ወደ ሀገር ቤት መሄድ የተለመደ ነበር። ከዚህም ከፍ ሲል በሚሊዮን የሚቆጠሩ የዓለም ሙስሊሞች የዐረፋ በዓልን ለማክበር ወደ ቅዱሱ ሥፍራ ወደ ሳዑዲ ይጎርፋሉ። ጥቁሩ፣ ነጩ፣ አፍሪካዊው፣ እስያዊው፣ አውሮፓዊውና ሌላውም ከያቅጣቸው ተሰባስቦ ዒድ አል-አድሐን በጋራ ሲያከብረው ኖሯል። ዘንድሮ ግን ነገሮች እንደቀድሞው ሊሆኑ አልቻሉም። መሰባሰብን የማይፈቅድ፣ አካላዊ መቀራራብን የሚከለክል ወረርሽኝ በማጋጠሙ ምክንያት በዓሉን በጥንቃቄ እንድናከብረው ግድ ብሏል።





ሁላችንም እንደምናውቀው በአሁኑ ወቅት በኮሮና ቫይረስ የሚያዙ፣ የሚታመሙና የሚሞቱ ወገኖቻችን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ ነው። ይህ ጉዳይ የሁላችንም ጉዳይ መሆን አለበት። የትምህርታችንና የጸሎታችን ጉዳይ መሆን አለበት። ወረርሽኙን መከላከልን እንደ አንድ ሐይማኖታዊ ግዴታ ልንወስደው ይገባል። ወረርሽኙ የፈጠራቸውን ክፍተቶች ለመድፈን ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት ይኖርበታል። አቅማቸው ደከም ያሉ ወገኖቻችንን እንድንደግፍ፤ ማዕዳችንን እንድናጋራ፤ በዚህ ፈታኝ ወቅት ለተቸገሩ ወገኖቻችንን አለኝታቸው መሆናችንን እንድናሳያቸው ስል ጥሪዬን አስተላልፋለሁ። ዒድ አል-አድሐ የመስዕዋትና የመዳን በዓል እንደመሆኑ መጠን ወደ ሐጅ የሚሄደው ሰው ብቻ ሳይሆን የማይሄደውም ጭምር ‹‹ኡድሒያ›› የማረድ ግዴታ እንዳለበት የእምነቱ አስተምሮ ያዛል። በዚህ አስተምህሮ መሰረት ለኡድሒያ ከሚታረደው አንድ ሦስተኛውን ለድሖችና ለተቸገሩ ወገኖቻችን በማካፈል በተለይም ይሄንን አስቸጋሪ ወቅት በስኬት እንደምንሻገረው አልጠራጠርም።

በሌሎች አጋጣሚዎች እንደገለጽኩት፣ በዚህ ወቅት ማከናወን ከሚገቡን ሐገራዊ ተግባራት መካከል ሌላው ከሕዳሴ ግድብ ጋር የተያያዘ ነው። በዚህ ወቅት ቀሪ የሕዳሴ ግድባችን ሥራዎች ላይ እንድንረባረብና የአረንጓዴ አሻራችንን በስኬት እንድንወጣ ከሁላችንም ይጠበቃል። አረንጓዴ አሻራችንን ከአሁኑ ማሳረፍ ካልቻልን የምንገነባው የሕዳሴ ግድብን ጨምሮ ሌሎች የልማት ሥራዎቻችን ሁሉ እድሜ አይኖራቸውም።

ኢትዮጵያ አረንጓዴ ሀገር መሆን አለባት። ድርቅን የምትቋቋም፣ ምንጮቿ የማይነጥፉ፣ አራዊቷና አዕዋፏ የማይሰደዱ ሀገር መሆን

አለባት። ይህ እንዲሆን ሕዝበ ሙስሊሙ ወሳኙን ሚና እንዲጫወት አደራ እላለሁ። በቀሪ የሕዳሴ ግድብ ግንባታና የዲፖሎማሲ ሥራዎች ላይ ርብርብ በማድረግ ቀጣዩ የዒድ አል-አድሐ በዓል ሲከበር ግድባችን እጅግ ከፍ ወዳለ ምእራፍ ተሸጋግሮ እንደሚሆን ቅንጣት አልጠራጠርም።

**በድጋሚ ለመላው ሕዝበ ሙስሊም፣ እንኳን ለዒድ አል-አድሐ በዓል በሰላም አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ!**

**አመሰግናለሁ!**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**





# በየአካባቢያችን የሚገኙ የግጭት ነጋዴዎችን በጋራ እንከላከል

2012ዓ.ም.

**የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ሕዝቦች**
**ክቡራትና ክቡራን**

ሁላችንም እንደምናውቀው የፖለቲካ መዝገበ ቃላችን የተሞላው ‹ምታው፣ ደምስሰው፣ ቁረጠውና ፍለጠው› በሚሉ የሞት ቃላት ሲሆን በመሳደድና ማሳደድ ዙሪያ መሽከርከር ከጀመረ ዘመናት ተቆጥረዋል። "ድርጊት ሲደጋገም ልማድ ይሆናል" እንዲሉ አሁን ያለው የፖለቲካ ባህላችን የተቀዳው ባንድ ወቅት እንደቀልድ በጀመርናቸው የሴራ፣ የመገዳደልና በጎራ ተከፋፍሎ ድንጋይ የመወራወር አጉል ልማዳችን ነው። በያጋጣሚው ሲነገር፣ ሲጻፍና ሲዜም የኖረው ይሄ የተበላሸ ፖለቲካችን በትውልድ ጅረት ተንከባልሎ እነሆ ዛሬ ላይ ደርሷል።

ይሄው እኛም እንደ መልካም ውርስ የመጠላለፍና የመገዳደል ባህልን ተቀብለን የየእለት ኑሯችን በቆምንበት መርገጥ፣ ዛሬም ነገም አንድ ቦታ

መሽከርከር ሆኗል። ሀገራችንን ወደፊት ለማራመድ የምንሻ ከሆነ ይሄንን ክፉ ውርስ አሽቀንጥረን መጣል ይኖርብናል፤ በመጥፎ ባህል ያደፈ ካባችንን አውልቀን በምትኩ በጋራ የምንበለጽግበትን ካባ ልንደርብ ይገባል። ለውጥ ሰዎችን በሰዎች፣ መሪዎችን በመሪዎች የመቀየር ሂደት ብቻ አይደለም። የተበላሸውን የፖለቲካ ሥነ ልቡና፣ የፖለቲካ ባህልና የፖለቲካ ሥርዓት ጭምር በአዲስ የመቀየር ጉዞ ነው። ተቋሞቻችንን፣ የእርስ በርስ ግንኙነታችንና የፖለቲካ ቋንቋችንን ጭምር መለወጥ ይገባናል። ይሄን ማድረግ ከቻልን እንደሀገርና እንደሕዝብ ወደ ምናስበው የብልጽግና ጎዳ እንሻገራለን። ካልሆነም የኋቀርነት አዘቅት ውስጥ ስንደፋደፍ ዘላለም መኖራችን ነው።

ሁላችንም ልብ ካልን ምንግዜም ከመከራ የሚያተርፉ አካላት በዙሪያችን እንዳሉ እንረዳለን። የከብት እልቂት ለገበሬ መከራ ቢያመጣም ለጅብ ግን ሠርግና ምላሽ ነው። የዶሮ እልቂት ለባለቤቱ ኪሳራ ለሸለምጥማጥ ደግሞ ትርፍ ነው። የሁለት በጎች ጠብ ጥቅም ካስገኘ የሚጠቀመው ተኩላው ነው። የሁለት እርግቦች ግብግብ አንጋጦ ለሚጠብቃቸው ድመት በረከት ነው። ምንም መልፋት ሳይጠበቅባቸው ድመቱና ተኩላው በእርግቦቹና በበጎቹ ጸብ ምክንያት በቀላሉ ሆዳቸውን ይሞላሉ። በተመሳሳይ በሰዎች ጸብም የሚያተርፉ ሞልተዋል። በእኛም ሀገር አሉ። አሁንም እርስ በእርሳችን እያጋጩን ከፍተኛ ጥቅም የሚያገኙት እነዚሁ ከቅርብም ከሩቅም ሆነው የሚጠብቁ የግጭት ነጋዴዎች ናቸው።

ለለውጥ ስንታገል ዋነኛው ዱላ የሚበዛብንም ከመከራችን ሲያተርፉ ከነበሩ አካላት እንደሆነ ግልጽ ነው። በሁላችንም ቤት ለዘመናት





የተዘራ የልዩነት መርዝ አለ። አሁን እዚህም እዚያም ሲፈነዳ የምናየው እሱን ነው። ዛሬ ቢፈነዳም ፈንጂው ከተቀበረ ግን ቆይቷል። ማህበራዊ የልዩነት ፈንጂው ምን እንደሆነ፣ የት የት እንደተቀበረ፣ በማን እንደተቀበረ ማወቅ ለአንድ አካል የሚተው የቤት ሥራ ሳይሆን የእያንዳንዳችን ኃላፊነት ነው። ማወቅም ብቻውን በቂ አይደለም፤ አንድ በአንድ እየተቀለቀመ መክሸፍ ይኖርበታል። ሕዝብ እንዲበጣበጥ፣ አንዱ ብሔር በሌላው ላይ እንዲነሣ፣ አንዱ ሌላውን እንዲገድል፣ ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያውያንን ንብረት እንዲያወድሙ፤ የጥላቻና የሞት ድግስ ቅስቀሳዎች በየሚዲያው እንዲካሄዱ የሚያደርጉት ፈንጅ ቀባሪዎቹ የግጭት ነጋዴዎች ናቸው። አንዳንዶች ከእነሱ ጋር ተባብረው በሕዝብ ላይ ፈንጅዎቹን ያፈነዳሉ። ሳያውቁ ቆመውበት የሚፈነዳባቸውም ይኖራሉ። አንዳቸውም ጉዳትን እንጂ ጥቅም አያስገኙልም። ከእንግዲህ ይበቃል፤ በጉያችን ይዘን ዘወትር መሰቃየት የለብንም።

## የሀገሬ ልጆች፣

አንገትን እንደ ሰጎን አሸዋ ውስጥ በመቅበር መፍትሔ የምናገኝበት ጊዜ ላይ አይደለንም። አጥፊዎቹን ፊት ለፊት እስካልተጋፈጥናቸው ድረስ የሚያደርሱትን ችግር በመሸሽ ብቻ አናመልጠውም። ላለማየት ጭንቅላትን ጎሬ ውስጥ በመቅበር ዘላቂ መፍትሔ ይገኛል ማለት ዘበት ነው። ዛሬ ጎረቤታችንን የጎበኘ እሳት ነገ ቤታችንን ማንኳኳቱ አይቀርም። ተነጣጥሎ አንድ ባንድ ማገዶ ከመሆን ይልቅ ተባብሮ የተለኮሰውን እሳት እስከወዲያኛው ማሰናበት ይበጃል። ለዚያም

ነገሮችን በጥንቃቄ መመልከት፣ ትዕግሥትና አርቆ አስተዋይነት በተሞላበት መልኩ መገምገምና ጥበብ ባለው ሁኔታ ተንቀሳቅሶ ዘላቂ መፍትሔ መስጠት ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል።

ማን ነው በየአካባቢያችን ሰላም እየነሳን ያለው? ከነማን ጋር ሆኖ ነው የሚበጠብጠን? ለምንድን ነው የሚበጠብጠን? ጥቂት ነውጠኞች የጫሩት እሳት ብዙኃኑን ሲለበልብ ለምንድን ነው እኛስ ማስቆም ያልቻልነው? ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ከያንዳንዳችን ይጠበቃል። እሳት ለኳሾቹ እነማን እንደሆኑ፣ ማገዶ እያቀበሉ እሳቱን የሚያቀጣጥሉት እነማን እንደሆኑ፣ ዳር ቆመው የሚያዩትና አብረው የሚሞቁት ጭምር እነማን እንደሆኑ ልናውቅ ይገባል። በመንግስት በኩል እነዚህን ጥያቄዎች በየደረጃው ለመመርመርና አስፈላጊውን ሕግ የማስከበር ርምጃ ለመውሰድ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ቁርጠኞች ነን።

እሳቱን ማጥፋት ሲገባቸው በቸልታ የሚያልፉት ሰዎች በአንድም በሌላም መንገድ መከራችንን የሚያበዙብን መሆናቸው አያጠያይቅም። የሚወድመው የሀገር ሐብት፣ የሚሞተው የሁላችንም ወገን ነውና ሕጋዊና ሞራላዊ ሀላፊነት እያለባቸው አይተው እንዳላዩ የሚያልፉ አካላት ፈጽሞ ከተጠያቂነት አያመልጡም።

የተጋረጠብን ችግር እስከወዲያኛው እንዲወገድ ወላጆች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሀይማኖት አባቶች እና የያካባቢው የባህልና የሐሳብ መሪዎች አስተዋጽኦችሁ ከፍተኛ ከመሆኑ አኳያ ያለማመንታት ሚናችሁን እንድትወጡ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ። ከምንም በላይ ሕዝባችን አስፈላጊውን ሁሉ ከማድረግ መቆጠብ እንደሌለበት





ሊታወቅ ይገባል። እያንዳንዱ ዜጋ ጥፋተኞቹ በማስረጃ ለፍርድ እንዲቀርቡ የበኩሉን ኃላፊነት መወጣት አለበት፤ ከሕግ አስከባሪዎች ጋር ተባብሮ መሥራት፣ የመንደሩንና የከተማውን ሰላምና ልማት ተደራጅቶ መጠበቅ አለበት። በየአካባቢው የተለየ እንቅስቃሴ ስናይ ለምን? ብለን ልንጠይቅ፤ እነማን እንደሆኑ ልናውቅ፤ ከጸጥታ አካላት ጋር በመሆን አጥፊዎችን ለሕግ ልናቀርብ ይገባል። ጎረቤቶቻችንን፣ የልማት ተቋማትን፣ የንግድ ድርጅቶችን፣ ሕዝባዊ ንብረቶችን፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን፣ የእምነት ተቋማትን፣ የትምህርትና የጤና ተቋማትን በጋራ እስካልጠበቅናቸው ድረስ ነገ የጉዳቱ የመጀመሪያ ሰለባዎች እኛው ስለመሆናችን ነጋሪ አያሻንም።

ለሚያልፍ ጊዜ የማያልፍ ጠባሳ እንዲቀመጥብን መፍቀድ የለብንም። የትላንቶቹ ጠበሳ ስላቆዩልን እኛ የዛሬዎቹ ምን ያህል አበሳ እያጨድን እንደሆነ ሁላችንም የሚገባን ይመስለኛል፤ ስለሆነም ከዚህ ስህተት ተምረን ዳግም አበሳው ወደ ልጆቻችን እንዳይሻገር ማድረግ የእያንዳንዳችን ኃላፊነት ነው። በጉያችን ታቅፈናቸው የሚዘርፉን፣ የሚያቃጥሉን፣ የሚያበጣብጡንና የሚያገዳድሉን ሰዎች የጊዜ ጉዳይ እንጂ የእጃቸውን ማግኘታቸው፤ ከእነሱ አልፎ በልጆቻቸው በኩል ብድሩን መክፈላቸው አይቀሬ ነው።

## ውድ ኢትዮጵያውያን፣

ሀገሩንና ሕዝቡን እንደሚወድ ዜጋ ከእያንዳንዳችን ሁለት ነገሮች ይጠበቁብናል። ከተጎዱ ወገኖቻችን ጎን መቆምና አለኝታነታችንን ማሳየት አለብን። የቦታ መቀያየር ይሆናል እንጂ እኛም አንድ ቀን

በተጎጂዎች ቦታ የማንቆምበት ምንም ምክንያት የለም። ስለሆነም በሞራል፣ በኢኮኖሚና በባህላዊ መንገድ ደግፈን ተጎጂዎችን ወደነበሩበት እንመልሳቸው። የተቃጠለና የወደመ ንብረታቸውን ለመተካት አጋርነታችን እናሳያቸው፤ ቁስላቸው ጠገግ እስኪል እናክማቸው፤ የፈረሰ ቤታቸውን እንገንባላቸው። የማይተካ ሕይወታቸውን ለተነጠቁ ዜጎቻችን ጸሎት፣ ለሟች ቤተሰቦች መጽናናት እንዲያገኙ እናድርግ። በሁሉም ዘርፍ ያሉ መሪዎች ለዚህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ ግንባር ቀደም ሆነው መልካም አርአያነታቸውን እንደሚያስመሰክሩ እተማመናለሁ።

ሰላማችንን ለማስጠበቅ ደፋ ቀና ሲሉ የተሰዉት ፖሊሶችና የጸጥታ አስከባሪዎች ያለእነሱ ትጋትና መስዕዋትነት የሚደርሰውን አደጋ በቀላሉ መቆጣጠር ባልቻልን ነበር። ለሀገርና ለሕዝብ ደህንነት ሲሉ የቆሰሉና የሞቱ የሕግ አስከባሪዎች የከፈሉት የሕይወት ዋጋ በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ በክብር የሚታተም ስለመሆኑ አልጠራጠርም። ለቤተሰቦቻቸው፣ ለወላጅና ለልጆቻቸው ጭምር ተገቢውን ክብር እንሰጣለን።

በመንግስት በኩል ዐቅም በፈቀደ መጠን የተጎዱትን ንጹሐን ዜጎችና የሕግ አስከባሪዎች ለመደገፍና ለማቋቋም ይሠራል። በሌላ በኩል የችግሩን ነዳፊዎች፣ ጠንሳሾች፣ ተልዕኮ ተቀባዮችና ፈጻሚዎችን በየደረጃው መርምሮና አጣርቶ ለሕግ ያቀርባል። ይሄን መሰል ክሥተት ዳግም እንዳይፈጠርም ማኅበረሰቡን ያሳተፈ የጸጥታ አካላት ሥምሪትን አጠናክሮ ይቀጥላል።





ከዚህ በተረፈ ሁላችንም ውድመትና ጥፋት ከእንግዲህ በሀገራችን ላይ እንዳይደገም አምርረን እምቢ ማለት ይኖርብናል። ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ለፖለቲካ ትርፋቸው ሲሉ በየሚዲያው ‹በለው፣ በለው› የሚሉ አካላትን አሁን በግልጽ ነቅሰናቸዋል። በያካባቢያችን የሚገኙትን የግጭት ነጋዴዎች በሚገባ አውቀናቸዋል። ለጊዜው የተደበቁ የሚመስላቸውም በቅርቡ አደባባይ ይወጣሉ። እሳቱን ለኩሰው ጢሱ እንዳይሸታቸው መሸሽ፤ ፈንጂውን ወርውረው ፍንጣሪ ሳይነካቸው እስከመጨረሻው ማምለጥ አይችሉም። ሰላም ወዳዱ ሕዝባችን በእሳት እየተቃጠለና ሕይወቱን እየተነጠቀ ከእንግዲህ ይቀጥላል ማለት ዘበት ነው። አብሮነትን የሚፈልገው ዜጋችን፣ ለማደግና ለመበልጸግ ሌት ተቀን ደፋ ቀና የሚለው ሕዝባችን እየተጎዳ የግጭት ነጋዴዎቹ በምቾት አይቆዩም። በሕዝብ መከራ ካላተረፍን ለሚሉ፤ በምስኪን ዜጎች ሞት ሥልጣን ለመያዝ ለሚቋምጡ ራስ ወዳዶች ‹አሻንጉሊት› መሆን ከእንግዲህ ይበቃል። ሰላማችንና ልማታችን፣ ዕድገታችንና ብልጽግናችን ደንታቸው ካልሆኑ አካላት ጋር አበሳን እንጂ መልካም ነገርን ስለማናጭድ ከጉያችን ፈልቅቀን ብቻቸውን ይቆማሉ። ምክር ካልመለሳቸው መከራውን ፈልገዋልና በሚገባቸው መንገድ እንዲጓዙ እንተዋቸዋለን።

## ክቡራትና ክቡራን፣

የሐሳብ ልዩነት ጌጥ እንጂ እርግማን አይደለም። የተሰማንን መግለጽና ጥያቄዎቻችንን ያለ ስጋት ማንሳት እስካዛሬ የታገልንለት ወሳኙ መብታችን ነው። የዚያኑ ያህል በሀገራችን ነገሮች በሥርዓት

እንዲከናወኑ፣ የአንዱ ጥቅም የሌሎችን መብት እንዳይጋፋ እና ዜጎች ሰላምና ደሕንነታቸው ተጠብቆላቸው በሀገራችን እንዲኖሩ ማስቻል የሁሉም ኢትዮጵያዊ ምኞት ነው። ኃይል እስካልተቀላቀለበት ድረስ የሐሳብ ልዩነትን በሰላማዊ መንገድ ማስተናገድ ለዘመናት የታገንለትን መብት ከማጎናጸፍ ባለፈ የሌሎች ዜጎችን ሰላምና ደህንነት እንዲጠበቅ ያደርጋል። ሐሳብ የሚሞገተውም የሚሸነፈውም በሌላ ሐሳብ እንጂ በጉልበት፣ በነውጥና በዐመጽ አይሸነፍም፤ ተሸንፎም አያውቅም። መነጋገር፣ መከራከርና መወያየት እንጂ መጠፋፋት ሥልጣኔን አምጥቶ እንደማያውቅ ማገናዘቢያ አዕምሮ ያለው ሰው ሁሉ በቀላሉ የሚረዳው ሀቅ ነው።

ወገኖቼ፣ ሌላው መታወቅ ያለበት ጉዳይ የምንገኝበት ወቅት ብዙ ጊዜ የማይሰጡ ፈተናዎች ከፊታችን የተደቀኑበትና ወሳኝ ድሎችን የምናሳካበት ወቅት እንሆነ ሊረሳ አይገባም። የግብርና ሥራችንን ሳይስተጓጎል መከናወን አለበት። ምርታማነትን በመጨመር ከውጭ የምናስመጣውን የምግብ እህል ጭምር ሊተካ በሚቻልበት አኳኋን ሥራችንን መቀጠል ይኖርብናል። ከገጠር ግብርናችን በተጨማሪ የከተማ ግብርና ላይ የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ። አምራች ኢንዱስትሪው የኮሮናን ሁለንተናዊ ተጽዕኖ ለመቋቋም የሚያስችሉ ምርቶችን ለማምረት ሌት ተቀን መድከም አለበት። ከዚሁ ጎን ለጎን እየተባባሰ የመጣውን የኮሮና ወረርሽኝ ተቋቁመን ለመዝለቅ የጥንቃቄ፣ የምርመራና የሕክምና ተግባሮቻችንን ሳንዘናጋ እንፈጽማለን። የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታችንን እያጠናቀቅን በዕቅዱ መሠረት የመጀመሪያውን የውኃ ሙሌት ሥራችንን በተያዘለት የጊዜ





ሰሌዳ እናከናውናለን። በዚህ ክረምት ለመትከል ያቀድነው የአራት ቢሊዮን ችግኞች "የአረንጓዴ አሻራ" መርሐ ግብርም ጥንቃቄ ባልተለየው መልኩ ተግባራዊ እናደርጋለን።

ምንም እንኳን ዛሬ የደረሰብን ፈተና ቢያሳምመንም የምንሠራው ለሀገር ነውና የነገውን ማየት አለብን። ሕዝብና ሀገር ይቀጥላሉ። ትውልድ ይቀጥላል። የተሻለ ትውልድ ፈጥረን የተሻለች ሀገር ማስረከብ ደግሞ ከኛ የሚጠበቅ የቤት ሥራ ነው። ነገሮች ወደ በጎ እልህና ቁጭት እንጂ ወደ መጥፎ ቁዘማና ትካዜ ሊወስዱን አይገባም። ችግሮች ትምህርት እንጂ እሥር ቤት ሊሆኑብን አይገባም። ሕዝብ መሥራት ያለበትን ባግባቡ ከሠራ፤ መንግሥትም ያለበትን ኃላፊነት በብቃት ይወጣል። ከከባድ ክረምት ማዶ መልካም አዲስ ዘመን ቆሞ እንደሚጠብቀን ሁሉ የሌሊቱን ግርማ የሚያሸንፍና ጽልመቱን የሚደመስስ የብርሐን ጸዳል ማልዶ ወደኛ እንደሚገሰግስ ሁላችንም እናውቃለን።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# የዘመን መለወጫ ንግግር

**ጳጉሜ 5፣ 2012 ዓ.ም.**

**የተከበሩ ፕሬዝዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ፣
የተከበራችሁ የሁሉም ብሔር ብሔረሰብ
ተወካይ የሆናችሁ የሀገር ሽማግሌዎች፣
የተከበራችሁ የሀገራችን ህዝቦች፣**

ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ፣ አዲሱን ዓመት በአዲስ ራዕይና በአዲስ ተስፋ ለመቀበል እነሆ የዘመን መለወጫው የዋዜማ ምሽት ላይ ደርሰናል። ከፊታችን ምንም ያልተፃፈበት አዲስ የዘመን መጽሐፍ ተዘርግቶልናል።

**እንኳን ለ2013 ዓ.ም በሰላም አደረሰን አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ።**

ማለፍና መምጣት የሚባሉ ሁለት የጊዜ ማጠንጠኛዎች ባይኖሩ ኖሮ የሰው ልጅ ህይወት ትርጉም አልባ ይሆን ነበር። አስቸጋሪና ፈታኝ ጊዜያት ባያልፉ፣ ተስፋንና ጉጉት የሰነቁ ዘመናት ከፊት ባይመጡ፣ ህይወት ምን ትሆን ነበር? የሰው ልጅ ባለፈው ነገር ተቸክሎ እንዳይቀር





እንደገና በአዲስ ተስፋ፣ እንደገና በአዲስ ጉልበት፣ እንደገና በአዲስ ሐሳብ እንዲነሳ፣ አዲስ ዓመት አንዱ መድሐኒት ነው።

የአዲስ ዓመት ዋዜማ መንታ ፋይዳ አለው። ያለፈውን ወደኋላ ወስዶ እንድንገመግመው ያደርጋል። እንድናበጥረው፣ እንድናበራየው ያደርጋል። “እንኳን አደረኩት” የምንለውን ያህል፣ “ምነው ባላደረኩት” የምንለው ሞልቷል። እንኳን ተደረገ የምንለውን ያህል ምነው ባልተፈፀመ የምንለው ሞልቷል።

የአዲስ ዓመት ዋዜማ ወደፊት እንድንተልም ያደርገናል። ምንም ያልተነካ አንድ ሙሉ ዓመት አለ። ከፊታችን ከቻለ ያለፈውን የሚያጠራ፣ ካልቻለ መጪውን የሚያበራ፣ ሙሉ ድፍን ዓመት ከፊት ተዘርግቶልናል። ብልህ ይመጥቅበታል። ሞኝ ይወድቅበታል። እኛ ግን ከብልህዎች ወገን ልንሆን ይገባናል። ለዚህ ነው የ2013 ዓ.ም የአዲሱ ዓመት መሪ ቃላችን “ወደ ልዕልና እንመጥቃለን ገና” ያልነው። ባገኘናቸው ድሎች ረክተን አንቀርም። ባሳለፍናቸው ፈተናዎች ታስረን አንቆምም። “ወደ ልዕልና እንመጥቃለን ገና”። ሺህ መሰናክሎች አያቆሙንም። ሺህ ድሎች አያረኩንም። “ወደ ልዕልና እንመጥቃለን ገና”፤ የኢትዮጵያ ልክ ላይ አልደረስንም፤ እና መምጠቅ ወደ ከፍታ መዝለቅ ነው - ልክ እንደመንኮራኩር።

ልእልና ከከፍታ ይለያል። ልዕልና ክብር አለው። ልዕልና በቀላሉ ከሚደረስበት ከተለመደው መዳረሻ ወደ ላይ እጅግ መራቅን ያመለክታል። ከምድር ስበት አልፎ፣ ከሚታየው በላይ ተሻግሮ ከህዋው በላይ መምጠቅን ይፈልጋል። “እንመጥቃለን ገና ወደ ልዕልና” ስንል፣ መታፈርና መከበር ወዳለው ከፍታ ነው፤ እንደምድር ስበት የሚጎትቱን ችግሮቻችን ሁሉ አልፈን ለዚህ በተዘጋጁና በቆረጡ መጣቂዎች ባዘጋጀነው የ10 ዓመት ፍኖተ ብልጽግና መንኮራኩርነት ሕብረ

ብሔራዊ አንድነት ከተሰኘ ማምጠቂያ ሥፍራ "ብልጽግና" ወደ ተባለ፣ ደርሰን ወደ ማናውቀው የመንፈስ፣ የቁስና የኢኮኖሚ ከፍታ እንመጥቃለን ማለታችን ነው።

በ2050፣ የዛሬ 30 ዓመት፣ የኢትዮጵያ የልእለ ኃያልነት ዘመን ይሆናል። ከሁለት የአፍሪካ ኃያላን ሀገሮች አንዷ ትሆናለች - ኢትዮጵያችን። እንዲያው እንደ ኢትዮጵያ እርሱም አይበቃንም እያልን ነው።

## ውድ ኢትዮጵያውያን፣

2012 ዓ.ም፣ በደስታና ሐዘን፣ በህይወትና በሞት፣ በክብርና ውርደት፣ በኩራትና ሐፍረት የተሞላ ዓመት ነበር። የኢትዮጵያ ፈታኞች አሉን ያሉትን ድንጋዮች ሁሉ ወርውረዋል፤ የቀራቸው ያለ አይመስልም። የኢትዮጵያ ጀግኖችም የቻሉትን ሁሉ ለሀገራቸው ሰውተዋል፤ ትርፍ ነፍስ ያላቸው እስኪመስል ድረስ በጀግኖቹ ብርታት፣ በመከራ ሁሉን ተሻግራ ኢትዮጵያችን ይኸው አለች።

ዛሬም ዓለም አቀፉ የኮሮና ወረርሽኝ መከሰት ያልጠበቅናቸውን ፈተናዎች ጋርጦብን ለጊዜውም ቢሆን ሸብቦ ይዞናል። "እውነት እኛ ኢትዮጵያውያን እንዲህ አይነት ነን" እስክንል ድረስ በወገኖቻችን ላይ እጅግ አሳዛኝ መከራዎች ወረደዋል። እንጀራችንን የበሉ ተረከዞቻቸውን አነሱብን። "የት ይደርሳሉ" ያልናቸው ጥጆች ቁራ ተገኙ። ለሰላምና ለዲሞክራሲ ብለን ያሰፋነው ሜዳ የመገዳደያ መስክ ሆነ። ልባችንን የሚከፍሉ፣ ሀሞታችንን የሚያፈስሱ ስንት ወሬዎች ሰማን። በ2012 ግን ኢትዮጵያ ጨለማ የማይበግራት የብርሃን ሀገር ናት። የብርቱ ህዝብ፣ የጽኑ ዜና ሀገር፤ የብርቱ ህዝብ፣ የጽኑ ዜጋ ሀገር፤ ድቅድቅ





የሚመስለውን ጨለማ የሚገፉ አስደናቂ ታሪኮችንም ባሳለፍነው ዓመት አይተናል።

ከብዙ ትውልዶች ጀምሮ ለዘመናት ስንናፍቀውና ለአመታት ስንታገልለት የነበረው የታላቁ የሕዳሴ ግድባችን የመጀመሪያ ዙር ውሃ ሙሌት ያለፈው ዓመት አንዱ ከፍታችን ነበር። የመጀመሪያዋን ሳተላይታችንን ወደ ህዋ አምጥቀን "ወደ ልዕልና እንመጥቃለን ገና" ያልነው ባሳለፍነው በ2012 ዓ.ም ነበር። ወደ ብልጽግና ማማ ሊያወጣ ራዕይ የሰነቀው ከፋፋይና ኋላ ቀር አስተሳሰቦችን በፍቅርና በመተባበር የተካው ሃገራችንን ወደሚገባት ልክ ሊያወጣት ራዕይ የሰነቀው ብልጽግና ፓርቲ፣ ጥይት እንኳ ኮሽ ሳይል የነበረውን አርጌ አስተሳሰብ አስወግዶ የተወለደው በዚሁ ዓመት ነበር። "ብልህ ከሌላው ይማራል" እንዲሉ፣ ኮቪድ 19 ስለሚያስከትለው ፈተና አስቀድመን ተዘጋጅተን በመመከታችን፣ ከተፈራው ቀርቶ ከታሰበውም መከራ ልንተርፍ የቻልነው በ2012 ዓ.ም ሥራችን ነበር።

አረንጓዴ ሀገር ለመፍጠር የጀመርነውን ትግል ቀጥለን 5 ቢሊዮን ችግኝ የተከልነው በዚሁ በ2012 ዓ.ም ነበር። ነባር ሀብቶቻችን አልምተን ለመጠቀም ምሳሌ የሚሆነው የአንድነት ፓርክ የተጠናቀቀው፣ የሸገርና የእንጦጦ ፓርኮች በፍጥነት የተገባደዱት፣ በቢሮ የጀመርነውን ኢትዮጵያን የማበልጸግ ስራ ወደ ሶስት የሀገራችን አካባቢዎች ለማስፋት የወጠነው፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የበጎ ፍቃድ አገልጋዮችን ያሰማራነው፣ አርሶ አደሮቻችን በኩታ ገጠም እርሻ ውጤታማ ሆነው የነገ የግብርና አካሄዳችን ምን መሆን እንዳለበት ያሳዩን በዚሁ ባለፈው 2012 ዓ.ም ነበር።

ላለፉት አመታት እያሽቆለቆለ የነበረው ኤክስፖርት በ14 በመቶ አድጎ ለመጀመሪያ ጊዜ ከ3 ሚሊየን በላይ የስራ እድል ለዜጎቻችን መፍጠር የቻልነውም ባለፈው ዓመት ነበር። እውነት ለመናገር እግዚአብሔር ታርቆናል፤ ግድባችንን ሞልቶልናል፤ ጠፍተው የነበሩ ሐይቆቻችን እነ ሐሮማያን፣ ወንዞቻችንን እነ አቢጃታን መልሶልናል። “ውሃ ሊያንሰን ይችላል” ብለው የሰጉ ጎረቤቶቻችን “ውሃው በዛብን” እስኪሉ ድረስ አድርሶልናል። እግዚአብሔር ታርቆናል።

ከልባችን መታረቅ ያቃተን እኛ ነን። በ2012 ዓ.ም ሲፈትኑን የነበሩ ችግሮቻችን ከድሮ የተሻገሩ ብቻ አይደሉም። አዳዲስ ችግሮች ብቻም አልነበሩም። አንዳንዶቹ ውርስ ችግሮች ናቸው፤ ዘመናትን ከእኛው ጋር የኖሩ እየተንከባለሉ፣ ከትውልድ ትውልድ እየተወራረሱ፣ ዛሬ ላይ የደረሱ ናቸው። ድህነትና ኋላ ቀርነታችን፣ ያልተገራ የህግና የፍትህ አረዳዳችን፣ ደካማና ሰንካላ የዲሞክራሲ ልምምዳችን፣ ተቋማትን ለመገንባትና ለማጽናት ደካሞች መሆናችን ሳይከፈል የኖረ እዳ ሆኖብናል። የቀድሞው ትውልድ ይህንን እዳ ከፍሎልን ቢሆን ኖሮ እኛ ዛሬ የመከራው ገፈት ቀማሾች ባልሆንን ነበር። ነገር ግን እኛም ዛሬ መፈፀም ካልቻልን የሚቀጥለው ትውልድ በመከራ የሚቀጥል ይሆናል። ስለዚህም፣ ይህ ትውልድ መከራን ለትውልድ የሚያወርስ ሳይሆን የበለጸገች ኢትዮጵያን የሚያሸጋግር ለመሆን ቆርጦ መነሳትና መደመር ይጠበቅበታል።

“በረሃብ ላይ ጥማት” እንደሚባለው በወረስናቸው ችግሮች ላይ ደግሞ የዘመናችንን ችግሮች ጨመርንባቸው። ነባሩን ችግር በአዲስ አቀራረብ ተሰማራንበት። ሚዲያውን፣ የማህበራዊ ትስስር ገጾችን፣ ሐብትና ገንዘብ ለማሰባሰብ የሚያስችሉ ዘመናዊ አሰራሮችን፣ የመገናኛ





ቴክኖሎጂዎችን፣ ነባር ችግሮቻችንን ለማስወገጃ ሳይሆን ለማባባሻ ተጠቀምንባቸው።

## ውድ ወገኖቼ፣

ስለ ዘመን መለወጫ በዓል ስናስብ ፈጥኖ ወደ ልባችን የሚመጣ አንድ ነገር አለ። ከጨለማ በኋላ ብርሃን፣ ከፈተና በኋላ ተስፋ፣ ከመለያየት በኋላ መገናኘት፣ ከውድቀት በኋላ መነሳት አለ። ከዘመን ወደ ዘመን የምናደርገው ሽግግር ትርጉም እንዲኖረው ካለፈው ዘመን ጋር አሮጌና ጎታች አስተሳሰባችን ተሰናብተን አዲስ እና ተራማጅ አመለካከትን ልንላበስ ይገባል። አምና ያደናቀፈን ድንጋይ ዘንድሮም ጠልፎ ከጣለን፣ ባለፈው ዓመት ግራና ቀኝ ያላጉን ጉዳዮች ያለ መፍትሔ ወደ ዘንድሮ ከተሻገሩ፣ በአሮጌ ሰውነት አዲስ ዘመን መኖር ይሆናል። መለወጥና በተለወጠ ዘመን መኖር ይለያያል። ብዙዎች ሳይለወጡ በተለወጠ ዘመን ውስጥ ይኖራሉ። አዲስ ዓመት ሲመጣ “እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሰህ” ብቻ ሳይሆን፣ በውስጥ በእሳቤዎቻችን ልብ እና አእምሮአችን የተለወጡ መሆናችንንና ያንን መልካም ማንነት የምናጋባ መሆናችንን እርግጠኞች መሆን ይኖርብናል።

የቀጣይ ዓመት ውጤታችን እና የመጪ ዘመናት እመርታችን የሚወሰነው ለመለወጥ በተዘጋጀነው መጠን ነው። የፖለቲካ አሰራራችና ባህላችንን በቅንነት ማሻሻል በመካከላችን የፈጠርነውን የልዩነት አጥር ለማፍረስ፣ የቦረቦርነውን የመቃቃር ጉድጓድ ለመድፈን፣ የመለያየትን ገደል ለመሻገር፣ ምን ያህል ተዘጋጅተናል? ማህበራዊ መስተጋብራችን መልካም ለማድረግ ምን ያህል ቁርጠኞች ነን? ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎአችንን ከልማዳዊ አሰራር በማላቀቅ ፈጠራን በሚጋብዝ መልኩ ለመቃኘት፣ የግል ኪስን ከመሙላት ባለፈ ሀገርና ወገንን እንዲጠቅም ለማድረግ፣ ከምንም በላይ የሀገርንና የደሀ

ወገናችንን ውስን አንጡራ ጥሪት ከዘረፋና አየር ባየር ማጭበርበር አጽድተን በሀቅ ላይ ተመስርተን ለመስራት ምን ያህል አቅደናል?

በዚህ የአዲስ ዓመት ዋዜማ ምሽት ላይ ሆነን፣ ሁላችንም እነዚህን ጥያቄዎች አስበን ምላሽ እንድንሰጥባቸው ጥሪዬን አቀርባለሁ። ስርቆት የምንጠየፍ፣ ትጋትን የምንወድ፣ በማካፈል ውስጥ የሚገኝ ደስታን የምንሻ፣ ለመቀበል ብቻ ሳይሆን ለመስጠት ዝግጁ የሆንን እንደሆነ ብልጽግናችን ይፈጥናል። የሀገራችን ብልጽግና በየሸንተረሩና በየጫካው ያሸበረቀውን አደይ ተከትሎ እንዲፈካ ኮትኳች ሊበዛ፣ ነቃይ ሊቀንስ ይገባል። ብልጽግና እንደ ዛፍ ነው፤ የሚጠብቀው፣ የሚንከባከበው፣ የሚያጠጣውና የሚኮተኩተው ካገኘ ያድጋል፤ ያብባል። ከተውነው ይተወናል፤ ከነቀልነው እርሱም ይነቅለናል።

ያለ ህዝብ አንድነትና ተሳታፊነት፣ ያለ ወጣቶች ትጋት፣ ያለ መፍሔ አፍላቂ ምሁራን አበርክቶና ተምሳሌትነት፣ የተገነባ ሀገር በዓለም ላይ አልታየም። ከአንጀት ካለቀሱ እንባ አይገድም እንደሚባለው ቆርጠን ከተነሳን ያለ ጥርጥር በጥረታችን ከተስፋ የሰፋ ተጨባጭ ለውጥ እናሳካለን።

በስልጣኔ አደባባይ ከፍ ብላ የምትታይ ጠንካራ ሀገር ለመገንባትና ከእኛ አልፎ ለልጅ ልጆቻችን የተደላደለ ነገን ለማስረከብ ዛሬ መልካም መሰረት መጣል እንችላለን። እግዚአብሔር ታርቆናልና እኛም ልንታረቅ ይገባል። መጪው ዓመት ስላለፈው የምንቆዝምበትና ቂም ቋጥረን በቀልን የምናስብበት ሳይሆን፣ በይቅርታና በእርቅ ሰላምን አውርደን በመተሳሰብና በመደማመጥ ልዩነታችንን አጥብበን፣ ህዝባችንንና ሀገራችንን በማስቀደም ወደ ልዕልና የምንመጥቅበት እንዲሆን ሁላችሁንም በትህትና ልጋብዝ እወዳለሁ።





የጀመርነውን የምንፈጽምበት ያሰብነውን ወደ መሬት የምናወርድበት ከዳር እስከዳር ስጋትና ግጭት ቀርቶ በሰላም እጅ ለእጅ ተያይዘን በጋራ ሰርተን በጋራ የምንደሰትበት ዘመን እንዲሆን እመኛለሁ። ብልጽግና የሁላችን ህልምና እሴት ብቻ ሳይሆን፣ እቅድና ግብ ሆኖ እንደ ሀገር ከፍ ወዳለ ሁለንተናዊ ልዕልና እንድንመጥቅ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

ዝቅታ አይመጥነንም። ከደረጃችን በታች ወርደን መጫወት አይመጥነንም። ኢትዮጵያን ወርደን አናውርዳት! ኢትዮጵያን ከብረን እናስከብራት! በልጽገን እናበልጽጋት! ሰልጥነን እናሰልጥናት! ልካችን ልዕልና መሆኑን ለዓለም ለማስመስከር በአንድ ልብ፣ በአዲስ መንፈስ፣ በአዲስ ዘመን ለመስራት ቆርጠን እንድንነሳ በትህትና ልጋብዛችሁ እፈልጋለሁ።

ባለፈው ዓመት ውስጥ ኮቪድን ጨምሮ በተለያዩ ህመሞች ወዳጅ ቤተሰቦቻችሁን ያጣችሁ ወገኖቻችን ፈጣሪ መጽናናቱንና ብርታቱን ይስጣችሁ። በተለያዩ የተፈጥሮ አደጋዎች በተፈጠሩ ግጭቶችና ሌሎች ሰው ሰራሽ ችግሮች ህይወታቸውን፣ ንብረታቸውን እና ሕልማቸውን ለአጡ የሀገሬ ልጆች ሁሉ የተሰማኝን ጥልቅ ሀዘንና የልብ ስብራት ልገልጽ እወዳለሁ። ደስታችሁ ደስታዬ የሆነውን ያህል፥ ህመማችሁ ህመሜ ነው። ቀንም ሌትም ሐሳቤና ህልሜ፣ ስራና ድካሜ ይህ ነገር እንዳይደገም ለማድረግ ነው። ደግሞም ከተባበርን እናደርገዋለን። መጪው ዘመን ያዘኑ የሚጽናኑበት፣ ተስፋ የቆረጡ የሚታደሱበትና የወደቁ የሚነሱበት እንዲሆን ከልቤ እመኛለሁ። የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት በመተባበር የደረሰባችሁን ሁሉ ፈጽማችሁ እስክትረሱ ድረስ ወደ ቀደመ ኑሮአችሁ እንደምንመልሳችሁ ተስፋዬ የላቀ ነው።

በዓመት ውስጥ እጃችን የገቡትን እድሎች ወደ ውጤት፣ የተጋረጠብንን ፈታኝ ትግሎች ወደ ድል የለወጣችሁ የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ልጆች ለእናንተ ምስጋናዬን ላቀርብላችሁ እወዳለሁ።

ግጭቶችን ተጋፍጣችሁ፣ ሊደርሱ ይችሉ የነበሩ ጥፋቶችን አምክናችሁ፣ ሰላምን ያሰፈናችሁ የጸጥታ አካላት፣ ሀገር ታፍራና ተከብራ እንድትኖር ሁለመናችሁን የሰጣችሁ የመከላከያ ሰራዊት አዛዦችና አባላት፣ በተከሰተው የኮቪድ ወረርሽኝ የራሳችሁንና የቤተሰባችሁን ህይወት አደጋ ላይ ጥላችሁ ወገኖቻችሁን የተንከባከባችሁ የጤና ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች፤ ሀገራችን በተፈጠሩባት ብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ ኢኮኖሚዋ እንዳይናጋ በትጋት የሰራችሁ የንግድና የኢንደስትሪ ባለቤቶችና ሰራተኞች፤ ሀገር የምትቀልቡ አራሽ ገበሬዎች፤ ህዝባችሁን ለማገልገል በየመስሪያ ቤቱ የደከማችሁ ዜጎቻችን፣ በውጪው ዓለም ለሀገራችን አምባደር ሆናችሁ ህዝባችንን ለመርዳትና የሀገራችሁን ገጽታ ለመገንባት ደፋ ቀና ያላችሁ ወገኖቻችን ሁሉ የምስጋና እውቅናችን ይድረሳችሁ።

በታላቁ ህዳሴ ግድብ በሸገር ፓርክ፣ በአንድነትና በእንጦጦ ፓርኮች ሃያ አራት ሰአት የሰራችሁ፣ የኢትዮጵያ ኩራት በሆነው የአየር መንገዳችን ሰራተኞችና አመራሮች ላሳያችሁት ምሳሌያዊ ትጋትና ውጤት በዚህ የአዲስ ዓመት ዋዜማ ምስጋናችን ይድረሳችሁ። በውስን አቅም መሰረታዊ ለውጥ ሳይደረግበት በኖረ መሰረተ ልማት ላይ ሆናችሁ የህዝባችሁን መሰረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ስትሉ አብዛኛው ሰራተኛ በኮቪድ ምክንያት ከቤት እንዲሰራ በተደረገበት ወቅት እናንተ በግንባር ቀደምትነት ተሰልፋችሁ ግዳጃችሁን የተወጣችሁ የኢትዮ ቴሌኮም፣ የመብራት ኃይል፣ የውሃና ፍሳሽ፣ የመንገድ ባለሥልጣን እንዲሁም ሌሎችም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አመራሮችና ሰራተኞች በራሴና በኢትዮጵያ ህዝብ ስም ላመሰግናችሁ እወዳለሁ።





በመጨረሻም በገጠርና በከተማ በሀገር ቤትና በውጭ ሀገራት ለምትኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሁሉ፥ አዲሱ ዓመት ያሰባችሁት የሚሳካበት፣ ተስፋችሁ እውን የሚሆንበት ማዕድ የማጋራት፣ ከተማ የማጽዳት፣ የተከላችሁትን ችግኝ የመንከባከብ፣ ገበታ ለሀገር በተሰኘው አዲሱ ፕሮጀክት ጎርጎራን፣ ወንጪንና ኮይሻን የማልማት መልካም ልማዶች የሚጠናከሩበት፣ የትጋትና የመከናወን ዓመት ይሆንላችሁ ዘንድ ልባዊ ምኞቴ ነው። ኢትዮጵያን ያህል ሀገር ይዞ ተስፋ አይቆረጥም። “ወደ ልዕልና እንመጥቃለን ገና” ኢትዮጵያን ከሚገባት ልክ ላይ ሳናደርስ እረፍት አይኖረንም።

በድጋሚ ለ2013 ዓ.ም የዘመን መለወጫ በዓል በሰላም አደረሳችሁ አደረሰን!

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘለዓለም ትኑር! ፈጣሪ ኢትዮጵያን እና ህዝቦቿን፣ የእጃችንንም ሥራ ይባርክ! አመሰግናለሁ!!**

# የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት ለተማሪዎች

## ከኮሮና ወረርሽኝ በኋላ ለተከፈተው የትምህርት ዘመን እንኳን በሰላም አደረሳችሁ !

**መስከረም 2013 ዓ.ም.**

**ከዐጸደ ሕጻናት እስከ ኮሌጅ፣**
**ከግል እስከ መንግሥት ትምህርት ቤቶች፣**
**በመላ ሀገሪቱ የምትገኙ ተማሪዎች በሙሉ፤**

ዓለም አቀፋዊው ወረርሽኝ «ኮቪድ-19» በሀገራችን መከሠቱን ተከትሎ በቀዳሚነት የወሰንነው ውሳኔ የእናንተን የነገ ሀገር ተረካቢዎቻችንን ሕይወት መታደግ ነበር። ትምህርት ቤቶችን በፍጥነት በመዝጋትና ሌሎች የመከላከል እርምጃዎችን በመውሰድ ወረርሽኙ ሊያስከትል የሚችለውን ከፍተኛ ሥጋትና አደጋ በእጅጉ ለመቀነስ ችለናል። በዚያ ወቅት የመከላከል፣ የመመርመርና የማከም ዐቅማችን እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነበር። ባሕሪውን በየጊዜው ስለሚለዋወጠው ወረርሽኝ የነበረን ዕውቀት በጣም ውስን ነበር። ቫይረሱ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተጽዕኖ እንዴት መቋቋም እንደምንችል በቂ ልምድ አልነበረንም።





በዚህ ምክንያት በልጆቻችን ላይ አንዳች ቸልታ ማሳየት ተገቢ እንዳልሆነ መግባባት ላይ ደርሰን ነበር። ለዚህም ነበር ትምህርት ቤቶችን የዘጋነው።

አሁን በሀገራችን የመጀመሪያው የኮሮና ቫይረስ ከተገኘ ሰባት ወራት አልፎታል። የሕክምና ባለሞያዎቻችንና የጤና ተቋሞቻችን ስለ ጉዳዩ የተሻለ ሞያዊ ብቃት አዳብረዋል። የመመርመር ዐቅማችን አድጓል። ማኅበረሰባችን ስለ በሽታውና ስለ መከላከያው በቂ ግንዛቤ አግኝቷል። የመከላከያ ቁሳቁሶች በቀላሉ በየአካባቢያችን ይገኛሉ። አንዳንድ የመከላከያ ቁሳቁሶችንም በቤት ውስጥ ለመሥራት ተችሏል። እነዚህን ነገሮች ከግምት ውስጥ ስናስገባ፣ ከዚህ ጊዜ በላይ ትምህርት ቤቶቻችንን ዘግተን ማቆየት ተገቢ ነው ብለን አላመንንም።

ዓለም አቀፍ የጤና ተቋማትና ባለሞያዎች፣ የኮሮና ወረርሽኝ ተጽዕኖ ለተወሰኑ ዓመታት ሊቀጥል እንደሚችል ግምታቸውን አስቀምጠዋል። ክትባትና መድኃኒት የማግኘቱ ምርምርም እንደቀጠለ ነው። በዚህ ጊዜ ይጠናቀቃል ብሎ ለመተንበይ ግን አስቸጋሪ ነው። ዓለም ከኮሮና ራስዋን እየተከላከለች እንቅስቃሴዋን መቀጠል የግድ ሆኖባታል። እኛም በአንድ በኩል እየተጠነቀቅን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎቻችንን ማከናወን እንዳለብን እናምናለን።

ከዚህ ጊዜ በላይ ተማሪዎቻችንን በቤት ውስጥ ማቆየት ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። በተማሪዎቻችን ላይ ሥነ ልቡናዊ ጫና ያሳድራል፤ አንዳንድ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በመተው በሌሎች አልባሌ መስኮች እንዲሠማሩ ያደርጋቸዋል፤ መጥፎ ሱስ ውስጥ ያስገባቸዋል። በአንድም በሌላም መንገድ ያለ እድሜ ጋብቻን ያበረታታል፤ በወላጆች

ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ጫና ያሳድራል፤ የቤት ውስጥ ጥቃት ቁጥሩ እንዲያሻቅብ ያደርጋል። ስለዚህም የተሻለው መፍትሔ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ ትምህርትን መጀመር ሆኖ አግኝተነዋል። ኮሮናንና መሰል ሀገራዊ ችግሮችን የሚያጠፉ ትውልድ መፍጠር የሚቻለውም በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ጭምር መማርና መመራመር የሚችል ትውልድ በመፍጠር ነው።

አስፈላጊ የሆኑ የንጽሕና ቁሳቁሶችን፣ የመታጠቢያና የመጸዳጃ ቦታዎችን፣ ርቀትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ የመማሪያ ክፍሎችን፣ በተቻላቸው መጠን ትምህርት ቤቶች እንዲያሟሉ እየተደረጉ ነው። የትምህርትና የጤና ቢሮዎች፣ ፖሊሶችና ወላጆች እነዚህን ነገሮች እንዲከታተሉ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል። በየትምህርት ቤቶች አስፈላጊ ነገሮች እንዲሟሉ ወላጆች፣ የበጎ አድራጎት ተቋማትና ባለሀብቶች ማኅበራዊ ኃላፊነታችሁን እንድትወጡ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ አቀርባለሁ።

## ውድ ኢትዮጵያውያን፣

የኮሮና ወረርሽኝ ተማሪዎቻችንን እንዳያጠቃብን መጀመሪያ ወላጆች፣ ቀጥሎም መምህራን ከባድ ኃላፊነት አለባችሁ። ልጆች የአፍንጫ መሸፈኛ እንዲያደርጉ፣ እጃቸውን በተደጋጋሚ እንዲታጠቡ፣ ዐቅም በፈቀደ መጠን የእጅ ማጽጃ ይዘው እንዲሄዱ፤ ርቀታቸውን ጠብቀው እንዲንቀሳቀሱ ወላጆች ወሳኝ ሚና አለባችሁ። ማስተማር፣ መምከርና መከታተል ይጠበቅባችኋል።

በትምህርት ቤት ውስጥ ለተማሪዎች ከመምህራን የቀረበ ማንም የለም። መምህራን ሁለተኛ ወላጆች ናቸው። ተማሪዎች በትምህርት





ቤት የሚኖራቸው ቆይታ፣ ተማሪዎችን ከኮሮና ለመጠበቅ የሚያስችል መሆኑን መከታተል ይገባቸዋል። በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ኮሮናን ለመከላከል የሚያስችሉ ነገሮች እንዲሟሉ የትምህርት ቤቶች ባለቤቶች፣ አመራሮችና መምህራን ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል። በእነዚህ ነገሮች ላይ የምናሳየው ቸልታ፣ ትውልድን የሚያሳጣን በመሆኑ፣ መንግሥት በዝምታ የሚያልፈው ነገር አይደለም።

ይህ የኮሮና ወቅት በታሪክ ምንጊዜም ስናስታውሰው የምንኖረው ነው። ይህን ወቅት የድል ወቅት በማድረግ የተሻለ ትውስታ እንዲኖረን እናድርግ። ያልተስተካከሉ ነገሮችን በማስተካከል፤ የጎደሉ ነገሮችን በማሟላት፤ ያልተመቹ ነገሮችን በማመቻቸት፣ ይሄን ዓመት የውጤት ዓመት እናድርገው። አካባቢያችንን በማጽዳት፣ ችግኞችን በመትከል፣ ለኮሮና መከላከያ የሚሆኑ አዳዲስ ነገሮችን በመፍጠር፣ የኮሮና ወቅት የስኬት ወቅት ሆኖ እንዲያልፍ እናድርገው።

ያለፈውን ዓመት ትምህርት ለመከለስ፣ ዘግይቶ የተጀመረውን የዚህን ዓመት ትምህርት ለማካካስ ሲባል በተማሪዎች፣ በመምህራንና በወላጆች ላይ ጫና መፈጠሩ አይቀርም። ሆኖም ግን አንድ ነገር እንድታስታውሱ አደራ ለማለት እፈልጋለሁ። ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ውጤታማ ሆነው ለክብር የደረሱት በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ አልፈው ነው። ብዙዎቹ ሳይንቲስቶች፣ ምሁራንና ሊቃውንት ለማዕረግ የበቁት በፈታኝ ሁኔታ ውስጥ አልፈው ነው። ስለዚህም እናንተ የመጀመሪያዎቹም፣ የመጨረሻዎቹም አይደላችሁም። ጀግና የሚፈጠረው በችግር ጊዜ በመሆኑ፣ የኮሮና ወቅት፣ የብዙ ጀግና ተማሪዎች መፍጠሪያ ጊዜ እንደሚሆን አምናለሁ።

## ውድ ተማሪዎች፣

ሀገራችን ኢትዮጵያ ትፈልጋችኋለች፤ ወላጆቻችሁ ይፈልጓችኋል፤ የሚያውቋችሁና የሚቀርቧችሁ ሁሉ ይፈልጓችኋል። ኮሮናን በተመለከተ የሚፈጠር ቀላል መዘናጋት፣ ከባድ ዋጋ ያስከፍለናል ጥንቃቄ አይለያችሁ። ጉዳዩ የሕይወት ጉዳይ ነው። ጉዳዩ የትውልድ ቀጣይነት ጉዳይ ነው። ኮሮናን ከመጠንቀቅ ፈጽሞ ችላ እንዳትሉ። ይህ ጊዜ ዐልፎ፣ እንዴት እንዳለፍነው የምንተርክበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም። ጥንቃቄ ሳይለያችሁ ትምህርታችሁን በርትታችሁ ተማሩ።

ከተማሪዎች ባለፈ ወላጆች፣ መምህራን፣ የትምህርት ቤቶች አስተዳደር ሰዎች፣ የጤና ባለሞያዎችና የጸጥታ አካላት ኮሮናን በትምህርት የሚያሸንፍ ትውልድ እንዲፈጠር ኃላፊነታችሁን እንድትወጡ ከፍ ያለ አደራ ተሰጥቷችኋል። አደራውን በብቃት እንደምትጠብቁም ሙሉ በሙሉ በእናንተ እተማመናለሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና**
**ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**





# የመስቀል በአል መልእክት

**መስከረም 17፣ 2012 ዓ.ም.**

በክርስቲያኖች ዘንድ መስቀል የድልና የፈተና ምልክት ነው። አባቶቻችን ያለ ፈተና ክብር አይገኝም ይላሉ። መስቀሉም በአንድ በኩል እስከ ሞት የሚደርስ መሥዋዕትነትንና ፈተናን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ማንም ሊያስቀረው የማይችለውን ድል አድራጊነትን ያስታውሰናል። ሀገር ልቃ እንድትወጣ በሁለቱም ውስጥ ታልፋለች። በፈተናና በድል ውስጥ። ፈተናው ብቻ ቢሆን ተስፋ በቆረጥን ነበር። ግን ድል እንዳለ ስለምናምን መከራውን ተቋቁመን እናልፈዋለን። ድል ብቻ ቢሆንም ተዘናግተን በተቀመጥን ነበር። የምትፈለፈል ቢራቢሮ ከዕንቁላሉ ለመውጣት የምታደርገው ትግል፤ ለጥንካሬዋ አስፈላጊ እንደሆነው ሁሉ፤ በፈተና ውስጥ በጽናትና በትግል ማለፋችንም መሠረተ ጽኑ ያደርገናል።

አንዳንዶች ስለፈተናው ብቻ ያወራሉ። ስለዚህም ተጨንቀው ሕዝብን ያስጨንቃሉ። ሰው ፈተናን ብቻ ካሰበ የዓለም መጨረሻ የደረሰ ይመስለዋል። ነገሮችን ሁሉ ያለቀላቸውና ያበቃላቸው አድርጎ

ያያቸዋል። ንግሥት እሌኒ መስቀሉን ለማውጣት ስትነሣ ብዙዎቹ ስለመቀበሩ ብቻ ነበር የሚነግሯት። የት እንደተቀበረ እንደማይታወቅ፤ ከተቀበረ ብዙ ዘመናትን ያስቆጠረ፤ ለማውጣት አስቸጋሪ የሆነ፤ ሁኔታው ሁሉ ተስፋ እንደሚያስቆርጥ ነበር የሚነግሯት። እርሷ ግን እንደተቀበረ ብቻ ሳይሆን እንደሚወጣም ታምን ነበር። እንደጠፋ ብቻ ሳይሆን ሊገኝ እንደሚችልም ታምን ነበር። እነርሱ ስለ ፈተና ሲናገሩ፤ እርሷ ግን ከፈተናው ወዲያ ስላለው ድል ጭምር ነበር የምታወራው። ልዩነታቸው እዚህ ላይ ነበረ።

‹ፈተና› ደካማና ተሸናፊዎችን ሲሰብራቸው በተቃራኒው ለአሸናፊዎች የትምህርት ዕድል ነው። አሸናፊዎች ከፈተናው ትምህርት ወስደው ይለወጡበታል፤ እንደ ብረት ጠንክረው፣ እንደ ካስማ ጸንተው ይወጡበታል። ፈተና ለሚሸነፉ ሰዎች ተስፋ መቁረጫ ጥቁር ጭንብል ነው። በፈተናው ይማረራሉ እንጂ ከፈተናው አይማሩም፤ ድቅድቁን ጨለማ እንጂ ደማቁን ብርሃን ሊያዩ አይችሉም፤ የፈተናው መንገድ እንጂ የፈተናው ፍጻሜ በጭራሽ ዐይታያቸውም።

በክርስቲያኖች ዘንድ መስቀል ‹ኃይልና ቤዛ› ተደርጎም ይታሰባል። የእምነታቸው ምልክትም ነው። መጽናናትና መዳንን ያገኙበት ውድ ስጦታቸው ነው። ይሄን የሚያውቁ የዚያን ዘመን ጨቋኞች መስቀሉን ሲቀብሩት ዓላማ ነበራቸው። ክርስቲያኖቹ ትእምርት እንዳይኖራቸውና በተሸናፊ ሥነ ልቡና ውስጥ እንዲኖሩ ይፈልጋሉ። ልክ እንደ መስቀሉ ጭንቅላታቸውን እንዲቀብሩ፣ ዝቅ አድርገው እንዲያስቡና ዝቅ ያለ መንፈስ እንዲላበሱ የማድረግ ጽኑ ፍላጎት ነበራቸው። ነገር ግን ይሄ በመስቀሉ የሚያምኑትን አላሸነፋቸውም። ከዓመታት በኋላ ውድ





ስጦታቸውን፣ ያንን የተቀበረ መስቀል በብዙ ጥረትና ትጋት ቆፍረው አውጥተውታል።

የብልጽግና ጉዟችን ለእኛ ለኢትዮጵያውያን እጅግ ወሳኝና ውድ ስጦታችን ነው። ለዘመናት በድህነትና ኋላቀርነት፣ በርሃብና በቸነፈር፣ በልዩ ልዩ ችግሮች ትከሻዋ የጎበጠው ሀገራችን ከሸክሟ የሚያሳርፏት፤ ብሩህ ነገዋን እንድታይ ቀና የሚያደርጓት፤ ክብርና ዝናዋን ከሚመጥን የብልጽግና ደረጃ ላይ የሚያደርሷት ልጆቿዋን ትሻለች። በጥቃቅን ፈተናዎች ሳይሸነፉ፣ በእንቅፋትና በጋሬጣው ተጠልፈው ሳይወድቁ፣ ከመከራው ወዲያ የሚታየውን የሚጨበጥ ተስፋ ይዘው ወደፊት እንዲገሰግሱ ሀገራችን ትፈልጋለች።

ያኔ መስቀሉ ተቀብሮ ሳለ በመስቀሉ ፊት ሦስት ዐይነት ሰዎች ነበሩ። የመጀመሪያዎቹ መስቀሉን የማይፈልጉትና ከመሬት በታች የቀበሩት ሲሆኑ ዓላማቸው የመስቀሉን ደብዛ ማጥፋት ነበር። በሁለተኛው ረድፍ ያሉት ተስፋ ቆርጠው ሌላውን ተስፋ ለማስቆረጥ ታጥቀው የተነሱት ናቸው። በያጋጣሚው መስቀሉን ቆፍሮ ስለማውጣት ሲነሳ የሚያከላክሉና አብዝተው ስለመከራው የሚናገሩ ነበሩ። ተዓምር ተፈጥሮ እስካልወጣ ድረስ የመስቀሉ ነገር እንዳከተመለትም ያምናሉ። በተቃራኒው ሦስተኛ ላይ ያሉት መስቀሉ እንዲወጣ ጽኑ ፍላጎት ነበራቸው፤ ከሁሉም በላይ ‹መስቀሉ ይገኛል› የሚል ጽኑ እምነት የነበራቸው ብርቱዎች ናቸው።

እነዚያ ብርቱ ክርስቲያኖች የተቀበረውን መስቀል ለማየት የበቁት ተራራውን ንደው፤ ከምሩን ቆሻሻ ደረማምሰው፤ አፈሩን ምሰውና ብናኝ

አቧራውን ባፍና ባፍንጫቸው ጠጥተው ነበር። ላብ ሳያስወጣ፣ ጉልበት ሳያብረከርክ፣ አቧራ ሳያለብስና ምንም ሳያስለፋ የሚሳካ መልካም ነገር የለም። የሀገራችን ዴሞክራሲ የሚሳካው፣ ነጻነትና እኩልነት እውን የሚሆነው ተገቢውን የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ተከትለን ስንሠራ እንጂ እንደ ተዓምር ከሰማይ የሚወርድልን ነገር አይደለም። ፖለቲካችን የሚስተካከለው፣ ኢኮኖሚያችን የሚያድገው፣ ብልጽግናችን እውን የሚሆነው ዳር ቆመን በመመልከት ወይም እንደ ታዛቢ አፋዊ አስተያየት በመሰንዘር ሳይሆን ባለቤት ሆነን ስንሠራው፣ የበኩላችንን ማበርከት ስንችልና የውጣ ውረዱ አካል ስንሆን ብቻ ነው።

እኛ ኢትዮጵያውያን መከራችንን ከሚያብሱና ፈተናችንን ብቻ ከሚነግሩን መሠናክሎች ማምለጥ አለብን። እነሱ ዘላለም ፈተናችን ላይ ብቻ እንድንጣድ የሚፈልጉ ናቸው። ዘወትር በልቅሶና በትካዜ እንድንኖር ከማድረግ ውጭ ለቁስላችን መድኃኒት፣ ለተራብ ሆዳችን ምግብ፣ ለታረዘ ገላችን አልባስ አያቀርቡልንም። በጊዜያዊ ችግሮቻችን እንድንጠመድ ከማድረግ በዘለለ ሥር ለሰደዱ ችግሮቻችን ዘላቂ መፍትሔ አያቀብሉንም። ከማላዘን ፖለቲካ ምን ጠብ የሚል ነገር እናገኛለን ብንል መልሱ ኪሳራ እንጂ ትርፍ፤ መከራ እንጂ ረፍት አይሆንም።

ኢትዮጵያ እስካሁን ተፈትናለች፤ አሁንም እየተፈተነች ነው፤ መጠኑ ቢለያይም ወደፊትም ፈተና ማጋጠሙ አይቀርም። ዋናው ቁም ነገር ከፈተና በኋላ እንደ ወርቅ ነጥሮ መውጣት መኖሩን አለመርሳት ነው። እሳት ለወርቅ ማቃጠያው ብቻ ሳይሆን ማንጠሪያውም ጭምር ነው። ይበልጥ በእሳት ሲመታ፤ ይበልጥ ንጹሕ ይሆናል። ይለወጣል።





ፈተናዎቻችን ነጥረን እንድንወጣ እንጂ ቀልጠን እንድንቀር አያደርጉንም።

ሀገራችን ወደፊት እንዳትራመድ አስረው የያዟት ትብታቦች የቱንም ያህል ቢበዙ ተበጣጥሰው ማለቃቸው አይቀርም። ግድግዳ ሆነው መንገድ የዘጉባት ቋጥኞች የቱንም ያህል ቢገዝፉ ተንደው ይወድቃሉ። ሕብዛችን ብሩህ ቀን እንዳያይ የሚያደርጉት የጽልመት መጋረጃዎች በብርሃን ሰይፍ ይቀደዳሉ። ገፍተው መስቀለኛ መንገድ ላይ ያቆሟት ሲያልፉ፣ ሀገራችን ተስፋ ባላቸው ጎሊናዎች፤ በተባበሩ እጆች፤ በቆረጡ ልቦች፤ በልዩነት ውስጥ አንድነትና ፍቅር እንዳለ በሚያምኑ ልጆችዋ ብርታት ከችግሮቿ በላይ ከፍ ትላለች፤ ብልጽግናዋም ያለጥርጥር እውን ይሆናል።

መስቀሉ ከተቀበረበት ቀን ይልቅ የወጣበት እለት እንደሚከበር ሁሉ ኢትዮጵያም የድል ታሪኳን እያከበረች መሄዷን ትቀጥላለች። ከእንግዲህ ስልጣኔና ብልጽግናዋን አፈር ለሚያለብሱ አካላት ቦታ የላትም። ለጊዜው መኖራቸው እያወቀች፣ መንገዷን እንደሚቆፍሩ እያየች፣ ‹አንድ ቀን ወደ ቀልባቸው ሊመለሱ ይችላሉ› በሚል ተስፋ ዐይታ እንዳላየ ታልፋቸው ይሆናል። ነገር ግን በየትኛውም እንቅፋት ከመንገዷ አትገታም። አቧራውን ጠርጋ፣ አፈሩንም ንዳ ታሪክ መቀጠል እንደምትችል፣ ጉድጓድ ሲምሱላት የነበሩም ራሳቸው ሲገቡበት ታያለች። የኢትዮጵያ ድል የፈተናዎቿን ብቻ ሳይሆን የፈታኞቿንም ታሪክ እንደሚዘጋ ምንም ጥርጥር የለውም።

የመስቀል በዓል በሀገራችን ከሐይማኖታዊ ዋጋው በዘለለ ባህላዊ ትርጉምም ተሰጥቶት ይከበራል። በተለይም በደቡቡ የሀገራችን ክፍል መስቀል የተለየ ግምት ይሰጠዋል። የተነፋፈቁ የሚተያዩበት፣ የተለያዩ የሚገናኙበት፣ ዝምድና የሚጠነክርበት፣ አንዱን ምዕራፍ ጨርሰው ወደሌላ ምዕራፍ የሚሸጋገሩበትና ብሩህ ተስፋ የሚበሰርበት እለት ነው። ቤተሰብ ተሰባስቦ በደስታ የሚያሳልፈው፣ ስለ ቀጣዩ ጊዜ የሚመካከሩበት፣ ልጆች ከወላጆቻቸው ምርቃት የሚቀበሉበት፣ ማህበረሰባዊ እሴት የሚጠናከርበት እለት ነው።

ይሄንን ሀገራዊ አንድነትና ትብብራችንን የሚጠናከርበት የመስቀል በዓልን ስናከብረው ከመብላት ከመጠጣቱ ጎን ለጎን የበዓሉን ሰሞን ቁም ነገር የምናከናውንበት እንዲሆን በዚሁ አጋጣሚ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ።

በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በሰው ሰራሽና በተፈጥሯዊ አደጋዎች ምክንያት ችግር ላይ የወደቁ፣ በድንገተኛ ጎርፍ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ወገኖቻችንን አስታዋሽ ይፈልጋሉ። ስለዚህ ከበዓሉ ጎን ለጎን የተቸገሩትን “አለን- ከጎናችሁ” ልንላቸው፣ የድጋፍ እጃችንን ልንዘረጋላቸው ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል። ከዚህ ባለፈ ወቅቱ አንዳንድ ሰብሎች አፍርተው ለመሰብሰብ ዝግጅት የሚጀምሩበት ወቅት እንደመሆኑ መጠን በቀጣይ ሳምንታት አርሶ አደሩን ለማገዝ፣ በዝናብ የሚበላሽ ሰብል እንዳይኖር ተጠቃሎ እህሉ ጎተራ እስኪገባ ድረስ ከጎናቸው ሆነን ርብርብ ለማድረግ ከወዲሁ ልናስብበትና ቅድመ ዝግጅት ልናደርግ ይገባል።





በመጨረሻም፣ ችላ በማለታችን የተነሳ የመስፋፋቱ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው የኮሮና ወረርሽኝ እንደ ሀገር እያደረሰብን ያለው ችግር ለመቀነስ የየበኩላችንን አስተዋጽኦ ከማበርከት መቦዘን የለብንም። በዓሉንም ስናከብር የበሽታው ስርጭት ከሚጨምሩ ድርጊቶች በመቆጠብና ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃዎች ተግባራዊ በማድረግ እንዲሆን እያሳሰብኩ በዓሉ የሰላም፣ የመረዳዳትና የመተጋገዝ እንዲሆን እመኛለሁ።

**በድጋሚ እንኳን ለመስቀል በዓል አደረሳችሁ፣ አደረሰን!**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘለዓለም ትኑር! ፈጣሪ ኢትዮጵያን እና ህዝቦቿን፣ የእጃችንንም ሥራ ይባርክ! አመሰግናለሁ!!**

# የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት ለኢሬቻ

መስከረም 22፣ 2013 ዓ.ም

## እንኳን ለኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ!

ኢሬቻ የምስጋና እና የተስፋ በዓል ነው። በኦሮሞ ሕዝብ ባህል መሠረት ኢሬቻ የሚከበረዉ ዝናብን፣ ሰላምን፣ ምርት እና የትዉልድን ቀጣይነት የሚሰጥ ፈጣሪ (ዋቃ)ን ለማመስገን ነዉ። በዝናባማዉ ክረምት በጅረቶችና ወንዞች መሙላት ምክንያት ተቆራርጠዉ የነበሩ ቤተ ዘመዶች የሚገናኙበት በዓል ነዉ። የጅረቶችና ወንዞች መጉደል ብሎም በጨለማ ሚመሰለዉ የክረምት ወራት አልፎ በብርሃናማዉ የመጸዉ ወቅት መተካት የመከራና የችግር ጊዜያትን በማለፍ አዲስ ብሩህ ተስፋን በመሰነቅ ይመሰላል።

ኢሬቻ ርጥብ ቄጠማን በመያዝ ለፈጣሪ ምስጋና የሚቀርብበት በዓል ነዉ። ርጥብ ቄጠማ የልምላሜና |የብሩህ ተስፋ ምልክት ነዉ። በኢረቻ በዓል የበዓሉ ተሳታፊዎች ርጥብ ቄጠማ በመያዝ የዘራነዉ ምርት





ደርሶ እሸት የሰጠን፣ ልምላሜ እና ብሩህ ተስፋን ያጎናጸፈን ፈጣሪ ይመስገን በማለት ምስጋና የሚቀርብበት በዓል ነዉ።

በኢሬቻ ላለፈው ምስጋና ይቀርብበታል። ለወደፊቱ ተስፋ ይሰነቅበታል። እነዚህ ሁለቱ እንደ ግለሰብም እንደ ሀገርም እጅግ አስፈላጊ ዕሴቶች ናቸው። ሕይወት ከምስጋና እና ከተስፋ ውጭ አትቀጥልም። በምስጋና ውስጥ ምሬትም እርግማትም አለ። ምሬቱ ግን ምስጋና ወሰን የሚያወጣለት ምሬት ነው። በምስጋና ውስጥ እርግማት አለ። እርግማቱ ግን ምስጋና ወሰን የሚያወጣለት እርግማት ነው።

ልክ በወጥ ውስጥ እንዳሉ ቅመሞች። በወጥ ውስጥ የሚያቃጥለው በርበሬ፣ የሚቆጠቁጠው ሽንኩርት፣ ከበዛ ሊጎዳ የሚችለው ጨው አሉ። ሁሉም ግን በልካቸው እንዲሆኑ ‹ወጥ› የተባለው ማሕቀፍ ወስኗቸዋል። ሁሉም ከሚፈለገው ጣዕምና ውጤት አንጻር ተለክተውና ተመጥነው ይቀርባሉ። ማቃጠሉም፣ መለብለቡም፣ መቆጥቆጡም ያስፈልጋል። ግን የወጡን የጣዕም ልኬት እስካላጠፋው ድረስ ብቻ ነው። የሁሉም መጠሪያና የሁሉም መሰብሰቢያ የሆነውን ወጥ እስካላበላሸው ድረስ ነው።

ምሬትና እርግማትም የሚያስፈልጉበት ልክ አላቸው። ያም የምስጋናውን ልኬት እስካላጠፉት ድረስ ነው። የሕይወትን መዓዛ፣ የሀገርን ፍቅር እስካላበላሹት ድረስ ነው። በምስጋና ውስጥ እርግማትና ምሬት አለ። በምሬትና በእርግማት ውስጥ ግን ምስጋና የለም። ልክ በወጥ ውስጥ በርበሬ እንጂ፣ በበርበሬ ውስጥ ወጥ እንደሌለው ሁሉ።

በኢሬቻ ጊዜ የምናቀርበው ምስጋናም እንደዚሁ ነው። የሚያስመርሩ ነገሮች ነበሩ፤ የጠፉ የሚታረሙ ነገሮች ነበሩ። ፈታኝ መሰናክሎች ነበሩ። ሕይወትና ንብረት ያጠፉ መከራዎች ነበሩ። ግን እነዚህን ሁሉ ተሻግረናቸዋል። አልፈናቸዋል። ተወጥተናቸዋል። ስለዚህም ምስጋና ይገባል። ዕንቅፋቶቻችን ሰብረው አልጣሉንም፤ ጎትተው አላስቀሩንም፤ ስበው አላቆሙንም - ስለዚህም ምስጋና ይገባል። ከችግሮቻችን ተምረናል፤ ከፈተናዎቻችን ነጥረን ወጥተናል፤ ከስሕተቶቻችን ታርመናል - ስለዚህ ምስጋና ይገባል። የፈታኞቻችን ዓላማ አልተሳካም። አሳምመውን ይሆናል፤ ግን አይገድሉንም። አዘግይተውን ይሆናል፤ ግን አያስቀሩንም። ስለዚህም እናመሰግናለን።

ኢሬቻ የተስፋ በዓል ነው። ሰው የትውስታ ዐቅም አለው። ስለዚህም ትናንትን ያስታውሳል። በትናንት ውስጥ መኖር ግን አይቻልም። ከትናንት ተምሮ ወደፊት መጓዝ የግድ ነው። ተስፋ በሌለበት ነገ የለም። ሰዎች በተዘጋ ግንብ ውስጥ ለዘመናት ኖረው ኅሊናቸው ሳይጎዳ እንዲወጡ የሚያደርጋቸው ተስፋ ነው። ነገን በተሻለ ማሰብ። ነገን እንደ አዲስ መጀመር። የትናንቱ ኮምጣጤ የነገውን ወተት እንዳያበላሽብን ማድረግ። የትናንቱ እንክርዳድ የነገውን ስንዴ እንዳይበክልብን ማድረግ። ተስፋ ማለት እርሱ ነው።

ተስፋ ከሁለት ነገር ይመነጫል። ከእምነትና ካለማወቅ። ነገ ያልተነካ ዐቅም ነው። ያልተነካውን ዐቅም የተሻለ አደርገዋለሁ ብሎ ማመን ወሳኝ ነው። ነገን ለመለወጥ ዐቅምም፣ ክሂሎትም አለኝ ብሎ ማመን ያስፈልጋል። በብርሃን አሻግሮ ጨለማ ከማየት፤ በጨለማ አሻግሮ





ብርሃን ማየት ይበልጣል ብሎ ማመን። ከእኔ የተሻለ የነገ ባለቤት መሆን የሚችል የለም ብሎ ማመን - ነው ተስፋ።

ሁለተኛው የተስፋ ምንጭ ስለነገ አለማወቅ ነው። መገመት ይቻላል። በርግጠኝነት ግን ነገ ምን እንደሚሆን ሠፍሮና ለክቶ ርግጡን መናገር አይቻልም። ነገ ባለማወቅ የተሞላ ነው። ነገን ወደ ዕውቀት መቀየር የብልህ ድርሻ ነው። አምኖ ከተሠማራ ሰው ውጭ ነገ በርግጠኝነት የተገለጠለት የተለየ ሰው የለም። ለዚህ ነው ነገ ለሁላችን እኩል የሚሆነው። ትናንት በምናውቀው ምክንያት ለሁላችን እኩል ባይሆን እንኳን፣ ነገ ግን ለሁላችንም እኩል ነው። በነገ ውስጥ የምንበላለጠው፣ በተሻለ መልኩ ተዘጋጅተን በተሻለ መልኩ ከሠራን ብቻ ነው።

ኢሬቻ የይቅርታ በዓል ነዉ። የተጣላና  የተቀያየመ ሳይታረቅ፣ ይቅር ሳይባባል ወደ ታላቁን የኢሬቻ በዓል ወደማክበር አይሄድም። ኢሬቻ ያለፉ ቁስሎች በይቅርታ  ታክመዉ የሚድኑበት፣ ቁርሾ እና ቂም በቀል ተወግዶ በዕርቅ የሚተካበት ታላቅ በዓል ነዉ።  ከታላቁ የኢሬቻ በዓል የቂም በቀል እና |የጥላቻን ምዕራፍ በመዝጋት በዕርቅ፣ ይቅር ባይነት የከረሙ ቁስሎቻችን እንዳያመረቅዙ  በፍቅር የማከም ሀገር በቀል ጥበብን የምንማርበት በዓል ነዉ።

ኢሬቻ የአንድነት በዓል ነዉ። በአስደናቂዉና ታላቁ ኢሬቻ በዓል ከሁሉም ኢትዮጵያ ጫፍ የሚመጡ ብሄር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦችን የሚወክሉ ተሳታፊዎች የሚታደሙበት፣ ወንድማቸዉ ለሆነዉ የኦሮሞ ሕዝብ የእንኳን አደረሰህ መልካም ምኞት የሚገጹበት በዓል ነዉ።

ተሳታፊዎች መጪዉ ጊዜ ብሩህ እንዲሆን የሚመራረቁት እና ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን በማጠናከር በወንድማማችነትና በዘመናዊ የማኅበረሰብ ዕሴቶች ላይ የተገነባች ጠንካራ አንድነት ያላትና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ምናደርገዉን ጥረት ለማሳካት የሚጠቅመን በዓል ነዉ።

ኢሬቻ ላይ ስንሆን እነዚህን ታላላቅ ዕሴቶች እናስባለን። ቀደምቶቻችን ሀገራችንን ለዛሬ ያደረሷት፣ ሁሉ በእጃቸው ሁሉ በደጃቸው ሆኖላቸው አይደለም። የሚፈልጉት ተሟልቶ፣ የታገሉለት ተሳክቶ ብቻ አይደለም። በብዙ ሕመምና በብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ አልፈዋል። የተሻለን ነገ ለማምጣት ሲሉ በትግልና ያለፈውን በምስጋና በመዝጋት ለዛሬ ደርሰዋል። ምሬት እንደ ቁስል እንዲመዘምዛቸው አልፈቀዱለትም። ኀትቶ እንዲያስቀራቸውና ጠልፎ እንዲጥላቸው አልተመቻቹለትም።

ለመሆኑ የሀገራችንን ጉዞ ከእነዚህ ዕሴቶቻችን ውጭ ማሰብ እንችላለን? የሀገራችንን ያለፉትን ዓመታት ጉዞ በምስጋና እንዝጋው። ስኬቶቻችንን ቆጥረን - ይሄንን አግኝተናልና እናመሰግናለን እንበል። ስሕተቶቻችንንና ድክመቶቻችንን ቆጥረን እነዚህ ስሕተቶቻችን አላስቀሩንም፤ የሚታረሙበትና የሚሻሻሉበት ሌላ ዓመት አግኝተናል - እናመሰግናለን እንበል። የመሳሳትን ፈተና፣ የማረም ዕድል ያሸንፈዋል። የጥፋትና የወድመትን መከራ፣ የልማትና የሕዳሴ ዕድል ይረታዋል።

መንገዳችን ያለቀ፤ መጽሐፋችን የተጠናቀቀ፤ ፋይላችን የተዘጋ፣ ወንዛችን የረጋ አይደለም። ከሠራንበት ዘመን ይልቅ ያልሠራንበት





የወደፊቱ ዘመን ይበልጣል። ችግሩ አስተምሮናል፤ ፈተናው አብስሎናል፤ ስሕተቱ ታይቶናል። ከትናንቱ ዕውቀታችን የዛሬው፤ ከትናንቱ ብቃታችንም የአሁኑ ይበልጣል። ስለዚህም ነገን በተሻለ ዐቅም እንጠቀምበታለን። ትናንትን የሚለውጠው ነገ ነው።

የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ። ከትናንት ተምረን፤ ትናንትን በምስጋና ዘግተን፤ ነገን የተሻለና የበለጠ ለማድረግ አንድ ሆነን እንነሣ። በኢሬቻ በዓል ላይ ወደ ንጹሕ የተፈጥሮ ውኃ እንሄዳለን። ርጥብ የተፈጥሮ ቄጤማ እንይዛለን። ሆራው ንጹሕ የሆነው፣ የደፈረሰው ጠርቶ ነው። ቄጤማው ለምለም የሆነው፣ የደረቀው ለምልሞ ነው። ኢትዮጵያም እንዲሁ ናት። የደፈረሱት መልኮቿ ደፍርሰው አይቀሩም፣ ይጠራሉ። የደረቁት ዕሴቶቿ ደርቀው አይቀሩም፣ ይለመልማሉ። ከሰኔ እስከ መስከረም ያለው ዝናብ በኦሮሞ ባህል የፈተናውን ዘመን ያስታውሳል። በወንዙ ሙላት መንገድ ይዘጋል፤ በክረምቱ ኃይል ወዳጅ ዘመድ ይለያያል። እህሉ ስለማይደርስ ቀጠና(ረሃብ) ይኖራል። Birraa(መከር/መፀው) ግን የተስፋ ዘመን ነው። እህል ይደርሳል፤ ውኃው ይጠራል፤ መንገድ ይከፈታል፤ ሰማዩ ይገለጣል፤ ወባ ይጠፋል። ጊዜውም Ganna ይባላል። የፈተናው ወቅት መዝጊያ ማለት ነው።

ኢትዮጵያ Ganna ወቅት ላይ ናት። የፈተናውን ጊዜ እየጨረሰች ወደ Birraa(መከር/ መፀው) ዘመን የምትሻገርበት። Birraa(መከር/መፀው) ምንም እንኳን አስደሳች ወቅት ቢሆን ሥራ ግን ይፈልጋል። እህሉን ከአጥፊዎች መጠበቅ፣ ዐቅምን አሰባስቦ በአንድነት ማጨድ፣ መከመርና

መውቃት፤ ወቅት ሳይጠብቅ የሚመጣ ዝናብ እህሉን እንዳይጎዳው ወትሮ ዝግጁ መሆን እና እህሉ በአጨዳና በዐውድማ ተፋስሶ እንዳይባክን ጥንቃቄ ማድረግ ናቸው። የሀገራችንም ሁኔታ እንደዚሁ ነው። የተስፋችን ዘመን - የኛ ትግል፣ ጥንቃቄ፣ ወትሮ ዝግጁነትና ጥበቃ ከታከለበት የተሳካ እንደሚሆን እምነቴ ነው።

**በድጋሚ መልካም የኢሬቻ በዓል ይሁን!**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፣**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘለዓለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያን እና ህዝቦቿን፣**
**የእጃችንንም ሥራ ይባርክ!**
**አመሰግናለሁ!!**





# የሰሜን እዝን ጥቃት በተመለከተ የተሰጠ መግለጫ

**ጥቅምት 23፣ 2013 ዓ.ም**

**ውድ የሀገሬ ህዝብ ሆይ፣**

ዛሬ ከሀዲ ኢትዮጵያዊያን ኢትዮጵያን ወግተዋታል። ኢትዮጵያ ያጎረሰ እጇ፣ ያጠባ ጡቷ ተነክሷል። ላለፉት 20 ዓመታት በቀበሮ ምሽግ ውስጥ በመሆን ሀገሬ፣ ወገኔ፣ ህዝቤ ብሎ በብዙ ሺዎች መስዋዕትነት ከፍሎ፣ ቆስሎ፣ ደምቶ፣ ደክሞ፣ ሀገሩንና ህዝቡን የታደገው የሀገር መከላከያ ሰራዊት ዛሬ ምሽት ከመቀሌ ጀምሮ በበርካታ ሥፍራዎች በከሃዲ ኃይሎችና ባደራጁት ኃይል ጥቃት ተፈጽሞበታል።

ይህ ጥቃት በሀገራችን እስካሁን ከደረሱ ጥቃቶች እጅግ አስነዋሪ የሚያደርገው ሰላም ለማስከበር በተለያየ ሀገር የተሰማራው የሀገር መከላከያ ሰራዊት እንኳ በውጭ ኃይሎች ያልደረሰበትን ጥቃት፣ በገዛ ወገኖቹ ከጀርባው እንዲመታ፣ ብዙዎች እንዲሰዉ፣ እንዲቆስሉ፣ ንብረቶች እንዲወድሙ ተደርገዋል።

ይህ የጥፋት ኃይል ላለፉት በርካታ ወራት እኩይ ተግባራት ሲፈጽም ቆይቷል። በተለይም በተለያየ የሀገራችን ክፍሎች ባሰለጠናቸው፣ ባስታጠቃቸውና ባሰማራቸው ኃይሎች በንጹሐን ዜጎች ላይ እጅግ ዘግናኝ የሆነ ጥቃት ሲፈጽም መቆየቱ ይታወቃል። የዚህ ጥቃት ዋነኛ ዓላማ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ትኩረቱን እንዲያጣ፣ እንዲበተን፣ ዜጎች በመከላከል ላይ እንዲያተኩርና ባሻቸው ጊዜ እዚያ ባለው ኃይል ላይ ጥቃት ለመሰንዘር የዘየዱት የእኩይ ዘዴ ነው።

ይሁንና ዛሬ በመቀሌና በአንዳንድ አካባቢዎች ከፈጸሙብን ጥቃት በተጨማሪ በዳንሻ በኩል በአማራ ክልል ላይ ጥቃት ፈጽመዋል። በአማራ ክልል የነበረው ኃይል ይህንን ጥቃት የመከተ ሲሆን በመላው የትግራይ ክልል ያለው ሰራዊት ለትግራይ ክልል ከእንግዲህ በኋላ "ጥይት አያስፈልግም፤ የጥይት ድምጽ አይገባውም፤ ይህ ህዝብ ብዙ ደክሟል፤ ብዙ ተቸግሯል፤ ለእነዚህ እኩይ ተግባር ለሚፈጽሙ ከሃዲ ኃይሎች የትግራይ ህዝብ ምሽግ ቢሆንም ለእኛ ወገናችን ነውና ወገናችንን ለእነዚህ ሰዎች ስንል አናጠቃም" ብሎ በከፍተኛ ትዕግስት የቆየው የሀገር መከላከያ ሰራዊት ባልጠበቀው ሁኔታ ጥቃት ተፈጽሞበታል።

ይህ ጥቃት በመላ ሀገራችን ቀድመው ባሰለጠኑት፣ ባሰማሩት፣ ባዘጋጁት ኃይል በተለያየ ከተማ፣ በተለያየ ቦታ፣ መሰል በንጹሐን ዜጎች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ሊካሄድ ስለሚችል መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከሚሊሻ፣ ከፖሊስ ሰራዊት፣ እንዲሁም በአካባቢያቸው ከሚገኝ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ጋር በመተባበር ቀያቸውን፣ ጎረቤታቸውን፣ ሰፈራቸውን፣ ከተማቸውን፣ አካባቢያቸውን በንቃት እንዲጠብቁ





እያሳሰብኩ፤ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ከጠቅላይ ሰፈር በሚሰጥ ትዕዛዝ መሠረት መለዮውን ሀገሩንና ህዝቡን እንዲከላከል። ለሚከፍለው መስዋዕትነት ዛሬም እንደተለመደው በታሪክ ውስጥ የሚታሰብ መሆኑን እየገለጽኩ፤ ይህ እኩይ ኃይል መጥፊያው በመድረሱ በሰላም፣ በንግግር፣ በውይይት ሊፈቱ የሚችሉ ነገሮችን ባለፉት ጥቂት ቀናት ካለምንም ሃፍረት በሚድያ በመውጣት፣ ከየትኛውም የውጭ ኃይል ጋር በመተባበር "ኢትዮጵያን እወጋለሁ" ብሎ ሲያውጅና ሲናገር የነበረው ኃይል፣ ይህን ለማመን የሚያስቸግር ንግግር በተግባር በዚህ ምሽት አረጋግጧል።

ይህ ጉዳይ ለኢትዮጵያውያን እጅግ አሳዛኝ አሳፋሪም ቢሆን፣ ዛሬም እንደተለመደው እኛ ኢትዮጵያውያን በተደመረ በተባበረ ክንድ፣ ይህንን ከሃዲ ኃይል ለማሳፈርና ለመደምሰስ አስፈላጊውን ሁሉ የምናደርግ መሆኑን እየገለጽኩ፣ የትግራይ ህዝብ ወገኔ፣ ዘመዴ፣ ህዝቤ ብሎ ላለፉት ሃያ ዓመታት በቀበሮ ምሽግ ውስጥ በመሆን በብዙ ሺዎች የሚቆጠር መስዋዕትነት የከፈለውንና አንተን ለመጠበቅ አስፈላጊውን ሁሉ ያደረገው የሀገር መከላከያ ሰራዊት የደረሰበት ጥቃት ጥቃትህ መሆኑን በመገንዘብ ከሀገር መከላከያ ሰራዊት ጋር በመሆን ሀገርህን እንድትከላከል፣ እንድትጠበቅ አሳስባለሁ።

በመላው የሀገራችን ህዝቦች አስፈላጊውን መረጃ በየጊዜው በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት የሚሰጥ መሆኑን እየገለጽኩ፣ ኢትዮጵያ ዛሬም እንደትላንቱ ተደምራ ተባብራ የገጠማትን ፈተና ትሻገራለች፤ ጠላቷን ታሸንፋለች።

ይህ አሳፋሪ ድርጊት በማይደገም ሁኔታ የሚቀለበስበትን መንገድ መላው የሀገራችን ህዝቦችና የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በመተባበር የሚፈጽሙት ይሆናል።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር! ፈጣሪ ኢትዮጵያና ህዝቦቿን ይጠብቅ!**





# በሕግ ማስከበር ዙሪያ የተሰጠ መግለጫ

**ጥቅምት 24፣ 2013 ዓ.ም**

በትናንትናው ምሽት ተስፋ የቆረጠውና ከሐዲው የሕወሀት ቡድን በሀገር መከላከያ ሰራዊት ላይ ያልታሰበ የማይጠበቅ ጥቃት በመፈፀም ሊያደርስ የፈለገው ኪሳራ መግለፄ ይታወቃል። ጦርነት ሰው በላ ነው፣ ጦርነት ሀገር ያደኸያል፣ ጦርነት ቤተሰብ ይበትናል፣ በዚህም ምክንያት በምድራችን ዳግም ጦርነት እንዳይፈጠር መንግስታችን እጅግ ማመን ከሚከብድ በላይ በከፍተኛ ትዕግስት አንዲት ጥይት እንዳትተኮስ ያደረግነው ጥረት በሙሉ ከንቱ እንዲቀር አድርገዋል።

በሀገራችን በሺህ የሚቆጠሩ  ጦርነቶች አካሄደናል። የጦርነት ታሪክ እየሰማን አድገናል፣ በጦርነት ውስጥ ኀልምሰናል፣ በዚህም ምክንያት ጦርነት የድህነት ሁሉ ምንጭ እንደሆነ ስለምንረዳው ጦርነትን ለማስቀረት ያደረግነው እልህ አስጨራሽ ትግል በዚህ ተስፋ በቆረጠ ኃይል ሳይሳካ ቀርቷል። ጦርነት በቅኖች ፍላጎት ብቻ ሊቆም እንደማይችል ዛሬ በተግባር ማረጋገጥ ተችሏል።

ጦርነት በክፉዎች ጠብ-ጫሪንት በማንኛውም ሁኔታ ሊቀሰቀስ እንደሚችል ይህ ከሃዲ ቡድን አሳይቶናል። የዚህ ጦርነት አላማ ኢትዮጵያን ማሸነፍ ኢትዮጵያን ማንበርከክ እንደማይቻል ካለመገንዘብ

ሳይሆን የኢትዮጵያን ሰራዊት በማዳከም ለውጭ ጠላቶች ሀገሪቱን አሳልፎ የመስጠት ከፍተኛ ፍላጎትና አላማ የያዘ ነው።

ይህን እንድል ያስደፈረኝ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ለሃያ አመታት ሲጠብቀው የኖረውን ህዝብ፣ ከአንበጣ መንጋ የታደገውን ህዝብ፣ አብሮት ያረሰና እርሻውን የሰበሰበ ህዝብ፣ መሐከል ላይ ሆኖ በዚህ ሁኔታ እጅግ አሳፋሪ በታሪክ ውስጥም ትልቅ ጠባሳ የሚሆን ጥቃት ተሰንዝሮበታል።

የመከላከያ ሰራዊት በዘር እንዲከፋፈል እርስ በእሱ እንዲባላ ከእርስ በእርስ ውጊያ ያለፈውም በሚሊሻ በልዩ ሐይል እንዲመታ ለእንቅስቃሴ የሚያደርገው ጥረት ለመግታት ከፍተኛ ሙከራ ተደርጓል።

ትናንት ከምሽቱ አራት ሰአት ገደማ መንግስታችን ምንም አይነት የውጊያ ጥርጣሬ ስላልነበረው ሁለት የካርጎ ኤርክራፍት ሙሉ አዲሱን የተለወጠውን ገንዘብ ወደ መቀሌ ልከን የተቀየረውን አሮጌ ለማምጣት ከምሽቱ አራት ሰዓት እስከ ምሽቱ አራት ሰአት ተኩል ሁለት የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላኖች መቀሌ ይገኙ ነበር፤ ምንም አይነት የጦርነት ድባብ ያለ እንኳ ቢሆንም በገዛ ሰራዊቱ ላይ ይህን መሰል ጥቃት ይሰነዝራል የሚል የእብደት እሳቤ አልታሰበም።

ይሁንና በመቀሌ የመብራት ቅርንጫፍ የሚገኙ አንዳንድ ሰራተኞች በመጠቀም መብራት እንዲጠፋ በማድረግ፣ ቴሌኮም እንዲጠፋ በማድረግ፣ ዛሬ በነበረው እንቅስቃሴ በየቦታው መንገድ እንዲዘጋ እና ሰራዊቱ ከአንድ ስፍራ ወደ አንድ ስፍራ ሔዶ ራሱን መከላከል





እንዳይችል ለማድረግ ይህ ከሃዲ ኃይል ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፣ እኩይ ተግባራትን ፈጽሟል። ይሁን እንጂ የትግራይ ህዝብ የጠበቀውን፣ አብሮት ያረሰው፣ አብሮት የአምበጣ መንጋ የተከላከለውን፣ የሚያውቀውን ጦር ላለማስጠቃት ያደረገው እጅግ የሚያኮራ ተግባር በህዝባችን እንድንኮራና እንድናመሰግነው አስገድዶናል።

የትግራይ ሚሊሻና ልዩ ሐይል “በዚህ ፍትሐዊ ባልሆነ ጦርነት ወገን በወገን ላይ፣ ወንድም በወንድሙ ላይ የሚከፍተው ጦርነት ተገቢ አይደለም” በማለት ላለመዋጋት ጥረት ከማድረጉም በተጨማሪ ወደሚመቸው አጎራባች ክልሎች በመሸሽ ከጦርነት ውስጥ ራሱን ለማግለል ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። ይህ ሊጠናከር የሚገባ የእርስ በእርሱን ውግያ ለመቀነስ ሳያቅ ተገዶ የአንድን አንጃ ቡድን ለማሳካት ህይወቱን እንዲማግድ የተገደደው ኃይል ሊወስድ የሚገባው እርምጃ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የአማራ ህዝብና የአማራ ሚሊሻ የአማራ ክልል ልዩ ሐይል በአንዳንድ የአማራ ክልል ላይ የተሰነዘሩ ጥቃቶችን እጅግ በሚያስደንቅ ጀግንነት በመከላከል ይህ ኃይል ያሻውን የመንሰራፋት፣ የመስፋፋት ፍላጎት በመግታት ከመከላከያ ሰራዊት ጋር በመቀናጀት የጦርነቱን ፍላጎት ባለበት መግታት ብቻ ሳይሆን አስፈላጊ ቦታዎችን ለመቆጣጠር ችሏል።

ከዚህ በተጨማሪ ከመላ ህዝባች ዛሬ የነበረው ግብረ መልስና ድጋፍ፣ የሞራል ድጋፍ፣ የሐሳብ ድጋፍ መንግስታችን በታላቅ ክብር የሚመለከተው መሆኑን እገልጻለሁ።

ለመላ የኢትዮጵያ ህዝብ ይህ ሁኔታ የማናውቃቸውን ጀግኖች የፈጠረ ይህ ሁኔታ ዛሬም ኢትዮጵያ ለአላማቸው፣ ለመለዮአቸው፣ ለባንዲራቸው፣ ለሀገራቸው እንዲሁም ለህዝባቸው የሚዋደቁ ለማመን የሚቸግሩ ጀግንነት የሚፈጽሙ የሰራዊት አባላት እንዳላት ማረጋገጥ ችለናል።

አዲጸብሪ በተባለ አንድ ቦታ የነበረች ሻለቃ የተከፈተባትን ጥቃት ለመላከል ንብረቷን፣ ማዘዣ ጣቢያዋን፣ ለመጠበቅ ያደረገችው ተጋድሎ እጅግ የሚያስደምም የሚያስደንቅ ነበር።

ከዚያ በተጨማሪ በሁመራ አካባቢ፣ በዳንሻ አካባቢ እንዲሁም ቅራቅር በተሰኘ በአማራና የትግራይ ክልል ድንበር ላይ በነበሩ ውጊያዎች ጀግናው ሰራዊታችን እንዲሁም የአማራ ልዩ ሃይል እና ሚሊሻ ያደረጉት አስደናቂ ተጋድሎ በህይወታችን የሚዘከር ይሆናል። በሃገር መከላከያ ሰራዊት ብርቱ የደህንነት ተግባር ይህ አንጃ ያሻውን ሳያደርግ ዛሬ የሞከራቸውን ሙከራዎች ሁሉ ከሽፈው ውለዋል።

ይሄንን ጉዳይ በማጠናከር የጀመረውን እኩይ ተግባር ለማስቆም እና የሃገራችንን አንድነት እና ሰላም ለማስጠበቅ የሃገር መከላከያ ሰራዊት የሚያደርገውን ጥረት ለመደገፍ ማገልገል እየቻሉ ልምድ ያላቸው ስመጥር ሶስት ሌፍተናንት ጄነራሎች ዛሬ ወደ ሃገር መከላከያ ሰራዊት እንዲቀላቀሉ እና ያለውን ሃይል በማጠናከር ተቋሙን ፍጹም ኢትዮጵያዊ አድርገው እንዲገነቡት ኢትዮጵያን የሚከላከል እና የሚጠብቅ የሁሉም ህዝቦች በእኩልነት የሚታዩበት እና በእኩል የሚኮሩበት ተቋም እንዲሆን ይሄንን ተግባር እንዲፈጽሙ ሌፍትናንት





ጀነራል አበባው፣ ሌፍትናንት ጀነራል ዮሃንስ፣ ሌፍተናንት ጀነራል ባጫ ይሄንን ሚሽን መንግስት ሰጥቷቸዋል።

ዛሬ ስራቸውን የጀመሩ ሲሆን መላው የሰራዊት አባላት በጀመራችሁት አሥደናቂ ጀግንነት በመተባበር እጅ ለእጅ በመያያዝ ይሄንን እኩይ ተግባር የማስቆም እና የመከላከል አቅማችሁን አጠናክራችሁ ይሄን ሃሳብ እንድታከሽፉ በድጋሚ እያሳሰብኩ፤ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሳንፈቅድ፣ ሳንወድ የተከፈተብንን እና የምንከላከለውን ጦርነት ዛሬ በሁሉም ግንባር በከፍተኛ ደረጃ እራሳችንን በመከላከል ተጨማሪ ቦታዎች እና ንብረታችንን እንዳይወሰዱ ለማድረግ የሰራን ሲሆን በሚቀጥሉት ቀናት በሚኖሩን ኦፕሬሽኖች የምንሰራቸውን ስራዎች እንደየአስፈላጊነቱ የምንገልጽ መሆኑን እገልጻለሁ።

አጠቃላይ የጦርነቱን አጀማመር፣ የጦርነቱን ታሪክ በሂደቱ የነበሩትን አሳፋሪ ተግባራት አጠቃላይ ኦፕሬሽኑ ሲጠናቀቅ ለህዝብ የምንገልጽ መሆኑን እየገለጽኩ፤ ለዛሬው በነበረው ውሎ ሁሉ በሁሉም ግንባር የጠላት ፍላጎት እና መሻት እንዳይሳካ አድርገን የዋልን መሆናችንን የሰራዊታችንን ጀግንነት እያየን እና አስፈላጊውን ተጨማሪ ሃይል እና ድጋፍ በማድረግ በሚቀጥሉት ቀናት ራሳችንን የመከላከሉን እርምጃ አጠናክረን የምንቀጥል መሆኑን በድጋሚ ለማረጋገትጥ እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያ ዛሬም እንደትላንቱ በጀግኖች ልጆቿ ታፍራ እና ተከብራ የምትኖር፣ የምትሻገር፣ አንድነቷ የሚጠበቅ ሃገር መሆኗ በድጋሚ የምናረጋግጥ መሆኑን እየገለጽኩ፤ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ ያደረገልንን ድጋፍ በማጠናከር ይህ እኩይ አላማ፣ ይህ እኩይ ተግባር ሙሉ በሙሉ ከሽፎ ሃገራችን አስተማማኝ ሰላም ተረጋግጦ እና

የብልጽግና ጉዞአችን ቀጥሎ የተሟላ ነገር ማረጋገጥ እስክንችል ከሃገር መከላከያ ሰራዊት ጎን በመሆን የሚጠበቅብንን ነገር ሁሉ እንድናደርግ እጠይቃለሁ።

ዛሬ በነበረን ውሎ የተሳካ፣ የጠላትን ፍላጎት ያኮላሸ፣ የወገንን ፍላጎት ያጠናከረ በሚቀጥሉት ቀናት ደግሞ ይበልጥ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ።

**አመሰግናለን!**





# የሕግ ማስከበር እርምጃውን በማስመልከት የተላለፈ መልእክት

ታህሳስ ፣ 2012 ዓ.ም.

**የተከበራችሁ የሀገራችን ሕዝቦች፣**

በትግራይ ክልል የጀመርነው ሕግን የማስከበር እርምጃ ሁለተኛ ምእራፍ ተጠናቅቋል። አሁን በመጨረሻውና በሦስተኛው ወሳኝ ምእራፍ ላይ እንገኛለን።

እየወሰድን ያለነው ሕግን የማስከበር እርምጃ ሦስት ምእራፎች እንዳሉት ቀደም ብለን የገልጻን ሲሆን፤ የመጀመሪያው ምእራፍ፥ በገዛ ወገኑ የተጠቃውን የመከላከያ ሠራዊታችንን አሰባስበንና አጠናክረን፣ ተቋርጦ የነበረውን የእዝ ሰንሠለቱን ወደ ቦታው መልሰን ግዳጁን እንዲወጣ ማስቻል ነበር። በዚህም መሠረት ሠራዊቱ በከፍተኛ እልህ፣

ቁጭትና ወኔ ከገጠመው አደጋ በፍጥነት አገግሞ፣ የሕዝቡን ከፍተኛ ድጋፍ በልቡ ይዞ የሀገር ክህደት የፈጸመውን የሕወሃት ቡድን ለሕግ ለማቅረብ በተለያዩ አቅጣጫዎች ተንቀሳቅሷል።

የእርምጃው ሁለተኛ ምእራፍ ዋና ዓላማ፥ የሕወሃትን ጁንታ ከየአካባቢው እያስለቀቀ፣ ዐቅሙንም ከጥቅም ውጭ እያደረገ፣ ሕዝቡን ከዚህ የከህደት ቡድን ይዞታ ነጻ በማድረግ፣ የመሸገበትን የመቀሌ ከተማ መክበብ ነበር።

ከመቀሌ ውጭ ያለውን ሕወሃት የያዘውን ቦታ ነጻ በማውጣት፤ የተዘረፉ ትጥቆችንና ካምፖችን መልሶ በመያዝ፤ የክህደት ቡድኑ የዘረፋቸውን ስትራቴጂያዊ የሆኑ መሣሪያዎችን ለውድመት ሳያውላቸው በፊት ከጥቅም ውጭ ማድረግ፤ በግዳጅ የያዛቸውን የሠራዊታችን አባላት ማትረፍ፤ የተሠውትን መቅበር እና አደጋ የሚደርስባቸውን ዜጎች መታደግ የሁለተኛው ምእራፍ እርምጃ ዝርዝር ዓላማዎች ነበሩ።

በዚህ መሠረት በዳንሻ፣ በሑመራ፣ በሽሬ፣ በሽራሮ፣ በአክሱም፣ በአድዋ፣ በአዲግራት፣ በአላማጣ፣ በጨርጨር በመሖኒ፣ በኮረምና በሌሎችም ቦታዎች በተወሰደ እርምጃ ሠራዊታችን ሕዝብ እየታደገና ድል እያደረገ ተጉዟል። ሕዝብ ለመታደግ በነበረው ዓላማ በተቻለ መጠን ሕግ የማስከበር እርምጃው በከተሞች አካባቢ ጥፋት እንዳያስከትሉ እና ሰላማዊ ዜጎች ዒላማ እንዳይሆኑ፤ ታሪካዊ ቅርሶች፣ የሃይማኖት ቦታዎች፣ የሕዝብ መገልገያዎች፣ መሠረተ ልማቶች፣ የተፈጥሮ ሀብቶችና የመሳሰሉት ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት





እንዳይደርስባቸው ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጓል። ምንም እንኳን የከህደት ቡድኑ የጥፋቱ ደረጃ ሰፊ እንዲሆን ቢፈልግም፥ በሕግ ማስከበር እርምጃችን ወቅት፥ የአየር ኃይል አውሮፕላኖቻችን ለሕዝቡ በነበራቸው ከፍተኛ ጥንቃቄ፣ ወደ ዒላማዎቻቸው የቀረበ አንድም ሰው እንኳን ከገጠማቸው የታጠቁትን ትጥቅ ይዘው እስከ መመለስ ደርሰዋል።

በዚህም፥ ምንም ዓይነት ኃላፊነት የማይሰማው ቡድኑ በሃይማኖት ተቋማትና በቅርሶች አካባቢ ተኩስ እንዲኖር የነበረውን ፍላጎት፣ በሠራዊቱ ተልዕኮን በጥበብ የማከናወን ችሎታ አማካኝነት የቡድኑ ፍላጎት ሊመክን ችሏል። ነጻ በወጡ አካባቢዎች በሀገር ሽማግሌዎች አማካኝነት ሕዝቡን መልሶ እንዲደራጅ፣ በመከላከያ ሠራዊቱ አማካኝነት የተጎዱ ወገኖቻችን እንዲደገፉ፣ ሕዝቡ የተፈጸመውን ነገር በትክክል እንዲረዳና ራሱን የሂደቱ አካል ለማድረግ ተችሏል። የተበላሹና የተበጣጠሱ ማኅበራዊ ተቋማትን፣ የመገናኛና የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶችን በመጠገን፣ ሕዝቡ የሰላም አየር መተንፈስ ጀምሯል።

ሁለተኛው የእርምጃው ምእራፍ ሕዝቡን የታደገ፣ የጁንታውን አከርካሬ ሰብሮ አቅሙን ወደ በመቀሌ ማጥበብ ተችሏል። አሁን የቀረው ጉልበት መቀሌ ላይ ያደራጀው ምሽግ እና አልፎ አልፎ የሚያሰማው ከንቱ ፉከራ ነው። በዚህ ሕግን የማስከበር እርምጃ ወቅት ሕዝባችን ከመከላከያ ሠራዊቱ ጎን መሆኑን በግልጽ አሳይቷል። ሕወሃት ስለ መከላከያ ሠራዊቱ የነዛው ፕሮፓጋንዳም ስሕተት መሆኑን

የትግራይ ሕዝብ በዓይኑ ለማየት ችሏል። የሠራዊቱን ደግነትና ከጥፋት ለመታደግ የከፈለውን መስዕዋትነት ሕዝቡ ራሱ መመስከር ጀምሯል።

በየአካባቢው ከዕለት ጉርሱ እየቀነሰ ለሠራዊቱ በማብላት፣ የከህደት ቡድኑ የሚሄድባቸውን መንገዶች በመጠቆም፤ የተደበቁ መሣሪያዎችንና ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን በማጋለጥ ከሠራዊቱ ጎን ሆኖ የሚያስደንቅ ተጋድሎ ፈጽሟል። በዚህም የትግራይ ሕዝብ ቀድሞም በሕወሃት የጥፋት መንገድ ምን ያህል እንደተንገሸገሸ በግልጽ አሳይቷል።

ሠራዊቱ ሽሬ በገባበት ጊዜ ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ በሆታ ከመቀበሉም በላይ፣ ጁንታው ያስታጠቀውን ከ200 በላይ መሣሪያ ሰብስቦ ለመከላከያ አስረክቧል። ሠራዊታችን አክሱም በደረሰም ጊዜ ሕዝቡ ራሱ በከህደት ቡድኑ ቁጥጥር ሥር የዋሉ የሠራዊት አባላትን ነጻ አድርጎ፣ የቆሰሉትን አክሞና ተከባክቦ፣ በክብር ለመከላከያ ሠራዊቱ አስረክቧል።

የአክሱም ሕዝብ የመከላከያ ሠራዊቱ ከእርሱ ጋር እንዲሆን ከመጠየቁም በላይ አብሮ ተሠልፎ የሕግ ማስከበሩ ዳር እንዲደርስ ቁርጠኝነቱን አሳይቷል። በተመሳሳይ ሠራዊታችን አዲግራት ሲገባ፣ ሕዝቡ ራሱ የተደበቁትን የልዩ ኃይልና የሚሊሻ አባላት እየያዘ ለመከላከያ አስረክቧል።

በተቃራኒው የቆመው የከህደት ቡድን ስንትና ስንት የሀገር ሀብትና ጉልበት የፈሰሰባቸውን መሠረተ ልማቶችን እያፈረሰ፣ ትምህርት ቤቶችንና የጤና ተቋማትን ከጥቅም ውጭ እያደረገ፣ መንገዶችና





ድልድዮችን እየደረማመሰ ሸሽቷል። የታሪካዊቷ አክሱም የአውሮፕላን ማረፊያ ላይ ጭምር ውድመት በማድረስ የቀጣይ ዓመታት የቱሪዝም እንቅስቃሴያችን ላይ ከፍተኛ ጠባሳ ጥሎ አልፏል። የክልሉ ነዋሪ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ የሚያደርግባቸውን መንገዶች በዶዘር ማፈራረሱ ሳይበቃው፥ የመቀሌ ከተማን ልክ እንደ ጦርነት አውድማ ለማድረግ በመዛት ቅንጣት ታህል ኃላፊነት የማይሰማው መሆኑን በግልጽ አሳይቷል።

## ውድ ኢትዮጵያውያን፣

አሁን ሕግ የማስከበር እርምጃው ወደ ሦስተኛውና ወሳኙ ምእራፍ ተሸጋግሯል። ሦስተኛው ምእራፍ በመቀሌ የሚካሄደውና የከህደት ቡድኑን ለሕግ ለማቅረብ የሚደረግ የመጨረሻው እርምጃ ነው። የዚያኑ ያህል ከፍተኛ ጥበብ፣ ጥንቃቄና ትእግሥት የሚፈልግ እንደሆነ ግልጽ ነው።

ይህ የከህደት ቡድን ለምንም ነገር ደንታ እንደሌለው፥ ለሕዝቡ፣ ለታሪኩ፣ ለባህሉ፣ ለቅርሱና ለእምነቱ ቅንጣት ርህራሄ እንደሌለው በግልጽ አሳይቷል። ሁሉም ነገር ጠፍቶ እርሱ ብቻ ቢተርፍና ከሕግ ቢያመልጥ ደስተኛ ነው። በዚህም የተነሣ በመቀሌ ከተማ ውስጥ የሐይማኖት ተቋማትን፣ ሆቴሎችን፣ የመንግሥት ተቋማትን፣ የሕዝብ መኖሪያ መንደሮችን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ ቅርሳ ቅርሶችንና መካነ መቃብሮችን ሳይቀር እንደ ምሽግ ተጠቅሞባቸዋል። መጥፋቱ ላይቀር ብዙዎችን ይዞ ለመጥፋት ተዘጋጅቷል። ልክ በአንዳንድ ሀገራት

እንደሚታዮት የሽብር ቡድኖች፣ ለሕዝብና ለሀገር ምንም ደንታ የሌላቸው አሸባሪዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ፣ ይሄ የጥፋት ቡድን መቀሌን እንደ ሕዝብ መኖሪያነት ሳይሆን እንደ ጦር አውድማነት ቆጥሯታል።

በዚህ ቡድን ምክንያት እንዲሞቱ የተገደዱት ነዋሪዎች ዜጎቻችን እንደመሆናቸው መጠን እና የሚወድመውንም ከተማ ነገ መልሶ ለመገንባት ዞሮ ዞሮ የእኛው ኃላፊነት እንደመሆኑ መጠን በመቀሌ የሚኖረን የሕግ ማስከበር እርምጃችን፥ ጉዳትን እጅግ በቀነሰ መልኩ መከናወን እንዳለበት እናምናለን። ስለዚህም፥ የመቀሌ ከተማን ከከፋ ጉዳት ታድገን ዘመቻውን በድል የምናከናውንበትን መንገድ እንደምንከተል ለመግለጽ እወዳለሁ። መንግሥት ይሄንን የሚያደርገው በዚህ የከህደት ቡድን የተነሣ ሕዝብና ሀገር እንዳይጎዳ ከመፈለግ ነው።

በመሆኑም፤

**አንደኛ**፡- የመቀሌ ከተማ ነዋሪዎች፥ በጀመርነው ሕግን የማስከበር እርምጃ ቁልፍ ተዋናዮች እንድትሆኑ፣ ከሠራዊታችን ጎን በመቆም ይሄንን የከህደት ቡድን አባላት ለፍርድ በማቅረብ ወሳኝ ሚናችሁን እንድትወጡ ጥሪ እናቀርባለን። ለጥቂት ስግብግብ ጁንታዎች ሲባል አንድም ሰው መሞት፣ አንዲትም ንብረት መውደም የለበትም። ለዚህም የእናንተ ትብብር አይተኬ ሚና የሚጫወትና ብዙ ጉዳቶችን እንደሚያቀል እሙን ነው።





**ሁለተኛ**፡- የከህደት ቡድኑን አላማ በማስፈጸም ላይ ያላችሁ የትግራይ ልዩ ኃይልና ሚሊሻ አባላት፥ አሁንም ቢሆን እጃችሁን በሰላም ለመስጠት ጊዜው አልረፈደም። ሕግ የማስከበር እርምጃው የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ መሆናችንን ተረድታችሁ የማያዳግመውን እድል እንድትጠቀሙበት፤ ከአሁኗ ሰዓት ጀምሮ ባለው በ72 ሰዓታት ውስጥ እጃችሁን በሰላም ለመንግሥት እንድትሰጡ የመጨረሻ ጥሪያችንን እናቀርብላችኋለን።

**ሦስተኛ**፡- የጁንታው አባላት፥ የጥፋት ጉዟችሁ ጀንበሯ እየጠለቀች መሆኑን አምናችሁ፣ ከማትወጡበት ቅርቃር ውስጥ መግባታችሁን ተገንዝባችሁ በቀጣይ 72 ሰዓታት ውስጥ እጃችሁን በሰላም እንድትሰጡ እንጠይቃችኋለን። የመጨረሻዋን እድል ተጠቀሙበት። ተጨማሪ የሕዝብ እልቂት ከመፍጠርና ከተማ ከማውደም ተቆጥባችሁ ከታሪክ ውግዘት እንድትድኑ ጥሪ እናቀርባለን።

በመጨረሻም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲረዳው የምንፈልገው ነገር ቢኖር ሦስተኛውን ምዕራፍ የሕግ ማስከበር እርምጃ ከማከናወን ጎን ለጎን በጥፋት ቡድኑ ምክንያት ቀያቸውን ጥለው ወደ ተለያዩ አካባቢዎች የሸሹ ወገኖቻችንን ለመመለስ፤ የተፈናቀሉትን መልሶ ለማቋቋም፤ መሠረተ ልማቶችን ለመጠገን፤ ነጻ የወጡ አካባቢዎች ላይ የሚኖሩ ዜጎች ወደ መደበኛ የሕይወት እንቅስቃሴያቸው እንዲመለሱ ለማድረግ በሁሉም ረገድ ዝግጅት አድርገናል። ወደ ትግበራ ስንገባ ከእጃችን እንዳያጥር እና ዐይናችንን ወደ ሌሎች እንዳናማትር ሁሉም ኢትዮጵያዊ የበኩሉን ድጋፍ ለማድረግ እንዲነሳ ጥሪ እናቀርባለን።

እኛ ኢትዮጵያውያን የቆየና የዳበረ እርስ በእርስ የመረዳዳት ባህል ስላለን፣ የማንንም የውጭ እጅ ሳንጠብቅ ወገኖቻችንን እኛው ልናቀዋቁማቸው ይገባል። ለዚህም በመንግሥትና በተለያዩ የማኅበረሰብ አንቀሳቃሾች አማካኝነት የተጀመረውን እንቅስቃሴ እንድትቀላቀሉ ስል ጥሪ አቀርባለሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና**
**ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**





# የገና በአል መልእክት

**ታህሳስ 28 ፣ 2013 ዓ.ም.**

የዘንድሮውን የልደት በአል የምናከብረው በዚህ ዓመት ያሳለፍነውን ፈታኝ ተጋድሎና ከፊታችን የሚጠብቀንን ወሳኝ ዕድል እያሰብን ነው። አሁን በፈተናና በዕድል መካከል እንገኛለን። ዓለምም የመጀመሪያውን የክርስቶስ ልደት ያከበረችው በፈተናና በዕድል መካከል ሆና ነበር። በአዳም በደል ምክንያት የመጣው የመከራ ዘመን እያለፈ፤ የመከራው ዋና ምንጭ የሆነው ዲያብሎስ፣ በማኅጸን በተጀመረ የማዳን ሥራ እየተሸነፈ፤ የጨለማው ንጉሥ እየተረታ፤ የዘመናት ቋጠሮ እየተፈታ ነበር። ከፊት ደግሞ የመዳን፣ የብርሃን፣ የሰላም፣ የነጻነት እና የፍቅር ዘመን እየመጣ ነበር።

ነገሩ ግን ሂደቱ ቀላል አይደለም። የጨለማው ዘመን አበጋዞች እንዲነጋ አልፈለጉም። ሊመጣ ያለው ድኅነት የማያስቀሩት ቢሆንም እንኳን፤ የሚያሸንፉት እስኪመስሉ ድረስ ተፍጨርጭረዋል። እየበራ ያለውን መብራት የሚያጠፉት ያህል ታግለዋል። የተከፈተውን የብሩኅ ተስፋ መስኮት የሚከረችሙት ያህል ፎክረዋል። የተሸነፈውን ዘንዶ ዳግም ሕይወት የሚዘሩለት ያህል ተገዳድረዋል። ግን ይህ ሁሉ አልሆነም።

ሄሮድስ ተነሥቶ ነበር። ብዙዎችንም በአሰቃቂ ሁኔታ ገድሏል። ዘመኑም የብሩኅ ተስፋ ሳይሆን የመከራ ዘመን መስሎ ነበር። በክርስቶስ መወለድ የተፈጠረው ደስታ፣ በቤተልሔም ሕጻናት ግድያ የደበዘዘ እስኪመስል። በበረት ውስጥ የተፈጠረው ተስፋ፣ በድንግል ማርያምና በክርስቶስ መሰደድ ያበቃለት እስኪመስል። በመላእክት ዝማሬ የተበሠረው አዲስ ዘመን፣ በሄሮድስ አበጋዞች ጭፍጨፋ ሕልምና ተረት እስኪመስል። የኦሪት ዘመን አበቃ ሲባል፤ በኦሪት ዘመን የማይሠራ ግፍ፣ በዘመነ ሐዲስ በቤተልሔም ከተማ ተከሠቷል። ብዙዎችንም ተስፋ አስቆርጧል።

ቢሆንም መከራው አላፊና ጠፊ እንጂ ዘላቂ አልነበረም። ያ እንደ ተራራ የገዘፈ የመሰለው ሽብር እንደ እንቧይ ካብ የሚፈርስ፤ እንደ ባሕር የሰፋ የመሰለው መከራ እንደ መጋቢት ወንዝ የሚነጥፍ፤ የማይሸነፉ የሚመስሉት ሁሉ እንደ ጎልያድ የሚወድቁ፤ አስጨናቂዎች ሁሉ መልሰው የሚጨነቁ መሆናቸውን - ያሳየ ኢጋጣሚ በዚያን ዘመን ተከስቷል። ለዚያም ነው ሁሉም አልፎ ዛሬ ድረስ የልደትን በአል ልዩ ትርጉም ሰጥተን የምናከብረው።

## ውድ የሀገሬ ሕዝቦች፣

አሁን ኢትዮጵያ በልደቱ ቀን ቆማ ልደትን የምታከብር ሀገር ናት። ተስፋዋን፣ ሰላሟን፣ ንጋትና ብልጽግናዋን እንዳታይ በዙሪያዋ የቆሙ የሄሮድስ አበጋዞች አሉ። በቻሉት መጠን መከራችን እንዲቀጥል ይፈልጋሉ። የተወለደልንን የተስፋ ብርሃን ለመግደል ይጥራሉ። ከተማዋን የዋይታ ከተማ ለማድረግ ይለፋሉ። ነገን እንዳናይ





መስኮቶችን ሁሉ ይዘጋሉ። ወደ ተስፋ መጠጊያ ዋሻችንን በቋጥኝ ደፍነው በቀቢጸ-ተስፋ ውስጥ እንድንቆይ የተቻላቸውን ያደርጋሉ።

ሆኖም ግን ፈተናችንን ያበዙብን ሄሮድሶች ከብልጽግና መንገዳችን አያስቀሩንም፤ እስከመጨረሻ ሕቅታቸው ወደኋላ ሊጎትቱን ቢጥሩም ጨርሶ ከጉዟችን ሊያስቆሙን አይችሉም። በመንገዱ ላይ የዘሩትን አሜኬላ እየለቀምን፣ እንቅፋትና ጋሬጣውን ተሻግረን ከተራራው እናት መውጣታችን አይቀርም። የተሰበረውን ድልድይ ጠግነን፣ ከችግሮቻችን በላይ ከፍ ብለን ያለጥርጥር ኢትዮጵያን ወደ ተስፋዋ አድማስ እናድርሳታለን።

ገና ያኔ የለውጥ ጉዟችን ሲወለድ ጀምሮ ተመሳሳዩን ሲያደርጉ ነበር። በየወቅትና ኢጋጣሚው ጉዟችን እንዲሰናከል ያልወረወሩት ድንጋይና ያልጣሉት ጋሬጣ አልነበረም። ከመንገዳችን ሳንሰናከል ገፍተናል፤ በፈተናዎቻችን ትምህርት፣ በችግሮቻችን ጥንካሬ፣ በእንቅፋቶቻችን ብርታት እያገኘን ዛሬ ላይ ደርሰናል። ከእያንዳንዱ ጨለማ ወዲያ ንጋት መኖሩን እያመንን፣ ዐይናችንን ወደ ውጋጋን አቅንተን ጉዟችንን ቀጥለናል። እኛ አንድ ወደ ፊት በተራመድን ቁጥር ችግሮቻችን ወደኋላ ይሸሻሉ፤ እኛ ይበልጥ በበረታን ቁጥር እነሱ ይሸነፋሉ።

ያም ሆኖ አንድ ልብ ሊባል የሚገባው እውነት አለ። ለኢትዮጵያ የፈነጠቀው የተስፋ ብርሃንን ከእንግዲህ ማንም ሊያጠፋው አይቻለውም ሲባል እስከናካቴው አይሞክርም ማለት አይደለም። የሄሮድስ ወታደሮች ሕጻኑን ክርስቶስ እስከ ግብጽ ድንበር ድረስ እንደተከታተሉት ሁሉ ፈታኞቻችን ነገም ይከተሉናል። እንቅፋቶቻችን

መልካቸውን እየቀያየሩ በመንገዳችን ላይ መቆማቸውን ይቀጥላሉ። ከእንግዲህ የኢትዮጵያ የትንሳኤ ጉዞ ፍጥነቱ ከምንም በላይ የሚወሰነው በእኛ ጥንካሬ እንጂ በእነሱ ችግር ፈጣሪነት መጠን አይደለም፤ መሆንም የለበትም።

እኛ እስካልፈቀድንላቸው ድረስ ለሀገራችን የተወለደውን ተስፋ ሊያመክኑት፣ የተለኮሰው ፋና ሊያጠፉት አይችሉም። ጨልሞባት የነበረችው ሀገራችን ምሽቷ መንጋት ጀምሯል - እኛ ከበረታን ዳግም በእነሱ አይጨልምም። ያነበጣት የዘመናት ፍዳ አንዴ መደርመስ ጀምሯል - እኛ ችላ እስካላልን ድረስ ዳግም አይቆለልም። ከእንግዲህ የኢትዮጵያ ስኬትና ውድቀት ማዕከሉ የእኛ ጥንካሬና ድክመት ነው ብለን ማመን አለብን።

**ውድ ወገኖቼ፣**

ከተስፋችን አንጻር ፈተናችን ብዙ ባይሆንም ወደፊት ይበልጥ መፈተናችን እንደማይቀር ማወቅ አለብን። ወደ ተስፋ በተጠጋን ቁጥር የመከራው ብርታት እንደሚጨምር ያለፉት ሦስት ዓመታት ጥሩ ማሳያዎች ናቸው። በመከራ ውስጥ ከሚመጣ መከራ ይልቅ በተስፋ ውስጥ የሚመጣ መከራ እጅግ ይከብዳል የሚባለውም ለዚህ ነው። በአንድ በኩል ልቡና ተስፋ እያደረገ ፈተና ሲገጥመው ያማርራል። በመከራ ውስጥ ሆኖ መከራ ሲገጥመው ግን ‹የበሰበሰ ዝናም አይፈራም› እንደሚባለው በአማራጭ ማጣት ይታገሣል። በተስፋ ውስጥ ፈተና የሚያጋጥመው ሰው ደግሞ እምነት ያጣል። አእምሮው ለሐሴት እንጂ ለሐኮት አልተዘጋጀም። ከትግል ጊዜ ይልቅ በድል ጊዜ ብዙዎች





ይሞታሉ የሚባለው ለዚህ ነው። በትግል ጊዜ የነበራቸው የመሥዋዕትነት ሥነ ልቡና በድል ጊዜ አይገኝም።

ኢትዮጵያ ሁለቱም ያጋጥማት ይሆናል። ተስፋ ባነገበች ሀገር ላይ ተስፋ መቁረጥ፤ ሰላም ባነገበች ሀገር ላይ ግጭት፤ ብልጽግናን ባነገበች ሀገር ላይ ውድመት ይመጣባት ይሆናል። መነሻችን ‹አያዎ› ነው - ‹አይ እና አዎ›። መድረሻችን ግን ‹አዎ› ብቻ ነው። ብርሃን ጨለማን፤ ሰላም ጦርነትን፣ ፍቅር ጥላቻን፤ አንድነት መለያየትን፣ ብልጽግና ኋላቀርነትን ማሸነፋቸው አይቀሬ ነው። በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ ማጨዳቸው የማይቀር ነው።

ከወፍ ዕንቁላል ውስጥ ጠንካራው ቅርፊቱ ነው። ጫጩቷ ቅርፊቱን ሰብራው ከወጣች በኋላ ግን ጠንካራ መሆኑ ያበቃል። ጫጩቷ ታድጋለች፤ ቅርፊቱ ግን በተቃራኒው መፈራረስ ይጀምራል። ጫጩቷ ትበራለች፤ ቅርፊቱ ዱቄት ይሆናል፤ ብሎም ይበሰብሳል። ጫጩቷ ወፍ ሆና ሌሎች ዕንቁላሎች ትጥላለች፤ ሌሎች ጫጩቶችንም ትፈለፍላለች። ቅርፊቱ ግን ይበልጥ እየበሰበሰ ወደ አፈርነት ይለወጣል። የኢትዮጵያም ችግሮች እንደዚሁ ናቸው። ለጊዜው ጠንካራና ዙሪያችንን ከብበው የያዙን ይመስላሉ። ይህ የሚሆነው ግን እስክንሰብራቸው ድረስ ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ እኛ ከችግሮቻችን መብለጣችን አይቀሬ ነው።

ከክርስቶስ ልደት የምንማረው ይሄንን ነው። የትናንቱ ሲያልፍ ዝም ብሎ አያልፍም። የመጨረሻ ሙከራውን አድርጎ ነው የሚያልፈው። ልክ እንደሄሮድስ ሙከራ። የነገውም ዝም ብሎ አይመጣም፤ በተጋድሎ

ነው የሚመጣው። ልደት ግን በሚያልፍ መከራና በሚመጣ ዕድል መካከል መሆኑ አይቀሬ ነው። ኢትዮጵያም እያለፈችው በምትሄደው መከራና፣ እያገኘችው በምትመጣው ዕድል መካከል ናት።

‹ዛሬ› በትናንትና በነገ መካከል ስለሆነ የሁለቱም መልክ ይታይበታል። ከትናንት የወረሰው መከራ፤ ከነገ የተዋሰው ደስታ አለው። ንጋት ማለት በሚያልፍ ጨለማና በሚመጣ ቀን መካከል ነው። መሽቷል ያለ ይተኛል፤ ነግቷል ያለ ይነሣል። የእኛም ምርጫ ይሄው ነው። መሽቷል ብለን እንተኛለን ወይስ ነግቷል ብለን እንነሣለን?

**መልካም የልደት በአል ይሁንልን!**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና**
**ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**





# የጥምቀት በአል በማስመልከት መልእክት

**ጥር 11 ፣ 2013 ዓ.ም.**

የኢየሱስ ክርስቶስን የጥምቀት በዓል ስናከብር የግድ ሁለት ነገሮችን እናስታውሳለን። የመጀመሪያው በዓሉ የትኅትና በዓል መሆኑን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በዓሉ የለውጥ በዓል መሁኑን ነው።

ሁሉን ቻይ፤ ሁሉን አድራጊ፤ ሁሉን ፈጣሪና ሁሉን ወሳኝ የሆነው አምላክ በውኆች መካከል ተገኘ። በዮሐንስ እጅ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ። ራሱን ዝቅ አድርጎ ወደ ዮሐንስ ዘንድ ወረደ፤ ምንም የሌለው መስሎ ከሰዎች መካከል ተገኘ። ምናልባት በዚያ ጊዜ በዮርዳኖስ ወንዝ ዙሪያ የተገኙት ሰዎች ከእነርሱ እንደ አንዱ ሊቆጥሩት ይችላሉ። በሄኖምና በዮርዳኖስ ማዶ ከሚኖሩት ሰዎች መካከል የመጣ መስሏቸው ይሆናል። ያ በመካከላቸው ደካማ መስሎ የቆመው ክርስቶስ እልፍ አእላፍ ሠራዊት እንዳለው አያውቁም ይሆናል።

የሚያጠምቀውን ዮሐንስን አስቀድሞ የላከ፤ በዙሪያ ሊጠመቁ የከበቡትን ከአፈር የፈጠረ፤ የሚጠመቁበትን የዮርዳኖስ ወንዝ ያስገኘ

መሆኑን አያውቁም። ዓይን ለማየት፣ ጆሮም ለመስማት የምትጓጓለት፤ ክብሩን ቢገልጥ ምድርና ሰማይ በፊቱ ሊቆሙ የማይቻላቸው መሆኑን አያውቁም። ትኑት ሆኖ በመካከላቸው ተገኝቷልና። በትኅትና ውስጥ ያለውን ኃይልና በትዕቢት ውስጥ ያለውን ድካም ዓለም አታውቀውም። በትዕቢት የወደቀውን ዲያብሎስ፣ ክርስቶስ በትኅትና ድል ነሣው። ዲያብሎስም የታለለው ኃይል ከትዕቢት ጋር ያለ መስሎት ነበር። በቤተልሔም በከብቶች በረት መወለድ የትኅትና ሥራ ነው። በዮርዳኖስ ከዮሐንስ ዘንድ ለመጠመቅ ከሰማያት መውረድ የትኅትና ሥራ ነው። ዲያብሎስ ሁለቱንም አላወቃቸውም።

ተዉ ማለት፤ እንታረቅ፣ እንስማማ ማለት፤ እንነጋገር እንወያይ ማለት፤ ጦርነትና ግጭት፣ ጠብና ጥላቻ አያስፈልገንም ብሎ መለመን ዐቅም ማጣት አይደለም። ድንበር ለሚጋፉ የሰላምን እጅ መዘርጋት፤ ለሚፎክሩ የፍቅርን ልብ ማሳየት፤ ለሚወርሩ የዲፕሎማሲን መንገድ መምረጥ ዐቅም ከማጣት የሚመጣ አይደለም። የኃያልነት ምልክቱ ትኅትናና ትዕግሥት ስለሆነ እንጂ። የትኅትና ገመድ የመጨረሻዋ ቋጠሮ ብርቱ ክንድ ናት። ከተሠነዘረች ሳታደቅቅ አትመለስም።

የጥምቀት ሥራ በልደት፣ የሆሳዕና ሥራ በጥምቀት፣ የስቅለት ሥራ በሆሳዕና፣ የትንሣኤም ሥራ በስቅለት ቀን አይሠራም። ክርስቶስ ያስተማረን ይሄንን ነው። ሁሉን በጊዜው መሥራትን። ሁሉም ሥራ የሚሠራበት ትክክለኛ ጊዜ አለው። ያ ቀን ሲደርስ ማንም ወደኋላ አይመልሰውም። ያ ቀን ሲደርስ ማንም ሽንፈቱን አይቋቋምም። ያ ቀን ሲደርስ አምባ ይፈርሳል፤ ያ ቀን ሲደርስ ተራራው ይናዳል፣ እሳቱም ይበርዳል።





የጥምቀት በዓል የለውጥ በዓል ነው። በሰው ልጅ ታሪክ ወስጥ ዓለም በንፍር ውኃ ጠፍታለች። የሰው ልጅ ራሱ የተፈጠረበት፣ ለሰው ልጅ ኑሮ ተብሎ የተፈጠረው፤ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ የዓለምን አንድ ሦስተኛ የያዘው ውኃ የሰውን ልጅ አጥፍቶታል። ኖኅና ስምንት ቤተሰቡ፣ ከእንስሳቱ ጋር ሲቀሩ ዓለም በጥፋት ውኃ ጠፍታ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ ለጥፋት የዋለውን ውኃ ለድኅነት፤ ለመቅሰፍት የዋለውን ውኃ ለበረከት ለውጦታል። የውኃውን ተፈጥሮ ሳይሆን የውኃውን አገልግሎት፣ የውኃውን ታሪክ ነበር የለወጠው።

ከዚህ ትልቅ ትምህርት መውሰድ አለብን። በሀገራችን ለጥፋትና ለመቅሰፍት የዋሉ ብዙ ነገሮች አሉ። ሕዝብ ለማፋጀት፤ ሕዝብ ለመከፋፈል፤ ሕዝብ ለማለያየት የዋሉ ብዙ መሣሪያዎች አሉ። ኢያሌ ሕጎችና አሠራሮች አሉ፤ ተቋማትና ሥርዓቶች አሉ። ውኃን ወደ መቅሰፍት የቀየረው የሰው ልጅ ክፋት ነበረ። እነዚህን ሕጎች፣ አሠራሮችና ተቋማት ወደ ጥፋት መሣሪያነት የቀየራቸው የሰዎች ክፋት ነው። እነዚህ መሣሪያዎች የሕዝብን ደኅንነት፤ የሀገርን አንድነት፤ የዜጎችን ሰብአዊ መብት፤ የኢትዮጵያን ብልጽግና እና ዕድገት እንዲያመጡ አድርገን መለወጥ አለብን። እሳት ምግብ ለማብሰያም ቤት ለማቃጠያም ይውላል። ወሳኙ ተጠቃሚው ሰው ነው። እሳትን ለጥቅም ለማዋል እሳቱን ወደ ውኃነት መቀየር አያስፈልግም፤ የእሳቱን አጠቃቀም መቀየር እንጂ።

ዓለም ለልማት፤ ለዕድገት፤ ለዴሞክራሲ፤ ለሰላም እና ለብልጽግና የተጠቀመባቸው ሕግጋት፣ ተቋማት፤ አሠራሮች፣ ሞያዎች፣ ሥርዓቶች፣

በሀገራችንም ከሞላ ጎደል አሉ። የምንፈልገውን ሰላም፣ ብልጽግናና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግን አላመጡልንም። የለውጥ ሥራችንን በሚገባ አልሠራንም ማለት ነው።

ለውጥ እያንዳንዱን የመቅሰፍት ዱካ እየተከተሉ መለወጥን ይጠይቃል። ክርስቶስ ሥራውንም ከዓይን ቅጽበት ባነሰ ጊዜ መፈጸም ይችል ነበር። የሰውን ልጅ ድኅነት ለማረጋገጥ ግን 33 ዓመት ከ3 ወራት በምድር ላይ ኖሯል። ከልደት እስከ ዕርገት የተሠራው ሥራ 34 ዓመታትን ወስዷል። ይህም ለእኛ ትምህርት እንዲሆነን ነው። እያንዳንዱን የሰውን ልጅ የመቅሰፍት ዱካ እየተከተለ መርገሙን ወደ በረከት፤ መቅሰፍቱን ወደ ምሕረት፤ ጥፋቱን ወደ ድኅነት፤ ሞቱን ወደ ሕይወት ለውጦታል።

በሀገራችን ውስጥ ለግማሽ ምዕተ ዓመት በየቦታው የተዘራው፣ የተቀበረውና የበተነው መቅሰፍት ብዙ ነው። ጠላት የዕዳ ደብዳቤያችንን በየቦታው ቀብሮታል። ዛሬ ምናየው የወገኖቻችን ስቃይ፤ ግፍ፤ መከራና ስደት የዚያ የዕዳ ደብዳቤ ውጤት ነው። በንጹሐን ላይ እየወረደ ያለው ውርጅብኝ የዚያ ዕዳ ደብዳቤ ውጤት ነው። ከግራ ከቀኝ የምንሰማው ፉከራ ሁሉ የዕዳ ደብዳቤው ዕዳ ነው።

እኛ ማድረግ ያለብን የመቅሰፍቱን ዱካ ተከትለን የዕዳ ደብዳቤውን መደምሰስ ነው። ጊዜ ይወስድ ይሆናል። ትዕግሥት ይጠይቅ ይሆናል፤ ደካማ አስመስሎ ያሳይ ይሆናል፤ ዐቅመ ቢስ ያስመስል ይሆናል፤ ወደ ታች መውረድ ይጠይቅ ይሆናል፤ ግን እያንዳንዱን መርገም ወደ በረከት፤ እያንዳንዱን መቅሰፍት ወደ ምሕረት፤ እያንዳንዱን ጥፋት





ወደ ድኅነት፤ እያንዳንዱንም ሞት ወደ ሕይወት መቀየራችን አይቀርም። የኢትዮጵያ አምላክ ከእኛ ጋር ነውና።

ጠላት በሕዝቡ ውስጥ የቀበረው፣ የዘራውና የበተነው ብዙ መቅሰፍት አለ። አንዳንዱን መዋቅራዊ አድርጎታል፤ አንዳንዱን የሕግ ቅርጽ ሰጥቶታል፤ ለአንዳንዱ ሥርዓት ሠርቶለታል፤ ሌላውን በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ አካትቶታል፤ ለአንዳንዱ በዓል ሰይሞለታል፤ ለሌላው ሚዲያ አዘጋጅቶለታል። ለአንዳንዱ ተቋም አቋቁሞለታል። አንዳንዱ የሕዝቡ ትርክት ሆኗል፤ ሌላው በዘፈን ውስጥ ገብቷል፣ ሌላውም የፓርቲ ፕሮግራም ሆኗል። ይሄን ሁሉ ዱካ በዱካ እየተከተልን የዕዳ ደብደቤውን መደምሰስ ይጠበቅብናል።

ለውጡ ጊዜ ይጠይቅ ይሆናል። እውነታው ግን አይቀሬ መሆኑ ነው። የክርስቶስ ሲወለድ መጠመቁ አይቀሬ መሆኑን አሳይቷል። መጠመቁ ደግሞ ማስተማሩ አይቀሬ መሆኑን አመልክቷል። ማስተማሩ መሰቀሉን፤ መሰቀሉም መነሣቱን፤ መነሣቱም ማረጉን፣ ማረጉ ዳግም መምጣቱ አይቀሬ መሆኑን አስረግጧል። ሁሉንም በየምዕራፉ ለማስቀም የሞከሩ ነበሩ። አልተሳካላቸውም። ሁሉም በጊዜውና በሰዓቱ ተፈጽሟል። የኢትዮጵያ ትንሣኤም ሂደቱ ይሄው ነው። የጀመርነው የለውጥ ሥራ አንዱ ለሌላው መሠረት እየሆነ፤ አንዱ የሌላውን መምጣት እያበሠረ፤ አንዱ የሌላውን አይቀሬነት እየተናገረ ይቀጥላል። በየደረጃው በአጭር ሊያስቀሩት የሚሞክሩ ይኖራሉ። ትርፉ ድካም ነው። የኢትዮጵያ መለወጥ እንደሆን አይቀሬ ነው። ዱካ በዱካ የዕዳ ደብዳቤዋ እየተደመሰሰ፣ መርገሙ ወደ በረከት፤ መቅሰፍቱ

ወደ ምሕረት፤ ጥፋቱ ወደ ድኅነት፤ ሞቱ ወደ ሕይወት መለወጡ አይቀሬ ነው።

ክርስቶስ ከውልደቱ እስከ ጥምቀትና ስቅለቱ፣ ትንሳኤና እርገቱ ያለው ሒደት ተስፋውን ሲጠባበቁ ለነበሩ ሁሉ፥ የሰው ልጆች የዘመናት ፍዳ የሚያበቃበት ጊዜ እየቀረበ መምጣቱን ጠቋሚ ነበር። በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ ክርስቶስ የፈጸማቸው ተግባራት፥ የአዳምን ዘር የመዳን ተስፋ ያለመለሙና ጠላት ዲያቢሎስን ያሸነፉለት በመሆናቸው ለሰዎች ልጆች ሁሉ ትልቅ ብስራት ናቸው። ታላቅ ደስታም አስገኝተውል።

ኢትዮጵያችን የዘመናት ፈታኞቿ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸነፉና ብሩህ ተስፋዋ እየበዛላት በመሆኑ ሁላችንም እንደሰታለን። ለዚያ ደስታ ስለታጨን በእርግጥም ሀሴት ማድረግ ይገባናል። ነገር ግን ለታላቅ ደስታ የታጨ ሁሉ እስከመጨረሻው በጽናት ይጓዛል፤ ድልን ይጎናጸፋል ማለት አይደለም። በክርስቶስ የማዳን መንገድ የአዳም ዘር በሞላ ለደስታ ቢታጭም እንደ ይሁዳ ያሉት በመንገዱ ተሸንፈው ስለወደቁ የድሉ ባለቤት አልሆኑም። ስለዚህ የተስፋ መንገዳችን በስኬት እንዲቋጭ ዛሬም ሆነ ነገ ፈተናውን በድል መወጣት ይኖርብናል። በየመንገዳችን የሚገጥሙን ፈተናዎች ወደ ተስፋ መሻገሪያ በሮቻችን ናቸው። ጥምቀቱና ስቅለቱ ለክርስቲያናዊው የቅድስና ጉዞ የመዳን በሮች እንደሆኑት ሁሉ እንደ ሀገር ለምናደርገው የዲሞክራሲ ጉዞ ከፊታችን የሚጠብቀን ምርጫ በድል ከተወጣነው አንዱ የተስፋ በራችን መሆኑ አይቀርም። ስለዚህ ሁላችንም ጥሩ ዝግጅት አድርገንና መንፈሳችንን አጽንተን በድል ልንሻገረው ይገባል።





ሌላው በአለ ጥምቀቱን ስናከብር ቅንነትን ተላብሰን፤ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች የተጎዱ ወገኖቻችንን በቸርነት ዓይናችን እያየን፣ የተቸገሩትን በድጋፍ እጃችን እየጎበኘን፤ ለመልካም ለውጥ ሳንሰንፍ፣ ከብልጽግና ጉዟችን ሳንደናቀፍ፣ የወቅቱን የኮቪድ-19 ስርጭት ችላ ሳንል ልናከብረው ይገባል። በአውሮፓና የአሜሪካ ሀገራት የኮሮና ወረርሽኝ ክትባት መጀመራቸው ይታወቃል። እኛ ክትባቱን እስክንጀምር ለጊዜው ያለን አማራጭ መከላከል ብቻ ነው። በእስከ ዛሬው የጥንቃቄ ዘዴዎቻችን አማካኝነት ራሳችንን ከወረርሽኙ እየጠበቅን፥ በፊታችን የሚፈነጥቀውን የተስፋ ጮራ አብረን ለማየት ያብቃን እላለሁ።

**በድጋሚ፣ መልካም የከተራና የጥምቀት በዓል እንዲሆን እመኛለሁ!**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# የ125ኛውን የዐድዋ ድል በዓልን በማስመልከት የተላለፈ መልእክት

**የካቲት 23 ፣ 2013 ዓ.ም.**

የዐድዋ ድል የኢትዮጵያውያን የጀግነት፣ የሀገር ፍቅር ስሜትና የጦርነት ጥበብ ውጤት ነው። ጎራዴ ታጥቆ መድፈኛን ለመጣል ከመንደርደር የበለጠ ጀግንነት የለም። ልዩነትን ወደ ጎን ጥሎ በጋራ ለአንድ ሀገር ግንባርን ለባሩድ፣ አንገትን ለካራ ከማቅረብ በላይ የጠለቀ የሀገር ፍቅር ከየትም አይመጣም። ሰፊ ጊዜ ወስዶ ራሱን በሴራና በስትራቴጂ ሲያዘጋጅ እና ከሌሎች በሚያገኘው እገዛ ሲደራጅ የከረመ ኃይልን ጥቃት መክቶ መልሶ በማጥቃት ማሸነፍ በቀላል ብልሃት የሚሆን አይደለም።

በደምና በላብ የወዛ፣ በሥጋና በአጥንት የቆመ፣ በጥበብና በመደመር የደመቀ የዐድዋ ድላችንን እኛ ለኢትዮጵያውያን የተለየ ትርጉም ሰጥተን እንድናከብረው የሚያደርጉን ብዙ ምክንያቶች አሉ። ከእነዚህ መሐል አንዱ፥ የዐድዋ ድል ሀገራችንን ማንም ሊያወርዳት ከማይችልበት ከፍታ ላይ የሰቀላት በመሆኑ ነው። ሀገራችንን ከዚህ ከፍታ ላይ





ገፍትሮ ለመጣል ባለፉት ብዙ ዘመናት አያሌ ጥረቶች ተደርገዋል። በቅርቡ ታሪካችንም እንዲሁ። ግን አልተቻለም። ኢትዮጵያን ለመከፋፈልና ለማለያየት፣ ለማበጣበጥና ለማባላት፣ የተደረጉት ሙከራዎች ሁሉ የከሸፉት በዚህ የተነሣ ነው።

ዐድዋ በከፍታ ላይ ከሰቀላቸው የኢትዮጵያ ዕሴቶች አንዱ ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችን ነው። ከምዕራብና ከምሥራቅ፣ ከሰሜንና ከደቡብ የዘመቱ፤ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በባህል፣ በመልክና በሞያ ኅብር የሆኑ፤ ነገር ግን ኢትዮጵያን ከቅኝ ግዛት የማዳን የአንድነት ዓላማ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ያስገኙት ድል ነው። በዐድዋ ዘመቻ ከ10 ዓመት ሕጻን እስከ 90 ዓመት አዛውንት ተካፍለዋል። ማየት የቻሉት ብቻ ሳይሆኑ ዓይነ ሥውራንም ዘምተዋል። ሴቶች ከስንቅ አዘጋጅነት እስከ ጦር መሪነት ተሰልፈዋል። የእስልምናና የክርስትና የሃይማኖት አባቶች ከጸሎት እስከ ግንባር ተሳትፈዋል። አዝማሪዎች በአንድ በኩል የሠራዊቱን ሞራል እየገነቡ፣ በሌላ በኩል ታሪኩን በግጥምና በዜማ እየከተቡ ዘምተዋል። ሌላው ቀርቶ ሽምጥ ጋላቢዎቹ ፈረሶቻችን በወኔ እሳቱ መሐል ሲገኙ፣ የጭነት አጋሰሶች በፈርጣማ ትከሻዎቻቸው ስንቅ ተጭነው፣ ሌሎችም እንስሳት መሥዋዕት ሆነው ዐድዋን የድል ቦታ፣ ኢትዮጵያን የድል ባለቤት አድገዋል።

ዛሬ በየትኛውም የኢትዮጵያ አካባቢ ብንገባ፣ የትኛውንም የብሔር ብሔረሰብ ታሪክ ብናጠና፣ በየትኛውም የሀገሪቱ አቅጣጫ ሄደን ብንጠይቅ፣ አያቶቹ ወደ ዐድዋ ያልዘመቱ ሕዝብ አናገኝም። መንገድና መገናኛ ባልተስፋፋበት፣ ዘመናዊ መጓጓዣ ባልነበረበት በዚያ ዘመን፣ ከመቶ ሺህ በላይ ሠራዊት ጫካዎቹንና ተራሮቹን በእግሩ እያቋረጠ

የመጣው ኢትዮጵያን ብሎ ነው። መንግሥታዊ ሥርዓቱ ተመችቶት፣ አገዛዙ ተስማምቶት አልነበረም። ኢትዮጵያ የምትባል፣ አያት ቅድመ አያቱ የነገሩት ሀገር ስለተነካችበት ነው። በትራንስፖርትና በመገናኛ እጥረት ሀገሩን ዞሮ ባያያትም፣ ሁሉም ግን ሀገሩ በልቡ ነበረች፤ ኮርታና ታፍራ የኖረች ብርቅዬ ሀገሩ በደም ሥሩ ውስጥ ትዘዋወራለች።

ይህ ሁሉ ኅብረ ብሔራዊ ሠራዊት የተለያየ ቋንቋ እየተናገረ፣ የተለያየ እምነት እያመነ፣ የተለያየ ዓይነት ምግብ እየተመገበ፣ የተለያየ ዓይነት ልብስ ለብሶ፣ የተለያየ ዓይነት ባህል ይዞ፣ በምን እየተግባባ ዘመተ? የሚለውን መጠየቅ ተገቢ ነው። የተግባባው በኢትዮጵያዊነቱ ነበር። ኢትዮጵያዊ ኅብረ ብሔራዊነታችን መግባቢያ ቋንቋ ነውና። አንድነታችን የሚሠራበት ሰበዝ፣ ጥንካሬያችንን የሚገነባው ቅመም፣ ውበታችን የሚኳልበት ቀለም የሚቀዳው ከሌላ ሳይሆን ከኅብረ ብሔራዊ ኢትዮጵያዊነታችን ነውና።

ልዩነትን የማግባቢያ ፍቱን መድኃኒቱ የላቀ ዓላማ መሆኑን የዐድዋ ዐርበኞች ነግረውናል። ማንም ከማይደርስበት ማማ ላይ የሰቀሉት ሌላው ዕሴታችን ይሄ ነው። ከግል ጥቅም፣ ከራስ ዝናና ከጊዜያዊ ሥልጣን የበለጠ፣ ዘለዓለማዊ የሆነ፣ ትውልድን የሚታደግ፣ ሀገርን የሚገነባ፣ የላቀ ዓላማ ካለ ልዩነቶች ሁሉ ውበት ብቻ ሳይሆኑ ጥንካሬ መሆናቸው የዐድዋ ዐርበኞች አስመስክረዋል። ልዩነቶች ለሀገር አንድነትና ለሕዝቦች መስተጋብር ፈተናዎች የሚሆኑት ሊያግባባቸው የሚችል የላቀ ዓላማ ከሌለ ብቻ ነው።





የዐድዋ ዘመቻ ኢትዮጵያውያንን ከጥንቱ በተሻለ ያስተሣሠረ ዘመቻ ነበረ። ኢትዮጵያውያን ከአራቱም ማዕዘን፣ ከሁሉም ብሔሮች፣ ከሁሉም እምነቶች፣ ከሁሉም ዓይነቶች ለአንድ ዓላማ፣ በአንድ ቦታ በዚህ መልኩ መገናኘታቸው ያጠራጥራል። ይብዛም ይነሥም ዛሬ ያለችውን ኢትዮጵያ የሚወክሉ ልዩ ልዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ወረኢሉ ላይ ተገናኝተዋል። ዐድዋ ላይ ዘምተዋል። ለዚህም ነው ብዙ ምሁራን ዐድዋ የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ መሠረት ነው የሚሉት። እኛ ሁላችን የዐድዋ ልጆች ነን የምንለውም ለዚህ ነው።

በውጊያው ጊዜ ከቅድመ አያቶቻችን መካከል አንዳቸው ጎድለው ቢሆን ኖሮ ዛሬ ዐድዋም፣ የዐድዋ ልጅነትም ከእናካቴው ባልኖሩ ነበር። የሀገርን ጥሪ እኩል ሰምተው በጋራ ባይዘምቱና ዐድዋ ላይ የድል ሰንደቅ ባይተክሉ ኖሮ፥ ዛሬ የምናከብረው የድል ቀን መሆኑ ቀርቶ እንደሌሎች አፍሪካውያን የነጻነት ቀን በሆን ነበር። በድል ቀንና በነጻነት ቀን መካከል የሰማይና የምድር ያህል ልዩነት አለ። ዐድዋ ከእኛ የድል ሰንደቅነት አልፎ ተርፎ ለብዙ የነጻነት ቀኖች እንደ ምንጭ ሆኖ ያገለገለ፣ ለጸረ ቅኝ አገዛዝ እንቅስቃሴዎች ፋና የለኮሰ፣ በሁለት ዘሮች በጥቁሮችና በነጮች መካከል የተገነባውን የበታችነትና የበላይነት ግንብ የፈረካከሰ፣ ባለ ብዙ መልክ ትዕምርት ነው።

ኢትዮጵያውያን ብዙ ጥፋቶችን ይታገሣሉ። መሪዎችና ቡድኖች የሚፈጽሟቸውን ስሕተቶች ይታገሣሉ። የመታረሚያና የመስተካከያ ጊዜ ይሰጣሉ። የመሪዎችና የቡድኖች ስሕተቶች ሀገራቸውን እንዲያፈርሱ ግን አይፈቅዱም። ይሄን የኢትዮጵያውያን ዕሳቤ የማይረዱ አካላት ተደጋጋሚ ስሕተት በታሪክ ውስጥ ሠርተዋል።

ኢትዮጵያውያን ነገሮችን ሲታገሡ የደከሙ፤ የተከፋፈሉ፤ አንድ ሆነው መቆም የማይችሉ ይመስሏቸዋል። በዐድዋ ዘመቻ ጊዜ ጣልያኖች ይሄንን ስሕተት ሠርተውታል። በኢትዮጵያ የአካባቢ መሪዎች መካከል የነበረው ትግል የሕዝቡ መለያየት የፈጠረው መስሏቸዋል። ሕዝቡ ነገሮችን በትዕግሥት እየተመለከታቸው መሆኑን አላወቁም። የመሪዎቹ እና የቡድኖቹ ስሕተቶች ሀገር የሚያፈርስ መስሎ ሲሰማው እንደ በረሐ ንብ ሆ ብሎ ተነሥቶ ሀገሩን እንደሚያድን አላወቁም።

በቅርቡም ጁንታው የጣልያንን የመቶ ሃያ አምስት ዓመት ስሕተት ደግሞ ተሳስቷል። ኢትዮጵያውያን በትዝብት ዝም ሲሉ፤ ጥቂቶች በየሚዲያው ኃይለ ቃል ሲወራወሩ፤ እዚህም እዚያም በሚፈጠሩ ግጭቶች ወገኖቻችን መከራ ሲቀበሉ፤ ውጥረት የነገሠ ሀገር የተተራመሰ ሲመስለው - ኢትዮጵያን የማፍረሻ ጊዜው አሁን ነው ብሎ ተነሣ። ኢትዮጵያውያን ጁንታውን የታገሡት የመታረሚያና የመስተካከያ ጊዜ ለመስጠት መሆኑን ረሳው። ‹ሲተኙ እንደ ሬሳ፣ ሲነሡ እንደ አንበሳ› የተባለላቸው መሆናቸውን ዘነጋው። ሀገራቸው አደጋ ላይ ወደቀች መሆኑን ሲያረጋግጡ ሁሉን ነገራቸውን ትተው፣ በኢትዮጵያዊነታቸው ተግባብተው እንደሚዘምቱ አላወቀም። የሆነው ግን ይሄው ነበር።

ዐድዋ የዕርቅንና የይቅርታን ኃይል ያሳየ ድል ነው። በየአካባቢው በነበሩ ግጭቶችና ውጊያዎች የተቀያየሙ መሪዎች ነበሩ። ጣልያኖችም እነዚህን ቅያሜዎች አስፍተው ኢትዮጵያውያንን ማንበርከክ እንደሚችሉ ገምተው ነበር። ሂሳባቸው ግን የተሳሳተ መሆኑን ያወቁት ወዲያው ነው። ኢትዮጵያውያን ቅሬታቸውን በዕርቅ፣ ቅያሜያቸውን በይቅርታ ሻሩት። ‹ሁሉም ከሀገር አይበልጥም› በሚለው





የኢትዮጵያውያን የቆየ መርሕ መሠረት ከመንግሥት ጋር የተጣሉት ሳይቀሩ ለሀገራቸው ለመሞት መጡ። ሀገርና መንግሥት የተለያዩ መሆናቸውን የሚያውቁት ኢትዮጵያውያን፣ ሀገርን የሚያድነው ዕርቅና ይቅርታ መሆናቸውን አምነው ንቃቃቱን ዘጉት። በተለያዩ አካባቢዎች አኩርፈው የሸፈቱ ሳይቀሩ ዕርቅና ሰላም እያወረዱ ከዐድዋው ዘማች ጋር ተቀላቅለዋል።

ዐድዋ የኢትዮጵያውያን የአመራር ጥበብ የታየበት ድል ነው። ዳግማዊ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ በአራት መንገድ ሠራዊቱን አደራጅተዋል። የኋላ ኋላ ዕውን የሆነው ድል በአንድ ጀንበር የመጣ ድል አልነበረም። ብርቱ የሀገር ልጆች በተለያዩ መንገዶች መሣሪያ በማሰባሰብ፣ ስንቅ በማዘጋጀት፣ ጥቂት ጊዜ መግዛት የሚያስችል የዲፕሎማሲና በመረጃዎች የመራቀቅ ሥራዎችን በማከናወን እና ሠራዊቱን አደራጅተው በመዝመት ያንን ድል አሳክተዋል። በየምዕራፉ የነበረውን ፈተና በልኩ እየተጋፈጡ፣ ጥቃቅን ችግሮችን እየታገሡ፣ በጸና ዲስፕሊን እየተመሩ፣ ብልጫ ሊገኝበት የሚቻልበትን መንገድ እየተጠቀሙ፣ የጠላት ጓዳ ጎድጓዳ ውስጥ ገብቶ ጠቃሚ መረጃዎችን እየመነተፉ በመታገል የተገኘ ድል ነው። ይህ የመሪዎችን የአመራር ብልሃትና የሠራዊቱን መርሕ ጠባቂነት ያሳየ ነበር። የአመራር ብልሃት፣ የመሣሪያ አጠቃቀም፣ የሠራዊት ብቃትና የመልክአ ምድር አያያዝ ተባብረው ያስገኙት ድል ነው።

በአጠቃላይ የዐድዋ ድል የማይቻል የሚመስለው የተቻለበት፣ የማይቀየረው የተቀየረበት ታሪካዊ ድል ነው። ያልዘመነ ጦር የታጠቀ አፍሪካዊ ኃይል ልዩ ልዩ የዘመኑ የጦር መሳሪያዎችን እስከ አፍንጫው

የታጠቀ አውሮፓዊ ኃይል ድባቅ መትቶ የጣለበት ውብ አጋጣሚ ነው። የማይቀየር የሚመስለው የነጮች የበላይነት ታሪክ በጥቋቁር አናብስት የተሸነፈበት፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም አደባባይ ጥቁር ፈርጥ ሆና ብቅ ያለችበት ድንቅ ጊዜ ነው። ዛሬ እንደ ተዓምር የምናያቸው ጉዳዮች፣ ከበለጸጉት ሀገራት ተርታ የመሰለፍ ጉዟችን በእርግጥም የሚሳኩ ስለመሆናቸው፣ የድህነት ታሪካችን በብልጽግና የማይሸነፍበት ምንም ምክንያት ስላለመኖሩ ከዐድዋ በላይ ምስክር ፈልጎ ማግኘት አይቻልም።

እናም ኢትዮጵያን ለማበልጸግ የምንጓዝበት መንገድ ከዐድዋ ዕሴቶች መቀዳት አለበት። ዐድዋ ድል ብቻ አይደለም። ዐድዋ የኢትዮጵያ መለያ ‹ብራንድ› ነው። የኢትዮጵያውያን ከፍታ እንዴት ሊመጣ እንደሚችል የሚያሳይ ፍልስፍና ነው። ኅብረ ብሔራዊ አንድነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከመተንተን ይልቅ ዐድዋን ማሳየት በሚገባ ለመረዳት ያስችላል። መሪና ተመሪ ተናቦና ተገናዝቦ ከሠራ ውጤቱ እንዴት ዓለምን እንደሚቀይር ዐድዋ የዘለዓለም ማሳያ ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ለአፍሪካና ለዓለም የሚተርፍ ሐሳብ እንዳለን ዐድዋ ትልቁ ምስክራችን ነው፤ ለወደፊትም ዐደዋን የመሰሉ፣ እንደ ዐደዋ የገዘፉ ምስክሮች እንደሚበዙልን አልጠራጠርም።

ጉዟችን ኢትዮጵያን ወደ ቀጣዩ ከፍታ ማሻገር ነው። የዐድዋን ሪከርድ መስበር ነው። እንደምንችል አረጋግጠናል፤ እንደምንችል ማሳየት ግን ይቀረናል። ሰንኮፎቻችን ሁሉ ቀስ በቀስ እየተነቀሉና መንሳፈፊያ ክንፎቻችን እየተዘረጉ ሲመጡ ያለ ጥርጥር ዘመናችን ብሩኅ ይሆናል፤ ጉዞውን ጀምረናል። ወደ ዐድዋ መድረሻው መንገድ ፈታኝ ነበር፤





የዐድዋ ድል ግን ጣፋጭ ነው። ወደ ብልጽግና መድረሻ መንገዳችን ፈታኝ ይሆን ይሆናል። ብልጽግናችን ግን እንደ ዐድዋ ሁሉ አይቀሬ ድል ነው። ኢትዮጵያ ከዐድዋ በታች አትወርድም። ከዐድዋ በላይ ወዳለው ከፍታ ደግሞ አንድ ሆነን እኛ እናወጣታለን።

**መልካም የድል በዓል ለሁላችንም ይሁን!**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘለዓለም ትኑር! ፈጣሪ ኢትዮጵያን እና ህዝቦቿን፣ የእጃችንንም ሥራ ይባርክ!**

# የጎርጎራ ፕሮጀክት ማስጀመሪያ



# ሃሙሽተ ክፍሊ

## መግለጺ ትግርኛ

# መግለፂ ትግርኛ

26 ጥቅምቲ፣ 2013 ዓ.ም

ዝኸበርካ ህዝቢ ትግራይ፤ እዚ መልእኽቲ እዚ አበቲ ብጉጅለ ጥፍኣት ተገዲድና ዘአተናዮ ዘሕዝን ኩነታት ኾይነ ከሕልፍ ከቢድ ጓሂ ይስመዐኒ።

መንግስቲ ንሃገርናን ህዝብናን ናብ ዝለዓለ ብርኪ ሰላም፣ ብልጽግናን ሥርዓት ፍትሕ ከብጽሕ ራእይ ሰኒቑ፣ መደብ ሃንጺጹ በዓብዩ ናህሪ አብ ምስራሕ አብ ዝርከበሉ እዋን እቲ ንዝሓለፉ ዓመታት አብ ማእገር ህዝቢና ቼቼ ዝብል ዘነበረ ሓይሊ ጥፍኣት ብተደጋጋሚ ጉዕዞና ክንዕቅፈና ምስፀንሐ ሐዚ ድማ ናብ ናይ መወዳእታ ብርኪ አብጺሒዎሎ።

አብ ውሽጢ ህወሓት ዘሎ ጠላምን ጭዋዩን ሓይሊ ደሕሪ ለውጢ አብዝለው ክልተ ዓመታት ፈረቃን ብዝተፈላለዩ መንገድታት ሰላምናን ልምዓትናን ክዕንቅፍ ከምዝፀንጠ ይፍለጥ። እዚ ሓይሊ እዚ በቀዳምነት ንዓኺ ህዝቢ ትግራይ ካብ ሓውካ ህዝቢ ኢትዮጵያ ነጺሉ ተቋዳሲ ሰላምን ብልጽግናን ከይትከውን ገይሩካ ፀኒሑ እዩ። ብካልኣይ ደረጃ ድማ በካልኦት ህዝብታት ኢትዮጵያ ንክትጽላእ ብሽምካ እናማሓለ ብዙሕ ግፍዒታት ይሰርሕ ነይሩ።





በቐፃሊነት ከዓ ነቲ ብደምን ዓጽምን ደቅኻ ዝተኸልካዮ ሕገ-መንግስቲ ሓደብሓደ እናበለ ብግልፂ ጥሒስዎ። እዚ ሓይሊ እዚ ንሽሙ "ሕገ-መንግስቲ ይከበር" እናበለ ነቲ ሕገ-መንግስቲ ግን ደጋጊሙ ጥሒስዎ ኢዩ። ከም አብነት ፈለማ ብፓርላማ ዘወፅኡ ሕግታት መብዛሕቲኦም ጥሒሲዎም፣ ብኻልኣይ ደረጃ ካብ ሕጊ ወጻኢ ምስ ዓለም ለኸ ትካላትን ሃገራትን ጎናዊ ርክባት ጀሚሩ።

ሳልሳይ ድማ አብ መላእ ዓለምን ሃገርና ኢትዮጵያን ብዝተኸሰተ ለበዳ ቫይረስ ኮረና ምክንያት ብቤት ምክሪ ፌዴሬሽን ዝተወሰነ "ውሳነ ምንዋሕ መረፃ" ብግልፂ ብምጥሓስ ዘይሕጋዊ መረፃ አካይዱ። ብረብዓይ ደረጃ ንፌደራል መንግስትን፣ ንክልላት መንግስታትን አፍልጦ ብምንፋግ ርክባት በቲኹ። ሓምሻይ እብ ዝተፈላለዩ ክልላት ምስ ዝርከቡ ፀረ-ሰላም ሓይሊታት እናተሻረኸ ሰላም ይዘርግ፤ ህይወት ንፁሃን ዜጋታት ከዓ የጥፍእ ኣሎ።

ዝኸበርካ ህዝብና፣ እቲ ገበነኛ ጉጅለ ኩሉ ሥርዓት አልቦ ስጉምቲታት ክወስድ ከሎ ንክብርኻን ደሕንነትካን ብምሕሳብ መንግስቲ ፌደራል ወላ ሓንቲ ስጉምቲ አይወሰደን። ብፍላይ ድማ አብዚ እዋን እዚ ኣቐዲምና እንሰርሖ ለበዳ ኮሮናን አምበጣን ምክልኻል ከምኡ ድማ ዝበፅሐ እክሊ ምእካብ ስለዝኾነ ናብ ከሚዚ ዓይነት ኩነታት ክንኣቱ ኣይሓሰብናን ነይርና። እቶም ዝጠቐስኩዎምን ካሉኦት ምኽንያታት ናብ ሓይሊ ስጉምቲ ዝደፍኡ እንኳ እንተነበሩ ንኽብርካን፣ ደሕንነትካን ኢልና ዋላ ሓንቲ ስጉምቲ ኣይወሰድናን።

ዝኸበርካ ህዝብና እዚ አብ ውሽጢ ህውሓት ዝተፈጠረ ዕሉል ገበነኛ ሓይሊ አብመወዳእታ ከዓ ነቲ ምሳኻ ነአስታት ዕስራ ዓመታት ዝነበረ፣ ዝሕልወካ ዝፀንሐ፣ ፀገምካ ዝተኻፈለን ብደም ዝተዛመደን ሓይሊ

ምክልኻል ደቂሱ ከሎ ኣብ ካምፕታት ኣቲዩ ብዘሰክፍ መንገዲ መጥቃዕቲ ፈንዩ፤ ነቲ ንህልውናኻ መስዋእቲ ዝኸፈለ ሰሜን እዚ ኣብ ዓለም ተራኢዩ ብዘይፈልጥ መንገዲ ጥቅዓት ኣብፂሒሉ። እዚ ክገብር ከሎ ድማ ምንም ዓይነት ርክባት ከይህሉ ቴሌፎንን፣ ኤሌክትሪክን ቖሪጹ ኣብጸልማት ጌይርዎ።

ዝኸበርካ ህዝብና፣ መንግስቲ ሓይሊ ስጉምቲ ንምትራፍ ዝነበሮ ትዕግስቲ በዚ ኣረመኔ ሓይሊ እዚ ፈሺሉ። ስለዝኾነ ድማ መንግስቲ ተገዲዱ ናብ ምክባር ሕጊ ኣቲዮሎ።

ዝኸበርካ ህዝብ ትግራይ እቲ ኣካል ናይ ምክባር ሕጊ ዝኾነ ሓይሊ ስጉምቲ ንኹሉ መዋቅር ህወሓት ኣይኮነን። ክምኡ እውን ምስ ሓይልታት ጸጥታ ትግራይ ኣይኮነን። የግዳስ ምስቲ ዘራግን ደመኛን ሓይሊ ጥራይ እዩ። እዚ ሓይሊ እዚ ኣብ ውሽጢ ህዝብን ህወሓትን ተወሺጡ ንመላእ ህዝቢ ኢትዮጵያ ዝዘርግ ዘሎ ሓይሊ እዩ።

ምሣዚ ተኣሳሲሩ ኣብ ከይዱ ምኽባር ሕጊ ናይ ኣየር ጥቅዓት ክህሉ ይኽእል እዩ። እቲ ጥቅዓት ንስቪላት ዒላማ ዝይኮነስ ነቲ ሓደገኛ ሓይሊ ዒላማ ዝገብር እዩ። ይኹን እምበር ዘይተሓሰበ ሓደጋ ከይህሉ ሲቪላት ኣብ ከተማታት ተኣኪልካ ምንቅስቓስ ክትቕንስ ይሕብር። ስለዝኾነ ድማ ህዝቢ ትግራይ ምስቲ ወገንካ ዝኾነ ሓይሊ ምክልኻል ሓቢርካ ዕድመዚ ጸላኢ ክተሕፅርን ካብ ዝተደበቐሉ ጉድጓድ ኣውጺኢኻ ንኣባላት ምክልኻል ክተርክብ ወይድማ ከትሕብር፤ ካልኣይ ምስ ሓይልታት ምክልኻል ሓቢርካ ነዚ ኣረመኔ ሓይሊ እዚ ከተቃበጽን ብፍጥነት ናብ ስራሕቲ ልምዓት ክትኣቱ ፃውዕተይ የቕርብ።





ዝኸበርኩም ሓይሊታት ጸጥታ ትግራይ እዚ ገበነኛ ሓይሊ እዚ ነኣኻትኩም ከም መከላኸሊ ተጠቒሙ ንህዝቢ ትግራይ ኣብ ሓደጋ ዘውደቐ ሓይሊ እዩ። መንግስቲ ምስቲ ገበነኛ ሓይሊ እንበር ምሳኹም ተጻቦ ከምዘይብሎ ፈሊጥኩም ኣብ ምወጋድ እዚ እኩይ ሓይሊ ክትነጥፉ ፃውዒተይ የቕርብ። ስለዝኾነ ድማ ናብ ጎረባብቲ ክልላት ወይ ድማ ናብ ኣብ ቀረባ ዘለዉ ሓይልታት ምከኻካል ዒድኩም ክትህቡን፣ ንኣባላት እዚ እኩይ ገበነኛ ሓይሊ ንክትወግእዎ፣ ኣባላትን መራሕትን እዚ እኩይ ሓይሊ ከይሃድሙ መንገድታት ክትዓፅውን ይፅውዕ።

ዝኸበርኩም መናእሰይ ትግራይ፣ ኣብ ሃገርና ገጢሙ ዘሎ ሓደጋ ኣብ ታሪክ ሪኣቶ ዘይትፈልጥን ዘገርምን እዩ። ኣቦታትኩም ዘሃነጽዋ ሃገር፣ ኣያታትኩም ዘተሰወኡላ ሃገር በዚ እኩይ ሓይሊ ተደፊራ ኣላ። እዚ ኃይሊ ኣብ ሓጺር ጊዜ ንሕጊ ክቀርብ ኣለዎ። ሰልዘኾነ ድማ ኣንጻሩ ክትላዓሉን ኣብ ሓጺር እዋን ዕማምና ዛዚምና ናብ ጉዳይ ልምዓትና ክናኣቱ ክትሕግዙና ይጽውዕ። ኢትዮጵያ ክትስዕር ኢያ።

**ይቐንየለን !**

# መግለፂ ትግርኛ

03 ሕዳር ፣ 2013 ዓ. ም

ዝኸበርካ ህዝቢ ትግራይ፣ ከምዝፍለጥ ሓመድ ዝበልዐ እኩይ ሓይሊ ኣብ ምዝዛም ኢና ንርከብ። እቲ ሓይሊ በኹሎም ኣንፈታት ተኸቢቡ ኣብ ጸቢብ ዕንክልል ኣቲዩ ኣሎ። መውጽእን መእተውን ስኢኑ ተዓፊኑ ኣብ ጸዕረ ሞት ዘርከበ ሓይሊ ኮይኑሎ። ኣብዚ እዋን እዚ ኣብ ግንባራት ተረኺቡ ኣመራርሓ ክህብ ኣብዘይክእለሉ ብርኪ በፂሑ ኣሎ።

ደቅኻ በብቦቱኡ ብዘይ ምግብን ማይን ኣደዳ ሞትን መቑሰልትን ይኾኑ ኣለዉ። ስለዝኾነ ደቅኻ ነዚ ዝቐበር ዘሎ ሓይል ምሰዋእቲ ካብ ምኻን በቅልጡፍ ኣድሕን። ደቅኻ ዝበልዕዎ ምግብን ዝሰትይዎ ማይን ዘይብሎም በኣፈሙዝ ከም እንስሳ እናተደፍኡ ድራር ዓረር ይገብሮም ኣለዉ። ሞት ደቅኻ ዕድመ እቲ እኩይ ሓይሊ ብሰዓታት ወይ ብመዓትታት ካብ ምንዋሕ ሓሊፉ ምንም ጥቕሚ የብሉን።

ሰብ ንዕላማ፣ ንሃገርን ሀዝብን እምበር ንጉጅለ ጥፍኣት ኢሉ ክመውትን ኣካሉ ክጎድልን ግቡእ ኣይኮነን። ካባኻ ንላዕሊ ሳዕቤንን በሳላን ውግእ





ዝፈልጥ የለን። እቲ ገባት ጉጅለ ንርእሱ ኣይመውትን ኣካሉ እውን ኣይጎድልን። ዝኸበረ ህይወት ደቅኻ ንጉጅለ ሽፋቱ መጣልዒ ክኸውን ኣይግባእን። ስለዝኾነ ህይወት ዕሽላት ደቅኻ ካብ ከንቱ ጥፍኣት ንምድሓን፣ እቲ ካብ ወረራ ኣንበጣ ዝተረፈ ኣዝመራኻ ንምእካብን፣ ናብ ንቡር ስራሕካ ብፍጥነት ንምምላስን ሻማ ሻማ ኢልና እዚ ጉጅለ ነቃብዖ ብምባል ይፅውዕ።

ዝኸበርካ ህዝብና ሓመድ ዝበልዐ ገበነኛ ጉጅለ ብሓጺሩ ወግኢና ናብ ልምዓታዊ ውራይና ክናኣቱ ይግባእ። ስለዝኾነ ህይወት ዕሽላት ደቅኻ ካብ ከንቱ መስዋእትነት ኣድሕን። ከምቲ ዝጀመርካዮ ድማ ንሓይሊታት ምክልኻል ሃገር ኣድላዪ ዝኾነ ሓገዝ ግበር። በዚ ኣጋጣሚ ነታ ብመስዋእትነት ዘሃነፅካያ ሃገር መሊስካ ኣድሕንን፤ ታሪክኻ ሓድስን። እዚ ሃገርካ ኢትዮጵያ ተቅርበልካ ዘላ ኽቡር ፃውዒት እዩ።

ኣብ ዝተፈላለዩ ምምሕድዳራዊ ብርክታት እትርከቡ ሲቪል መራሕቲ። እቲ ተፃብኦ ምስቲ ኣብ ውሽጢ ህወሓት ዝተሓብአ ጉጅለ ጥራሕ እዩ። ስለዝኾነ ርእስኹም ካብዚ እኩይ ሓይሊ ክተርሕቑ ፃውዒት ቐርቢልኩም ኣሎ። በቢዘለኩምዎ ህዝቢ ወድብኩም ምስ ሓይልታት ምክልኻል ሃገርና ኮይንኩም ሃገራዊ ዕማምና ክትዛዚሙ ይግባእ። ከምዚ ብምግባር ዕድመ እቲ ጉጅለ ኣብ ምሕፃርን፣ ርእስኹም ድማ ካብ ተሓታትነት ኣብ ምድሓን ግብኡኩም ፈፅሙ።

ኩልኹም ኣባላት ፀጥታ ትግራይ ኣብዘን ዝሓለፉ መዓልትታት እንታይ ከምዝገጠመኩም ሪኢኹም ኣለኹም። ናይቲ ሥርዓት ተረባሕቲ ብኣፈሙዝ እናደፍኡ ናብ ሓዊ የእትውኹም ኣለዉ። ንሳቶም እናበልዑን እናሰተዩን ይድቅሱ፤ ንስኻትኩም ኣብ ጥራሕ ከብድኹም ኣደዳ ዓረር ትኾኑ ኣለኹም። ንሳቶም ግና ደሞም ንምፍሳስ ይትረፍ

ድምፂ ተኹሲ ክሰምዑ ኣይደልዩን። ነየናይ ዒላማ ኢኹም ዕሽላ ዕድመኩም ተሕፅሩ ዘለኹም? ንትግራይ ኸ ንምንታይ ወላድ መኻን ትገብሩዋ ኣለኹም? ንምንታይ ጉልበትኹም ኣብ ልምዓት ዘይተውዕልዎ? ንምንታይ ንትግራይ ጠወርታ ካብ ምኻን ኣካልኩም ጎዲሎ ሽኽማ ትኾኑ? ኣብ ምንዋሕ ዕድመ እዚ ዝተሰዓረ ሓይሊ ንምንታይ ደምኹም ተፍስሱ? ህይወትኩም ትግብሩ? ካብ መዓልትታት ዕድመ ንዘይብሉ ዝተሰዓረ ሓይሊ ህይወትኩም ክትግብሩን ደምኹም ክተፍስሱን ፈፂሙ ኣይግባእን።

ኣንፃር እቲ ጉጅለ ተላዓሉ ወይድማ እድኩም ንምክልኻል ሃገር ሃቡ እቲ ሃገርኩም ዝሃበትኩም ዕድል ከየምለጠ ኣብዘን ክልተ ሰለስተ መዓልትታት ርእስኩም ኣድሕኑ። ኢትዮጵያ ብሓቀኛታት ደቃ ክትስዕር ኢያ!!!

**ይቐንየለን !**




INTERNATIONAL AIRPORT